# መንትዮሙ



በ አብዱራህመን አ[illegible] ና [illegible] አየለ ተካ

t.me/OLDBOOKSPDF

# ሙሽራው

# እና

# ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች

ከአብዱ ራህማቶ እና ንጉሤ አየለ ተካ

Are Gifts More Precious Than

ለአብዲ ዘካሪያስ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፸፱

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ
TEL. } 11 27 19

ፖ.ሣ.ቁ.
P.O.Box } 30 93 33

አዲስ አበባ ADDIS ABEBA

ኢትዮጵያ ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved

የሽፋን ሥዕል — ሉቃስ አማረ

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ


1. የጨሌ ንገሬ ብዕር
ከአብዱ ራህማቶ ........................................ 5

2. ሙሽራው
ከአብዱ ራህማቶ ........................................ 23

3. ዱብ ዕዳ
ከአብዱ ራህማቶ ........................................ 63

4. ስንኩል ዕጣ
ከአብዱ ራህማቶ ........................................ 87

5. አውጫጭኝ
ከአብዱ ራህማቶ ........................................ 95

6. ኡፋንቻ
ከአብዱ ራህማቶ ........................................ 116

7. የካዛንቺስ ቀጠሮ
ከንጉሴ አየለ ተካ ........................................ 129

8. አደራው
ከንጉሴ አየለ ተካ ........................................ 146

9. ወጥመድ የገባ ወጥመድ
ከንጉሴ አየለ ተካ ........................................ 177

10. ዱር ያበበ ፍቅር
ከንጉሴ አየለ ተካ ........................................ 201

11. እንተነህ
ከንጉሴ አየለ ተካ ........................................ 220


t.me/OLDBOOKSPDF

# የጨነገፈ ብዕር

ንድፉን እንኳ ካሰፈረው ከረም ብሏል። ብቻ ሙሉ ሐሳቡን ጭሮ የሚጨርስበት ቀን አልሞላልህ እያለው ብዙ አቆይቶታል። ዛሬ ነገ በማለት ቀነ ቀጠሮ እየሰጠ እነሆ መንፈቁ። አሁንም ጽፎ አልጨረሰውም ። ዛሬ ግን እስካሁን እራሱን በማሳነፉ ቆጭቶት፡ ቢሆንም ባይሆንም በሚል ድርሰቱን ሙሉውን ጽፎ ለመጨረስ ወስኗል። ለሥነ ጽሑፍ ከፍተኛ ዝንባሌና ተስጥኦ እንዳለው የሚያውቅና ሰዉም አዘውትሮ የሚነግረው ቢሆንም አንድ እራሱን የቻለ ድርሰት ጽፎ አያውቅም። ከማንበብ የተወገደበት ጊዜ ግን የለም። የኋላ ኋላ በቅርብ ጓደኞቹና በሥራ ባልደረቦቹ በመገፋፋት አጫጭር ድርሰቶችን ለመጻፍ ተነሣሣ። ከሕይወት ገጠመኞቹ መሐል ለድርሰቱ ሕይወት የሚሰጡ ባሕርያትንም መረጠ። ይኸው ይህን ንድፍ እንኳ ካረቀቀ ስድስት ወር አልፎታል። በመጨረሻ ግን የመጀመሪያ ሙከራውን አጠናቅቆ ለአንባቢ ለማቅረብ በመቁረጥ ጠረጴዛው ላይ ወረቀቱን አመቻችቶ ብዕሩን እንሥቶ መጻፍ ጀመረ . . .

ረዥም ጊዜ ያለፈው የተዘነጋ ጉዳይ ነው። ከእንግዲህ አያስጨንቀኝም ብላ ከተወችው ብዙ ጊዜ አልኾል። በአንድ ቀውጢ ወቅት ያጋጠማት የሕይወቷ ነጸብራቅ ጊዜው እየራቀና ድርጊቷም እየተረሳ ቢሔድም ከዕለታት አንድ ቀን የበቀል በትሩን ይሰነዝርብኛል ብላ ከቶ አልገመተችም።



t.me/OLDBOOKSPDF

የፀነሰችው አስባው አልነበረም። በትሩንም ቢሆን የልጅነት መንፈሷ በእድሜታ ልቧ እንዲነዝር አድርጓት እንጂ ዘላቂ በሆነ የፍቅር ወጥመድ አስሯት እንዳልነበረ የተረዳችው ወዲያውኑ ነው። ገዢም ብሎ ልጅነት፣ የተቃጠለ የስሜት ወላፈን፣ የሴጋነት ወሲብ፣ አጣጻሬ ጥያቄ። እናም አለ ስንቱና አለ ቦታው መዋደቅ! ይኸው ነበር። የልምድ እጦት ሁለቱንም ለጥንቃቄ ያላሰናዳ ስለነበር ተፀነሰ። በቃ! ለጊዜው ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት አደረባት። በበትሩም በኩል ቢሆን ችግሩ ቀላል አልነበረም። "መውለድ እኮ አልችልም። አይገባህም? ፍጹም የማይታለም ነው። ያ ከሚሆን እራሴን ከመግደል ወደ ኋላ እንደማልል አታውቅም? እረ አንተ ሰው መላ ፈልግ!" ብላ አላስቆም አላስቀምጥ አለችው ። ሰው ማወቅ ደግ ፡ ከዚህም ከዚያም ተሯሩጦ ንብረት ሸጦና ብድር ጠይቆ ፡ የተጠየቀውን ብር ፈላልጎ አመጣ ። ሐኪሙ ተለምኖ በትሩ አሳሩን አይቶ ካመጣው ገንዘብ ውድ ዋጋ ተከፍሎት ቂሳቁ ሱን እንግቶ መጣ ። ብቻዋን ወደ አንድ ክፍል አስገብቶ መርፌ ወጋት ። ራሷን ሳተች ። ከዚያም በኋላ ያደረጋትን አታውቀውም ።

ሕሊናዋን ስትገዛ ደሙን አየችው። ሌላ መርፌ፣ ጥቂት ኪኒኖች፣ እናም ፅንሱ ወረደ። እንጭጩን ዘሯን በእንጭጩ ቀጨችው። አለቀ ደቀቀ። ከጭንጋፉ ጋር አብሮ የእርሷና የበትሩ ጅምር መዋደድም በጅምሩ አከተመ። ዳግም አልተያዩም። ልታገኘው፣ ልታየው አልፈለገችም። እርሱም እንደ ዚሁ። ፍቅራቸው በመግቢያው መደምደሚያው ሆነ። ስለዚህ ይህ የቆየ የተረሣ ድንገተኛ ያንድ አፍታ ገጠመኝ በቀጣዩ ሕይወቷ ላይ ለውጥ ያመጣል ብላ ከቶ አላሰበችም። ረሳችው፣ ገዳምነሽ።

በነጩ የሥራ ልብሷ ላይ የደረበችው ሰማያዊ ሹራቧን



t.me/OLDBOOKSPDF

ብቻ ነበር። ጉልበት የሚደርሰው ነጩ የእግር ሹራብ፣ ነጩ ሹማ፣ ነጩ ቀሚስ እንዳለ ነው። ቆቡን ግን አውልቃዋለች። ከቅጥር ግቢው ስትወጣ የሥራውን ለሥራ ሰዓት በማለት፣ በሕሊናዋ ሲጉላላ የነበረውንና ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ያከናወነችውን የሥራ ሐሳብ ከግቢው ጋር ከወደ ኋላዋ ለመተው ሞከረች። እንደዚሁም ከመ ቤቱ ወጥቶ እርሷ እንደ ናፈቀችው ሁሉ እርሱም እየናፈቃት ወደ ጋራ ቤታቸው የሚያዘግመውን የትዳር ጓደኛዋን እንደሻውን በማስታወስ ስለ ትዳራቸው ለማሰብ ጥረት አደረገች። ብዙ መቀጠል ግን አልቻለችም። ሐሳቧ ተመልሶ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ባከናወነችው ሥራ ላይ አጸንአት አበጀ።

በንጹሕ አንሶላ የጠቀለለችው ሕፃን ልቅሶ እንደ ሙዚቃ ሁሉ የደስታ ስሜት እያሰማት፣ በፍቅር ዐይን እየተመለከተች በጥንቃቄ ወደ ደረቷ ስታስጠጋው፣ መልአክ የገባው ይመስል ሕፃኑ ልቅሶውን አቁሞ ማየት አንጂ ማስተዋል በማይችሉ ዐይኖቹ ሲዳስሷት ታወሳት። "መልካም ሆነ ክፉ መፀነስ የማይችለው ጮርቃ ሕሊናው ገና የጸዳ ነው። ፍጹም ባዶ። ያላደፈ ንጹሕ አእምሮው ገና ደግም ሆነ መጥፎ ሐሳብን ለማስላት ያልበቃ እንቡጥ! ግና ነገስ? ወደፊትስ? ይህ ሕፃን ዛሬ በሕሊናው የሚያሳድረው ምንም ባይኖረው ዐይኑን፣ ግንባሩን፣ እጁን፣ ሁለመናውን እንዳስተላለፉት ወላጆቹ የመልካቸው ግልባጭ፣ የአካላቸው ምስል ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰባቸው ቀናነትና ወልካፋነትም ዘሩ እውስጡ ይኖር ይሆን? ወይስ እያደገ ሲሔድ ከአካባቢው ይማራቸዋል?..." እያንዳንዳቸውን ነፍሰ ጡሮች አገላግላ፣ ከእንግዴ ልጃቸው የተላቀቁትን ሕፃናት አጣጥባ፣ ከብደታቸውን መዝግባ፣ ተፈላጊውን እንክብካቤና ምርመራ በማድረግ ወደ



t.me/OLDBOOKSPDF

እናቶቻቸው በመለሰቻቸው ቁጥር በሕሊናዋ የሚሠረጽባት ሐሳብ ነበር ለሁለት ዓመታት ። የእናቶች ምጥ ምጢ፣ ማልማላቸውም ማልማይ ነው። ሲሠቃዩ አብራ ተሠቃይታ እፎይታቸውንም አብራ ነው እፎይ የምትል ። በሞያም ከተሠማራችበት ጊዜ አንሥቶ፡ ሲስተር ገጻምንሽ።

ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ከወጣች በኋላ እንኳ ያገላገለቻቸው እናቶች፡ አዲስ የተወለዱት ሕፃናት፡ እውጪ የሚጠብቁት የቤተዘመድ ሁኔታ ከሐሳቧ አይወገድም። ዛሬም እንደዚሁ። ምንም ያህል ሌላ ነገር ለማሰብ ትሞክር እንጂ የወሊድ ክፍሉ ሁኔታ ከሐሳቧ ራቅ አላለላትም። "መግባት ክልክል ነው" የሚል ማስታወቂያ ከተለጠፈበት በር ፊት ለፊት ካለው አግዳሚ ላይ ቁጭ ብሎ በር በሩን እየተመለከተ ከንፈሩን በኃይል የሚነክሰው አባት፡ ከሸሚዝ ላይ ሹራብ፡ ከዚያ በላይ ኮት፡ ከኮት በላይ ኩታ አጣፍቶ፡ ከእግሮቹ ሌላ የሱሪውንም ጥንድ ሜዳ ጨምረው በከተቱት የላስቲክ ቦቴ ጫማ ወለሉን በኃይል እየረገጠ ከላይ ታች፡ ከወዲያ ወዲህ የሚንጐራደደው ባል፡ ጸጉሩ በቅጡ ያልተበጠረና የተሞነጫጨረ፡ ከለበሰው የፒጃማ ኪስ ውስጥ ሲጋራውን አሁንም አሁንም እያወጣ በማቀጣጠል ቁና ቁና እየማገ፡ መሬቱ ላይ ያዝረከረከውን ዐመድ በነጠላ ጫማው እየሰበሰበ ያቀረቀረው አባወራ፡ የጠጣው አልኮል ሽታ መተላለፊያውን አውዶት፡ የደም ሥሮቹ ግንባሩ ላይ እንደ ዛፍ ቅርንጫፎች ተገታትረው እየታዩ፡ አግዳሚው ላይ ብድግ ቁጭ እያለና ሐኪሞችና ነርሶቹ ወጣ ገባ ባሉና በሩ በተከፈተ ቁጥር እየተንደረደረ፡ "ደህና ተገላገለች? ሲስተር በጎ ናት?" እያለ የሚጮኸው ባለቤት፡ ነጠላቸውን ከመልበስ ይልቅ ወገባቸውን ጥፍር አርገው አስረውበት፡ ቁና ቁና እየተነፈሱ፡ በሩ ላይ ተለጥፈው



t.me/OLDBOOKSPDF

''የጭንቅ፣ አማላጅዋ አንቺ ስውሪን'' እያሉ የሚማጠኑ አሮጊቶች፣ ሴሎች ሌሎችም የተለያዩ ሰዎች ገጽታ በጭንቅ ላይ እየተፈራረቁ ተደቀኑባት ። ነፍስ ጡሯ ስትጨነቅና ስታምጥ እውጭ የሚጠባበቁት አባቶችና ቤተዘመድም አብረው ይጨነቃሉ፣ አብረው ያምጣሉ። ስትገላገል አብረው ይገላገላሉ ። ዕልልታቸውን ያቀልጡታል። ሲስተር ገዳምነ ሽም እንዲህ አብራ ተጨንቃ፣ አብራ ወልዳ፣ አብራ ዕልል ትላለች። ሁለት ዓመት ሙሉ በሙያው ስትቆይ፣ ''መውለድ እንደምን ከባድና እንደምንስ መልካም ጸጋ ነው? መውለድን፣ ከጭንቅ መገላገልን የመሰለ ምን ጥሩ ነገር ይገኛል? ማዋለ ድን ከጭንቅ ማገላገልንስ የመሰለ ምን ክቡር ሙያ ይኖራል? ለሕይወት ከትሚያ ሳይሆን ለሕይወት ጀማሪ፣ ለመኖር ማብቂያ ሳይሆን ሕይወት እንዲቀጥል ከሚያግዝ ሙያ የተሻለ ምን ተግባር ይገኛል?'' አለች ሲስተር ገዳምነሽ በመጨረሻ። ቀድሞ ልትረሳው ከፈለገችው ሐሳብ ጋር አንድነት የመሠረተች ይመስል ይበልጥ እየሰጠመችበት።

በዚህ ሙያ ስትሠማራ ሁለት ዓመት ሆኗታል። ጥንት በእንዲህ ዐይነት የሥራ ገበታ ላይ እሠማራለሁ ብላ ገምታም፣ አልማም አታውቅ። የእንጀራ ጉዳይ ሆኖ ረዥም መስሎ የታያትን የትምህርት ገበታ በአቋራጭ ለማምለጥ ስትል የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት እንዳጠናቀቀች ነበር ወደ ነርሶች ማሠልጠኛ ማዕከል የገባችው። ያኔ የሙያው ባሕርይ ይህን የዛሬውን ይመስላል የሚል ግምት አልነበራትም። ስለ ሕፃናትና ስለ ሌሎችም ቢሆን ደንታ ቢስ ነበረች። ''ልጅና ችጋር አልወድም'' ከሚሉት መሐል አንዷ ነበረች። ኮርሱን በመከታተል ሳለች ግን ዝንባሌዋ ከፍ እያለና ፍላጎቷም እጨመረ መጣ። ተመርቃ አገልግሎት መስጠት


t.me/OLDBOOKSPDF

ከጀመረች ወዲህ ለሙያው ከፍተኛ ግምት እየሰጠችው በመሔዷ በተለይ አዋላጅነትን አለቅጥ ወደደችው። የልጅ ፍቅርም አሳደረባት። ሕፃናት አካባቢዋ እንዲቀርቡ የማትሻዋ ገዳምነሽ ከጊዜ በኋላ በመንገድ ያየችውን፣ በየደረሰችበት የሚገጥሟትንና የጎረቤት ሕፃናትን ሁሉ እያቀፈች መሳምና ማጫወት ስትጀምር በልጅነት ጠባይዋ መቀየር የማይደነቅ አልነበረም።

ከእንደሻው ጋር የተዋወቀችው በነርሶች ማሠልጠኛ ማዕከል የሁለተኛ ዓመት ተማሪ በነበረችበት ወቅት ነው። በማሠልጠኛ ማዕከሉ የቤተ መጻሕፍት ኃላፊ የነበረውን እንደሻውን በሙሉ ዐይኗ ማየት የጀመረችው ለጥናት ቤተ መጻሕፍት በምትመላለስበት ጊዜ ነበር። መልከ ቀና፣ ጠባየ ሸጋና ረጋ ያለ ከመሆኑም በላይ በቶሎ ተግባቢና ከተማሪዎቹም ጋር መልካም ግንኙነት የነበረው በመሆኑ ልትወደው ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም። ከተመረቀች በኋላና በሥራ ዓለምም ተሠማርታ ግኑኝነታቸው ባለማቋረጡ በመኻላቸው የነበረው መቀራረብ እየጨመረ፣ ይበልጥ እያወቀችውና ይበልጥ እያፈቀረችው በመሔዷ፣ ለጋብቻ ያቀረበላትን ጥያቄ ለመቀበል አላንገራገረችውም። እነሆ አሁን ከተጋቡ ዓመታቸው ነው ፡ የፍቅራቸው ግለት እየጨመረ መሔዱን አላቋረጠም።

“ውይ! ምነው እበራፍ ቆምክ?” ከቅጥር ግቢያቸው ደጃፍ የቆመውን ባለቤቷን እንደሻውን ድንገት ስትመለከት ከሐሳቧ ባነነች።

“ከርቀት አይቼሽ አንቺን እየጠበቅሁ” አላት። ያቀረበችለትን ከንፈሯን ከከንፈሩ ጋር እያጋጨ።

“ምን ታስቢ ኖሯል?”

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንም።"

"አጠገቤ እስክትደርሺ ድረስ አላየሽኝም?"

"እም... እዎን አላየሁህም። አቀርቅሬ መሬት መሬት ሳይ ነበር" አለችውና እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ቤታቸው አመሩ።

"የሌለ አይናፋርነት ከየት መጣ?"

"መሬት መሬት ማየት የዐይን አፋሮች ብቻ ነው?"

"ወይም ሕይወትን ፊት ለፊት እያዩ መጋፈጥ የሚፈሩ ናቸው የሚያቀረቅሩ።"

"ካልክስ ሕይወትን ማየት ከፊት ለፊቱ፡ ከጀርባው፡ ከታችም ከላይም ነው፡ አንድ አማራጭ ለማግኘት። ያቀረቀር ኩት ግን ለእሱ አይደለም። ዐይኔ ከአንተ የተሻለ ያይና ልቤ ይከተለዋል ብዬ በመሥጋት ነው" አለች ወደ በለጠ ቀልድ ጭውውቱን እየመራች።

"በእይታ ብቻ ተስበሽ የምትሸነፊ ቢሆንልኝማ አንገ ትሽን በጂሶ አሳሽጌ፡ ማቀርቀር እንዳትችይና ሁሉን እንድት ማትሪ ባረግሁሽ ነበር።"

"ምን ልታገኝ? ልቤ ዐይኔን ከተከተለው እከ ታጣኛለህ።"

"እርሱን አይደል የምልሽ? እንውለድ ስላት ነገ ተነገወ ዲያ የማትለኝ ሽጋ ፊልጌ ለማግኘት ነጻነቱን እንዳውጅ።"

ቀልዱ ሳይታሰብ ወዳልፈለገችው አጣጣሜ ሲያመራ ቅሬታዋን ከፊቷ ላይ መደበቅ አልቻለችም። ጨዋታው እየመረረ ሳይሔድ የውይይቱን ርእስ ለመቀየር ብላ፡ "ምንድ ነው የያዝከው? ምን ደግሞ ገዝተህ መጣህ?" አለችው ሳሎን ውስጥ ከሶፋው ላይ ዐረፍ እንዳሉ።

"ለልጄ የገዛሁላት ልብስ" አለና በእጁ ይዞት የነበረ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውን በጋዜጣ የተጠቀለለውን ዕቃ ከባዶው ሶፋ ላይ ወረወረው። ገዳምነሽ ርዕስ የመቀየር ሙከራዋ እንዳልሠመረ ታወቃት።

“ለምን በቁም ነገር ስጠይቅህ በፌዝ ትመልስልኛለህ?” አለችና ጥቅሉን አንሥታ መፈታታት ቀጠለች። ጋዜጣው ሲገለጥ የተመለከተችው ነገር ይብስ አስደነገጣት። ዐይኖቿ አንዴ ወደ ዕቃው፡ አንዴ ወደ እንደሻው ተንከራተቱ። የምትናገረው ጠፍቷት ግራ ስትጋባ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ግንባሯን እየሳመና ፊቷን በከንፈሩ እየዳሰሰ፡

“አዎን ለልጄ አዲስ ልብስ! የገዛ ልጄ አባት መሆን አለመቻሌን ሲያይ ነው መሰለኝ፡ ለማ ለልጁ የክርስትና አባትነትን ሰጥቶኛል። በሥጋ ቢቀር በመንፈስ እንኳ አባት ልሁን እንጂ!” አሁንም መልስ አልሰጠችውም። የሕፃኑን ልብስ መልሳ እየጠቀለለች ዐይን ዐይኑን አየችው።

“ሕጻኑ ክርስትናው ነገ ስለሆነ አብረን ነው የምንሔድ” በማለት ጥቅሉን ተቀብሎ ወደ ሶፋው ተመልሶ ተቀመጠ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ የእጆቿን ጣቶች አቆላልፋ እያንቋቋች ፡“ለምን በነገር ትወጋኛለህ? ለልጅ ፍቅር ከአንተ የበለጠ እንዳለኝ ታውቃለህ ። ግን ጥቂት እንዘግይ!ታገሥ ። ‘ዝም ብሎ አይወለድም ፡ ዝግጅት ያስፈልጋል ነው’ ያልኩህ ። ትንሽ ታገሥ እንጂ እንደሻው ።”

“ታግሼማ ነው እስካሁን ዝም ብዬ ቁጭ ያልኩ ። አለያማ በአንድ ጊዜ ከሦስት ባላነሱ ዲቃላዎች ቤቱን እንሞላው ነበር እኮ!” ለመቀለድ ሞከረ ።

“የልጅ ፍቅር ፡ የልጅ ፍላጎት ፡ ወልዶ የማቀፍና የመሳም ጥም በእኔም ልብ ውስጥ ሲቃጠል ብዙ ጊዜ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖታል ፡ ከጋብቻችን ዕድሜ የበለጠ ። ነገር ግን አንተ ትዕግሥት ሊኖርህ አልቻለም ። 'ተሰናድተናል ፡ ጠቅቴ ነው' ብለህ የምታምን ከሆነ እሺ እሁ … ን …" ዐረፍተ ነገሩን ሳትጨርስ ተናንቃት ። ልትል ያሰበችውን እንዳትል አንድ የማታውቀው ነገር አገዳት ። በመውለድ ፍላጎት ከእንደሻው እንደምትበልጥ ታውቀዋለች ፡ ዝግጁ አይደለንም የምትልበ ትን ምክንያት ግን እሷም አታውቀውም ። ብቻ "እንውለድ ፡ ተዘጋጅተናል ፡ አሁን" ለሚለው የልቧ ጥያቄ ደንቃራ የሚሆንባት አንድ ነገር አለ ። የማርገዝ ሐሳብ በአዕምሮዋ ሲነግ እንዲሁ ፍርሃት ፍርሃት ይላታል ። ምክንያቱን ግን አታውቀውም ። ዝም ብሎ በደመ ነፍስ ። አሁንም "እሺ እንወልዳለን" ለማለት የጀመረችውን ዐረፍተ ነገር ሳትጨ ርስ የሆነ ነገር ለጐማት ። ዐይኖቿ ዕንባ አቀረሩ ።

እንደሻው ፡ የፊቷ መለዋወጥና መላ ሁኔታዋ አስደነገ ጠው ። አልተዘጋጀንም ብላ መልስ ከመስጠት በስተቀር እንዲህ ሁለመናዋ ሲቀያየር አይቶ አያውቅም ። ግራ በመጋ ባት በዝግታ ተነሥቶ ከጎኑዋ ቁጭ ብሎ አቀፋት ። በተራው እርሱ ራሱ ርዕሱን በመቀየር ያረጋጋት ገባ ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ ገዳምነሽ የፅንስ መቈጣጠሪያ ኪኒኖቹን መውሰድ አቋረጠች ። ይሁን እንጂ ለእንደሻው አልነገረችውም ። እርሱም ቢሆን የዚያን ዕለቱ ዐይነት ሁኔታ ይፈጠራል ብሎ በመሥጋት ደግሞ የመውለድ ጥያቄ አላነሣ ባትም ። ቢሆንም አሁንም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ያላወቀ ችው ጭንቀት አደረባት ። ብቻ በራሷና በእንደሻው መኻል የነበረው ንትርክና አለመግባባት ተወገደ ። ፍቅራቸውን እንደ ቀድሞው በጋለ መንፈስ ቀጠሉ ። በቤታቸውም ሰላም ሰፈነ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ገጸምንሽ የዕንስ መቈጣጠሪያ መድኃኒት መውሰድ ካቆመች እነሆ ሁለት ወራት ያህል አለፉት ። ያ በጉጉት ስትጠባበቀው የነበረው ዕንስ ግን እስካሁን አልተሳካም ። የወር አበበዋ ቀኖቹን ሳያዛንፍ በተከታታይ መምጣቱን ቀጠለ ። ሥጋቷ ከፍ እያለ ሔደ ። ጭንቀቷም እየየለ ከወር ወር እየጨመረ ገደቡን አለፈ ። ይሁን እንጂ እስካሁን ለእንደሻው የሆነውን እንዱንም አላሚጠተችውም ። ለጥቂት ወራት በዝምታና በትዕግሥት ጠበቀች ። የወር አበባዋ ግን መምጣቱን አላቋረጠም ። በመጨረሻም ቁርጡን ለማወቅ በመወሰን የምትሠራበት ሆስፒታል ለሚገኙት የማሕፀን ልዩ ሐኪም አማከረች ። በራሷ በኩል የተሟላ ምርመራ ተደረገላት ። የተጠየቀችውን የባሏን ሽንትና ደም ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮች እንደሻው ሳያውቅ በከፍተኛ ጥንቃቄና በዘዴ ይዛ ቀረበች ። የምርመራውን ውጤት ከጥቂት ቀናት በኋላ አረደች ። ጉድለቱ በባሏ በኩል ሳይሆን የራሷ ሆኖ ተገኘ ። "ለካስ የፈራሁት ይኸው ኖሯል?" ብላ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። ባላወቀችው ምክንያት የእርግዝና ጥያቄ ፍርሃት ፍርሃት ሲላት የከረመው ሰውነቷ ይህንኑ አስቀድሞ ሲያስጠ ንቅቃት ነው? ያ ከዚህ በፊት የፈጸመችው ፡ ያ የማስወረድ ተግባሯ የፀፀት ጥላውን እንደገና ዘረጋባት ?

በደመ ነፍስ የመውሰድን ሐሳብ የፈራችው ለዚሁ ይሆን?.... የማሕፀን አበክሮ ሞያተኛው በሁኔታዋና በተሰ ማት ጥልቅ ኀዘን በመንካታቸው ሊረዷት የሚችሉበትን መንገድ ለረዥም ጊዜ ሲያውጠነጥኑ ቆዩ ። የምርመራ ውጤቷንም ደጋግመው አጤኑት ። በመጨረሻም በቀዶ ጥገና የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ እንደሚችሉ ፍንጭ ስለ ታያቸው ቢያማክሯት ሳታንገራግር በደስታ ተስማማታ ፡ ይህንንም



t.me/OLDBOOKSPDF

ቢሆን ለእንደሻው ሳታሳውቅ በሌላ በሽታና አሳማኝ በሆነ
የሐሰት ሽፋን ሆስፒታል ተኛች ። እየተመላለሰ ያስታመማት
ቢሆንም ከነርሶቹና ከሐኪሞቹ ጋር በተደራደረችው ስምም
ነት መሠረት የሌላ ምክንያትና የበሽታ ስም እየተነገረው
እውነተኛውን ሕክምናዋን ሳያውቅ ሰነበተ ። በመጨረሻም
ሐኪሙ የቀዶ ጥገናው የተሳካ መሆኑን አብሥረዋትና ፣ ግን
እስኪያጠግግ ድረስ ከእርግዝና ለጥቂት ወራት እንድትቆ
ጠብ ተነግሯት ከሆስፒታል ወጣች ። ከአንድ ወር በኋላም
ወደ መደበኛ ሥራዋ ተመለሰች ።

እራሷን አላመነችውም ። ድንገተኛ ስሕተት መሰላት ።
የደስታ ሲቃ ሲተናነቃትም ገና ለእንደሻው ማሳወቅ አልፈለ
ገችም ። በመጀመሪያ ማረጋገጫዋን በእጇ መጨበጥ ፈለ
ገች። ከቀዶ ጥገናው ስድስት ወር በኋላ የወር አበባዋ ድንገት
መቋረጡ ሕልም መሰላት ። እዚያው በምትሠራበት ሆስፒ
ታል ላቦራቶር ሽንቷን አስመረመረች ። የምርመራው
ውጤት የተጻፈበትን ወረቀት እንብባ ልታምነው አልቻለ
ችም ። ማስረጃዋን ከጨበጠች በኋላ የሥራ ሰዓት እስኪያበቃ
ድረስ መታገሥ ስላልቻለች ወደ ቤቷ አፈተለከች ። ውድ
ባለቤቷ ፣ የምታፈቅረው የትዳር ጓደኛዋ እንደሻው እስኪ
መጣ ድረስ አንዳንድ ነገሮችን ለማድረግ ወሰነች ። ጠቅላላ
ለውጥ! ይህ በቀላሉ የምታበሥረው የምሥራች አይደለም ።
አፍኖ ጸጥ ቢልም የልጅ ጥያቄ የልብ ትርታው መሆኑን
ታውቃለች ። ‘በመጨረሻ ሆነ!’ ብላ በረጅሙ ተነፈሰች ።
የአልጋው አቀማመጥ ፣ የምግብ ቤቱንና የሳሎኑን ወንበሮች፣
የመጻሕፍት መደርደሪያውን ፣ የቁም ሣጥኖቹን ፣ የቴፕ
ሪከርደሩን ፣ የቴሌቪዥኑን … የሁሉንም አቀማመጥ ከሠራተ
ኛዋ ጋር በመተጋገዝ ቀየረች ፣ ቤቱ የሌላ ሰው ቤት መሰለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በቀላሉ የማይቀበለውን የምሥራች በቀላሉ ልትነግረው አልፈለገችም ። ላላሰበው ውስጣዊ ፍንደቃ ያልታሰበ ድንገቴ ለውጥ ሳይደርስባት ዝግጅቷን ለማጠናቀቅ ከጊዜ ጋር እሽቅድድም ያዘች ። አካላቷን ተጣጥባ ከውስጥ እስከ ላይ አዲስ ልብስ ቀየረች ። አዲስ የውስጥ ሱሪ ፡ አዲስ የጡት መያዣ ፡ አዲስ የውስጥ ልብስ ፡ አዲስ ቀሚስ በተለያየ ምክንያት ለብሳው የማታውቃቸውን ጨርቃ ጨርቅ ከቁም ሣጥኗ አውጥታ ለበሰች ። ጸጉሯን በሚያምር ቅርጽ ተሠርታ ፡ አምሯ ተኳኩላ ጠጣች ። ለእንደሻው መድረሻ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሯት መስናዶውን አጠናቅቃ ሶፋው ላይ በቁንጥ ተኮፍሳ ጠበቀችው ።

እንደሻው በሩን ከፍቶ ገባ ሲል ድንግጥ አለ ። የገባ ቤቱ የሌላ ሰው ቤት ሆኖ ታየው ። መኖሪያውን የሳተ መስሎት ወደ ኋላው አፈገፈገ ። ከቤት ዕቃዎቹ አቀማመጥ ለውጥ ሌላ ከፊት ለፊቱ የሚያያትንም ውብ ሴት የማያውቃት ስለ መሰለው መሳሳቱን ሊያምን ምንም አልቀረው ።

"ግባ እንጂ! እንደ… ምነው ደነገጥህ?" ስትለውና ድምጿን ሲሰማ እሷው ገጻምነሽ መሆኗን ዐወቀ እንጂ ይቅርታ ጠይቆ ሊመለስ ቃጥቶት ነበር ። ዐይኑን ማመን አቃተው ። አዲስ ሴትዮ ፡ በአዳዲስ ልብሶች ያጌጠች ፡ እናም ደስ የሚል ጠረን! … አዎን ሽቶ… የተቀባችው ሽቶ ቤቱን አውዶታል ። ግር አለው ። ሲያቅማማ ቆይቶ "ምንድነው?" አለ ፡ መሐል ለመሐል እንደ ቆመ ።

"ምኑ ነው ምንድነው?"

"ይኸ ሁሉ"ከራሷ ጀምሮ ቤቱን በእጁ አዟዙሮ ጠየቃት ።

"ዱሮ የማውቀው እንዲህ ሆኖ አይደለም ።" ሲፈራ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲቸር ፈንጠር ብሎ ከአንዱ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ዐረፍ አለ ።

"እሱማ ብዙ ተለውጧል" አለችው ፈገግ ብላ ። እርሷም በዐይኑዋ ቤቱን ከማዕዘን ማዕዘን እያማተረች ።

"እንዴት ማለት?"

"እንዴት? እንዴት ማለት? መለወጥ ነዋ! ሁሉም ተለውጧል ።"

"ለምን ?"

"ምንድነው ለምን ? ለውጥ አይስፈልግም እንዴ?"

"ቀልዱን ትተሽ የሆነውን ንገሪኝ እንጂ! ልቤን አንጠለጠልሽው ።"

ፈገግ ብላ እጇን በመዘርጋት ፡ " ና በመጀመሪያ እንደ ወትሮህ አቅፈህ ሳመኝና እነግርሃለሁ" አለችው ።

"እባክሽ አታስጨንቂኝ ንገሪኝ ! እንደ ወትሮው እንዳልስምሽም እንደ ወትሮው ሆኖ ያገኘሁት ነገር የለም ።"

"እኮማ ለዚሁ ነው እንደ በፊቱ ብድግ ብዬ ከንፈሬን በማቀበል ፈንታ እጄን ዘርግቼ እንተው መጥተህ እንድትስመኝ የምጠብቀህ ።"

"ቀልዱ ይብቃሽ ገዳም! ንገሪኝ ፡ ንገሪኝ! " ትንሽ ቆጣ ፊቱም ኮስተር አለ ። ድምፁም ሎከ ያለ ነበር ። አስተያየቱም ተቀየረ ።

"ምን ልንገርህ?" እርሷም ድምጿን ሆን ብላ ቀየር አረገችው ።

"ይህን ሁሉ! የቤቱን ፡ የዕቃዎቹን አቀማመጥ ፡ ያንች የራስሽን..."

"ኡፍ እንግዲህ አትጨቅጭቀኝ ። እንግዳ መጥቶብኝ ነው ። ዕረፈው ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

“እም? የምን እንግዳ? ማን የሚሉት?”

“እዲስ እንግዳ የማታውቀው እንግዳ።”

“እኔ የማላውቀው?”

“አዎን አንተ የማታውቀው” ብላ ብድግ አለች ። በሚያምናት ባለቤቱ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥርጣሬ በር ተቆረቆረበት ። ግን ገና ሊቀበለው አልቻለም ።

“ምንድነው የምታወራው?” ዝቅ ባለ ድምፅ ረጋ ብሎ ጠየቃት ።

“እንደሻው! የምነግርህ አይገባህም? እንኳን አንተ እኔም በውል የማላውቀውና ግን አንጀቴን ሥርስር ውስጡን ዘልቆ የገባ እንግዳ መጥቶብናል ። እ … እም መጥቶልናል ። ብቻዬን ሳልሆን አንተም እራስህ በጉጉት ስትጠብቀው የነበረ …” ብላ እጁን ዘረጋች ። ገና አልተረዳትም ።

“እኔም የምጠብቀው? ማን ሁለታችንም የማናውቀው” ብሎ የጀመረውን አልጨረሰም ።

“ያውልህ” አለችው ። የዘረጋችውን እጅ ከፍ አድርጋ። ፊቱን ከፊቷ … አድርጎ የተዘረጋው እጇ የያዘውን ወረቀት ተመለከተ ። ሳይናገር ተቀብሎ አየው ።

ዘሎ ተጠመጠመባት ። አጥብቆ ያዘ ለረዥም ደቂቃዎች ከንፈሯን ሳመ ። መልሳ ሳመችው ። አቅፎ ብድግ አደረጋት ። የደስታ ሲቃ ተናነቀው ። የእርሷም ዐይኖች የደስታ እንባ አቀረሩ ። ቤቱ ዛሬውኑ የሞቀ ፡ ዛሬውኑ የደመቀ መሰለ ። ሁለቱን የፍቅር መንትዮች ፍቅራቸውን ይበልጥ ሊያጸና የሚችል ፡ የራሱ የፍቅራቸው ውጤት የሆነውን ፍሬ ገና ሳያዩት በመጎምገት ብቻ ፈነደቁ ። ገና ሳይደርስ መንገድ መጀመሩን በመስማታቸው ደስታቸው መጠኑን አለፈ ። ለአቀባበል መስተንግዶውን ያኔውኑ ጀመሩ ። ሰፊው ቤት



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠበባቸው ።

ሲስተር ገዳምነሽ ከጓመኛነት በፊት እንደ ቋመጠችው ፡ ከረዥም ጊዜ ቀደም ብሎ ሲያምጡ እምጣ ፡ ሲገላገሉ እንደ ተገላገለችው ፡ በእውን እርግዛ ከዚህ ቀደም እርሷው እንደ ረዳቻቸው እናቶች ፡ በተራዋ በመሰል አዋላጅ ጓደኞቿ እየተረዳች ስትወልድ ታየች ። አሁን አሁን መሰላት ፡ የረዥም ጊዜ ሕልም እውን ሲሆን ።

ፍቅራቸው እየጨመረ ሔደ ። ዘጠኙን ወራት በደስታ ፡ በጉጉት ፡ በመሰናዶና በዝግጅት ያሳለፉት ቢሆንም እንደ ጠበቁት ቶሎ አልመጣም ። ቀናቱ የማያልቁ ፡ ወራቱ ረገርዥም ሆነውባቸው ከረሙ ። እንደሻው ወደ መ ቤቱ ሲሔድና ሲመለስ ለዐይኑ የገጠመውን ፡ በየመደብሩ ያየውን የሕፃናት ልብስ ፡ መጫወቻ አሻንጉሊት ፡ የሕፃን አልጋ ፡ የማንሸራሸሪያ ጋሪ ···· ሌሎችንም ሲገዛ ከረመ ። ገዳምነሽም ወደ ሥራዋ በተመላለሰች ቁጥር አስፈላጊውን ምርመራ ፡ ጥንቃቄና ሕክምና ስታደርግ ቆየች ። እቤት ውስጥም ስትውል በስፌት፡ በሹራብ ሥራው ፡ ለሕፃን በሚሆኑ ተመሳሳይ ዝግጅት እራሷን አጥምዳ ከረመች ። በመጨረሻ ምጧ ዕለታት የወሊድ ፈቃድ ወስዳ ከሥራ ቀረች ።

የዕለቱ ዕለት ጧት ደህና መስላ ስለ ታየችው እንደሻው ወደ ቢሮው ሔደ ። ጥቂት ቆይቶ ግን ገዳምነሽን እየደከማት በመሔዱ ለመ ቤቱ ስልክ በመደወል አንቡላንስ አስጠርታ ሆስፒታል ተወሰደች ። ወዲያው ወደ ማዋለጃው ክፍል በሥራ ጓደኞቿ ታጅባ ገባች ።

እንደሻው ስልኩ እንደ ተደወለለት ደቂቃ አላጠፋም ። እየከነፈ ወደ ሆስፒታሉ መጣ ። እንደ ደረሰ ግን ገብቶ ሊያያት አልቻለም ። "መግባት ክልክል ነው" የሚል ጽሑፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከተለጠፈበት ክፍል ትይዩ መጠበቂያ አዳራሹ ውስጥ እየተቁነጠነጠ ይጠባበቅ ጀመር ። ከዛሬ በፊት ባለቤቱ ዛሬ በምታምጥበት ክፍል ውስጥ ለሌሎች ዕርዳታ ስታደርግ ፡ የሴቷ ቤተዘመድና ባለቤት አሁን እርሱ በሚንጎራደድበት ክፍል ውስጥ በሲቃ እንዴት እንደሚጠባበቁ ታስበው ። አምኖበት የማያውቀውን ጸሎት ለመጸለይ ከጀጀለው ። በድንገት በሩ ሲከፈት ግባ እስኪባል አልጠበቀም ። ተንደርድሮ ዘው አለ ። በመውጣት ላይ የነበረችውን ነርስ ገፍትሮ ሳይጥላት ለጥቂት ዳነች ። መጋረጃውን አልፎ ወደ ገዳምነሽ አልጋ ተጠጋ ። ዐይኖቿ ተከድነው ነበር ። "ጥቂት ዕረፍት ታድርግ" የምትለዋን ነርስ ድምፅ አላዳመጠም ። በርጋታ ግንባሯን ሳም አደረገው ። ዐይኗን ግን አልገለጠችም ። አልጋው ጫፍ ላይ በቀስታ ዐረፍ ብሎ በፍቅር ተመለከታት ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንዲት ሌላ ነርስ በነጭ አንሶላ የተጠቀለለ ሕፃን አቅፋ ከፊት ለፊቱ ቆመች ። እስከ አሁን ጸጥ ብላ የነበረችው ገዳምነሽም የነርሷን መምጣት ያደመጠች ይመስል ዐይኗን ገለጥ አድርጋ አንገቷን ወደ ነርሷ አዞረች ። አትስቅም ፡ ፈገግም አላለች ። ነርሷም እንደዚሁ ። ዝም ዝም ሆነ ። እንደሻውም ልቡ መታ ። የገዳምነሽ አፍ ሲላወስ ታየው ። የተናገረችውን ግን ማድመጥ አልቻለም ። ነርሷ የተጠቀለለውን ሕፃን በዝግታ አኑራ ቀና ስትል በዕንባ ጭጋግ የተጋረዱ የገዳምነሽ ዐይኖች በሕፃኑ ላይ ዐረፉ ። የእንደሻውም ዐይን ተከተላት ። ሕፃኑ አይላወስም ። አያለቅስም ። ዐይኖቹ እንደ ተጋጠሙ ናቸው ። የእርሱም ዐይኖች በዕንባ ተሞልተው አንዴ ወደ ገዳምነሽ ፡ አንዴ ወደ በድኑ ሕፃን በአቅመቢስነት ተንከራተቱ ። የገዳምነሽ ዐይኖች ግን በሕፃኑ አስከሬን ላይ እንደ ተተከሉ ቀሩ ። የማይፈስ ዕንባ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳቀረሩ ።

ያ ተዘርግቶ የቆየው የአንዳፍታ የሕይወት ገጠመኝ እንደ ተረሳት አልቀረም ። ከዓመታት በኋላ ሕሊናዋን ቆጠቆጠው ለረዥም ጊዜ ፡ ያለፈና የተዘነጋው ጉዳይ ፡ ያለፈና የተዘነጋ እንደሆነ አላበቃም ። ከሌላ ገጠመኝ ጋር ተሳስቦ ቆይቶ አቆሰላት ። ራሱን የኋሊት ሳያጠነጥን ወደፊቱ ብቻ እያዘገመ የኖረው የተረሳ ተውኔት ከዕለታት አንድ ቀን ለሥራችው ጥፋት የበቀል በትሩን ይሰነዝርብኛል ብላ ከቶ አልገመተችም ። ያ የቆየ ፡ የተረሳ ፡ ድንገተኛ የአንዳፍታ አጋጣሚ በቀጣዩ ሕይወቷ ላይ ለውጥ ያመጣል ብላ ከቶ አላሰበችም ። ረሳችው ። ዘነጋችው ። ይኸው ነበር ··· ግን እንዳያ ሆኖ አልቀረም ። የዚያ ቀጥተኛ ተቃራኒ ተደቀነባት። እንግዲህ ልትረሳው አትችልም ። ከእንግዲህ አትዘነጋውም። ጠባሳውን ይዞ አብሯት ይኖራል ። የሆነው ይህ ነው ·····

ጽሑፉን አብቅቶ ብዕሩን ከጠረጴዛው ላይ ጣል አርጎ ቀና አለ ። ብዕር የጨበጡበት ጣቶቹን እያሻሸ ፡ አንድ ቦታ በማየት የፈዘዙ ዐይኖቹን ጨመቅ ጨመቅ እያደረገ ፡ አንገቱን አንዴ ወደ ግራ አንዴ ወደ ቀኝ እየወነጨፈ እራሱን አዝናና ። ዕረፍቱን አቋርጦ ጽፎ ያበቃውን ድርሰት ለመጨረሻ ጊዜ አንሥቶ አነበበው ። ደስ አልተሰኘበትም ። ጉድፉን ሲጀምር ፍጻሜው ይህ ይሆናል ብሎ አልወጠነም ። ሐሳቡ እያስጋለበ የመራው ያበቃል ብሎ ወዳሰበበት አልነበረም ። የድርሰቱ ፍጻሜ ይህ በመሆኑ ቅሬታ ገባው ። በደራሲያን የድርሰት አጨራረስ ላይ እራሱ ይጠላውና ይተቸው የነበረ ውን አሳዛኝ ፍጻሜ እራሱ ሳያስበው በመጻፉ ተናደደ ። "መጨረሻው ማሳዘን ፡ ፍጻሜው ማሳቀቅ ፡ የድርሰት ውበት ነው ያለው ማነው ቅቢ እንኳች በማለት ቀድሞ በገዛ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደቢቱ ሌላውን እንዳልወቀሰ ዛሬ በራሱ ብዕር ደሀን በመጻፉ ተበሳጨ ። የመጀመሪያ ሙከራው ሁለተኛ ብዕር ላይነካ የሚያስተቸው ስለ መሰለው ለእንባቢ ሕሊና ዳኝነት ሳያቢቀው ጅምር ድርሰቱን በጅምሩ አስቀረው ። በንዴት ረቂቁን በማጨቀው ። "እድያ! የጨነገፈ ብዕር!" ብሎ ቁርጥራጩን ለቃቅሞ ከቆሻሻው ቅርጫት ውስጥ ጨመረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፀሁ ሽ ራ ዉ

“ ቼኮ — ላ;ታ …. ሆ!
ቼኮ — ላ;ታ ….ሆ!
ቼኮ ላ;ታ — የማ;ታ የማ;ታ …. ”

« አትሽኟትም ወይ!.. አትሽኟትም ወይ!
መሔዴ አይደለም ወይ! …..»

ትንሿ መንደር ገና እንደ ደረሰ ከተማፈረበት አውቶቡስ ሳይወርድ በጩረፍ;ታ ይሰማው የነበረው ዜማ ከመኪናው ሲወርድ እውን መሆኑ ለይቶ ;ታወቀው ። የአንዴን መሬ ቃል ተቀብለው የሚያዜሙት የአጃቢዎች ድምፅ ከከበሮው በልጦ ጎልቶ ለመሰማት የልጃገረዶችን ላንቃ ሰንጥቆ ሲወጣ፡ የትንሿን መንደር ወርድ ዘልቆ ከራስጌ ከተንጣለለው ተራራ ;ጋር እየተ;ጋጨ ሁለት ሦስቴ ያስተ;ጋባል ። አንድ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ እየሆኑ ፈንጠር ፡ ፈንጠር ብለው የተሠሩት ባለቆርቆሮ ልባስና የሣር ክዳን ያላቸው የመንደሩ ዛኒ;ጋባዎች ከወይ ዳር የተጣለውን ድንኳን መ;ጋረድ የሚያስችላቸውን ያህል የበዙ ስላይደሉ ዳሱን የተመለከተው ከመለስተኛው አውቶቡስ ሳይወርድ ነበር ።

“ቼኮላ;ታ …. የማ;ታ የማ;ታ” አለ ፍቅሩ ከመኪናው እንደ ወረደ ፡ እንደ “እንኳን ደህና መጣህ” የተቀበለውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዜማ በልቡ እየደገመ ። ማለዳ በሐይ ጮራዋን ስትፈነጥቅ ከዋናው ከተማ ተነሥቶ የጀመረው ጉዞ የማታ ማታ ከሰበበት አዝልቆት በቼከላታ ተቀበለው ። "የማን ሠርግ ይሆን?" አለ፡ ራሱ ለራሱ መልሱን ይሰጠው ይመስል ። በትንሿ መንደር ከትንሽ እስከ ትልቁ ነዋሪ ያውቀዋል ። እንኳንስ ዓመት ኖሮበት ይቅርና ያኔ ገና በመጣ በማልስቱ ነበር መንደሬው ሁላ ያወቀው፦ መምህር ፍቅሩን ።

"ቲቸር! ቲቸር! ሻንጣውን ልያዝልዎት!" አለው አንድ ታዳጊ ወጣት ከአንድ ዛኒጋባ በረንዳ እየሮጠ መጥቶ ።

"እንደምን አለህ? አንተ ኩታራ .... እሺ እንካ ፡ የምትችለው ከሆነ" በማለት ሻንጣውን እያስያዘ በዐይኑ ወደ ድንኳኑ አመለከተውና ፡ "ምንድነው ይኼ?" ብሎ ጠየቀው ።

" የቱ?"

"ያ እዚያ ማዶ?"

"ድንኳን ነው ።"

"ድንኳን መሆኑማ ይታየኛል ። ግን የምን ድንኳን?"

"የዕድር ።"

"እሱን ማን ጠየቀህ! የሚዘፈነው ለምንድን ነው? ነው የምልህ ።"

"ዘፈን ነዋ! ቼከላታ!"

"ዘፈንነቱማ ይሰማኛል እኮ ። ለምንድነው የሚዘፈነው?"

"አሃ! ሠርግ ነዋ"

"የማን ሠርግ?"

"የሙሽሮቹ ።"

"ሙሽሮቹ እነማን ናቸው?"

"እነ ቲቸር ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንማ? አግቢዋ ማናት?"

"ቲቸር ነቻ! ቲቸር ።"

"የቷ ቲቸር?"

"የት ቤታችን ። የእናንተዋ ቲቸር!"

"ማንን ነው የምታገባው?"

"ቲቸርን ።"

"ቲቸር ማንን?"

"የእናንተን ቲቸር ነው ። ቲቸር እርስዎም ለሠርጉ ነው የመጡት?" ለራሱ ጥያቄ ሁነኛ መልስ ሳያገኝ ገጠሬው ወጣት ያቀረበለትን ጥያቄ አሰላሰለ ።

"ሌላ ትልቅ ሰው እዚህ አካባቢ የለም?" አለ ። ለራሱና ለወጣቱም ደንቃራ ጥያቄ በቂ ምላሽ ለማግኘት የሚቻልበትን መንገድ እያሰላ ።

"ሁሉም አሉ ። ድንኳኑ ውስጥ! ሻንጣውን ቤትዋ ልውሰደው?"

"የት ቤት?" አለና ወጣቱን በመገረም ተመለከተው ። ከዚህች መንደር ከወጣ ሁለት ዓመት የሞላው ቢሆንም ወጣቱ ግን የጊዜውን ርዝመት ባለማጤን አሁንም እንደቤተኛ አድርጎ ስለ ገመተው ፈገግ አለ ።

"የኔ ቲቸር ቤት! የእናንተ ቤት ። የሠርጉ ቤት" ፍቅሩ ደንገጥ አለ ።

በዱሮ ቤቱ ውስጥ አሁን የሚኖሩት እነማን እንደሆኑ ያውቃል ። ላቀረበው ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ በማግኘት ፈንታ የወጣቱ አመላለስ ያናደደው ቢሆንም ፡ የልቡን ጥያቄ ከሚያየው ሁናቴና ልጁ ከሰጠው ፍንጭ ጋር ሊያገጣጥም ሞከረ ። ከሙሽሮቹ መሐል አንዱ ሁላገርሽ አለበለዚያ ምንተስኖት መሆናቸውን ለመጠርጠር የማይችል ደደብ



t.me/OLDBOOKSPDF

አልነበረም ። ያስደነገጡትና እንቆቅልሽ የሆኑበት ፡ «ሙሽሪ ዶቱ ሁላገርሽ ከሆነች ማንን ሊታገባ? ምንተስኖትስ ከሆነ ከማን ጋር ሊሞሽር?» የሚሉት ጥያቄዎች ነበሩ በጭንቅላቱ የሚመላለሱት ። ትክክለኛው መልስ ምንተስኖትንና ሁላገርሽን ሙሽሮች ያደረገስ እንደሁ? የመጣው ለሁላገርሽ ለራሷ እንጂ ለሠርጓ አይደለም ። ያልተዘጋጀበት ዱብ ዕዳ ለድንጋጤ መጋበዙ የፍላጎት ሳይሆን የግድ ነውና ከው አለ ። የመጣበት ዓላማ ሲከሽፍ ታየው ። ለዚሁ ሁሉ ብቃት የዳረገውን ሁኔታ አንድ አፍታ አሰበ ። ከካቻምና እስከ ዘንድሮ ፡ ከትላንት እስከ ዛሬ የሆኑትንና የተፈጸሙትን የረዥም ጊዜ ገጠመኞች ፡ ከመኪና ተራው እስከ ድንኳኑ ያለውን ርቀት ለመጨረስ በፈጁበት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በጨረፍታ አያቸው መምህር ፍቅሩ ።

እንደ ጨረቃ ከብና ጠፍጣፋ ቅርጽ ያለው የአናት መብራት ጠፍቶ ፡ ባለ ቀይ ቀለሙ የራስጌ መብራት ሲበራ የመኝታ ቤቱን የበለጠ አሳምሮታል ። ደንገዝገዝ ብሎ ግን የቤቱን ሁለመና ማሳየት የሚችለው ቀዩ የሌሊት መብራት ክፍሉ ውስጥ ያሉትን ቁሳቁሶችና አልጋው ላይ የተኙትን ጥንድ አቅልሞ በውበት ላይ ውበት ጨምሮላቸዋል ። ከግራ ቀኝ ማዕዘናት ርቀቱን እኩል ጠብቆ ማዕከላዊ ቦታ ይዞ የተዘረጋው ሠፊ አልጋ ከሁለቱ በቀር ሌላ አንድ የእነሱ ዐይነት ጥንድ አጣምሮ መጨመር የሚችል ነው ። የአልጋው ልብስ ወርቃማ መልኩን ከተቀበለው የአምፑል ቀለም ጋር አዋህዶ የብርድ ልብሱን እኩሌታ ሸፍኖ እስከ ግማሹ ድረስ ተገልጧል ። እንደ ውጪው አየር ሁኔታ ተፈላጊውን ሙቀት በተፈላጊው ወቅት መስጠት የሚችለው ብርድ ልብስም ዶማቁን ነጭ አንሶላ እስከነአካቴው አላለበሰውም ። በጠራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስማይ ግርጌ በተንጣለለው ውብ ሐይቅ ዳርቻ ዕርቃናን የቆሙት ባለ ረጂም እግር ፡ ሌላ ቆንጆ ሴት የምትታይበት የራስጌው የፎቅ ፍሬም ምስሉን ከፊት ለፊቱ ላለው ሦፊ የቁምሣጥን መስታወት እያንጸባረቀ ከግድግዳው ቀለም ጋር በቅጡ ተዛምዶ ለክፍሉ ተጨማሪ ጌጥ ሆኖታል ። በተጨማሪ ከግድግዳው ጥግ እስከ ጥግ የሚደርሰውን ባለ ብርጭቆ መስታወት መስኮት ሙሉ ለሙሉ የጋረደው የሐር መጋረጃ የመኝታ ክፍሉ ልዩ ውበት ነው ።

ከአልጋው ጋር ተጋጥመው ከራስጌ ቀኝና ግራ በተሠሩት ኮመዲኖዎች ላይ በአንዱ የሲጋራ መኮስተሪያ ፡ መለኮሻና የተከፈተ የሲጋራ ፓኬት ፡ በሌላኛው ግማሽ የጐደለ የውስኪ ጠርሙስና ሁለት የተሞሉ መለኪያዎች ተቀምጠው በታል ። ከዶረቷ በታች በነጩ አንሶላ የተሸፈነችዋ ቤተል ሔም እኛን በከፊል ከፍታ ድብን ብላ ተኝታለች ።

ፍቅሩ በዝግታ ቀና ብሎ ከሁለቱ የውስኪ መለኪያዎች አንዱን ጨለጠና ዐይኑን ከፊት ዘጋ በማድረግ እየጨመቀ የክፍሉን ሁለመና ከላይ እስከ ታች ማተረ ። መለየቱ ያሳዘነውና ቅር ቅር ያሰኘው ከቤተልሔም ከሰውነቷ ይልቅ ይህንን መኝታ ቤቷን ነበር ። መለስ ብሎ ግማሽ ዕርቃናን የተኛችውን ቤተልሔምን አያት ። ውብ ነች ። ቀንጅናዋን ምራቁን በመዋጥ ለራሱ መሰከረ ። ቢሆንም ያጋራችው የአኗኗር ደረጃዋ ፡ ያቀመሰችው የምቾት ሕይወትና ቦርሣው እንዳይራቆት የረዳው ንዋይዋ ባይደመር ኖሮ ውበቷ ብቻውን እንደማያሸንፈው ጠንቅቆ ያውቀዋል ። የልጅነት እይታዋ በደመ ነፍስ ልቧ እንዲርድና ከእሱነቱ መካከል በአንድ ተሰጥአና ምግባሩ ጊዜያዊ ሽንፈት ላይ ጥሏት እፍፍ ብላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትወደዋለች እንጂ ፍቅራቸው ጽኑ መሠረት የሌለው በመሆኑ እንደማይዘልቅ የገባው ገና ከመጀመሪያው ነው ። ብቻ ሎሬቶንቷና የእስተዳደጓ መረንነት ፡ ትሆናለች ብሎ ዱሮ የሚያስባትን ሔዋን ዐይነት ባትሆንም ጥሬ ፍቅሯን እሷ ሳታውቅ እየከፈለችበት ፡ እሱ ግን በነጻ የተጋበዘው በመሆኑ ፊቱን ሊያዞርባት አልቻለም ። እይዘልቅም እንጂ መዝለቅ የሚችል ቢሆንማ በማን ዕድሉ ! ግን እምነቱንና ሰብአዊ ግምቱን ለንዋይ ሲል መለወጡን ለአንድ አፍታ እንኳ ማመን አይሻም ። “ከወደድችኝ ልወዳት እችላለሁ ። ደግሞም ብርቱ ከሆንኩ ልለውጣት የማልችልበት ምክንያት የለም ። ድንገት የእይታ ውዴታ ከመቀራረብና አብሮ ከመሆን ወደ እውነተኛ ፍቅር ሊያድግ የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም ። ደግሞስ በወግ ከተገራች ፡ በቅጡ ካስተዋለችና ከፍቅረ ንዋይ ይልቅ በጎ ምግባርን እንድትማር ከተደረገ ፡ እእምሮዋ በመልካም ሊታነጽ የማይችልበት ምን ምክንያት አለ?” በማለት ራሱን እየሸነገለ ድርጊቱን ዘወትር ለመጠየቅ ይጥራል ። ወጣም ወረደም ግን ለፍቅር ሲል እንደማይወዳት ያውቃል ። “ማንም ሊጋበዘው የሚችለውን ገላዋን ለማግ ኘት ስል መጥፎ ድርጊት እስከልፈጸምሁ ድረስ የጥሩ ሕይወቷና የተድላ ኑሮዋ ተካፋይ መሆኔ ነውር አይሆንብ ኝም” ይላል ለራሱ የሕሊናው ሙግት ስሕተተኛነቱን እያከበደ ገፍቶ የመጣበት ዕለት ። ግን ሙሉ ለሙሉ ተስፋውን አላመነመነውም ። ለጋብቻ ሊበቁ እንደሚችሉ ትንሽ ትንሽ ጭላንጭል ይታየዋል ።

ቤተልሔምን የሚያውቃት ገና ዱሮ ሕፃን ሳለች ነው ። ያኔ እሷ እሱን አታውቀውም ። የበቃላቸው የሀብታም ሰው ልጅ ነበረች ። ለወላጆችዋ አንድ በመሆኗ እንደ ዐይን ብሌን



t.me/OLDBOOKSPDF

ተንከባከበው ነው ያሳደጓት ። መሜወቻ አሻንጉሊቶቿ ለዛች እንዲት ሕፃን የተዘጋጀው ብዙ ሕፃናትን ሊያስተናግድ የሚችል ፡ የግቢያቸው መዝናኛ ሥፍራ ፡ የኸርቀኸርዊው ፡ የመኸከርከሪያው ፡ የመንሸራተቻው ፡ የብስክሌቱ.... ምኑ ተወርቶ ያልቃል ። እንኳንስ ለድሃ ልጆች ይቅርና ደህና ለሚባሉት የአካባቢው ነዋሪዎች ብርቅ ሆና ያደገች በመሆኗ ቤተልሔምን በሠፈሩ የማያውቃት የለም። አባቷ ቀድሞ የመንግሥት ባለሥልጣን የነበሩ ከመሆናቸውም በላይ በገጠርና በከተማ ከርስት አንሥቶ እስከ ኪራይ ቤቶች ፡ ከእርሻ ትራክተርና እስከ እህል ወፍጮ ፡ ከበርካታ የርባታ ከብቶች እስከ ሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶችና ሌሎችም የነበሯቸው የጠገቡ ሀብታም ነበሩ ።

እንዳለ የሚኖር የለምና የብዙ ሠርቶ አደሮችን ወዝ እንደ ሎሚ መጦ የተገነባው ንዋይ ቀድሞ የነበረውን ይዞት እንደ ጨበጠ አልቀጠለም ። ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ሁሉም በየደረጃው ለየተገቢው ሥራና ድርጅት ወደ ሕዝብ ንብረትነት በመሸጋገሩ ፡ ከሕዝቡና የሕዝቡ የነበረው ወደ ትክክለኛ ባለቤት ንብረትነት ሲለወጥ የቤተልሔም ቤተሰቦች እብጠትም በመጠኑ ተነፈሰ ። ብቻ በጥሬ የነበረው ገንዘብ ፡ የመኖሪያ ቤትና አንዲት አውቶሞቢል ቀርታቻዋለች ። እናም አሁንም ቢሆን ያጡ የነጡ የሚባሉ ሳይሆኑ ፡ ጣራ ያለፈ ከበርቴም ሳይባሉ የተደላደለ ኑሮአቸውን ቤተልሔምና እናትየው አላጡም ። አባትየውን ግን ገና የለውጡ ሰሞን፤ ብዙ ጊዜ አብሯቸው የኖረው የልብ ድካም ተቀስቅሶ ፋታ ሳይሰጥ ለሞት ዳርጓቸዋል ። የቤተልሔም እናት ለረዥም ጊዜ ጥቁር ልብሳቸውን ባያወልቁም ጥቂት አዝነው ያን ማንም የማይደፍረውን የመኖሪያ ቤታቸውን ፡ "ምርጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሀገር ባህል ምግብ ቤት" የሚል ስያሜ በመስጠት አቅሙ ለፈቀደለት ሁሉ በራቸውን ክፍት በማድረግ ልዩ የንግድ ሥራ ተያይዘዋል ።

ፍቅሩ በዚያው መንደር ውስጥ በአንድ መጠነኛ የመኖሪያ ቤት ብቻውን የሚኖር ሀመለ ሸጋ ወጣት ነው ። እንደነቤተልሔም የተንዛዛ ሀብት ባይኖራቸውም ወላጆቹ መጠነኛ ኑሮ የሚኖሩ ፣ በጠባያቸውና በመልካም ምግባራቸው የተመሰገኑ ፣ ጎረቤት ሁሉ የሚወዳቸው ጨዋዎች ነበሩ። የፍቅሩ ወላጆች በተከታታይ የሞቱት ገና ፍቅሩ ከመምህራን ኮሌጅ ሳይመረቅ ነበር ። ለእሱ እንግዳ ያልሆነችውን እሷ ግን የማታውቀውን ቤተልሔምን መጀመሪያ በአይኑ የነደፋት በወጣት ማኅበራቸው አማካይነት ለቀበሌው ሕዝብ ቴያትር ባሳዩበት አንድ በዓል ላይ መሪ ተዋናይ ሆና በተጫወተበት ዕለት ነበር ። የተዋናይነት ተሰጥዎው በቤተልሔም ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በተመልካች ላይ ትዝታውን ጥሎ ያለፈ ነበር ። ከዚያ በቀር ጊታር መጫወት የሚችልና ድምፁም ማራኪ ስለነበረ ከዚያን ዕለት ማራኪ ዜማዎች መሐል በተመልካቹ እንዲደገም ሳይጠየቅ ያለፈ አንድም አልነበረም ። ከዚህ ተሰጥኦውና ችሎታው በቀር ፍቅሩን ምንንም የማታውቀው ቤተልሔም ፣ የቅምጥል ሕይወቷ ለማመዛዘን ያላበቃውን ልቧን ፣ የፍቅሩ ተዋናይነት፣ የጊታር ችሎታና ድምፅ ከመልካም ቁመናው ጋር ተዳምሮ አራደው ።

አንድ የሳምንት መጨረሻ ከመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ተመልሶ ወደ ቤቱ በሚወስደው መንገድ አንገቱን ደፍቶ ሲራመድ ፣ ቤተልሔም ከቅጥር ግቢያቸው በራፍ ላይ ቆማ ጠበቀችው ። አጠገቧ እንደ ደረሰም "ሀይ ፍቅሩ! እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ዋልክ?" አለችው   አሰባበሩና ዜማው በተስተካከለና ባማረ እንግሊዝኛ ።

"እንደምን ዋልሽ ቤተልሔም" አላት ፍቅሩም አፀፋውን በአማርኛ መልሶ ።

አለወትሮዋ ሰላምታ ስለ ሰጠችው እየተገረመ አቀርቅሮ መንገዱን ሊቀጥል ሲል ፡

"የቤትህ መንገድ ጠፍቶብህ ተሳስተህ ሌላ ቤት ሔደህ አታውቅም?" አለችው እጇን ዘርግታ እንደ ነገሩ መንገዱን እየዘጋችበት ።

"የቤቱ መንገድ እኔ ጠፍቼበት እንደሆን እንጂ እሱስ ጠፍቶብኝ አያውቅም ። ግን ጥያቄው እንዴትና ለምን ተነሣ?" አለ ግራ በመጋባትና እርግጠኛ ባልሆነ አመለካከት።

"ጥያቄው የተነሣው ለመግባቢያና ሐሳብ ለመለዋወጫ በር እንዲከፍት በማለት ብቻ ነው ። የቤትህን መንገድ የምትጠፋበት እሱ ሳይሆን አንተ መሆንህን በተግባር ለመተርጐም ትችላለህ?"

"ይህ በተግባር እንዲተረጐም የኔን ፈቃደኛነት የሚጠይቅ አይደለም ። ዳሩ ምንም ያልበደለኝን ቤቴን እንደምን በፈቃዴ እጠፋበታለሁ? በጊዜያዊ የሕሊና መምታታት ላፍታ ብስተውም አቅሌን ስገዛ እመለስበታለሁ ። ግን ቢልቱ የት የሚያደርስ ነው?"

"ምሳ ልትጋብዝህ ሙሉ ፍቃደኛ ወደሆነችው ወደ ቤተልሔም ሳሎን ።"

"ከልብ አመሰግናለሁ ። ታዲያ የእኔንስ ፈቃደኝነት ከጥያቄ ውስጥ አኑረሽዋል ?"

"እንዴታ! ቢልቱን ልተወውና ወደ ፍሬ ነገሩ ልመል



t.me/OLDBOOKSPDF

ስህ ። ለቁም ነገር ስትፈለግ እምቢተኛነትን እንደሚታሳይ ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁና እኔም የፈለግኩህ ልታስረዳኝ ትችል እንደሆነ አንድ ያልገባኝን ጥያቄ እንድታብራራልኝ ነው ። በመንደሬችን ጥሩ ሥነ ምግባርን ከበሰለ ልቡና ጋር የተለገ ስክ አንዱ በመሆንህ ምሁራዊ ምክር ብጠይቅህ አታሳፍረ ኝም በሚል ነው ። ርዕሱ ሊሰፋ ስለሚችልና በዚህ አጋጣሚ የምሳ ሰዓትም በመሆኑ እቤት ጎራ ብለህ እንድንወያይ ብዬ ነው” አለችው የሚያማምሩ ፍንጭት ጥርሶቿን በውብ ፈገግታዋ እያጋለጠች ።

ፍትሩ ከሌለው ጸጋ በላይ ባወረደችበት የሙገሳ ካብ ልቡ ከማበጥ ይልቅ የዐይኑ ሽፋን እየከበደው በኃፍረት እንዲያቀረቅር ተገደደ ። እጇን ይዛ ጎትታ አስገባችው ። ፈራ ተባ እያለ ተከተላት ።

በዚያ ገነት በመሰለው የቢተልሔም የምግብ አዳራሽ ውስጥ እንደተቀመጠ ፍርሃቱ እየጨመረ መጣ ። ግን የቢተልሔም ጨዋታ ፡ እቤቷ ውስጥ በተቀጠሩ መምህራንና በድምፅ መሣሪያዎች የተማረችው የቋንቋ ችሎታ ፡ ቀልድ ዐዋቂነቷና ቧልተኝነቷ ቀስ እያለ አዝናናው ። ምርጥ ምሳ ውድ ከሆኑ የውጭ አልኮል መጠጦች ጋር ተጋበዘ ። በመጨረሻም ፍርሃቱ እስከናካቴው ለቀቀው ። በተለይ የቢተልሔም ርዕስ እሱን በጣም ሊስበው የቻለ ኪነትና ሥነ ጽሑፍ ነክ በመሆኑ ፡ ከአስተዳደግ መረንነት የተነጣ ተራ ነች ብሎ የሚገምታት ቢተልሔም በኪነት መስክ የመጠቀች ሆና ስላገኛት እዚያ የቆየበትን እያንዳንዱን ደቂቃ ወደደው ። የእናቷ እቤት አለመኖርና ሠራተኞቿም ቢሆኑ የደወል ጥሪ ካልሰሙ በቀር ብቅ የማይሉ በመሆናቸው ፍጹም ብቸኝነት እየተሰማውና ከቢተልሔምም የብዙ ጊዜ ትውውቅ እንዳላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቾው ሁሉ እየተግባቡ ስለዋሉ ቀኑ ሲመሽም ጨርሶ አልታወቀውም ። ሳያስበው ፉት የሚለው አልኮልም መጠኑ እየጨመረ በሔደ ልክ የራሱን ድርሻ ተጫውቷል ። የተቀረው አላስቸገረም ። ወደ መኝታ ቤቷ ሲገቡ አዲስ ነገር መስሎ አልታየውም ። ከገዛ ቤቱ ውጭ እሌላ ሰው መኖሪያ ቤት መኝታ ላይ መውደቁም አልታሰበውም ። ግራ መጋባት ፡ በሆነውና በተፈጸመው መደነቅና መገረም ፡ ሕልም መስሎ በሚታይ እውነት ውስጥ መውደቁ ሌሊቱ እስኪነጋ ድረስ አልታወቀውም ነበር ። ሳያውቀው የከረመ ረኀቡን ተወጣባት ። እሷም የወረት ጥሟን ረካችበት ። የውኑ የዐሥራ አንድ ስዓታት ምሽት የዐሥራ አንድ ደቂቃን ያህል አልቆየላቸውም። የዐሥራ አንድ ደቂቃው እቅፍት ግን የዐሥራ አንድ ዓመታትን ያስታ አከለላቸው ፡ ለእሱም ለእሷም ። ፍቅሩ ፡ በተከታዮቹ ዕለታት በድንገቴው ድርጊት ሸበብታ ላይ እወድቃለሁ ብሎ እንደ ሠጋው ተሸብቦ አልቀረም ። ይልቁን ውስጣዊ ግፊቱ እየበረታ እናቷ ሳይቀሩ ለተመልካች ሁሉ ደንታ ቢስ በመሆን ሳሎኑንና መኝታ ቤቷን አዘወተረው ። ፋታ ስላልሰጠችው ፋታ ሳይሰጣት ስላዘወተራት በዕድሜና በልምድ ያልሰከነ መላ አካሏን በቁጥጥሩ ሥር አዋለው ። እሱ እሷን እንደሆነ ሁሉ ለሚለብሰው ፡ ለሚጫማው ፡ ለሚበላው፡ ለሚጠጣው ሁሉ ትጠበብ ጀመር ። እጇ አጭር ስላልነበረ ሰው ላይ ሲያምር ያየችውን ሁሉ እንዲያምርበት አደረገች ። እሷነቷን ለእሱ ከማቅረቧም በላይ ቸር እጇ ገባው። አብረው ከረሙ ። እስከ ተመረቀበት ጊዜ ድረስ የነበረው የስምንት ወር ዕድሜ የስምንት ቀን ያህል ሳይሰማው አለፈ ።

ለጊዜው በመምህርነት ተመድቦ ወደ ክፍለ ሀገር



t.me/OLDBOOKSPDF

መውጣቱ አሳስቦት ነበር ። እሷም ብትሆን "ምናባቱ ይትረፍ! ለየትኛው ሥራና ይመጠገን ነው ቁንቀቱ" ሳትለው አልቀረችም ነበር ። ሆኖም ለጊዜው እና ያስባለው ምናምኗ ሁሉ በዓመታት የተገነባ የእስተሳሰብ ጥርቅሙን አልመዘነበትም። እራሱ እምኖበት መሔዱን የግድ አሳመናት ። አንድ ዓመት ማለት ከአንድ ሰው ዕድሜ በጣም አጭር ጊዜ እርዝማኔ ነው ብሎ አጽናናት ። ግን ተመልሶ ሲመጣ ይህ የቀመሰው ሁሉ እንዳይቀር በቃል ኪዳን ጸንታ እንድትጠብቀው ተማጠናት ። እሷም ተማጠነችው ። ነገርን በርቀት ጠሊቃ ሳታይ ለዳኘንኗ ሁሉ ዛሬን ብቻ እየጠየቀች እጠብቅሃለሁ አለችው ። በዚህ ተማምለው ነበር የመጨረሻ አዳራቸውን አዲስ በተከፈተው ውስኪ በውቡ መኝታ ክፍሏ ሊያሳልፉ የበቁት ።

የመኝታ ክፍሏ ጣራና ግድግዳ የሲኒማ ቤት አቡጀዲ ይመስል የስምንቱን ወራት የሱንና የቤተልሔምን የፍቅር ጊዜ በአጭር ደቂቃዎች ውስጥ አየበት ። ገልበጥ ብሎ ፊቱን ወደ እሷ መልሶ ስስ ገላዋን እየዳበሰ ታሽቶ እንደ እንጀራ በቀላው ከንፈሩ ግንባሯን ፡ ዐይኗን ፡ አፍንጫዋን ይነካካ ጀመር ። "ደህና ሰንብት አንተ ቤተ ገነት ፡ የቤተልሔም መኝታ ቤት ። ደህና ሰንብች አንችም ውዴ ፡ እንግዲህ አልቀረም መሔዴ" እያለ ተጣበቃት ። ሙቀቷ እየሞቀው ፡ እየጋለ በጣም ቀረባት ፡ ተጠጋት ። እንደ አጀማመሩ መሆኑ ቀርቶ ዳበሳው ጠንከር ፡ ጫን ያለ ሆነ ። እጁ ከአንሶላው ውስጥ ወደ ውስጥ ዘለቀ ። ቤተልሔም በዝግታ ተንቀሳቅሳ ዐይኗን በተንሸ ገለጥ አረገችው ። ለከናፍሩ ጥያቄ ከናፍሯ ተገቢውን አፀፋ መለሱ ። ላፍታም ቢሆን ሁለቱም ያሉበትን ሥፍራ ረሱ ። ብቻ ሄደው አልቀሩም ። ወደ ራስነታቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ተመለሱ ። ነጋ ። ከእናቷ ቦርሳ የመኪናውን ቁልፍ አውጥታ አውቶቡስ ተራ ድረስ ሸኘቻቸው ። እሷ በአውቶሞቢሏ ወደ ከተማ ሺላዋ ፡ እሱም በአውቶቡሱ ወደ ገጠር ጐጆው ሁለቱም በየፊናቸው ተጓዙ ።

ቁልቁል የተጻፉትን የዕጣ ወረቀቶች እንዳፍታ ተመለ ከታቸው ። እንደ አዲስ አበባው ግን የዕጣው ጉዳይ አላሳሰበ ውም ። ያኔ አስጨናቂ የነበረው የትኛው ክፍለ ሀገር እሔድ ይሆን የሚለው ነበር ። ወደዚህ ክፍለ ሀገር ከመጣ በኋላ ግን ወደ የትኛውም አውራጃና ወረዳ ቢመደብ ግድ አልነበረ ውም። ሳያመነታ አንዱን ብድግ አደረገ ። እፊት ለፊቱ የተቀመጡት ሰው ወረቀቱን ተቀብለው አነበቡት ። ፊቱ ላይ ቅሬታ ባለማየታቸው እየተደነቁ የሚሞላው ፎርም ላይ የአውራጃውንና የወረዳውን ስም አሠፈሩ ።

መምህር ፍቅሩ ወደዚች መንደር መጀመሪያ የመጣው በእንዲህ ዐይነት ነበር ። የወረዳዋ ከተማ አነስተኛ መሆን አላስጨነቀውም ። የሚያስተምርበት ት/ቤት ከመንደሩ የ3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ መሆኑም አላሳሰበውም ። የአንድ ዓመት የአገልግሎት ዘመኑን እስኪጨርስ ድረስ ለወረዳውና ለአካባቢው ሕዝብ ሊያበረክት ስለሚችለው ድርሻ እንጂ ከአዲስ አበባ ከመውጣቱ በፊት ሲያስጨንቀው እንደ ነበረው ከዚያ ትልቅ ከተማ ወጥቶ ገጠርን መልመድ እንደምን ይቻላል የሚለውን እርግፍ አድርጎ የተወው ወዲያው ነው ። ከተማዋንና ነዋሪዎቹን ሊለምዳቸው ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም ። ከአኗኗራቸው ዝቅ ማለት ፡ ከሥልጣኔ ራቅ ብለው መገኘታቸው እንጂ በሰውነታቸው ሊቀረቡ ፡ ሊወደዱ ፡ ሊፈቀሩ የሚችሉ ሆነው ነው ያገኛቸው ። ለአስተማሪ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነት የመጀመሪያ ጊዜው ቢሆንም ሙያውን ለመውደዱና ከተማሪዎቹም ጋር ጥሩ ዝምድና ለማትረፍ የወሰደበት ጊዜ አጭር ነበር ።

ከመምህርነቱ ጋር በመንደሩ የተከበረ ትልቅ ሰው ሆነ። በአካባቢው በልማትና በማኀበራዊ ኑሮ እንቅስቃሴ ንቁ ተሣትፎ በማሳየቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በልጅ በሀዋቂው ተወዳጅነትን አተረፈ ። የወረዳው የመሠረተ ትምህርት ኮሚቴ ጸሐፊ ሆኖ ከመመረጡም ሌላ የወረዳው የልማት ኮሚቴ አባል አደረጉት ። ሽማግሌው ወጣቱ ፡ ባልና ሚስቱም፣ በተጣሉና ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ለእርቅ ይጠሩ ጀመር ። ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ትልቅ ሽማግሌ ሆነ ፡ ወጣቱ መምህር ፍቅሩ ።

“ኧረግ! አድባሬቱ ተቀብላህም የለ እንዴ !” አሉ አንድ አዛውንት የመጣ ሰሞን መንገድ ላይ አግኝተውት ።

“እንዴት ማለት!”

“እንዴትማ ይኸው የጠበደለ ሠንጋ መስለህ! የግንባርህ ወዝ ከርቀት ያብረቀርቃል” አሉ እየቀለዱ ።

“አዎን ተስማምቶኛል ። እናንተን የመሰለ ዘመድ አግኝቼ እንዴት አይስማማኝ ብለው” አለ ፈገግ ብሎ ።

“ጎጆ አፍርተሃል ወይስ በነጠላው ነው እንዲህ የተወለወልክ?”

“መኖሪያማ ወዲያው ነው ያገኘሁ ። ቀድሞ ከነበረው መምህር እሸቱ ጋራ ተዳብያለሁ ።”

“እሱንማ መቼ አጣሁ?”

“ታዲያ ምኑን ነው የጠየቁኝ?”

“የመኝታው ጉዳይ ነዋ! በምኑም በምኑም የሚደጋገፍ ጥሩ ሴት ባትገኝ አካባቢውም ደግየ ነው ፡ ቶሎ ነው የሚደላ”



t.me/OLDBOOKSPDF

አሉት ግራ ሊገባው አባባላቸው ማብራሪያ ለመጠየቅ አፉን እንደ ከፈተ ፋታ ሳይሰጡት ።

"በነገራችን ላይ ልጄን ለምንድነው ያወደቅኸው?"

"የቱ ልጅዎን?"

"ደሞ እሱ ጠፋህ? አንተነህ ቀጥአርጋቸውን ፡ የእኔን ትልቁ ልጄን ፡ ስድስት የደረሰ አንዱ የእኔ ልጅ ።"

"ታዲያ ምን አወደቅሁት?"

"አወደቅኸው እንጂ ! ሌላውንስ እሺ ባዕድ ባዕዱን ይሳተው ። አፉን የፈታበት የእናት የአባቱን ቋንቋ ጠፋው ብለህ ነው ባማርኛ ያወደቅኸው?"

ፍቅሩ የሚሰጠው መልስ ጠፋው ። ልጃቸው የወደቀበትን ምክንያት ለማስረዳት ሞከረ ። ሊያሳምናቸው ግን አልቻለም ። ብቻ በጥሞና አዳምጠውት ሲያበቃ — "በል ደግ ነው ለወደፊቱ አስጠንቅቀዋለሁ ። አንተም ለቀቅ አድርገው ታዲያ! አንዳንዴ እኮ ስሕተታችሁ የጉድ የሚያሰኝ ነው ። ይኸው በሙያዋ ንብ የተሰኘችው የእኅቴ ልጅ ሙጭት እንኳ ባልትና ትምህርት ወደቀች ቢሉኝ የጉድ ነው ያልኩት ። እናቲቱም በወጡም ፡ በፈትሉም ፡ በማዕድቤት ሥራ የሚተካከላት የለም ። ልጅቱም በዚሁ ወጥታ ነው መሰል ፈትሏ መነን ፡ የዶሮ ወጥዋ ጣት የሚያስቆረጥም ፡ ጠላዋ የዶሮ ዐይን የመሰለ…ኧረ እንዳው ተወኝ አንዳንዴ…" ብለው የጀመሩትን ሳያበቁለት ፡ "በል ብዙ አላቁምህ ። እኔም ሸንጎ አለብኝ ደህና ዋል" ብለው እንደ ፈዘዘ ጥለውት ሔዱ ።

ይህን የመሰሉ ብዙ አስደናቂ ነገሮች ዘወትር ይገጥሙታል። ታዲያ ከብዙዎቹ ትምህርት ወሰደባቸው እንጂ በሰዎቹ አላዋቂነት አልተሣለቀም ። ይልቁንም ለሕዝቡ ያለው ፍቅር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ነው የሔደው ። የጥቂት ወራት



t.me/OLDBOOKSPDF

የከተማው ፍቅር ትዝታ ዐልፎ ዐልፎ ቢጎበኘውም ከግዴታው ፡ አካባቢውን ከመለማመድና ሙያውን ከመውደድ አልገታውም ። በወር በሁለት ወር ፡ የበረታ ሲሆን በሳምንት፡ ከፋ የተባለ ለት በየዕለቱ ቤተልሔምን እየዘከረ ፡ ለእሷ፡ በትንሹ ለቅምጥል ሕይወቷ በብዙ መናፈቁ አልቀረም ነበር።

እንዱ የት ቤቱ መምህር ቤቱን አዳብሎታል ። ፍቅሩ ምግባሩ ፡ "እሱን በሆንኩ" የሚያሰኝ ስለነበረ መምህራኑ ከጓደኝነት አላራቁትም ። ቶሎ ነው የተግባቡ ። ጓደኛው የቤት ሠራተኛ ስለ ነበረው የቀለብ ችግር አልገጠመውም ። ሌሎች መምህራን በአቅራቢያው ይኖሩ ስለ ነበር ብቸኝነት እንኳ ብዙ አልዳሰሰውም ። በተማሪዎቹ ብዙውን ጊዜ ይደሰታል ። ከማሰብ ደረጃዎች እያስተካከለ ዝቅ ብሎ ሊገባቸው በሚችል መንገድ ያስተማራቸውን ሲይዙለት ይፈነድቃል ። ሳይገባቸው የቀረ እንደሆን ደግሞ ድክመቱ የራሱ እንደሆን ሁሉ ይከፋል ። በእንዲህ ዐይነት የገጠሩ ሕይወት ብዙ ሳይመስለው ሰባት ወራት ያህል ተገባደደ ።

ብቻ ብዙ የጊዜ ቀዳዳ ስላልነበረው የትዝታው ሙግት ቢመጣም አልጋው ላይ ጋደም ሲል ነበር ። ይህም ድካም ተጫጭኖ እስኪያሸልበው ድረስ ። በመደበኛው የትምህርት ሰዓት ት/ቤት ፡ በምሽት መሠረተ ትምህርት ፡ በሰንበት፡ የልማት ኮሚቴ ስብሰባና የሽምግልና ሸንጎ ...በየሥራ መስኩ ተጠምዶ ነበር ። ጊዜው ከተለመደው አካሔድ የተቀየረ መስሎ ሲያዘግምበት የከጀለው ፡ ያዳበለው ጓደኛው የእሸቱ፡ ድንገተኛ የቅያሬ ደብዳቤ ሲመጣ ነበር ። ጓደኛው እሸቱ ቤቱንና ሠራተኛውን ጥሎለት ተሰናብቶት የሔደ የዕለቱ ዕለት ነበር ቤቱ እና የመሰለው ። ያን ዕለት ቤተልሔምን በጣም አስታወሳት ። አሰባት ። ሔጂ እያታለሁ ብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያሰበበት የክረምት ወራት በጣም ሩቅ መስሎ ታየው ። ደብዳቢ በብዙ አለመጻጻፋቸውም የተሰማው ያኔ ነበር ። እሱ ሁለት ረገፕዥም ደብዳቤዎች የጻፈላት ቢሆንም ፡ ከእርሷ የደረሰው ምላሽ፡ አጥጋቢ አልነበረም ። ከአራት ወራት ቀደም ብሎ ከአንድ ባለ ቀለም ፎቶግራፍ ጋር የላከችለት ደብዳቤ የሚያረካ አልነበረም ። ብቻ ተስፋው እስከንአካቴው አልጨለመበትም ።

"....ሀይ ....ፍቅርዬ! የጻፍከው ደብዳቤ ያሳለፍነውን ጊዜ የሚያሳስብ ነው ። ሆኖም መልእክትህ የሚተነብየው ምንም ነገር የለም ። እርግጥ ያኔ በስምንቱ ወራት ድንቅ ጊዜዎች እንደ ነበሩን እንደ ሲኒማ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ። በተመረጡ ቃላት የተዋቡ ዐረፍተ ነገሮችን ያዘሉ ደብዳቤዎችህ ፡ እንዳለሁ እንድጠብቅህ አደራ በማለትህ ግን ገጠሩ ገጠሬ ያደረገህ መሰለኝ ። ምነው እንዳለሁ የምቆይ? ስታስተምረኝ የነበረው ባለበት የሚቆይ ፡ እንደነበረ የሚ ኖር፡ ምንም ነገር እንደሌለ ....ሁሉም ተለዋጭ ፡ አዳጊ ... መሆኑን፡ አይደለም! ታዲያ ብማርልህስ ...'ብህ' — አይደ ለም 'ልህ' ነው ፡ ብማርልህ ። አባባሌ ከገባህ ሰርዞኝ የሚል ነገር እንደሌለው ትረዳለህ ። እና ወጣ ብዬ ለመማር አቅጃለሁ። ፈረንጅ አገር ። አንድ ጀርመን ኤምባሲ የሚሠራ ጀርመናዊ ለመውጣት እንድችል የሚረዳኝ መሆኑን ቃል ገብቶልኛል ። ተሳክቶልኝ የምሔድ ከሆነ እጽፍልሃለሁ ። እስከዚያው ፎቶግራፌን እነሆ ..." ቤተልሔም ...ትራማይሴ ነው የሆነበችት ። መለወጥና መቀየር ከሆነም ቀደም ብሎ ይገምተው የነበረ በመሆኑ እስከናካቴው ቅስሙን አልሰበረ ውም ። እንደ ነገሩ ቀናነት ያለውም ስለሚመስል የሚያጣት አልመሰለውምና ተስፋው አልሟሟም ። ግን ደብዳቤውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ካገኘበት ዕለት ይልቅ ብዙ አውጥቶ ያወረደውና በነገሩ የተብከነከነው ጓደኛው የተቀየረ ጊዜ ነበር ።

ሁኔታውን የሚያባብስ ነገር አላጣውም ። ጓደኛውን መምህር እሸቱን በሽኝ ማግሥት እቤት ሲገባ ሠራተኛዋ ዕቃዋን ቀርቅባ አያት ። ግር ተሰኝቶ ጠራትና ፡ "ምን ነው?" አላት ።

"እንዴት ምነው?"

"ዕቃሽን ቁጣጠርሽ እሳ?"

"መሔዴ ነዋ! ከእንግዲህ ምን አደርጋለሁ?"

"እንዴት ምን አደርጋለሁ! እኔ እኮ ሌላ ሠራተኛ የለኝም ። እሸቱ ይከፍልሽ የነበረውን እከፍልሻለሁ ።"

"እንዴት ይሆናል?"

"እንዴት ነው የማይሆነው?"

"ኧረ ነውር ነው ጌታዬ ሰው እንዳይሰማ።"

"ምኑ ነው ነውር! ሠርተሽ እየበላሽ አብይኝ ማለት?"

"የገዛ የጓደኛዎትን! ዝም ይበሉ አገር ጉድ ይላል።"

"አገር ጉድ የሚል እንቺን! በገዛ ብሬ ልቅጠር ባልኩ.....?"

"አሁን ከልብዎ ነው?"

"እንዴት ነው ከልብዎ ነው ማለት?"

"ጓደኛዎ የለመደውን ገላ ሲመኙ ገላዎ እሺ ይሎታል....."ደነገጠ ። ብዙ ግር የተሰኘ ይሁን እንጂ መጨረሻ ላይ አባባልዋ ጥርጣሬ ላይ ጣለው ። ይህን ሁሉ ጊዜ ሲቀመጥ ጠበብ ባለችው ክፍል ውስጥ እሱ ብቻውን ፡ ጓደኛው ሰፋ ያለው ክፍል ውስጥ ከሷ ጋር መተኛታቸውን ከምንም ነገር ጋር አገናኝቶት አያውቅም ነበር ። ለሠራተኛዋ ለብቻዋ አልጋ አለመኖሩን እንኳ አጢኖት አያውቅም ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ይቅርታ የእኔ እኅት አልገባኝም ነበር ። ሆ …ሆይ! ግን" አለ ትንሽ ሲያመነታ ቆይቶ በእጆቻቸው ጫፍ ግንባሩ ላይ ጠፈፍ ያለውን ወዝ እየጠረገ፡ "ግን አንድ ሁለት ቀን ሌላ ሠራተኛ ..ማለቴ የቤት ሠራተኛ እስካገኝ ለመቆየት ፈቃደኛ ብትሆኚ…." እንጠልጥሎት ትክ ብሎ አያት ።

እንደ መሽኮርመምና እንደ ማፈር ዐይኗን ወደ መሬት ሰበር አደረገች ።

"…እ… እርስዎን ካልተሰማዎ መቼስ ምን አደርጋ ለሁ—…ይሁን" አለች ። በግራ እግሯ አውራ ጣት መሬቱን እየጫረች ።

ሰውነቱን ያላወቀው ነገር ወረረው ። ፈጠን ብሎም "የለ ….የለ….እግዜር ይስጥልኝ ሒጂ….መሔድ ትችያለሽ። የቀረሽ ሒሳብ ካለ …."

"ሒሳብስ ትናንት በትክክል አስበው ጋሼ እሸቱ ሰጥተውኛል ። ምንም ሳይቀር ። ግን ከፈቀዱ ።"

ሳትጨርስ በፍጥነት አቋርጧት ….."ደህና ሰንብች የእኔ እህት" ብሏት ወደ ጠባቧ ክፍል ዘው አለ ።

በነገሩ እጅግ ነው የተገረመው ። "ለካስ እንደ ሚስት በሰማኒያ ፡ እንደ ገረድ በደሞዝ የሚባለው ተረት ብቻ አይደለም" አለ ለራሱ ። በእናው ቤት ውስጥም እየተንቆራ ጠጠ ከምንጊዜውም የበለጠ አዲስ አበባንና ቤተልሔምን በጥልቅ አሰበ ።

ከዚያን ዕለት በኋላ በዚያች የገጠር ባለሁለት ክፍል ዛኒ ጋባ ውስጥ የብቸኛነት ኑሮውን ተያያዘው ። አንዲት ጠና ያለ ሴት ቀላቢ አገኘ ። ምግቡን እያዘጋጁለት በልሮ በልሮ አቤታቸው እየሔደ ፡ ብዙውን ጊዜ ግን ቤቱ እያስመጣ፡ ይመገብ ጀመረ ። ቤቱን በማጻዳት ፡ ልብሱን በማጠብና፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በመላላክ የሚያገለግለው እርሱም በአንዳንድ ነገሮች የሚረዳው አንድ ተማሪ ወጣት ነበር ። ከሁሉም ይበልጥ ብቸኝነቱን ያስዘነጋው ግን ከአንድ አዛውንት የገዛው በቅሎ ነበር ።

ፍቅሩ የከተማ ልጅ ስለ ነበር ስለ በቅሎ የሚያውቀው ብዙ አልነበረም ። የሦስት ኪሎ ሜትሩን የት/ቤት መንገድ ለመጓጓዝ እንዲረዳው የገዛው በቅሎ ብዙ ችግር አቃለለት። በቅሎ ላይ መቀመጥም ብርቅ ሆነበት ። አንዳንድ ጊዜ በበቅሎው ተቀምጦ ወደ ተማሪ ቤቱ ሲሔድ ከኋላ ኋላ እየተከተሉ ሱክ ሱክ የሚሉት ተማሪዎች የቀድሞዎቹን ፊውዳሎች እያስታወሱት በራሱ ይገረም ነበር ። በተለይም ያ የሚላላክለት ተማሪ ለበቅሎው ገርና መኖ እየሰበሰበ ያመጣለትና ዱሮ ማድቤት ከነበረው ትንሽ ክፍል ውስጥ በቅሎው ሲያጋብሰው ማየቱና ጩኸቱን መስማት ያዝናናዋል ። መኪና ቢገዛ ይህን ያህል የሚደሰትበት አልመሰለውም ። ይህም ቢሆን ብዙ አልቆየም ። በቅሎው በተገዛ በሁለት ወሩ መጀመሪያ ላይ ሆዱ እየተነፋ ሕመም ላይ በመውደቁ መንቀሳቀስ ተሳነው ። ፍቅሩ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጣ። የበቅሎው ሕመም የራሱ ሕመም እንደሆነ ሁሉ ጭንቅ አለው ። በመንደሩ ወዲያ ወዲህ ቢሯሯጥም በወረዳው የከብት ሐኪም ስላልነበረ መፍትሔ አላገኘም ። መድኃኒት የተባለውን ሥራ ሥር ሁሉ ከዚያ ከሚላላከው ተማሪ ጋር በመሆን አጠጣው ። አንድ የመንደሩ ሽማግሌ ሚጥሚጣ ጥሩ ነው በጥብጥና አጠጣው አሉት ። ሚጥሚጣ ከቀላቢው ሴት ቤት ለምኖ ፣ በጣሳ ሙሉ በጥብጦ በትግል ለብዙ ሆነው በቅሎውን አጠጡት ። ሌሊቱን ሙሉ በቅሎው ሲያቃስት አደረ ። ፍቅሩም የበቅሎውን የሲቃ ድምፅ እያዳመጠ እንቅልፍ ሳይወስደው ሌሊቱን አጋመሰ ። የበቅሎው የሲቃ


t.me/OLDBOOKSPDF

ድምፅ ጋብ ሲል ፍቅሩንም እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰ ደው። በበነጋው ልብሱን ሳይለብስ ከነመኝታ ልብሱ ወደ በቅሎው ማደሪያ በፍጥነት ሔደ ። የሠጋው አልቀረም ። የትንሽ ጊዜ ጓደኛው በቅሎው ሞቶ አገኘው ። ሰው የሞተበ ትን ያህል አዘነ ። ከእኔ ጋር የቀረበና የተዛመደ አብሮኝ ላይዘልቅ የተከተለኝ ክፉ ዕጣ ይኖር ይሆን በማለት ተከዘ ።

የሁለተኛ ሴሚስቴር አጋማሽ ላይ በሔደው እሸቱ ምትክ አንዲት ሴት መምህር ተመድባ መጣች ። ለጊዜው ማረፊያ ስላልነበራት በእሸቱ ቦታ ከፍቅሩ እንድትዳበል ርዕሰ መምህሩ ፍቅሩን ጠየቁት ። ፍቅሩም ሳያመነታ ፈቃደኛ ሆነ። ጠባይዋን ባያውቅም አለቅጥ ተሰምቶት ለነበረው ብቸኛነት ማስታገሻ ትሆነኛለች በሚል ውስጡን ደስ ተሰኘ።

እንዳሰበውም ሆነለት ። ሁላገርሽ ፀባይዋ ሸጋ ነበር ። ቁመናዋ እንደ ዕድሜዋ ለጋ ቢመስልም አስተሳሰቧ የበሰለ በመሆኑ ከፍቅሩ ባሕርይ ጋር መሳ ለመሳ ገጠመ ። ፍቅሩ ከተማሪ ቤትና ከሽማግሌዎች ሸንጎ ፡ እንዲሁም ከሚሠራባ ቸው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሲመለስ ሁላገርሽ ቤቱን አጽድታ፡ የራሷንና የእሱንም ልብስ አጣጥባ ፡ አጫጭሳ ፡ ቡና አፍልታ ትጠብቀው ጀመር ። ቤቱ ሰው ያለበት ፡ የሞቀ የትዳር ቤት ፡ መሰለ ። ቀስ በቀስም በቀላቢ መመገቡ ቀርቶ እቤት ውስጥ እያዘጋጀች አብረው መመገብ ጀመሩ ። ቀን ሲሠሩት የዋሉትን ማታ ማታ በመወያየት በውጭና በቤት ሥራ በመተጋገዝ ፡ ለወረዳውና ለትምህርት ቤታቸው ልማትና መሻሻል በጋራ ሲያወጡና ሲያወርዱ ፡ እርሱ ስለእሷ እርሷም ስለእሱ ሕይወት ሲጠያየቁና በገጠሩ የእሳት ዙሪያ ቀልድ እየተቃለዱ ትርፍ ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ፡ ለረዥም ጊዜ አብረው እንዲኖሩ ሁሉ እየተዋደዱ በደስታ መኖር ጀመሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያም ሆኖ የመኝታ ሰዓት ሲደርስ እርሱ ከክፍሉ ፡ እሷም ከክፍሏ በየመኝታቸው ከመኮርመት በቀር የሁለቱን ክፍል መገናኛ በር ጥሶ ያለፈ አልነበረም ።

እንድ ቀን ምሽት እንደወትሮው ከራት መልስ የመመገቢያ ዕቃቸውን ቦታ ቦታ ካስያዙ በኋላ ሳያስቡት እርስ በርስ የየራሳቸውን ያለፈ ሕይወት ይመረምሩ ገቡ ።

"ነገርኩህ እኮ! ፍቅር ይዞኝ አያውቅም ። ግን እናቴንና አባቴን ካልዳራችሁልኝ አላስቆም አላስቀምጥ ብሎ ያስቸግር የነበረው ሰው የሚፈልገውን ከእኔ በማግኘቱ ወንድ አላውቅም አልልህም ።"

"ከእሱም ጋር ቢሆን ፍቅር አልያዘኝም ነበር ነው የምትይው?"

"ከሆን የሚያስደብቅ ምክንያት የለኝም ። እውነቱ ግን እንኳን ፍቅር ሊይዘኝ ያ ድርጊት በመፈጠሩም በይው በይው ይለኝ ነበር ። እርግጥ ለቤት መምረጊያ ተቆልሎ የነበረው ጭድ ላይ ከጣለኝ በኋላ የሆነው ሁሉ ስሜት አላሳደረብኝም አልልህም ። ያኔ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ ። አየህ እስከዚህ ነፍስ ያላወቅሁ ልጅ አልነበርኩም ማለት ነው ። ታዲያ ጅንበር አዘቅዝቃ ዐይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ከጓደኛዬ ቤት አጠናበት የነበረበትን ደብተር ይዤ ወደ ቤቴ ስመለስ ፡ ከጎረቤታችን ለቤት መምረጊያ በተከመረው ጭድ ውስጥ ተደብቆ ኖሮ ዘሎ ሁለት እጄን ጥርቅም አርጎ ይዞ ጭዱ ላይ ጣለኝ ። ጉልበቱ አይጣል ነበር ። ከሰው ጋር ሳይሆን ከአንበሳ ጋር የምታገል የመሰለኝ ። የሰውነቱ ግለት ፡ የማንባሩ ወዝ ፡ የትንፋሹ መሻከር ፡ በዚያ ላይ ወገቤን ዙሪያውን ጥብቅ አድርጎ የያዘበት እጁ መጠንከር ተስፋ አስቆረጠኝ ፡ ጉልበቱ ዝሎ ራሴን ለማላቀቅ የማደርገው


t.me/OLDBOOKSPDF

መፍጨርጨር አቁሜ ሰውነቴን ሳላላው አፌን ባፉ ጎረሰው። እንደ እጁ ከተሜሲ ሥር ገብቶ የውስጥ ሱሪዬን ዝቅ ሲያደርገው በእንዲህ ዐይነት ሙያ የተካነ ይመስል ቅጽበት አልፈጀበትም ፤ ለስላሳውን ባቴንና ጭኔን በሞቃት እጁ ሲነካካኝ እንደ ኤሌክትሪክ ነዘረኝ። ያኔ ሳላስበው የልቤ ምት ፍጥነት ጨመረ ። ከዚህ በፊት የማላውቀው ልዩ ስሜት ወረረኝ ። በመጨረሻም እኔነቴን የተረጸሁት እቤቴ በራፍ ስደርስ ነበር ። ታዲያ ይህንን ሳስታውስ የምናደደውን ያህል አንዳንድ ጊዜ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እስኪል ድረስ መኝታዬ ላይ እየተገላበጥኩ ድርጊቱን አሰላስል ነበር ። እና ይህ ማለት ፍቅር ይዞኝ ነበር ማለት ነው?”

“አይደለም ። ግን ከዚያ በኋላስ?”

“ከዚያ በኋላ ከሁለትና ከሦስት ያልበለጡ ወንዶች ተዛምጃለሁ ። ለዚያውም ከአንዱ ጋር ብቻ ለሦስት ወር ያህል ከመቆየታችን በቀር ከሌሎቹ ጋር ካፍታ ግንኙነት በቀር አልተካረርንም ። የእኔ ወረተኛነት ሳይሆን አጋጣሚ ሆኖ የቀኑኝ ወንዶች ፍላጎት የወሲብ ጀብድ እንጂ እውነት ላይ ለተመረኮዘ ፍቅር ስላልነበረ ባጭሩ እንዲቀጭ የማደርግ እራሴው ነኝ ። እየሀ ፍቅር በስሎ የሚቀርብ መብል ሳይሆን በጥሬው ተጀምሮ ውሎ እያደረ የሚበስል ፤ ተመግበኸው እየቆየ ሥር የሚሰድና ሕይወት የሚሰጥ የጊዜያት ሂደት ነው። ታዲያ ከወንዶች ጋር ስገናኝ በጥሬው ስለሚሆን ገና በትኩሱ ፍቅር ላገኝ አልችልም ብዬ ማንም ላይ በር አልዘጋም ። ዕድገቱን ለመከታተል እሞክራለሁ ። ሳይሆን ከቀረ ግን በጊዜው የፈጸምኩት የአልጋ ጭውውት ፀፀት ውስጥ አይዶለኝም ። ይህ የእኔ እምነት ነው ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

ጭውውቱ ስለዶሩ ዝናብ ጣራውን የሚበሳ ይመስል በኃይል ይጥል እንደነበር ሁለቱም አልታወቃቸውም ፡ ፍቅሩ እሷ ከመምጣቱ ቀደም ብሎ ጓደኛው እሸቱ የሔደ ጊዜ የተሰማውን ብቸኛነት ሲያጫውታትና ይልቁንም የፍቅረኛው የቤተልሔም ትዝታ የጎዳው ያኔ እንደነበርና እሷ ከመጣች በኋላ ግን ይኸ ሁሉ መቅረቱን ከተናዘዘላት በኋላ ነበር ሳያስበው "አፍቅረሽ ታውቂያለሽ?" ብሎ የጠየቃት ። እናም ወሬው ሥር እየሰደደ ሲመጣ ፡ ሁለቱም በጨዋታ በመመሰጣቸው የዝናሙን በኃይል መዝነብ አላጤኑትም ነበር ።

« ይህ የእኔ እምነት ነው » ብላ ቀና ስትል እሱም ቀና ሲል ላፍታ ዐይን ለዐይን ሲጋጠሙ ፡ የሁለቱም ልብ ድንገት ፍጥነቱን ጨመረ ። ነጎድጓዱ አጓርቶ መብረቅ ብልጭ ሲል በሩ አለመዘጋቱና ዝናብ በኃይል እየዘነበ መሆኑ ሲታወቃ ቸው ሁለቱም ተገረሙ ።እየተሣሣቁ መዝጊያውን ለመዝጋት ሲነሡ ፡ ወፊፎ ከበሩ ዘልቆ ቤት መግባቱን ሲያዩ ተደነቁ ። የ«የት ነበርን?» ዐይነት እየተያዩ በሣቅ ተንከተከቱ። እየሣቀ መኝታ ክፍሏን ዐልፎ ወደ ክፍሉ ሲገባ እየሣቀች ተከተለ ችው ። ሳይገባበዙ ፡ ሳይጠያየቁ ፡ ሳይተፋፈሩ በቁም ተቃቅፈው እንባ እስኪረግፋቸው ድረስ ተሣሣቁ ። ሲስማት ሳመችው። የተቀረው ለሁለቱም ሕልም የሚመስል ነበር ። ልብሳቸው ወልቆ ከአልጋው ዳር ግራና ቀኝ ፡ ራስጌና ግርጌ ሲወድቅ ፡ አንሶላው ተገልጦ እውስጥ ሲገቡ ፡ ሙቀቷን እሱ ፡ ሙቀቱን እሷ እየፈለጉ ሲቀራረቡ ፡ ሙቀቱ ግለት ሆኖ መጀመሪያ ብርድ ልብሱ ከዚያ አንሶላው እርቃናቸውን ትቷቸው ሲወድቅ ሲገላበጡ እሱ ከግራ እሷ ከቀኝ ፡ እሷ ከግራ እሱ ከቀኝ ሲቀያየሩ ፡ አንዱንም አያውቁትም ነበር ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም ካበቃ በኋላ እንሶላውን ፣ ብርድ ልብሱን የወይቀውን ልብስ በቅጥ በቅጡ ካበጃጀ በኋላ እጅ ለእጅ ተቆላልፈው ለጥቂት ደቂቃ ያህል ተያዩ ።

«በጣም ይቅርታ በመሳሳቴ ፣ ትክክል እንዳልሆንኩ ይገባኛል » አላት ። አልማዝ እንዳለቀ ቴፕ ሪከርደር በጎረናና ድምፅ ።

«አብረን ከነበርንበት ቀን አንሥቶ ካደረግነው ድርጊት ሁሉ እንደ ዛሬ ትክክል ሆነን አናውቅም » አለች ፈገግ እያለች ። ያላሰበው መልስ አስደነቀው ። የሚናገረው ጠፍቶት ግራ ሲገባው አይታ በመላ አካሉ መጫወት ጀመረች ፣ በስስ ጣቶቿ ከራስ ጠጉሩ እስከ እግሩ እየዳሰሰች ። እንደገና እንደገና ደመ ሞቀ ። እንደገና ሕዋሱን አስፈነደቀ ። እንደገና ሚዛኑን ለቀቀ ። ሲያበቃ እሱም እሷም ተዳክመው እንደ ተቃቀፉ ድብን ባለ እንቅልፍ ተዋጡ ። እናም ከዚያን ቀን በኋላ መኝታ ቤታቸው አንድ ሆነ ።

ፍቅሩ በሁላገርሽ ውስጧ ቢዋጥም ዐልፎ ዐልፎ ግን ቤተልሔምን ማስታወሱ አልቀረም ነበር ። ሁላገርሽን እዚህ ገጠር እስከቆየ ድረስ እንጂ አዲስ አበባን ሲያስብ ከቤተል ሔም ጋር ሊያመዛዝናት አልቻለም ። ግን የወደፊት ትዳሩን ለመቀለስ በምግባርና በጨዋነት ሁላገርሽ እንደምትበልጥና ፍቅሯም ንጹሕና መሠረቱም ጠንካራ መሆኑን ቢያምንም በዘመናይነትና በንዋይ ቤተልሔም እንደምትበልጥና የደስታ ኑሮዋም ተካፋይ መሆን እንደሚሻል በማሰብ ብቻ ሁላገርሽን ለትዳር መቀበል አልቻለም ።

ሁላገርሽ ግን የትዳር ጥያቄ ለጊዜው ባይነሣም በገዛ ራሷ የአስተሳሰብ ጥልቀት የምትተማመን በመሆኗና ፍቅሩ ንም የተገራና ልዝብ ሆኖ ስላገኘችው እየዋለ ሲያድር እራሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያነግዋል የሚል እምነት ነበራት ። ጊዜው እየገፋ በመሔድ የመጨረሻውን አጋማሽ ፈተና ከሰጡ በኋላ በየፈናቸው የመበታተኛው ጊዜ እየቀረበ ቢመጣም ስለ ትዳር ከሁለቱም አንድም ነገር ሳይነግ በመቅረቱ ሥጋት አደረባት ። የትዳር ነገር አይነግ እንጂ በዚያ የጋራ አልጋቸው ላይ ሲገናኙ ሁለቱም ረኃባቸው ያየለና ፍቅራቸውም የሀውሬ ዐይነት ፡ የሚያብላላ ነበር።

አንድ ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ፍቅራቸውን አከትመው እጃቸውን ለእንቅልፍ ሊሰጡ ሲሉ ፡ «ታዲያ ስለ ክረምቱ ምን አሰብክ? » አለችው ፈራ ተባ እያለች ። ፍቅሩ ከሸልብታው መለስ እያለ ፡ «እ.ም? » አላት የሰማውን ጥያቄ እውነትነት ለማረጋገጥ እንዳልሰማ እየሆነ ።

«ክረምቱን የት ነው የምታሳልፈው? » አለችው በድጋሚ እየፈራች ።

«ያው አዲስ አበባ ነዋ! እዚህማ ምን አለኝ ት ቤት ከተዘጋ።»

«እሱማ እኔስ ምን አለኝ? …ከዚያስ?»

«ከዚያ ያው እንደ ነገርኩሽ ዩኒቨርስቲው ከተቀበለኝ ትምህርት እቀጥላለሁ።»

«ከዚያስ?»

«ከዚያ…እ…እንጃ ከዚያ ምን ዐውቃለሁ ።»

«እወድሃለሁ እኮ!» አለችው ወደ ነጥቡ ልታመጣው የምትችልበትን መንገድ እያሰበች ።

«አውቃለሁ ። እ— እኔም እወድሻለሁ አይደል?»

«እንዴት አይደል? ትጠራጠራለህ እንዴ?»

«ኧረ እወድሻለሁ ። ታውቂዋለሽ ማለቴ ነው ።»

«እም — አዎ — እኔ ክረምቱን እናቴጋ እሔዳለሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ ተመልሼ እዚሁ ማስተማር ነው የምቀጥለው ። እ··
ዩኒቨርስቲው ካልተቀበለህ እዚሁ መጥተህ አታስተምርም?»

«የለ ይቀበለኛል እንጂ ለምን አይቀበለኝም?»

«እ··· እሺ ዕረፍት ሲኖርህ መጥተህ አትጠይቀኝም ?»

«እጠይቅሻ ይሆናል።»

«እንዴት ይሆናል — ግልጽ ሁንልኝ እንጂ ።»

«እንቢ — ያንቺም ጥያቄ ግልጽ ይሁንልኝ እንጂ!» አላትና ቀና ብሎ በክንዱ ትራሱን ተመርኩዞ በመዳፉ ራሱን ደገፍ አደረገ ።

ያበጠው ይፈንዳ አለችና ፡ «ስለ ትዳር ምን ታስባለህ? » አለችው ።

«አሁን ምንም አላስብም ። ጊዜው ሲደርስ እሱ ራሱ ያስበኛል » አላት ሁኔታውን ወደ ቀልድ ለመቀየር እየሞከረ።

«እኔ እኮ ላገባህ ነው የምፈልገው ።»

«እኔማ እሾኛ እንዳለችኝ ነግሬሻለሁ » አላት ።

«ዐረፍኩት!» አለች በልቧ ። ሌላ ምንም አላነሣችበትም ። አላኮረፈችምም ። እንዲያውም ይግረምህ ብላ ጸጉሩን እየዳበሰች እንቅልፍ አስወሰደችው ።

በተከታዩ ሳምንት ምንም እንዳልሆኑ ሁሉ እንደ ቀድሞው በደስታ ጊዜያቸውን አሳለፉ ። ፍቅሩ በልበ ጠንካራነቷ ውስጡን እያደነቃት ከፍቅር ገበታ ሲጨልፍ ሰነበተ ። ከመቼውም ይበልጥ ያን ሳምንት ገበያ የወጣ ሰው ይመስል ቤተልሔምንና ሁላገርሽን ሲመዝን ከረመ ። ቢሆንም የአዲስ አበባ ልጅ ነውና የገጠር ኮንትራቱን የጨረሰ ስለ መሰለው ለአዲስ አበባዋ አደላ ። በእውነቱ እንደምትወደው የሚያረጋግጠውን ሁላገርሽን ለቀቅ አድርጎ ፡ በጥያቄ ምልክት ላይ ያለችውን ቤተልሔምን በሐሳቡ ጠበቅ አደረገ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የመጨረሻው ዕለት በወግ አውቶቡስ መሣፈሪያው ድረስ ሸኙትው ። ከአሁን አሁን ዕንባዋን ዘረገፈችው እያለ ዐይኗን ቢያይም በሐሰት ፈገግታ ተላብሳ በልበ ሙሉነት ሸኘችው ። መኪናው የመንደሩን ወርድ ዘሎ የገጠሩን ኮረኮንች ሲያያዘው የእውነት ኀዘን ሰውነቱን ወረረው ። እውነተኛዋ ወደ ኋላ ቀረች ። አጠራጣሪዋ እፊት ለፊት ትጠብቀው ጀመር ። አዘነ ።

ሁላገርሽ አቤትዋ እስክትደርስ ድረስ መንገዱን እን ደጨሰ እንደ ጨረሰችው አላወቀችም ። እየተጣደፈች ጓዳዋ ገብታ ከድንኳ አልጋዋ ላይ ዘፍ እንዳለች የታመቀ ዕንባዋን ዝርግፍ አደረገችው ። ጎላጋይ በሌለበት ፡ ልቧ ውስጥ ለሚነደው እሳት ማጥፊያ ይመስል ከዐይኗ የሚወጣው ዕንባዋ እንደ እሳት አደጋ ደረቷን አረጠበው ። እርሚን ስለ ማፍቀሯ እርግጠኛ ብትሆን ፡ እርሚን ስለ መፈቀሯ ብታረጋ ግጥ ፡ የሚያፈቅራት ከፍቅር ይልቅ ለንዋይ ሲል ፍቅሩን ብቻ አስታቅፏት ፡ ፍቅሯን ብቻ ታቅፎ ፡ ሌጣዋን ጥሏት ከብለለ ፡ ያልታደለች ።

«የት ሔደች?»

«አለች ። ግን ከሰው ጋር ነች ።»

«ፍቅሩ ነው የሚፈልግሽ በሉልኝ ።»

«ብለናል ። ግን አሁን አይመችኝም ከእንግዳ ጋር ነኝ ። ነገ ብቅ በል በሉት ነው ያለችን ። »

ከው አለ ። ዱሮስ መች አጣሁት ብሎ አሰበ ። ገና አውቶቡሱ ከበስተኋላው ሁላገርሽንና ያችን የገጠር መንደር እየራቀ መሔድ ሲጀምር ነበር ስለ ቢተልሔም መጠራጠር የጀመረው ። ከተማም እንደገባ ከታክሲ ወርዶ ወደ ቤቱ የሚወስደውን መንገድ ሲያያዘው ፡ ከንቢተልሔም ቤት



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመድረሱ በፊት ነበር ሰውነቱን ቅፍፍ ያለው ። ቅጥር ግቢያቸው በራፍ ላይና ውስጥ የተሠገሠገው መኪና ብዛት ግር አሰኘው ። በአንድ በኩል የፈረንጅ ሙዚቃ ፡ በሌላ አቅጣጫ የአገር ባህል አዝማሪ ድምፅ ከአንድ ቤት ውስጥ ሲወጣ ያ ጸጥታ የነበረው የነቤተልሔም ግቢ ወደ ሁካታ ቤትነት መቀየሩ ማስደነቅ ብቻ አልነበረም — አሸበረው ። የዚያኑ ዕለት ጎራ ሲል ቢከጅልም ድካም ስለ ነበረበትና በአቧራ የተለወሰው ልብሱ ቤተልሔም ጋ የሚያስቀርብ ስላልመሰለው እቤቱ ገባ ። ወደ ገጠር ሲሔድ ቤቱን ትቶለት የሔደው በጣም የሚያፈቅረው ጓደኛውን ዓለሙን እንኳ በቅጡ ሳያነጋግረው ተኛ ። በበነጋው ገላውን ታጥቦ ፡ ልብሱን ቀያይሮና ባለው አቅም ሁሉ ተሽቀርቅሮ ሲመጣ ይኸው «ከሰው ጋር ነኝ አይመቸኝም » ብላ ሰው ላከችበት ። ብሽቀት፡ ብግነት ፡ ንዴት ፡ ፀፀት ፡ ኀዘን ፡ ባለ፡ንደላቸው ተረባረቡበት ፡ አደነዘዙት ፡ እንደ ፈዘዘ ጓደኛው ዓለሙ ጎትቶ እቤት ወሰደው ።

በማልስቱ አቅሉን ሲገዛ ወደ ገጠሩ መንደርና ወደ ገጠሩ ሁላገርሽ ወዲያውኑ ለመመለስ ቃጥቶት ነበር ። ግን «እናቴ ጋ እሔዳለሁ» ስላለችው ዋጋ እንደሌለው ገምቶ ቀረ። ክረምቱ በክረምትነቱ ላይ ነጠላነቱን አጉልቶ አበረደው ። የነዓለሙ የማጽናኛ ቃል ፡ ጨዋታቸው ፡ ሲኒማ ቤቶች ፡ ቲያትር ፡ ኳስ ሜዳ አንዳቸውም አልጥምህ አሉት ። ትንሽ የበረደለት ዓለሙ አላስቆም አላስቀምጥ ብሎ ሰንጎ ስለ ያዘው ታሪኩን ካጫወተው በኋላ ነበር ። ዓለሙ ጉዳዩን አጥልቆ ተመለከተና በነገሩ በጣም ተሰምቶት ሲያስብ ከቆየ በኋላ ብቸኛውን አማራጭ አዋየው ።

«ቤተልሔም ገደል ትግባ ። እንዳባባልህ ሁላገርሽ


t.me/OLDBOOKSPDF

እውነተኛና ቋም ነገረኛ ናት ። ስለዚህ ከምዝገባው በኋላ ለአንድ አምስት ቀናት ያህል ትሔዳለህ ። ከቻልክ ያዘሃት መምጣት ፡ አለበለዚያም ቃል ኪዳን ተጣሥረህ ለአንተም ለሷም ልብ ዕረፍት ሰጥተህ በኋላ ትምህርትህን ትማራለህ ። ሌላ ምን አለ…ይኸው ነው ።»

« ይኸው ነው ! » አለ በልቡ ፍቅሩ ። ክረምቱ እስኪያበቃ ተጣደፈ ። « በነዚህ ሁለት ወራት ውስጥ መቼም ተቀይራ አትቆየኝም » ብሎ አሰበ ። « ግን ማን ያውቃል? ስለ ቤተልሔምስ መች እንዲህ አስቤ አውቃለሁ? » በማለት ሥጋ። ወይደም ጠላም ሊያደርገው የሚችለው ምንም ነገር ባለመኖሩ ክረምቱን በሐሳብና በሥጋት እንደ ተኮራመተ ሰነበተ ።

እንዳሰበው ዩኒቨርሲቲው ተቀበለው ። ከምዝገባው በኋላ ግን እንደ ጓጓው ወደዚያች ገጠር ለመሔድ የሚያስች ለው ጊዜ አላገኘም ። ጨነቀው ። ዲፕሎማውን በዲግሪ ለመቀየር የሚያስፈልገው ሁለት ዓመታት ካለ ሁላገርሽ ፡ ካለ ቃል ኪዳኗ ሁለት ምዕት ዓመት መስሎ ታየው ። በራሱ ድርጊት ተፀፀተ ። ለዚህ ዓመት ትምህርቱን ለመተውና ወደ ገጠሯ ለመመለስ ቃጣ ። ነገር ግን እውነተኛ ጓደኛው ዓለሙ «ትክክል አይደለህም » ብሎ ወትውቶ አስቀረው ።

በሳምንቱ ከዩኒቨርስቲው ቤተ መጻሕፍት የተዋሰ ውን መጽሐፍ ለይስሙላ እያገላበጠ ሳለ ዓለሙ እየሮጠ መጣና «መፍትሔ አገኘሁ » አለው ። የዓለሙ ጓደኛ የነበረ የመምህራን ኮሌጅ ተማሪ ከምረቃው በኋላ እሱ ወደ ነበረበት ክፍለ ሀገር መመደቡን አጫወተው ። ዕድል ካጋጠመው ወደዚያች መንደር ሊመደብ እንደሚችልና ፡ ምድቡ ሌላ አውራጃና ወረዳ ቢሆንም እንኳ ከክፍለ ሀገሩ ት/ቤቶች


t.me/OLDBOOKSPDF

ጽ ቤት ወደዚያ የሚመደበውን ሰው በቀላሉ ሊያገኝ እንደሚችል ነገረው ። ፍቅሩ በነገሩ አሰበበት ። የቀድሞው ጓደኛው እሸቱ በክፍለ ሀገሩ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ምደባ ክፍል እንደሚሠራ ያውቃል ። አዲሱ መምህር ፈቃደኛ ከሆነ ወደዚያች ወረዳ ለመሔድ የሚከለክለው ነገር እንደማይኖር ገመተ ። በሳምንቱ ወጣቱን እቤታቸው ጋበዙት።

ፍቅሩ ፡ ምንተስኖትን ወዲያው ወደደው ። ጨዋታውና ረጋ ያለ ሁኔታው እምነት እንዲጥልበት አደረገው ። ምንተስኖት ከሌላ ክፍለ ሀገር የመጣ ስለነበር አዲስ አበባ ቤተሰብ የለውም ። ስለዚህም ወደ ምድብ ቦታው እስከሚሔድ ድረስ እነሱ ጋ እንዲያድር እነ ፍቅሩ ያቀረቡለትን ግብዣ ሳያመነታ ተቀበለው ።

በዐሥራ አምስተኛው ቀን ፍቅሩና ዓለሙ ፡ ምንተስኖትን በደንብ ተዘጋጅተው ሸኙት። ፍቅሩ ልዩ ልዩ የስጦታ ዕቃዎችንና ከዐሥራ አንድ ገጽ በላይ ደብዳቤ ለሁላገርሽ ጽፎ ላከላት ። በሦስተኛውም ቀን ክፍለ ሀገር ጽ/ቤት ደውሎ ምንተስኖት ወደ ወረዳው ተመድቦ መሔዱን ሲሰማ የአእምሮ ዕረፍት አገኘ ። ከፍተኛ ሥጋት ሆኖበት የነበረው ደብዳቤ የሚያደርስለት ሰው አለማግኘቱ ሳይሆን የሚያምነውና ሁላገርሽን የሚያሳምንለት ፡ ብሎም የሁለት ዓመት ትምህርቱን እስኪጨርስ ድረስ በሐሳቧ ጸንታ እንድትቆየው የሚያደርግ ከጎኗ የሚቆምላት ጓደኛ ማግኘቱ ነበር ። እሊያማ ደብዳቤ ለመጻፉ ፡ ይዘግይ እንጂ ፖስታ ቤትስ አለ አይደል?

አብረው በቆዩበት ዐሥራ አምስት ቀናት እራሱ እንዳየውና የረዥም ጊዜ ጓደኛው ዓለሙም እንዳስረዳው ምንተስኖት እምነት የሚጣልበት ስለነበረ የልቡን ዘክዝኮ አጫወተው ። ለሁላገርሽ እራሱ ከጻፈላት ደብዳቤ በቀር በቃል ብዙ


t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር እንዲነግርለት አደራ አለው ። ምንተስኖትም በነገሩ አበክሮ ከማሰብ ያለፈ ፡ « በእኔ ይሁንብህ » ብሎ ስለ አጽናኛው ፍቅሩ ሜንቀቴ በመጠኑ ለቀቀው ።

በወር ከግማሹ ከሁላገርሽ የደብዳቤ ምላሽ አገኘ ። ፖስታውን ቀዶ ቁራጩን ወረቀት ሲያየው ግን ደስታውን ወዲያው ነዘን ዋጠው ። « ለፀሎራ አንድ ገጽ ደብዳቤ ግማሽ ወረቀት ምላሽ ከአሉታ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም » ብሎ አሰበ ።

> « ሀይ ፍቅሩ ! እንኳን በደህና ደርሰህ ለከፍተኛ ትምህርት በቃህ። በደብዳቤህ አልተደነቅሁም ። ከስሜትህ ጋር ግብ ግብ መግጠምህን ያወቅሁት ቀደም ብዬ ነው ። እንደምትወደኝ ፀሎራ አንድ ገጽ ሙሉ ድርሳን ፍቅር መጻፍ አያስፈልግህም ነበር ። ዱሮውኑ በደንብ አድርጌ አውቃለሁ ። ስሜትህን በውሳኔ መገደብህ ደስ ብሎኛል ። በል በርታ አሁን ዕረፍት አድርግና ትምህርትህን አጥብቅ ። እኔም ለሕሊናዬ ዕረፍት ሰጥቼ መምህርነቴን በቅጡ ተያይዤዋለሁ ። ለምትወደውና ለምታፈቅረው ሕዝብ አገልጋይነት እንድትበቃ ቀልጥፍ ! በጀመርከው መንገድ ያለሁበትን አካባቢ ሕዝብ ባለኝ አቅም ለመርዳት እጥራለሁ . . . ቻው ! ሁላገርሽ ።»

እወድሃለሁ የለ? ያኔ እኔ ስሸሸው ገፍታ ያመጣችው የትዳር ጉዳይ አልተነሣ? የደብዳቤዋ መልዕክት ምንድን ነው? ግራ ተጋባ ። «አሁን ዕረፍት አድርግና...» ምን ማለት ነው? «ለሕሊናዬ ዕረፍት ሰጥቼ....'ትቼሃለሁ ፡ ሌላ ላገባ ነው ፡ ረስቼሃለሁ ። ለሕሊናዬ ዕረፍት ሰጥቻለሁና አንተም ዕረፈው ነው ነገሩ? ወይስ . . . ምንድነው ይህ እንቆቅልሽ? የለ !'



t.me/OLDBOOKSPDF

አባባሏ 'ወይ እኔ በመመለስህ የአእምሮ ዕረፍት አግኝቻለሁ። እኔም ያንተ ነኝና የአእምሮ ዕረፍት አግኝ ' ማለቷ ነው? . . . ከራሱ ጋር ብዙ ተሟገተ ። ውሎ ሳያድር ጻፈላት ። «አልገባኝም ! ምን ማለትሽ ነው? ይሆናል ወይም አይሆንም በይኝ » ብሎ ። ይሁን እንጂ ይሆናልም ፡ አይሆንምም የሚል መልስ ሳያገኝ ብዙ ጊዜ አለፈው ።

ዓመቱን በትምህርት ተወጥሮ ልቡ በፀ. አባባል አሉታ ነትና አዎንታነት እሁለት ተከፍሎ ፡ የኔውም ፡ የአይደለምም መልስ ሳያገኝ ጨረሰ ። ሐሊናው ነጻ ሆኖ ትምህርቱ ላይ ሙሉ ለሙሉ ማተኮር ሳይችል በመቅረቱ ያገኘው ውጤት አጥጋቢ አልነበረም ። ይባስ ብሎ በክረምት እፀ. ዘንድ እሔዳለሁ ብሎ ያወጣውን ዕቅድ ሲያከሽፈበት አንድ ኮርስ ክረምቱን መድገም እንደሚኖርበት ተነገረው ። ለምረቃ የሚያበቃው ነጥብ ለማግኘት በዚህ ኮርስ አማካይ ውጤት ማግኘት ነበረበት ። በሚቀጥለው ዓመት የሚኖሩት የኮርሶች ክፍለ ጊዜ ፋታ ስለማይሰጠው ፡ ይህን ኮርስ በክረምት ካልደገመ በቀር በሚኖጥለው ዓመት ለምረቃ መብቃቱ የሚያጠያይቅ ስለ ሆነበት ቅስሙ ተሰበረ ። ይህንኑ በመግ ለጽ ደብዳቤ ጽፎ እፀ. እንድትመጣ ለማድረግ ሞከረ ። ከወር በኋላ ያገኘው ምላሽ ግን ፡ « እናቴ በጠና በመታመማቸው ወደ እዚያው ሔዳለች » የሚል ነው።

ዓለሙ የጓደኛው ሁኔታ ሥጋት ላይ ስለ ጣለው የውሽት ወሬ በመንገር በትምህርቱ እንዲበረታታ ብዙ ጥረት አደረገ። «ሁላገርሽ እንደምታፈቅረውና ትምህርቱን አጠናቆ እስኪ. መረቅ ድረስ በቃል ኪዳን ጸንታ እንደምትጠብቀው ፡ ከእርሱ በቀር ሌላ የትዳር ጓደኛ ሊኖራት እንደማይችል ጓደኞቿ ምንተስኖት ጽፎልኛል » እያለ ሐሰት የተቀላቀለበት ማጽ


t.me/OLDBOOKSPDF

ናኛ አከታተለበት ። ፍቅሩ ሙሉ በሙሉ ባያምንም ትክክል ነው በማለት ትምህርቱ ላይ በማተኮር አሳለፈ ። ከሁላገርሽ እንድም ደብዳቤ ሳያገኝ፤ እሱም ሳይጽፍ ፡ ጥረቱ የተሻለ ሆኖ የመጨረሻው ዓመት ትምህርቱን በጥሩ ውጤት አጠናቅቆ ተመረቀ ።

በምረቃው ማግሥት ሰክኖ የነበረው የሁላገርሽ ፍቅር እንደገና በልቡ ላይ ተንተከተከ ። ከሁሉ አስቀድሞ የሚወደ ብበትን መ ቤት ከመስማቱ እንኳን በፊት ወደ ሁላገርሽ ለመክነፍ ይጣደፍ ጀመር ። ግን አንድ ነገር ግራ ገብቶት ነበር ፡ የዓለሙ ሁኔታ ።

ዓለሙ ከምረቃው በኋላ የራሱ የሆነ ምስጢር ያዘለ ይመስል ስለ ሁላገርሽ ሲወራ ቀዝቀዝ ይልበት ጀመር ። በሌላ በኩል ብር ብድር ሲሯሯጥ ፡ አዲስ ልብስ ሲገዛና ሲዋስ ፡ ገቢያ ሲወጣና ወዲያ ወዲህ ሲቅበዘበዝ አየው ።

« ምን ሆነሃል ዓለሙ? ይህን ሰሞን የገጠመህ ምንድ ነው? ብቻህን ወዲያ ወዲህ ስትታመስ አያሃለሁ ። ስለ ሁላገርሽ ሳወራልህ እንደ ወትሮህ ሐሳብ አትሰጠኝም ምን ነው? » ብሎ ጠየቀው አንድ ቀን ግራ መጋባቱ ሲበዛበት ።

«አይ ምንም. . .ግን አንድ ጓደኛዬ ለሠርግ ስለ ጠራኝ ወደ ገጠር ልሔድ ነው ። ለዚህ ነው የምሯሯጠው » ብሎ መለሰለት። የዓለሙ አመላለስ ግዴለሽ ሀይነት ሆነበት ።

"ከእኔ ጋር አትሔድም ማለት ነው?"

"የት?"

"እኔ እኮ በሚመጣው ሳምንት ሁላገርሽን ላመጣ መሔዴ ነው ። "

"የለም ይቅርታ አድርግልኝ ፍቅሩ ! እኔ ነገ መሔድ አለብኝ ። ጓደኛዬ ለሚዜነት እኔን ስለ መረጠና ካለእኔ ደግሞ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላ ማንም ስለሌለው መሔድ ይኖርብኛል ። ”

"እሺ እስ ካባሰብህ እንዳልክ ። ግን እኔ የማላውቀው ጓደኛህ ማን ነው?”

"ማወቅ ታውቀዋለህ ። ግን ካንተ ጋር ብዙ አትቀራረቡም ። በዚያ ላይ ደግሞ ከልጁ ጋር የሥጋ ዝምድና ስላለን...”

"እሺ ደግ ተወው .... ታዲያ ነገ መሔድህ ነው?”

"አዎን እንዲያውም እሔዳለሁ ስላልኩኝ ፈራሁ እንጂ እንደምታውቀው ምንም ገንዘብ ስለሌለኝ ፡ ከሰውም ቢሆን አንድ ሁለት መቶ ብር እንድትፈልግልኝ አስቤ ነበር ። ”

"ኡ ! ከየት አመጣለሁ ። እንደ ነገርኩህ ሁላገርሽ ጋ ከሔድኩና እንደ ፈራሁት ሳይሆን ፡ እሺ የምትለኝ ከሆነ ይገኝ ስለምመጣ ....”

"ገባኝ ። ግን እኮ ከመጣሁ በኋላ ስለምተካልህ ...”

"እንግዲያው እስከ ዛሬ ድረስ ጠይቀሽኝም አታውቅ ። በዚያ ላይ በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር አንተ ለገንዘብ ብድር እንደማትነሣ ስለማውቅ ፡ መቶ ሃምሳ ብር ልስጥህ ።”

"ደግ ! ‘ታንኪው’ ፍቅሩ በጣም ነው የምፈልገው ። ስመለስ ከሁላገርሽ ጋር ሆነህ እንደምትጠብቀኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ”

" እንደ አፍህ ያርገው ። ”

ፍቅሩ በዓለሙ ሁኔታ ግር እንደ ተሰኘ ቢሆንም ሊያስቀይመው ስላልፈለገ ፡ የጠየቀውን መቶ ሃምሳ ብር ሰጥቶ በበነጋው ሸኘው ። አዝማሚያው ግን አላማረውም ። የዓለሙ ሁኔታ ለሰው ሚዜነት ወይም ለሌላ ሰው ሠርግ የሚሔድ ሳይሆን እራሱ የሚያገባ ነው የሚመስለው ።

እሱም በስድስተኛው ቀን ዕቃውን ቆጣጥሮ እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀድሞው ቤቱን የሚጠብቅ ሰው ባለመኖሩ ቆላልፎ ወደ ግቢሯና ወደ ግቢሩቱ ፍቅረኛው ሁላገሯሽ ጉዞ ቀጠለ ። ልቡ በፍርሃት እየተንጠለጠለ ፡ "ዝምታዋ የደግ አይደለም ። ፈቃደኛ ብትሆን ኖሮ እስከ ዛሬ ትጽፍልኝ ነበር እንጂ ልቤን እንጠልጥላው ጸጥ አትልም ነበር ። እስቲ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ትዳር ጓደኛ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እውነተኛዋ የፍቅር እመቤት ልዝመት!" አለ ለራሱ አውቶቡሱ ላይ ከወጣ በኋላ ከመስታወቱ ጥግ ሥፍራ እየያዘ ። ሁላገሯሽን በልቡ እንደገና አውጥቶ አወረዳት ። በዚያ በዱሮ ቤታቸው ውስጥ ብቻዋን ትኖር ይሆን? ወይስ ሌላ ደባል ገብቷል? ከገባስ ምን ዐይነት… እንስት ወይስ ተባዕት? ተባዕት ከሆነ የማድግዳው ድንበር ተጠብቆ ይኖር ይሆን? አንድ የኋይለኛው ዝናብ ምሽት ከሁለት አንዳቸውን ድንበር ላለማላቱ ምን ዋስትና አለ? ልክ እንደ ያኔው ከእኔ ጋር እንደ ነበረው ..." ልቡ በቅናት እየተቃጠለ ሊሆን ይችላል ብሎ የሚገምተውን አሰላሰለ ። እሱና እሷ በዚያን የዝናብ ዕለት ማታ የሆኑትንና የሠሩትን ሲያስታውስ በዚያ መኝታ ላይ በእሱ ፈንታ ሌላ ሰው ፡ ለሱ የጋበዘችውን ገላና ፍቅር ሲጋበዝ በሐሳበ ሕሊናው ማየቱ አእምሮውን አሰቃየው ። እሱ እንዲህ ሊሆን ወይም ላይሆን በሚችል ነገር ውስጥ እንጀቱ ሲቃጠል ፡ ሐሳበ ልቡናው በቅናት ሲነድ ፡ የተሣፈረበት አውቶቡስ ነዳጁን በከርሱ እያቃጠለ ሲነጉድ አይደረስ የለም — የማታ ማታ ከትንሿ መንደር ደረሰ ።

...............

ወደ ድንኳኑ እየቀረበ ሲመጣ "ቾኮላታ" የሚለው የልጃገረዶች ዘፈንና የከበሮው ድምፅ ከተጓዘበት የአራት



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓመታት ሕይወት የሐሳብ ባሕር አሽቀንጥሮ መለሰው ።

"የማታ የማታ "አለ— ሻንጣውን የያዘለት ታዳጊ ወጣት ። መኖሩን ዘንግቶት የነበረውን ወጣት ድምፁን ሲሰማ ልብ ብሎ አየውና ቀደም ብሎ አቅርቦለት የነበረው ጥያቄ ትዝ አለው ።

"ማናት አልከኝ የምታገባው ሁላገርሽ ትሆን? "

"አዎ ! ቲቸር ሁላገርሽ ናት" አለ ወጣቱ እየሣቀ ። የፍቅሩ ሰውነት ግን በድንጋጤ ተሽማቀቀ ። የፈራው አልቀረም ። የካቻምና ስሕተቱ ለዳግም ውድቀት ሲያበቃው ታየው ። የሁለት ዓመት ሕልሙ እና ሲቀር ተሰማው ። እግሮቹ አልነሣ አሉት ። መራመድ ተሣነው ።

በሲቃ አፉን ከፍቶ ፡ "ማንን ነው የምታገባው? " አለ በአእምሮው ምንተስኖትን እያሰላሰለ ።

"ቲቸር ....." የወጣቱን መልስ ከመስማቱ በፊት አንድ አባውንት እየሮጡ መጡ ።

"እንኳን ደህና መጣህ !" ብለው አንገቱ ላይ ተጠመጠሙ ። ለጊዜው ሕሊናውን ሳተ ። በየት በኩል እንደገባ ፡ ማንን እንደሚያይ ፡ ከማን ጋር እንደሚያወራ ፡ ማን አቅፎ እንደ ሳመው አልታወቀውም ። ድንጋይ አድርጎ ያስቀረው ፡ ያፈዘዘውና ያደነዘዘው ለሁላገርሽ ሲል መጥቶ በሠርጓ መድረሱ ብቻ ሳይሆን ከድንኳኑ ጀርባ ጥቁር ሙሉ ልበስ ፡ ነጭ ሸሚዝና ጥቁር ከረቫት አርጎ ያየውን ሰው ማንነት ማወቁ ነው ።

ሕሊናው ለማመዛዘን ፡ አውጥቶ ለማውረድ አላበቃውም ። ፍጹም በድን ሆኖ ቀረ ። ከበሮው ፡ ጫጫታው ፡ ዘፈኑ፡ ትርምሱ ፡ አንዱም አልተደመጠውም ። አልታየውም። ከወንበር ላይ ዘፍ እንዳለ ሐውልት ሆኖ ቀረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ሰከረ ሰው እየደጋገፉ ፡ እየጎተቱ ወደ ጓዳ አስገቡት ። የሚዳብሰውን ለስላሳ እጅ ፡ የሚሰማውን ለስላሳ አንደበት የማንነት አላወቀም ። እንደ ኩበት ደርቆ እንደ ውሻ አፍንጫ የቀዘቀዙ ከናፍሩን የሚስሙት እርጥብ ለስላሳና ሞቃት ከናፍር የማን እንደሆኑ ሁሉ ወዲያው አልታወቀ ውም።

"የሚበላውን አምጡለት እንጂ!ከመንገድ ነው የገባ።"

"ነይ ማነሽ ከጠጁ ቅጂለት እንጂ !"

"የለ ተነሽ ፡ ተነሡ እንጂ ሰዓቱ ገፍቷል ። መጀመሪያ ልብሱን ይቀይር ።"

"የታል — ያን ሚዜውን ጥሩለት ። ማነህ ! ማነው ስሙ? ያ እንግዳው ሚዜ .... እ ... ዓለሙ ናማ ወዲህ ።"

ያን ከድንኳን ጀርባ ጥቁር ሙል ልብስ ፡ ከነጭ ሸሚዝና ጥቁር ክራቫት ጋር ለብሶ ያየው የቀድሞው ጓደኛውን ዛሬ ወደ ድንጋይነት የተቀየረውን "ሰይጣን" ስም ሲሰማ ከእንቅ ልፉ እንደ ባነነ ሰው ፊቱን ዘወር አርጎ አየው ።

"አትጫወትም እንዴ? አልናፈቀችህም?" አለው ዓለሙ ፈገግ እያለ ።

"እዩት ደግሞ ይህን አጋንንት ! ሰይጣን ! ጥርሱን ያገጥ ብኛል ! ደሞ አትጫወትም? ማንን? ... ማን ... ን ..." ሲል በልቡ ከራሱ ጋር እያወራ እጆቹን የምትዳብሰውን ሴት ለማየት ከ"ሰይጣኑ" ጓደኛው ላይ ፊቱን መለስ አደረገ ። ሁላገርሽ ነበረች ። ነጭ በነጭ የሙሽራ ልብስ ለብሳ ፡ ተኳኩላ ከመቼውም ይበልጥ አምራ ከጎኑ ሸጉጥ ብላ እያት ።

የሞት ሞቱን ደረቷ ላይ ደፋ ብሎ ፡ "ሁላገርሽ ይቅርታ አድርጊልኝ ። አመጣጤ ለሠርግሽ ሳይሆን ያኔ ከመሔዴ በፊት ከእኔ ጋ እንድንጋባ ላቀረብሽው ጥያቄ እምቢ በማለቴ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይቅርታ ጠይቁ ቢቻል እጅሽን ለመጨበጥ ነበር ። ይቅርታ ..
ባይልልኝ ነው ።"

"ምንድን ነው የምታወሪው? ይግሞ ከአሁን በኋላ ምን ይፈጠር ልትል ነው ፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ... ሐሳብህን ልትቀይር ነው?"

ሐሳቤን እኮ ወዲያው ነበር የቀየርኩት ። ይቅርታ ብዬ ሀሥራ አንድ ገጽ ሙሉ ጽፌልሽ ካንቺ ሌላ እንደማላገባ የተናና..."

"ሐሳቢን ወዲያው ነው የቀየርኩት? መቼ? የምትጽፍ ልኝ ደብዳቤ ሁሉ በቃል ኪዳን ጸንተሽ ቆይ የሚል አልነበ ረም?"

"ታዲያ እሱ ለእኔ እንጂ ... ለእኔ ለራሴ በቃል ኪዳን ጸንተሽ ቆይኝ እንጂ ለሌላው ቆይለት አላለም ። "

"ምንድነው የምታወሪው?" አለችው ግራ ተጋብታ ፡ ግራ የገባውን ፍቅሩን የበለጠ ግራ ስታጋባው ዓለሙ ከት ብሎ እየሣቀ ጣልቃ ገባ ።

"ይቅርታ ፍቅሩ ! እንደዚህ የሚያስደንግጥህና ሕሊና ህን የሚያስትህ አልመሰለኝም ነበር ። ድንገተኛ የሐሴት ዱብ ዕዳ ላርግብህ ብዬ ነው ።–መቶ ሃምሳ ብሩንም የጠየቅሁህ ለመደገሻ ገንዘብ ስላልነበረኝ ነው ። የአንተን አስመስለን እኔና ምንተስኖት ደብዳቤ ጽፈን ሠርጉን በዛሬው ቀን ስንቆርጥ ..."

ሳይጨርስ ከድንኳኑ ውስጥ አንድ አዛውንት ብቅ ብለው "ምን ነካችሁ? ሽማግሌዎች እኮ እየጠበቁ ነው ። የልጅ ነገር አታርጉት ። ሙሽሮቹን አምጧቸው" አሉ ።

ዓለሙም ይንግጦ ተነሥ! ተነሥ ፍቅሩ ልብስህን ቀይር። ያው እዚያ አልጋ ላይ አሰናድቼልሃለሁ ። አግዝሮው



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁላገርሽ .. ፍጠኑ" ብሎ ወደ ድንኳን ሮጠ ።

ፍቅሩ ያበደ መሰለው ። ሰው ሁሉ ያበደ ፤ ሁሉ ያበዱ ፤ እሱም ያበደ ፤ ሁላገርሽም ያበደች መሰለው ።

"በል ተነሥ ሙሽራዬ ልብስህን ቀይር" አለችው ሁላገርሽ ። ብድግ ብሎ ወደ ጓዳው ተከተላት ። የቅድሙን "ሰይጣን" እንደገና በድንገት ወደ "መልአክነት" የተቀየረውን ጓደኛውን ዓለሙ በዐይኖቹ ድንኳን ውስጥ ተከተለው ። ልብሱን በመቀየር ላይ ሳለ ነገሩን በልቡ መልክ ለማስያዝ ሞከረ ። አቃተው ።

"ሙሽራዬ" አለችው ሁላገርሽ ።

"ወዬ የኔ ሙሽራ !" አላት ፍቅሩ ። ልብሱን ከቀያየረ በኋላ እጅ ለእጅ ተጠላልፈው ከጓዳ ሲወጡ ። ዓለሙና ምንተስኖት እየሮጡ መጥተው ጎን ለጎን ቆመው አጀቧቸው።

"ቾኮ — ላታ ..." አሉ ልጃገረዶቹ በሚያምር ድምፃቸው ።

"ማታ የማታ" አለ ፍቅሩ ። በልቡ ሊለው የፈለገውን ሳያስበው ሎክ ብሎ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዱ ብ ዕ ዳ

ፍጹም እንዳጣት አልፈልግም ። ለረዥም ጊዜ አለዝባ የያዘችው ፍቅር ከእርሷ ይልቅ ዛሬ እኔ ላይ ጎልቶ መታየት ጀምሯል ። እኔን ትወድበት የነበረው የፍቅሯ ዘዴ እጅግ በጣም እንዳፈቅራት ስላረገኝ ስትርቀኝ አልወድም ። የምደርስባቸውን ፡ የምሔድባቸውንና ትርፍ ጊዜዬን የማሳልፍባቸውን ፕሮግራሞች በቀላሉ ታውቅ ነበር ። በየወቅቱ የሚለዋወጡ የሥራ ስልክ ቁጥሮችን ከእኔ በፊት በጥያቄ አጥንታ የምታውቅ እርሷ ነበረች ። ጓደኞቼ እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ጊዜ አይፈጅባትም ። እያንዳንዳቸውን ሔዳ ዐይን በማውጣት ያላለቀሰችባቸውና ሁኔታዋን አይተው ያልወቀሱኝ አልነበሩም ። ከስድስት ዓመታት በፊት ገና ስንተዋወቅ “ወድጄሻለሁ” ብላ ደጋግማ በራሷ አፍ ስትነግረኝ ምን ዐይነቷ ዐይነ ደረቅ ነች እል ነበር ። ስሸሻት ትከተለኛለች ። ሳጥላላትና ሳንቋሽሻት በየደረሰችበት ክባ ታሞግሰኛለች ። በአጠቃላይ ለእኔ ያላትን ፍቅር ለመግለጽ ያልተጠቀመችው ዘዴ የለም ። የኋላ ኋላ ግን ድል መታኛለች ። ዛሬ የእርሷ ፍቅር ከበፊቱ ባይቀንስም የእኔው ግን በጣም አመዝኗል ። ወጥሮ የያዘኝ ትምክህቱ እጅ መስጠቴን በግላጭ ላለማወጅ ቆምጨጭ ቢያሰኘኝም በቁጥጥሯ ሥር እንዳዋለችኝ ከሁኔታዬ ስለተረዳች እንደ ቀድሞው መቅበጥበጧ ቀርቷል ። ቀን አብሬያት ውዬ ማታ ስለያት እረበሻለሁ ። የዕረፍት ቀናቶችን



t.me/OLDBOOKSPDF

የምናፍቃቸው ከእርሷ ጋር ለረዥም ሰዓቶች መቆየት ስለሚያ ስችሉኝ ብቻ ነው ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እመቤት በላቸው የቀን ተቀን ሕልሜ ሆናለች ።

ባለፈው ወር የሳምንት መጨረሻ ላይ ተቃጥረን በተለ መደው ስፍራ ከፈርማታ አጠገብ ተገናኘን ። እንደ ሌሎች ቀናቶች ወደ ቤት መሔዱን ለለውጥ ያህል ሥርዞን ከአንድ ሠዋራ ሥፍራ ጭር ያለ ቡና ቤት መርጠን ገራ አልን ። አንድ ጥግ ይዘን የምንጠጣውን አዘዝንና የባጥ የቆጡን መዘላበድ ቀጠልን ። በጨዋታችን መሐል ስለ መዋኛ ሥፍራዎችና መዝናኛዎች ታነሣና ድንገት ስሜን ጠርታ "ለምን የዓመት ዕረፍትህን አትወስድም ?" አለችኝ ።

"ምን ልሆንበት ?" አልኩና ጥያቄውን በጥያቄ መለ ስኩ ።

"ሰፋ ያለ ጊዜ አግኝተን ደስ በሚሉ ሥፍራዎች ጥሩ ጊዜ እንድናሳልፍ እፈልጋለሁ ።" መልስ አልሰጠኋትም ። ጥቂት ቀርቶት የነበረውን የኮካ ኮላ ብርጭቆዬን አጋባሁት ።

"የትርፍ ጊዜ አበክሮ — ልምዶችህ ምን ምን እንደሆኑ በወሬ ልስማ እንጂ በውል አላየኋቸውም ። የንባብ ፍቅርህ ፡ ዋና ፡ ፎቶግራፍ መሰብሰብ የምትላቸውን ሁሉ በእኔ ዙሪያ ስታደርጋቸው ማየት እወዳለሁ ። ምን ይመስልሃል ?" አሁንም ዝም አልኩ ፡ ከተጋባው ባዶ ብርጭቆ ጋር እየተጫ ወትኩ ። ትንሽ አሰብ አደረገችና "ድሬዳዋ ይሻለናል" አለችኝ ።

የድሬዳዋን ስም ስትጠቅስ ቀና አልሁና "እወደዋለሁ" አልኳት ።

"መልካም በቃ እዚያ እንሒድ" ብላ አትኩራ ተመለከ ተችኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሐሳብሽ ይግዬ ነው ብቻ ..."በረፍት ነገሩን ሳልጨር ሰው እንጠልጥዬ ተውኩት ።

"...ብቻ ምን?" አለችኝ እንድቀጥልላት በመሻት ።

"አንድ ልጅ አለኝ" አልኳት ።

ዘወትር የምንቀላለድበት ጨዋታ ስለነበር ሣቅ አለችና "ከእናትህ ጋር ያኖርከው?" አለችኝ ። ርዕስ ለመቀየር ያደረግሁት ሙከራ ሳይመስላት አልቀረም ብዬ ገመትሁ ።

"አይ ፣ ድሬዳዋ እትቴጋ" ብዬ መለስኩላት ።

አሁንም እየፈዘችና እየቀለደች "እውነት? አንተን ይመስላል ?"

ቀልዷን በቀልድ አልመለስኩም ። ኮስተር ብዬ "ከልቤ እኮ ነው" አልኳት ። ከሁለት ዓመት በፊት በአንዳንድ ምክንያቶች ከዓመት ለበለጠ ገዜ ከእርሷ ጋር ተለያይተን በነበርንበት ወቅት ያሳለፍኩት የጭንቅና የመከራ ጊዜ የትዝታ ኩታውን አከናንቦ ወደ ኋላ መለሰኝ ። የፊቷ መለዋወጥና የድምፏ መቀየር የዛሬው ቀልድ አለመሆኑን ስላረጋገጠላት ታሪኩን እንዳጫውታት ወተወተችኝ ። እየቀለደችና ልታጓጓኝ "ልጅ አለኝ" እንደምትለኝ "እኔም አለኝ እኮ" ብዬ ከማፌዝ ባሻገር ያን ያሳለፍሁትን የመከራ ጊዜ እውን ታሪክ ላጫውታት አልሻም ነበረ ። "አፍ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም" እንዲሉ አፌ ስቷልና ማምለጫ አጣሁ ። ትዝታዬን ብናህ ያደረገው ይመስል አንድ ቢራ አዝዤ ጉሮሮዬን አጣራሁና ታሪኬን ማውጋት ቀጠልሁ ። እርሷም አፏን ከፍታ በጥሞና ታዳምጠኝ ጀመር ።

መድረኩ ላይ በብዙ ሺህ ሰው ፊት ድርሻዬን ያህና አድርጌ ተጫወትሁና መብራቱ ቀስ እያለ ጠፍቶ መጋረጃው ሲዘጋ በሰመመን ተውጬ ወደ ልብስ መቀየሪያው ዘው



t.me/OLDBOOKSPDF

አልሁ ። አዳራሹን ያስተጋባው ጭብጨባ አልተደመጠኝም። ድርሰቱ የራሴ ይሁን እንጂ ፣ በተዋናይነት ልጫወተው አልፈለግሁም ነበር ። ግን ባሕርዩ በጣም የሰፋና ጥናቱም ከበድ ያለ ስለነበር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲደርስ የራሴን ድርሰት ራሴው እንድጫወተው ተገደድኩ ። ያን ዕለት ለመጀመሪያ ለሕዝብ መቅረቡ ነው ።

ልብስ መቀየሪያው ውስጥ ትዕይንቱን በሙሉ ልዟ ትከታተል የነበረችው ወይንሸት ተንደርድራ መጣችና እጇን አጥብቃ ጨብጣ ፣ "ግሩም አርገህ ተጫወትኸው" አለችኝ ።

"እውነት?" አልኳት ወዜን በሹራቧ ጠረግ እያደረ ግሁ።

"ሙሉ ሙት" ብላ በጣም ተጠግታ ትከሻዬን አጥብቃ ያዘችኝ ። እንደዚህ ተቀራርበን አናውቅም ነበር ። በኪነት ቡድን መሐል እኔም ሆንኩ እርሷ ዘወትር የምንጨነቀው ስለ ተጣለብን ኃላፊነት ስለነበር ፣ እንደዚህ ተቀራርበን የምንጫ ወትበትና የምንቀላለድበት ዕድል አግኝተን አናውቅም ። ስለ ኪነቱ ዕድገትና ጥንካሬ እንጂ ከዚያ ውጪ በሌላ ርዕስ የተወያየንበት ጊዜ አልነበረም ።

የቲያትሩ ዕለት በመልበሻው ክፍል እንዲያ ተጠግታኝ ባልተለመደ አቀራረብ "ድንቅ ተዋናይ ነህ" ስትለኝ የተሰ ማኝ ደስታ መጠን አልነበረውም ። እርግጥ ልዩ አመለካከት ኖሮኝ ሳይሆን ብስለቷን ስለማውቅ አድናቆቷ ከልብ መሆኑን ስለ ተረዳሁት ነበር ። ግን በእንዲያ ሀይነት ተጠጋግተን ደቂቃ ባለፈ ቁጥር ሙቀቷ በይበልጥ እየተሰማኝ መጣ ። ተከታዩን አጠር ያለ መጋረጃ ለማየት ብጓጓም ያልጠበቅሁት ሐሳብ ሕሊናዬን ስለሞላው ልብ ብዬ መከታተል አልቻል ኩም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምን አንወጣም? እዚህ በጣም ይሞቃል" ብትለኝ መልስ ሳልሰጣት ቀደም ብዬ ብድግ አልሁ ። በጓሮው በር ወጥተን ከግቢው መናፈሻ ውስጥ መንጎራደድ ቀጠልን ።

"አልማዝ ገረድህ ሆና ስትሽኮረመም አንተ ፒፓህን እያቀጣጠልህ እንደ ቢሮክራት ስትውረገረግ ተመልካቹ በአድናቆት እንዴት እንዳጨበጨበልህ ልብ ብለሃል?" አለ ችኝ ። ግራ እጇ በወገቤ ተጠምጥሞ የግራ እጇን ጣቶች በጣቶቿ እያፍተለተለች ።

"እም..."አልኳት ። ስለ መድረኩ ፣ ስለ ተውኔቱና ስለ ተመልካቹ አላስታወስኩም ። ጥያቄዋንም በትክክል ማዳመጤን እጠራጠራለሁ ። አዕምሮዬን ያስጨነቀው ያላሰብኩት ልዩ ትኩሳቷ ነበር ።

"ግን ወይንሸት ፣ ይቅርታ አድርጊልኝና በጣም እወድ ሻለሁ ።" ስለ ተዋናይነት ችሎታዬ የምታኸጎደጉደውን አድናቆት መጠለያ አድርጌ የሞት ሞቴን ተነፈስኩ ።

"እኔ የድርሰት ችሎታህን እንጂ እንዲህ የመድረክ ሊቅ መሆንህን አልገምትም ነበር" በማለት ጥያቄዬን እንዳልሰ ማች ሁሉ ስለ ተዋናይነቴ አስተያየትዋን መስጠት ቀጠለች ።

"እንደማፈቅርሽ ልነግርሽ እየቃጣሁ ብዙ ጊዜ እጠጋ ሽና ወኔ ይከዳኛል ። "

"ደሞ ያንን ድንን ያለ ሣቅ ከየት አመጣኸው? የተመል ካቹን ልብ በሣቅ አፈረስከው እኮ!"

"ግን እንደምወድሽ ታውቂ ነበር? "

"ለመሆኑ ከዚህ ቀደም ቲያትር ሠርተህ ታውቃለህ? ፈጽሞ የመጀመሪያህ አይመስልም ።"

ለጥያቄዬ ምላሽ መስጠት ደንታ የነበራት አትመስ ልም። በዝምታ ጥቂት ተራመድን ። ከዕፅዋቶቹ መሐል ካለው



t.me/OLDBOOKSPDF

የድንጋይ መቀመጫ ላይ ዘፍ አለች ። እኔም አጠገቧ ተቀመጥሁ ። በዝግታ እጇን በትከሻዋ ላይ ጣል አድርጌ ከራሴ ጋር በሐሳብ ተሟገትሁና እንገቷን ወደ እኔ መለስ ስታደርግ ከንፈሯን ሳምኳት ። አልተቃወመችኝም ። የልቤ ምት ፍጥነት ጨመረ ። 'ዝግጅቱ እስኪያልቅ ለምን እዚያ እንቆይም?' ስፈራ ስቸር ሐሳብ አቀረብኩ ።

"የት?"

"እዚያ ።"

"እኮ የት?"

"ከቅጥር ግቢው ፊት ለፊት ካለው ሆቴል ። ጸጥ ያለ ምቹ ነው ።"

ብድግ ብላ ተከተለችኝ ። ክፍል ተከራይቼ ይገዋት ገባሁ ። እስከ ምሽቱ ሰባት ሰዓት ድረስ ቆየን ። ስንመለስ ፕሮግራሙ አልቆ ሁሉም ተበትኖ ነበር ።

በስብሰባ ላይና ጽ/ቤት አካባቢ ብንታይም በውል ተገናኝተን ሳንጨዋወት ረዥም ጊዜ አለፈን ። ከሦስት ወራት በኋላ ከስብሰባ አዳራሹ ስንወጣ አመቺ ሁኔታ ጠብቄ ልገናኛት ስሞክር እርሷም ፈልጋኝ ኖሮ እየጃፉ ስትጠብቀኝ አገኘኋት።

ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ፡ "ዛሬ ከሰዓት አብረን እንዋል" አልኳት ።

በአቅራቢያችን ወደሚገኘው ቁርስ ቤት እያመለከተች "ለጊዜው ቡና ጋዛልኝ" አለችኝ ።

ወደ ቁርስ ቤት በማዝገም ላይ ሳለንና ተቀምጠን ቡና ካዘዝን በኋላ ስለ ቲያትሩ ከተመልካች የተላከልንን አስተያየትና ስለ ኪነቱ አንዳንድ ነገሮች አነሣሁላት ። ፍላጐት ያደረባት አትመስልም ነበር ። ጨዋታ ቀየርሁና የቅድሙን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ በድጋሚ አቀረብኩላት ። "አብረን እንውልም?" እንገቷን ዝቅ አድርጋ በዝግታ ነቀነቀችው ።

"ለምን? ደስ አላለሽም?" ዐይኖቿ እንባ ሲያቀሩ ተመለከትሁ ። ሁኔታዋ እንግዳ ሆነብኝ "ተናገሪ እንጂ! በእኔ ምን ቅር ያለሽ ነገር አለ?" አልኩና ጉንጯን በመዳፌ ነካ አደረግኋት ። የተጣበቀ ከንፈሯን በዝግታ አላቅቃ መልስ ልትሰጠኝ ነው መሰል ቀና ስትል አስተናጋጁ የያዘውን ቡና ይዞ መጥቶ ኖሮ ዝም አለች ። አቅርቦልን ከሔደ በኋላ ትቀጥላለች ብዬ ዐይን ዐይኗን ባያት በዝምታዋ ጸናች ።

"ምን ነክቶሻል ወይንሸት ለምን አትናገሪም? " ስል አጥብቄ ጠየቅኋት ።

ዝቅ ባለ ድምፅ "አሞኛል" አለችኝ ያልቀመሰችውን ቡና በማንኪያ እያማሰለች ።

"ምንሽን? "

"ሆዴን"

"እንዴት ያረግሻል?"

"ዝም ብሎ ያመኛል ።"

"ምንድነው እሱ? ለምን አትመረመሪም?"

ድንገት ቀና ብላ ዐይን ዐይኔን እያዩች ፡ "ተመርምሬዋለሁ" አለችኝ በፍራቻ ።

"እህስ?"

ፊደሎቹን አንድ በአንድ እየቈጠረች "እርግዣለሁ" አለችኝ ። ክው አልኩ ። መላ አካላቴን ላብ አሰጠመው ።

"ምን ሆኛለሁ?" አልኩና ትክ ብዬ አየኋት ። በአንድ ቀን ግኙኝነት እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት ከራሴ ጋር ተሟገትሁ ። ቅዠት መሰለኝ ።

ከተቀመጥንበት ተነሥተን መውጫው በራፍ ስንደርስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከበስተኋላ አስተናጋጁ "ሒሳብ አልተከፈለም ወንድም" ሲለኝ እንደ መዓትን ብዬ የሆነውን ለማስታወስ ሞከርሁ ።

ከሳምንት በኋላ ጽ/ቤታችን ቅጥር ግቢ ውስጥ ጓደኛዋ አገኘታኝ ፤ "ይህች ልጅ ሆዷ እያስታወቀ መምጣቱ ነው ። ለምን ዝም ብለህ ታያታለህ? አንድ ነገር አድርግ እንጂ" አለችኝ ።

ላደርገው የምችለው ምንም አልነበረም ። መልስ ሳልሰጣት እቆመችበት ትቻት ቢሮ ገባሁ ። በሩን ቆልፌ እወንበሬ ላይ ተከንቸርሁና ብዙ አሰብሁ ። ሦስት ሰዓት ሙሉ ከተቀመጥሁበት ሳልነሣ ፤ ከዚያ ሁሉ የረዥም ሰዓት የሐሳብ ንትርክ መሐል አንድም ስንኳ ሁነኛ መፍትሔ ሳላገኝ ቀረሁ። ሞቴን ተመኘሁ ። ከሷ ጋር የተገናኘንበትን ቀን በጥላቻ እያስታወስሁ ያን ሰዓት ፤ ያን ቀውጢ ደቂቃ ረገምሁ።

በደባልነት ያኖረኝ የነበረውን ጓደኛዬን የገጠመኝን ችግር ሁሉ ዘርዝሬ ገለጽሁለትና መላ ፈጥሬ አንድ ቦታ እስከወስዳት ድረስ ለጥቂት ቀናት አብራን እንድትኖር ለመንኩት ። እርሱም ታዲያ "ምናልባት ለጥቂት ጊዜያት ትምጣና ትቀመጥ ። የቀለቧን ነገር አስብበት ፤ ከሆነ ወደ ቤት ውሰዳት" አለኝ ። ይህም ቀላል አልነበረም ። ከቤቷ ምን ብላ እንደምትወጣና የቀለቧም ጥያቄ አወዛጋቢ ነበር ። ብቻ ከሌላው ችግር አልበለጠምና መጣች ።

ቤተሰቦቿ ሳያዩዋት ዕቃዋን ጠቅልላ በወጣች በሳምንት እሩቅ አገር ሔጃለሁ ብላ ቅጥፈት የተመላው አሳዛኝ ደብዳቤ ጻፈችላቸው ። ያን ሰሞን መጠነኛ የመንፈስ ዕረፍት ብታገኝም ፤ ያልለመደችውን ሕይወት መግፋት እጅግ አዳግቷት ነበር ። መለስተኛ የወጥ ቤት ቁሳቁሶችን እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ክሰል ምድጃና ብረት ድስት የመሳሰሉትን ከጓደኞቿ ብታጠረ ቃቅምም አስቤዛውን በቀላሉ ማግኘት አልተቻለም ነበር ። ብዙ ተሯሩጬ በብድር አንድ ጆንያ ከሰልና ሩብ ኩንታል ጤፍ አስገባሁ ። እኛ ቀን ቀን እቤሮ ስንውል ጓደኛዋ እየመጣች በጋገራውና በአንዳንድ ሥራ እንድትረዳት ተነጋግረን እስኪሰለቻት ድረስ ብቻ ብቅ ትል ነበር ፡ እርሷም ብትሆን በወሯ መምጣቷን አቋረጠች ።

ጎረቤታችን የነበረው ባለኪዮስክ አንዳንድ ነገሮችን በዱቤ እንድወስድላት ስለ ፈቀደልኝ ውለታውን አልዘነጋውም ። በእንዲህ ዐይነት እቤት ከመጣች ከሦስት ወር በላይ ሆናት ። አንዳንድ ቀን ፍራንክ ሳጣና ሲርበኝ በዚያ ደካማ ዐቅሟ የሠራችውን ምግብ ዐልፎ ዐልፎ ልጋራት እገባ ነበር። የሚያስፈልጓትን ነገሮች ባለማግኘቷና የኑሮን ከባድ ሸክም በልጅ ትከሻዋ ልትቋቋም ባለመቻልዋ ብዙ ተጎዳች ። እኔም ነጻ ሆኜ እንደ ተቀሩት የሥራ ባልደረቦቼና የዕድሜ እኩያ ዎቼ ሕይወቴን እንደ ፈቀደኝ መምራት ባለመቻሌ ተበሳጨሁ ። ጓደኛዬ ለእኔ ያለው ግምትና አስተያየት ብዙ መቀየሩን ከዕለት ዕለት በሁኔታው በመረዳቴ ተከፋሁ ። "ለዚህ ሁሉ መንሥዔዋና ተጠያቂዋ ወይንሸት የምትባል ጣጠኛ ነች" በሚል እጉል እምነት ተማረርሁባት ።

አንድ ቀን በልደታ ሰሞን ፡ ደሞዜን ተቀብዬ ለዚህም ለዚያም ቀናንሼላት ለባለኪዮስኩና ለጎረቤቶቹም ዕዳዬን ከፋፈልሁና የተረፈችኝን ሁለት ፓውንድ ይዤ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ስዞር አመሸሁ ። አንድ ሁለት ስንባባል የመለኪያው ቁጥር ከፍ አለና ሞቅ አለኝ ። ኪሴ ሊከዳኝ ዝርዝር ፍራንክ ብቻ ሲቀሩኝ "ደህና እደሩ" ተባባልንና ወደ ቤት አቀናሁ ። እግቢው አጠገብ ስደርስ በጣም ተጫጫነኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወይንሽትን ማየት አንገሽገሸኝ። ወደ ፊት ሕይወቱን በፈለግ ሁትና ባመቸኝ መንገድ አቅጄ መኖር እንዳልችል ደንቃራ የሆነችብኝ መሰለኝ ። ባየኋት ቁጥር ብስጭት ይገባኛል ። እርሷን የማላይበት የትም መሔድ አስመኘኝ ። በሩን ሳላንኳኳ ጎራ አልኩ ። ዳቦ በሻይ እያማገች ስትበላ ደረስሁና ቃል ሳልተነፍስ ተቀመጥሁ ።

"ሻይ ልስጥህ?" አለችኝ ። በአንገት ጥቅሻ አሉታዬን ገለጽሁላት ።

"የት አምሽትህ ነው በዚህ ሰዓት ...?" እስከትጨርስ አልጠበቅኋትም ።

"መጠየቅ መብትሽ አልመሰለኝም ።"

"ሀው-ቃለሁ...ግን ለምን ትጠጣለህ?"

"ለምን እንደሆነ ታውቂዋለሽ ። በአንቺ ምክንያት መጠጥ ባቻ ሳይሆን ገና መርዝም ሳልጠጣ አልቀርም ።"

"እንዲህ እንድትለኝ አልፈልግም ። በእኔ ልትናደድ ከቶ አይገባህም ። ዕዳህን ፡ መከራህን በመሸከሜ አንገቱን ደፋሁ እንጂ አንተን አላማረርኩም ። የወላጆቼን የሞቀ ቤት ትቼ በዚህ ጨለማ ጎጆ ቁም ስቅል በማየቴ በዕድሌ እንጂ በአንተ አላዘንኩም ። ነውርህንና የእኔንም ነውር አደባባይ ላለማውጣት በእና ክፍልህ ውስጥ እኔ ተሸሽግሁ እንጂ አንተ ከዚህ ቀደሙ የተለየ ምንም አልሆንክም ።"

"በፈጠረሽ አንቺ ልጅ ከፉ አትናገሪኝ ። መቈጣጠር ያልቻልሽውን ግንፍል ስሜትሽን ማብረጃያ በማድረግሽ ፡ ብሩህ የሆነውን መጪውን ሕይወቴን አጨልመሽብኛል ። ከዚህ የላቀ ምን እንደሆን ትፈልጊ ኖሯል ። በቃሽ! ይብቃሽ!



t.me/OLDBOOKSPDF

ይብቃሽ ዝም በይኝ!" በማለት ቤቱን በጩኸት አናጋሁት ።

"እንዲህ ስንኩልና ደካማ አስተሳሰብ ይኖርሃል ብዬ ፍጹም አስቤ አላውቅም ። የምትናገረው ከአንተ አንደበት መውጣቱን ማመን አዳግቶኛል ። 'ግንፍል ስሚትሽን' አልከኝ? ፍላጎቱ እንኳን የጋራችን ነበር ። እኔም ሆንኩ አንተ ተከታዩ ይህ ይሆናል ብለን አላሰብንም ። ዳሩ ግን ዛሬ በአጋጣሚ ከተፈጠረው ሁኔታ ልታጽናናኝ ሲገባህ ተጠያቂዋ እኔን ብቻ አድርገህ በማቅረብህ በጣም አዘንኩ" ብላ ሲቃ እየተናነቃት ጨረሰችና ቃላት ገድበዋቸው የነበሩት ሁለት ዐይኖቿ እንባዎቿን ለቀቋቸው ።

"ተከታዩ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ የምትችይው ና መቈጣጠር የሚገባሽ አንቺ ነበርሽ ። ልትፀንሽ የምትችይበትን ጊዜ ማወቅ ያንቺ እንጂ የእኔ ድርሻ አይደለም ። እውነቱ ይህ ስለሆነ በእንባ ሽፋንነት የምታጉርፊያቸው ቃላት ሊዋጡልኝ አይችሉም ።"

"የምፀንስበትን ጊዜ ሳላውቀው ቀርቼ አይደለም ።"

"ሆን ብለሽ ነው ማለት ነዋ !"

"ለምን ነው ሆን ብዬ? አይደለም ።"

"እምቅ ወላፈን ስሚትሽን ለመወጣት ፡ ታዲያ ለምን ነው?"

"መሳሳት ሊኖር እንደሚችል ይገባሃል?"

"እህ...ስሕተት! እም...በፀት ፡ መማር ፡ መታረም ፡ የማያቀኑት ድፍን ስሕተትሽ ነዋ የኑሮዬ እንቅፋት! በሞኝ ለቅሶሽ ባትነዘንዥኝ ። እረ ላንደበትሽ ልጓም አብጅለት አንቺ ሴት! ማቅኛ በሌለው ጠማማ ስሕተትሽ መረገሚ አንሶኝ በምላስሽ ዥለጣ ዕረፍት ትነሺኝ ?"

አልመለሰችልኝም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥታ ሆነ ። ሬዜኸቴን ሲያስተጋባ የነበረው ክፍል በትንኞች የአዝዝታ ድምፅ ተተካ ። ዳግም ጸጥታውን እኔው አደፈረስኩት ።

“መዕንሰንስ በነሰሽ ። ግና በእንጭጩ ብትገልጪልኝ መንገድ ልንሻለት ስንችል ለምንድነው አፍጦ እስኪመጣ ዝም ያልሺኝ ?”

“ለብቻዬ መፍትሔ የማገኝለት መስሎኝና እንተንም ላለማስጨነቅ ስል እንጂ ፣ ከአንተ የማረግዘውን ልጅ ወርቅ አድርጌ በማየቱ አይደለም ። ለምን ካንተ መውለድ የጓጓሁ አርገህ ትገምታለህ? ራስህን ለምን ከበህና አልቀህ ታያለህ? በየቦታው የምታላዝንለት የትምክህተኝነት ወገዛ ከየትኛ ውም ጉልተኛ ይልቅ ጎልቶ ይታይብሃል ። ለመሆኑ አንተ ምንድነህ? ማነህ አንተ?”

መልስ መስጠት ተሰኖኝ ድንገት ብድግ ብዬ በጥፊ አላስኳት ። ጸጥ አለች ። መላ ሰውነቷ በንዴት ተንቀጠቀጠ ። ብድግ ብዬ እመኝታ ቤት ገባሁና ተጋደምሁ ።

እንቅልፍ ፈጽሞ አልወሰደህም አለኝ ። በአልጋው ግራና ቀኝ ለረዥም ጊዜ ብዙ ተገላበጥሁ ። ወይንሸት እሳሎኑ ውስጥ እሶፋ ላይ ተደፍታ ስታለቅስ ሕቅታዋን ሰማሁ ። ርህራኄ የለሹ የንዝንዛዬ መንሥኤና ውጤት እንጀት የሚያበግን ዐዐት ውስጥ ዶለኝ ። የአዕምሮዬን አለመብሰልና ኋላ ቀርነቴን ላንድ አፍታ አመንኩኝ ። ትምክህት ምን ያህል እንደ ተጠናወተኝ ተሰማኝ ። የእኔን ነውር ኃጢአቴን በማዘሏ ከወላጆቿ እቅፍ ተላቅቃ በአና ጎጆ በዕውር የሕይወት ሳንክ መማቀቋ ሳያንሳት በእኔ የሞቅታ ድንፋታ የማይድን ቁስል እንዳኖርኩባት ብልጭ አለብኝ ። ዐይኖቼ እንባ አዘሉ ። በቅድሙ የወንድነት ትምክህቴ ሊደፈን ሳይችል በመቅረቱ


t.me/OLDBOOKSPDF

ትራሱን አረጠብኩት ። ተነሥቼ ላጽናናት የመንፈስ ዕረፍት ታገኝ ዘንድ ይቅርታ ልጠይቃት ቃጣሁ ። የዕብሪቱ ቅሪት ግን ተጫጭኖ አስቀረኝ ። እንባዬ በብዙ ሲፈስ የእዕምሮዬን ጭንቀት ያሚሚው ይመስል እንቅልፍ ወሰደኝ ።

በበነጋው አርፍጄ ተነሣሁ ። ለባብሼ ከጓዳ ስወጣ እምድጃ ላይ ሻይ ጥዳ አገኘኋት ። ፊቴን ታጥቤ ጠጉሬን አበጃጀሁና ልወጣ ስል ፡ "ቆይ ሻይ ጠጥተህ ሒድ" አለችኝ በአሳዛኝ ዜማ ድምፅ ። ይብስ ጭንቀት ተሰማኝ ። ዳግም የምታናግረኝ አልመሰለኝም ነበር ። የምሽት ምግባሬን የሚሰርዝልኝ ቃል አጣሁ ።

"ለመሆኑ ከትላንት ወዲያ ሐኪም ቤት ምን አሉሽ?" አልኳት ። የካርድ ማውጫ ሰጥቼያት ልደታ ክሊኒክ እንድትመረመር ነግሬያት ነበር ።

"ዛሬ ተመለሽ ብለውኛል ። ይህንን መድኃኒትም አዘውልኛል ። ግን ከአንድ ወር በላይ የሚኖረኝ አልመሰለኝም" አለችኝ ።

ወጥቼ ከሱቅ 5 ብር ተበድሬ መሐጃ ብዬ ሰጠኋትና የታዘዘላትን የመድኃኒት ወረቀት ተቀብዬ ወደ ቢሮዬ ሔድኩ።

ውሎ ሳያድር ሆዷ እየገፋ ፡ ቀኗም እየቀረበ መጣ ። ቤቱን ያዳበለኝ ጓደኛዬ "ስለዚህች ልጅ ምን አረግህ?" አለኝ ።

"ዛሬ ለእኅቴ እደውልለታለሁ ። ምንም ምርጫ ስለሌለኝ ቀና ባይመልስልኝም የግድ እዚያው እሱ ጋ ይገርት እሔዳለሁ ። ቢከፋም አውጥቶ አይጥላትም" አልኩት ።

መጣጣም ከተውን ሰንብቷል ። "መቼ ነው የምትሔደው?" ባለኝ ቁጥር ነገ ተነገ ወዲያ እያልኩት ብዙ ቆየ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በፊት ለፊት ይናገረኝ የነበረውን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመተው ወዳጄ በሆነች የቡና ቤት ደምበኛ በኩል ነጋ ጠባ ያስወተውተኝ ጀመር ። አሁን ካለችበት ሁኔታ የተለየ ሊያደርገው የምችለው ምንም ዐይነት ነገር አለታይህ ስላለኝ "አላስብክበትም" የሚሉኝን ሁሉ ጠላኋቸው ። የወይንሸት ንም ፊት ማየት ዘወትር መንፈሴን ይረብሸው ስለነበር ዐልፎ ዐልፎ ሌሎች ጓደኞቼ ዘንድ አድር ነበር ።

አንድ ቀን እውጪ አድሬ በበነጋው ማምሻ ላይ ወደ ቤት ብመጣ አደጃፍ ላይ ልብሶቼ ተከምረው አየሁ ። ወይንሸት እንዲያ ሆዴ ተንቀፍድዶ ምግቧን ከማዘጋጀት ዐልፋ ዘወትር የምቀይራቸውን ልብሶች ታጥብ ነበር ። ውሃ ልትቀዳ ሔዳ ይሆናል ብዬ ወደ ቧንቧው ብቅ ብል አጣኋት ።

ባለ ሱቁን ብጠይቀው "የት እንደምትሔድ አልነገረች ኝም ግን ፣ ከአንዲት ልጅ ጋር ስትወጣ አይቻታለሁ" አለኝ ። ግራ ተጋባሁ ። ወትሮ ከቤት ወጥታ አታውቅም ። ምን ሆና ይሆን ብዬ አሰብሁና ወደ ጓደኛዬ ወዳጅ ቡና ቤት አዘገምሁ። ጎራ ስል ጓደኛዬ ሰለሞን ከወዳጄ ጋር ካርታ ሲጫወት አገኘሁት ።

ጥቂት አብሬያቸው ተጫወትሁና የወይንሸት ቤት አለመኖር አሳስቦኝ ልወጣ ስል "እፈልግሃለሁ" አለኝ ። ወዳጄ ጉዳዩ የገባት ይመስል ክፍሉን ትታልን ወጣች።

"ስማኝ ሙሉጌታ ፣ ይህችን ልጅ ነገውኑ ወደምትፈል ግበት ቦታ ውሰድልኝ ። እኔ ብዙ ተጨነቅሁ ። ሥጋት ፣ ሐሳብ ፣ እንቅልፍ ነሥቶኛል ። ዘወትር ብጨቀጭቅህም ልትሰማኝ አልቻልክም ። ከእንግዲህ ትዕግሥቴ ተሟጦ አልቋል ። ዐዋቂ በሌለበትና በእኔም በአንተም ኪስ ውስጥ ቤሳ በማይገኝበት ወቅት ይህች ሴት ምጥ ቢይዛት መጨበጫ


t.me/OLDBOOKSPDF

የለንም ። ኋላ እቤት ውስጥ ብትሞት ጣጣው የእኔ ነው ። ለምን በገዛ እጄ እስር ቤት እገባለሁ? 'ከእንግዲህ መላ ብትፈልግ ይሻልሃል ። ነገ ጠዋት' አለኝ ።"

እንገቴን አቀርቅሬ ለብዙ ደቂቃዎች ዝም አልሁ ። መፈጠሬን ጠላሁ ። የተወለድሁበትን ቀን ረገምሁ ። ብዙ ችግሮችን አብሬው ልካፈልና ሊካፈለኝ እምነት ከጣልሁበት ሰው ይህን መስማት ሞት መሰለኝ ። ሕይወቴን ለማጥፋት ተመኘሁ ። ጥፍሮቼን በጥርሶቼ እየነከስኩ እንገቴን እንደ ደፋሁ ቀረሁ ።

"ሰምተኸኛል? ነገ ወደምትወስድበት ውሰድልኝ" አለኝ።

"ሰምቼሃለሁ ፡ እወስዳታለሁ" አልኩት እንገቴን ካቀረቀርኩበት ሳላቀና ። እዚያው የተቀመጥኩበት ጥሎኝ ወጣ።

ወዳጄ ከንዳ ብቅ ብላ ተራዋን ትነዘንዘኝ ገባች ። "ሰለሞን የሚነግርህን በከፋ አትውሰደው ። ለአንተም ሆነ ለእሷ የሚላችሁን መምረጡ እንጂ ሊጎዳችሁ አስቦ አይደለም። ደጋግሜ ብነግርህ አልሰማሽ አልከኝ እንጂ የሚያዋጣህ ወደ እናቷ ዘንድ መውሰዱ ነው ። ከእናት የተሻለ የልጅን መከራ የሚችልና የሚሸከም የለም ። አሁንም ሰው የሚልህን እሺ ብትል ውሰዳት ፡ እቤተሰቦችዋ ዘንድ ትውለድ ፡ ምንም ቢሆን የወለደች እናት..."

ከዚህ በኋላ አልሰማኋትም ። እርሷ ግን ማውራትዋን አላቋመችም ። ብዙ ለፈለፈች ። ሰለሞንም እንዲናገረኝ የመከረችውና የገፋፋችው እሷ ሳትሆን አትቀርም ብዬ ገመትሁ ። ወይንሸትን ወደ እናቷ ቤት ውሰድ ስለሚለው ነገር ስትወተውተኝ ይህ የመጀመሪያዋ አይደለም ። ንግግሯ



t.me/OLDBOOKSPDF

አልዋጥልህ አለኝ ። ወይንሸትም ብትሆን ወደ ቤተሰቦችዋ ስለመሔድ ከሚነግባት እራስዋን በራሷ መግደል እንደምትመርጥ ብዙ ጊዜ ትናገራለች ። ያም ሆኖ ይህ ስለምንና ወዲያ ልክ ናቸው ። በኪሴ ቢሳ ሳይኖረኝ የሰው ሰው በእና ቤት አጋድሜ ድንገት ምጥ ቢያዛት መድረሻ የለኝም ። የመጀመሪያዋና ልጅ በመሆኗም ምጡ ቀላል ላይሆን ይችላል ። ታዲያ እንድ ጉዳት ላይ ብትወድቅ ጣጣው ለነስለሞን መትረፉ መች ይቀራል? ሊናገሩ ይገባቸዋል በማለት አቀርቅሬ ብዙ አሰብኩ ። ይሁን እንጂ የአይጥ መውጫ ቀዳዳ ታህል የተኘለ አማራጭ አልታየህ አለኝ ።

መጨበጫ የሌለው ሐሳብ በአዕምሮዬ እያብላላሁ ወደ ቤት አዘገምሁ ። እቤት በራፍ ስደርስ እንዴት የኀረቤት ሴትና ባለኪዮስኩ መዝጊያው ላይ ቆመው አየኋቸው ። የእኔን መምጣት ሲያዩ ተጠቃቅሰውና ተቻኩለው ወጡ ። ሰላምታ ሲሰጡኝ ከወትሮው የተለየ መልስ አየሁባቸው ። ገባ ስል ወይንሸትን ሸራ አልጋዋ ላይ እንደ ተጋደመች አገኘኋት ። ፊቷ ፍም መስሏል ። ክንፈሯም እንደ ኩበት ደርቋል ።

"ምን ሆንሽ?" አልኳት ።

"ምንም" ስትል የጋቢዋን ጫፍ ቁጨት እያፍተለተለች በቀስታ መለሰችልኝ ።

"እመመሽ? ደግሞስ ጎረቤቶች ያለ ወትሮዋቸው እየተጠቃቀሱ እኔ ስመጣ ተቻኩለው የወጡት ለምንድነው?"

"እንዲያው ... እንደዬት ዋልሽ ሊሉኝ መጥተው ነው" አለችኝና በአፋር ዐይኗ ቀስ አርጋ ተመለከተችኝ ። አንድ ነገር እንዳለ ተሰማኝ ። በቀላሉ ልትነግረኝ እንደማትፈልግ ገባኝና ተነሥቼ ወደ ተጋደመችበት ድንክ አልጋ ሔድኩና እሜና ላይ ቁጭ አልሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ወይንዬ ንገሪኝ ። ምን አዲስ ነገር አለ?" በማለት ጸጉሯን እየዳበስኩ ካረገዘችበት ቀን እንዖሥቶ አላይቻት በማላውቀው ልዩ ልስላሴ ጠየቅኋት ።

"ዐይኖቿ እንባ አቅርረው መሬት መሬት እያየች ፡ "ምንም አዲስ ነገር የለም" አለችኝ ። ጎንበስ ብዬ ግንባሯ ላይ ሳም አደረግኋት ። ዐይኖችዋን በጣቶቼ አበስኩና የሆነችውን እንድትነግረኝ ተማጠንኳት ።

"ጧት ልብስህን ላጥብ አወጣሁና ውሃ ቀድቼ ስመለስ ሰለሞን በድንገት ደርሶ ነይ ብሎ ወደ ቤት አስገባኝና ይህን ልጅ አትመኚው ። ነገና ከነገ ወዲያ የሚደርስብሽን አስ ቢው። እዚህ ቤት ውስጥ እወልዳለሁ ብለሽ ፍጹም እንዳትጎ ዳቺ አለኝኮ !" በማለት ቅድም መጠዋ ቤት ውስጥ ለእኔ የነገረኝን ሁሉ እንደ ተናገራት አጫወተችኝ ።

"አንቺስ ምን አልሽው?"

"እኔማ ምን እለዋለሁ ። ድንገት ተነሥቶ ነገሁን ሕጂልኝ ማለቱ ችግር ውስጥ ሊጥለኝ ነው ብዬ ሠጋሁ ፡ እርግጥ የእኔ እዚህ መቆየት በኑሮው ላይ እንቅፋት መሆኑን ባምንበትም ፡ ለአንተ ፡ ለእኔም ሳይል ላረገዝኩት ሕፃን ሲል ይቅርታ እንዲያደርግልንና ለአንድ ሳምንት ያህል ብቻ እንዲታገሠኝ ለመንኩት ። ሆኖም እርሱ ዐይኖቹን ጠበብ አድርጎና እጆቹን ጨብጦ ጠረጴዛውን በኃይል እየመታ አንገቱን ነቀነቀና..." በማለት እንባዋን ዘረገፈችው ።

የሰጣትን መልስ መገመቱ አላዳገተኝም ነበር ። የምይዝ የምጨብጠውን አሳጣኝ ።

"ከዚያስ?" አልኳት ።

"ከዚያማ በኋላ ተመናጭቆ ጥሎኝ ወጣ ።"

"እኔ ስመጣ ያጣሁሽ የት ሔደሽ ነው?" ስል ጠየቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኋት።

ዓይናለም ወይምትባል ባለ ትዳር ጓደኛዋ ጋ መሔድዋ ንና ችግሯን አጫውታት የምታርፍበትና የምትወልድበት ቦታ እንደ ጠየቀቻት ፤ ሳይሳካላትም መምጣቷን እያነባች ነገረችኝ ።

“በኋላስ?”

“ይኸው ነው”

“ጎረቤቶቹና ባለ ኪዮስኩ ታዲያ ምን አይተው ነው እንዲያ የተቅበጠበጡት?”

“ምንም ይኸው ነው በቃ ።”

መልሷ አላጠገበኝም ። ያልነገረችኝ ነገር እንዳለ ታወቀኝ። ከዚያ በላይ እንደማታወራልኝ ገባኝና እንባዋን በመሐረቤ እየጠራረግሁላት አጽናንቻት ወጣሁ ። ባለ ኪዮስኩን ወደ ውጪ ጠራሁትና ምን እንደ ተፈጠረ ቢነግ ረኝ ብዬ ተለማመጥኩት ።

“አትራቃት ፤ ምንም የተፈጠረ ነገር የለም ፤ ብቻ አትራቃት” አለኝ ከንፈሩን እየመጠጠ ።

“ናስር ፤ ከእኔ የምትደብቀው ነገር እርሷን ምንም አይጠቅማት ። በነገሩ እንዳስብበት የሆነውን ብትነግረኝ ይሻላል” አልኩት ።

እጇን ጨብጥ አድርጎ ወደ ጎን ጎተተኝና ‘የሙልዩን ልብስ ላጥብ ነው ፤ በረኪና ስጠኝ’ አለችኝ ። እኔም ደግሞ ‘አሞ ቅድም ወስደሽ አልነበረም ወይ’ ብላት ‘ነጭ ሸሚዝ ነው ፤ አሞ አያስለቅቀውም’ ስላለችኝ ሰጠኋት ። አስተያየቷና ሁለመናዋ ይቀፍ ነበር ። ተጠራጥሬ ተከትያት ስገባ በረኪናውን ልትጠጣው ስትል ደረስኩባት ። እጇን እንዴ፡ እንዳስለቀቅሁት አይታወቀኝም ። ስሮጥ ገብቼ ጸጉርዋን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጨምድጄ አቀናሁዋትና በቃሬያ ጥፊ አጮልኳት ። በንዴት እየተኮላተፍኩ ብዙ ቀባጠርኩ ። ምን እንዳልኩ ግን አላስታውስም" ብሎኝ ራሱን ደፋ ።

እሷ ሽራው አልጋ ላይ ፣ እኔ ደግሞ ቀድሞ ትተኛበት የነበረው ሶፋ ላይ እንቅልፍ ዝር ሳይልብኝ ሁለታችንም እንደ ተፋጠጥን አደርን ።

ዘወትር በሐሳብ ጭልጥ ስልና ጥንት የነበረው ተጫዋችነቴና ቀልደኛነቴ አለመታየቱን ለረዥም ጊዜ በማየት ምን እንደ ሆንኩ እንድነግራቸው ሲነዘንዙኝ ለነበሩት የሥራ ባልደረቦቼ በዚያን ምሽት ማግሥት ምስጢር አድርጌ ይዤው የነበረውን ታሪኬን ዝርዝር አድርጌ አጫወትኳቸው። በጣም አዘኑ ። ብዙም ተጨነቁልኝ ። መላ ሲያወጡና ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ ተሰባስበው በዕቁብ መልክ በርከት ያለ ገንዘብ ሰጡኝ ። ለአማራጭ ካቀረቡልኝ ሐሳቦችም መሐል ወደ አጎቴ ቤት ይገኘት መሔዱ ጸደቀ ።

የዚያኑ ዕለት ማታ የባቡር ትኬት አስቆረጥኩና ኅዘኔን ጠቅልለን ጉዞ ወደ ሐረርጌ ጀመርን ። ሲነጋጋ ድሬዳዋ ከተማ ደረስን ። በባቡር ጣቢያው በረፍ ላይ ከዕቃዎቼ ጋር አቆይቻት አልጋ ለመከራየት ሔድኩ ። እግረ መንገዴን አጎቴ ቤት ጎራ አልኩና ብጠይቅ ለሥራ ጉዳይ ወደ ሌላ ቦታ መሔዱን ባለቤቱ ነግራኝ እንድገባ ጠየቀችኝ ። ያለሁበትን ማወቅ ተሳነኝ ። መላው ዓለም በተቃውሞ የተነሣብኝ መሰለኝ ። ለአጎቴ ባለቤት ጥያቄ ምላሽ ሳልሰጥ እንዳበደ ሰው ከንፌ ወደ ባቡር ጣቢያ ሔድኩ ። ዕቃዎቼን ተሸክሜ የተከራየሁት ሆቴል አደረስኳትና ሌሊቱን ያለ እንቅልፍ በመጓዛችን እንድትተኛ ነግሬያት እኔ ወደ ቡና ቤት ገባሁ ። የደም ሥሮቼ ሲነዝሩ ይሰማኛል ። መላ ሕዋሳቴ ዝለዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሳላፊው እስኪያንቀው ድረስ ሦስት ቡና አከታትዬ ጠጥቼ ወጣሁ ። ከጋሼ መ ቤት ደረስሁና ደብልዋ ለማጣራት ጠየቅሁ ። ሐረር አንድ የተከፈተ ኤክስፖ ላይ በአስረጂነት መመደቡ ተነገረኝ ። እዚያው ሆቴል እንደ ተኛች ትቻት ወዲያው ታክሲ ተከራይቼ ወደ ሐረር አመራሁ ።

በተባለው ኤክስፖ ላይ አገኘሁት ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በሥራ ምክንያት ብዙ ሊያጫውተኝ እንደማይችል ገልጾልኝ በምሳ ሰዓት አንድ ሆቴል ቀጠረኝ ። እስኪረፍድልኝ ድረስ ያለምንም ዐላማ ሐረርን ከላይ እስከ ታች ዞርኳት ። በምሳ ሰዓት ሆቴሉ ውስጥ ሲጠብቀኝ አገኘሁት ። አብረን በልተን ስለ ዘመድና ስለ ኑሮአችን ተጠያየቅን ። ሊሔድ ሲል ወደ ድሬዳዋ ሔጄ እቤት እንድጠብቀው እርሱ ግን ለሦስት ቀናት ያህል እንደሚቆይ ነገረኝ ። ያኔ የምናገረው ጠፋኝ ። እሺ ብዬው ተለያየሁ ። መኪና ተራ ስደርስ ግን ሐሳቤን ቀይሬ ወደ ድሬዳዋ የተከራየነው ሆቴል ስልክ አደረግሁ ። ቦዩ ገና እንዳልተነሣች አረጋግጦ ነገረኝ ። ቀስቅሶ ምግብ እንዲሰጣትና ለዘ ዩን ቀን መመለስ እንደማልችል እንዲነግራት ለምኚው ለሚገጥማት ችግር ሁሉ አጠገቧ ሆኖ እንዲረዳት አደራ ብዬው ተመለስኩ ።

እኅቱን ቀን ምሳ የበላንበት ሆቴል አልጋ ይዤ ጠበቅሁት ። ሲመሽ መጣ ። አለመሔዴን ሲያይ ተገርሞ ጠየቀኝ ። ሐረርን ብዙ ስለማላውቃት አመቺ ሁኔታ ስለ ገጠመኝ ነው ብዬ ዋሸሁት።

ከራት በኋላ ቢራ ጋብዞኝ ፤ እየጠጣን የባጥ የቆጡን ስናወራ አመሸን ። በጫወታው መሐል ሐሳብ ይዞኝ ጭልጥ ስል ግራ እየገባው ምን ሆንክ ይበለኝ እንጂ እንዴት እንደምነግረው ግራ ተጋብቼ ብዙ አቅማማሁ ። ለቢራው



t.me/OLDBOOKSPDF

ፋታ አልሰጠሁትም ። በአጠጣጡ ሳይገረም አልቀረም ። ብቻ ጠርሙሱ ባዶ መሆኑን ባየ ቁጥር ያስጨምርልኝ ነበር ። የኋላ ኋላ ግን ውስጥ ውስጡን አምቆ ይተናነቀኝ የነበረውን ጉዳዬን አፈነዳሁት ። በጥሞና አዳመጠኝ ፤ በሁኔታውም በጣም አዘነ። ለረዥም ጊዜ አሰበና "አልማዝን አማክሬታለሁ" አለኝ ። አልማዝ ባለ ቤቱ ናት ።

"ጋሼ የመጨረሻ ተስፋዬ አንተ ነህ ። ከእንግዲህ የምደርስበት የለኝም ። ቀላል ለሆኑ ነገሮች እንኳ አንተን ማስቸገር ምን ያህል እንደምፈራ ታውቃለህ ። ዛሬ ግን የራሳ ሳጥኑን ትክ ብሎ የሚያስተውል በድን ብቻ በመሆኔ ለአካባቢዬ ነውር ደንታ ቢስ ሆኛለሁ ። ትርፍ አማራጮቼ ማጥኔ ውስጥ መግባት ወይም የጋፍረት ማቄን አጥልቄና በሰው ዘንድ ተዋርጄ ሦስት ነፍስ ማዳን ነው ። እባክህን አንተም በርህን አትዝጋብኝ" አልኩት ፤ በሚተናነቀኝ የእንባ ጭጋግ መሐል እያየሁት ።

"ዐቅሜ በፈቀደው መጠን ማድረግ የሚቻለኝን አደርጋለሁ ። ሥጋት አይደርብህ" አለኝና የጠጣነውን ዋጋ ከፍሎ ወደ መኝታው ሔደ ።

ያኔ ብቻ ሕይወት እንዳለኝ ተሰማኝ ። ያኔም ብቻ መንፈሴ በውል ታወቀኝ ። ትከሻዬን አጉብጦ የተጫነኝን ሸክም ከላዬ ላይ ያወረደልኝ ይመስል ቀለለኝ ። ለብዙ ሰዓታት ባልተኛም ቅሉ ያልታወሰኝ ዕረፍት ማጣትና እንቅልፍ ድካሙ ያን ጊዜ ተሰማኝ ። እክፍሌ ገብቼ ልብሴን ሳላወልቅ ድብን ብዬ ተኛሁ ።

በበነጋው በሱ ቦታ ሰው ተክቶ ጋሼ አብሮኝ ወደ ድሬዳዋ መጣ ። በቅድሚያ ወይንሸት ወዳለችበት ሆቴል ሔድን ። ጥቀርሻ መስላለች ። ዐይኖቿ ሰርጉደዋል ። ጸጉርዋ


t.me/OLDBOOKSPDF

ተንጨፈብሯል ። ከገፋው ሆዷ በስተቀር ቆዳ የተለጠፈበት ዐፅም መስላለች ። የዘጠኝ ወር የመንፈስ ጭንቀትና ጉስቁልና እንጂ የዘወትር መልኳ አለመሆኑን መገመት አልተሳነውም። በሁኔታዋ በጣም አዘነላት ።

ባለቤቱ ጥቂት ብታመናጭቀውም የወይንሸትን እቤት ውስጥ እንዳትወልድ አልሞገተችውም ። ወይንሸትም ብዙ አልቆየች ። አጎቴ ቤት በገባች በ፬ኛው ቀን ምሽት ወንድ ልጅ ተገላገለች ። እኔም ወዲያው አዲስ አበባ ተመልሼ ወደ ሥራዬ ገባሁ ። ሦስት ወር ሙሉ ልጇን እያጠባች አብራቸው ከረመች ። በኋላም ጋሼ ስልክ ደውሎልኝ ወይንሸት ወደ ቤተሰቦቿ መሔድ መፈለጓንና እንደሚሸኛት አስረዳኝ ። ልጇን ግን እዚያው አስቀረው ።

ከዚያ በኋላ አይቻት አላውቅም ። ብቻ በአራት በአምስት ወር እየሔደች ልጇን እንደምታይ ጋሼ ነግሮኛል ። "አሁንማ ልጇን ብታይው ትልቅ ሆኗል ። ጋሼ በአምስት ዓመት ጋብቻ ምንም ልጅ ባለማፍራቱ እንደ ራሱ አድርጎ አቀማጥሎታል ። በጣም የሚገርመው ግን ይህ በሆነ ዓመት ከመንፈቅ ባልሞላ ጊዜ አንዲት ሴት ልጅ ለማግኘት በመ ቻሉ ማሙሽን ሲሳይ ብሎ ስም አውጥቶለታል " በማለት ጨዋታዬን ጨረስኩና በረዥሙ ተንፍሼ ቀና አልኩ ።

እመቤትም በተመስጦ ስታዳምጠኝ ቆይታ ኖሮ ከእኔው ጋር እኩል ተንፈሰችና ጣቶቿን እንቋቁታ ፡ "ወይንሸትንስ ከዚያ በኋላ አላገኘኻትም?" አለችኝ ።

በጭራሽ" አልኳት ፡ ድጋሚ የያዝኩትን ቢራ በአንድ ትንፋሽ ግማሽ አድርሼው ።

"እውነትህን ነው?"

"እውነቴን ነው ። ብቻ ከሦስት ወር በፊት አንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ረኝም ደብዳቤ ጽፋልኛለች ። ፩ ገጽ ሙሉ ።"

"ምን ብላ?"

"ነገሩ ብዙ ነው ። ጠቅለል ባለ መልኩ ባለፈው ሁለት ዓመት ስላሳለፍነው የሥቃይ ጊዜ ፤ ስላየችው መከራ ፤ እንዴት እንሳቁላት እንደ ነበርና እኔም በእርሷ ሁኔታ ላብድ ጥቂት ቀርቶኝ እንደ ነበር ፤ ስለ ትምክህተኝነቴ... ይሞም ምን ያህል እንደምትወደኝ ፤ እንዴት ጠልታኝ እንደ ነበርና እንደምታፈቅረኝ...ብዙ ብዙ..."

"ልጇንስ መውሰድ ትፈልጋለች?"

"እሷ ብትፈልግም ጋሼ ፈቃደኛ አይሆንም ።"

"እህህም" በማለት አንገቷን ወዘወዘችና "እንሒድ" አለችኝ ።

"ቆይ እንጂ ትንሽ እንጫወት ገና ነው " አልኩና ሰዓቴ ተመለከትኩ ። እውነትም ሳናውቀው ብዙ ገፍቶ ነበር ።

"ከእንግዲህ ለምን ትሔጃለሽ? አብረን ብናድር አይሻልም?" አልኳት ። እመቤት የቢሮ ሠራተኛና ባለትዳር ከሆነች ከታላቅ እኅቷ ጋር የምትኖር ስትሆን ብዙ ቁጥጥርና የቤተሰብ ተፅእኖ የለባትም ። አብረን ባመሸን ቁጥር ሰዓቱ ሳናስበው ከገፋ ለእኅቷ ስልክ ደውላ በመንገር ብቻ አብረን እናድር ነበር ።

ዛሬ ግን ጥያቄዬን አልተቀበለችም ። በዝምታ ብድግ ብላ ወደ በሩ አመራች ። ሒሳባችንን ከፈልኩና ተከተልኳት። አልጠበቀችኝም ።

"እመቤት!" ስል ጠራኋት ዝም ብላ ሔደች ። እንዲያውም እርምጃዋን አፈጠነችው።

"ስሚ እንጂ..እመቤት..ምን ነካሽ? ዝም ብለሽ" መለስ ብላ እንኳ አላየችኝም ። አውቶቡስ ፌርማታው አጠገብ


t.me/OLDBOOKSPDF

ስትደርስ ታክሲ አስቁማ ዘው አለች ።

በመስኮት አንገቷን ብቅ አድርጋ "ቻው" አለችኝ ፤ "ቻ" ን ጠበቅ አድርጋ ።

ምንነቱ ብዬ አሰብኩ ። ከእኔና ከእርሷ የጋለ ፍቅር ባሻገር ከወይንሸት ጋር ያደረግሁትን ድንገተኛ ግንኙነትና የተፈጠረውን ሁኔታ መስማት ሊያስቆጣትና ሊያበሳጫት የሚችል አልመሰለኝም ።

በእርግጥ እመቤትን ከወይንሸት በፊት ዐውቃት ነበር። ታዲያ ያኔ ያህ ሁኔታ ሲፈጠር እርሷ ራቅ ያለ ቦታ ለሥራ ተለይታኝ ስለነበር ልገናኛት አልቻልሁም ። ለረዥም ጊዜ በርቀት ስንለያይ ከሌሎች ጋር እንዳልገናኝ ተጽእኖ አርጋ ብኝ አታውቅምና የቁጣዋ ምክንያት አልገባህ አለኝ ። ሌሊቱን ጥሩ እንቅልፍ ሳይወስደኝ አደርኩ ።

ሰኞ ቢሮዬ ገብቼ የሰዓት ፊርማዬን ፈረምሁና ሌቱን እንቅልፍ ሲነሣኝ ላደረው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በመቸኮል ወደ ስልኩ ተጠጋሁ ። የእመቤትን ቁጥር ዘውሬ "ሀሎ!" አልኩ ።

"ማን ልበል?" "እመቤትን ነበር እባክዎን።"

"ነኝ"

"ሙሉጌታ ነኝ ። እንዴምን አ..."

"ይቅርታ! ሁለተኛ እንዳትደውልልኝ ። ስሜን ከእንግ ዲህ ብትረሳው ይሻላል ። እኔም ያንተን እረሳዋለሁና ። ስለ ወይንሸት ስለ እመቤትና ስለ ራስህ የምትተርክላት ሌላ ሴት ታገኝ ዘንድ ምኞቴ ጽኑ ነው ፤ ደህና ሁን" ብላ ስልኩን ጆሮዬ ላይ ጥርቅም አረገችው ።

ከተቀመጥኩበት ስፍራ ሳልንቀሳቀስ እንደ ሎጥ ሚስት የጨው ዓምድ ሆኜ ቀረሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ስንኩል ሰጣ

ደመናው ጠቁሮ ምሽቱን ድፍን ጨለማ ቢያለብሰውም ፥ ነጐድጓድ እያስገመገመ ብልጭ ድርግም ቢልም ሰማዩ የደነፋውን ያህል ውሃ አላወረደም። ካፊያው ግን ጠብ ጠብ እያለ አላቆም በማለቱ ያገኘውን ሁሉ ለማበስበስ ዐቅም አላነሰውም ። ባፍታ ተጠራቅሞ ጎርፍ መሆን ባለመቻሉ ቀስ እያለ የሚንጠባጠበው ዝናም የመረረውን አፈር አጨቅይቶታል ። መንደረተኛው የሚያደርገው ከመኪና ጎማ የተሠራው ጫማ መሬቱን መቆንጠጥ አልቻለም ። ተፈጥሮ ከሰው ጋር ጠለፋ የሚጫወት ይመስል ማንንም የጎማ ጫማ ያጠለቀ ፥ ምንም ተጠንቅቆ ቢራመድ ጭቃው አሽቀንጥሮ ይደፋዋል ።

"ይህች ልጅ ዝናብም አትፈራ ሊያበሰብሳት እኮ ነው" አሉ አቶ አለባቸው ። ከምድጃው አጠገብ ቦግ ብሎ የሚነደውን እሳት እየሞቁ ። አይወጡ ፥ ጭቃውን እንዴት ይድፈሩት ! አርፈው አይቀመጡ ፥ የደረሰች ልጃገረድ ልጃቸው አለወትሮ ብዙ አመሸች ። የሚሠሩት ጠፍቷቸው ከራሳቸው ጋር ሲሟገቱ ቆዩ ።

"ኢዲያልኝ ! እሱ ደግሞ ወይ ዘንቦ አይዘንብ ፥ እንዲሁ እየተነዛነዘ ሊያድር ነው እንግዲህ" አሉ ምሽታቸው ። እርሳቸውም እንደ ባለቤታቸው ግራ ተጋብተው ። "እንዲያውም ቀኑም ሲከብደኝ ነው የዋለ ። ቅድም እንኳ በቅጡ ሳይጨልም ፥ ደመናው ሰማዩን አጥቁሮት ዝናሙ ጠብ ጠብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማለት ሲጀምር፡ አማልክት ክፉ ነገር እንደ ደረሰ ሁሉ ባዘኔታ የሚያለቅሱ እየመሰለኝ ሰውነቱን ሁሉ ውርር ነው ያደረገኝ።"

ይህን ተመላልሰው ምንም ያህል ሳይቆዩ ቸፍ ቸፍ በሚለው ካፊያ መሐል ኡኡታ የተቀላቀለበት የመንደራቸው ደወል በተደጋጋሚ ሲደወል ተሰማቸው ።

"ምንድነው እሱ? በዚህ ሌሊት ፡ በዚህ በዝናብ ስብሰባ ውጡ ሊሉን ነው እንዴ ደወል የሚደውሉ ?"

"ኧረ አይመስለኝም ። ያ ዐረ — ሰብል አውሬ ሰው ተተናኩሎ እንዳይሆን ! ጩኸትም ይሰማል እኮ!"

"ሱሪየን— ሱሪየን ወዲህ በይልኝማ ፡ ይህች ልጅ ..." ብለው ሳይጨርሱ በጭቃው እየተንደፋደፉ ድም ጨቅ ፡ ጨቅ ድም የሚለው ኮቴ እበሩፋቸው ተጠግቶ መዝጊያቸው ድንገት ብርግድ ብሎ ተከፈተ ።

ከአባትና ከእናቷ ይበልጥ ኀዘን ያኮማተረው በለጠን ነበር ። እንደ ወትሮው እንግዶቹን ብድግ ቁጭ እያለ በማስተናገድ ፋንታ በፍራሽ ላይ ከተቀመጡት ዘመዶቿ ጥቂት ፈንጠር ብሎ አንገቱ ላይ ተኮራምቶ ሕቅ እንባውን ያነባል። በተሰማው መሪር ኀዘን በሁኔታው ያላዘነለት መንደርተኛ የለም ። ከሚቿ ጋር የነበረው የቅርብ ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ ሁሉም ያውቃል ። ኩታውን እስከ አፍጢሙ ተጣፍቶ እንባው ለይሉኝታ ጊዜና ቦታ ሳይሰጥ ኩልል ይላል። የሱው የባሰ ይሁን እንጂ በዚህ አሰቃቂ አደጋ ያላለቀሰ የለም።

በለጠን አጠገቡ ተቀምጠው ከሚያጽናኑት ጓደኞቹ ጥቂት እልፍ ብሎ የሁለት ሰዎች ሹክሹክታ ጆሮውን ተሰማው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ጥፋቱ የኛው ነው ። ያያረግነው ለመልካም አስበንም ቢሆን ምን ያስከትላል? ምን መጥፎ ነገር ሊያመጣ ይችላል? ብለን መመዘን ነበረብን ።”

“አሁን እንዲህ በሆነ ፡ እንዲያ በሆነ የሚለው ምን ያመጣል ። ባለፈው መፀፀት የሆነውን አይቀለብስምና እንተወው ። ይልቅስ ለወደፊቱ ትምህርት ይሁነን ።

ይህን በሰማ ጊዜ በይበልጥ ኀዘኑ ገላውን ሰርስሮ የገባ ይመስል ውስጥ አንጀቱን በረበረው ።“ተጠያቂው እኔው ብቻ ነኝ” አለ ለራሱ ። በኩታው ዐይኖቹን እያደራረቀ ። “የሰነዘርሁት ሐሳብ ይሁን ተብሎ ያን መጥፎ ዕቅድ ሥራ ላይ ባናውል ይኸ መቼ ይመጣ ነበር?”

በለጠ ኀሽሜ ፡ በዚያ መንደር ውስጥ በጨዋነቱ በእርቆ አሳቢነቱና በአስተዋይነቱ ከልጅ እስከ ሽማግሌ የሚያደንቀው ነው ። ክፋት ተንኮልና አጉል ምግባሮች ፈጽሞ አይታይበትም ። ንግግሩ ረጋ ያለና ምክንያታዊ ነው ። ሥራ ወዳድና ደከመኝን የማያውቅ ፡ የሰውን ችግር ፈጥኖ የሚረዳና የሚያዳምጥ ፡ ለኅብረተሰቡ ብልጽግናና ዕድገት ምንም ዐይነት መሥዋዕትነትን የሚከፍል ብልህና ትጉህ ኀረምሳ ነው ። ከዚህም የተነሣ ባለፈው የመኸር ስብሰባ ላይ የገበሬ ማኅበሩ በአዲስ መልክ ሲጠናከር በእርሻ ተቈጣጣሪነት የተመረጠው ያለ አንድ ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ ነበር ። ከዚያን ዕለት አንሥቶ በለጠ ለማኅበሩ ጥንካሬና ለምርት ዕድገት ሌትና ቀን ሳይል በመድከሙና የእርሱንም አርአያነት በመከተል አባላቶቹ ተግተው በመሥራታቸው የገበሬዎቹ ኑሮ ታይቶ ያልታወቀ ሆነ ።

ውሎ ሲያድር ሰብሉ እያሸተ መምጣት ሲጀምር የገበሬዎቹም ተስፋ እንዲሁ እየፋፋ ሲመጣ በመሐሉ ድንገት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳያስተውል ከግንዱ እየቆረጠ ቡቃያውን የሚያጠፋ አውሬ ሌሊት ሌሊት እርሻውን ያወረው ገባ ። መላው ገበሬም የድካሙን ውጤት የሚያመነምን ፡ የተስፋውን ውጋጋን የሚያደበዝዝ ፡ የአዲስ ሕይወት ፈለጉን የሚያጨልም እንግዳ ነገር ሲፈጠር በንዴት ጥርሱን ነክሶ ወገቡን አስሮ በአጭር ታጥቆ ተነሣ ። ለጉዳዩም ፋታ ሳይሰጠው ይህ ጨለማን ለብሶ ድካማቸውን መና ሊያስቀር የዘመተውን አጥፊ የአውሬ መንጋ ለመከላከል አጣዳፊ ስብሰባ ተጠራ ።

"ጎበዝ አድፍጠን እንጠብቅና ዛሬውኑ ሌሊት ያለንን መሣሪያ ይዘን ይህን ዐረ ሰብል አውሬ ድምጥማጡን እናጥ ፋው እንጂ ።"

"ሰው የሚተናኮል እንደሆንስ?"

"በመጀመሪያ ዝንጀሮ ይሁን ጦጣ ፡ ወይም ሌላ አውሬ ተለይቶ ይታወቅ ። ኋላ የበለጠ ችግር ላይ እንዳንወድቅ ።"

"ዛሬ በአዲስ መልክ ፡ በአዲስ ብርታት ፡ በአዲስ ጥንካሬ ተግተን ያፈራነውን ምርት ዐይናችን እያየ የአውሬ መንጋ አያጠፋውም ። ዝንጀሮ ሆነ ጦጣ ፡ አንበሳ ሆነ አንበጣ ሁላችንም በአጭር ታጥቀን እንውጣ ፡ በሕይወታችን ቆመን ሰብላችን ሲጠፋ ከምናይ የመጣው ይምጣ።"

ማልዶ ምልዓተ - ገበሬው እስብሰባው ቦታ እንደ ተገኘ ወትሮ የነበረው የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መልኩን ሳይዝ አንዱ ለአንዱ ወረፋ ሳይሰጥና ተራ ሳይጠብቅ ሁሉም በየራሱ ፍላት ያንሜሜ ነበር ። ይኸኔ ነበር እንደ ተቀሩት አባላቶች ሁሉ በሁኔታው ብስጭት ያለው የማኅበሩ እርሻ ተቈጣጣሪ በለጠ ፡ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ቆሞ እጁን በማጨብጨብ ጸጥ ካሰኘ በኋላ መፍትሔ ይሆናል ብሎ የገመተውን ሐሳብ ያቀረበው ። አባላቱ ከፍተኛ እምነት የጣሉበት የእርሻ ተቈጣጣሪ በለጠ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሰነዘረው ሐሳብና መላ ፡ አማራጭ እንደሌለው አርገው
በመውሰድ ያለአንዳች ተቃውሞ ተቀበሉት ። የማኅበሩ ሊቀ
መንበር ሐሳቡን ሙሉ ለሙሉ አጸደቁት ። ወዲያው ነገ ተነገ
ወዲያ ሳይባል አውሬውን ለማጥመድና ለማደን በወጣው
ዕቅድ መሠረት ሁሉም በእርሻው መሐል ሲሠራ ዋለ ።

የዚያን ዕለት ይመናሹ አለባቸው ለሴቶች ማኅበር የእጅ
ሥራ አገልግሎት የሚውል ቁሳቁስ ለመግዛት ገበያ ውላ
ስለነበረ በስብሰባው ላይ አልተገኘችም ። የተወሰነውን
ውሳኔና የተወሰደውንም እርምጃ አልሰማችም ። ገበያው
ከሠፈራ መንደራቸው ጥቂት ራቅ ይል ስለነበረ ጀንበር
እስክትጠልቅ ድረስ አልተመለሰችም ነበር ።

ይመናሹ አለባቸው በበጎ ምግባሯ ፡ በመልካም ሥራ
ዋና በአስተዋይነቷ እንደ በለጠ የተደነቀች ዐመለ ሸጋ ነች ።
በዕድሜዋ አነስተኛ ብትሆንም ቅሉ አስተሳሰቧ በጣም
የጠለቀ በመሆኑ መንደሬው እንደ ልጅ አያያትም ። ለዕው
ቀት አዕምሮዋ የተከፈተ ፡ የተነገራትን ወዲያው የምትይገ
ንቁ ነች ። ካቻምና አሁን በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር
ተደራጅተው ወደሚገኙበት የሠፈራ መንደር ሳይመጡ
በፊት አንድ ፍሬ ልጅ ነበረች ። ከዚያ በኋላ ግን ሰውነቷም
እየደነደነ አዕምሮዋም እየበሰለ በመምጣቱ በመንደሩ ተደና
ቂነት ካተረፉ ጨዋ ባለሞያ ሴቶች መሐል አንዷ ሆናለች ።
በአስተዳደጓ ፍጥነት ግን ያልተደነቀ አይገኝም ። በሴቶች
ማኅበር ውስጥም በእጅ ሥራ ኮሚቴ አባልነት ስትመረጥ
ልጅ ናት ያለ አልነበረም ። በመንደሩ እርሷን የማይመርቅ
ሽማግሌ ፡ እንትፍ የማይልባት አሮጊት ፡ የማይባርካት
አዛውንት ፡ የማይወዳት ሕፃን ፡ የማያደንቃት አባወራና
የማይመኛት ጎረምሳ አይገኝም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከነዚህ ሁሉ በላይ ግን በተለይ መንፈስና ለየት ባለ ሁኔታ አለመጠን የሚያፈቅራት የማኅበሩ እርሻ ተቈጣጣሪ በለጠ ነበር ። እርሷም ብትሆን ለበለጠ ያላትን ፍቅር የምትገልጽበት ቃል አግኝታ አታውቅም ነበር ።

ልብ ለልብ ከተገናኙ ሰንብተዋል ። ሥራ ውለው ፡ ትምህርት አምሽተው ፡ ሁሉም ከየጉሮኖው ሲከተት በለጠና ይመናሹ ከመንደሩ ፈንጠር ብሎ ከመጀመሪያው ሁዳድ መግቢያ ትይዩ ካለው ውድማ ላይ በስውር ተገናኝተው ዘወትር ይጫወታሉ ። ስለ ውሏቸው ፡ ስለ መንደራቸው ዕድገት ፡ ስለ ማኅበሩ ጥንካሬና ብልጽግና እናም ስለ ፍቅራቸው … የሱን ለሷ ፡ የሷን ለእርሱ በውይይታ ፍቅራቸ ውን በቅጡ ይለዋወጣሉ ፡ ገደቡን ሳይስቱ ።

የዚያን ዕለት ማታም ገበያ ውላ እንደ ተመለሰች እተለመደው ሥፍራ ተገናኝተው የወትሮ ጭውውታቸውን ቀጠሉ ።

ከሰላምታ ልውውጥና ገደቡን ከማይስተው መዳራት በኋላ በለጠ ስለ ዕለቱ ስብሰባና ስለ ተወሰነው ውሳኔ በቀኑ ስለ ተገባደደውም ሥራ ሲያጫውታት በመቻኮል ፡ “ እናም ይኸውልሽ ያን ዐረ - ሰብል አውሬ ለማስወገድ” ብሎ ሳይጨርስ አቋረጠችውና “እኔ የምጠይቅህን መልስልኝና እርሱን በኋላ በርጋታ ትነግረኛለህ” አለችው ።

“ምንድነው የምትጠይቂኝ?”

“መቼ እንደምንጋባ …”

“ቆይ እንጂ ይመናሹ ፡ ልጨርስልሽ …”

“ሠርጋችን መቼ እንደሚሆን ንገረኝና …” ፋታ አልሰጠችውም ።

ገበያ ወዲያ ወዲህ ስትል እግረ መንገዷን ገዝታው


t.me/OLDBOOKSPDF

የመጣችውን የብር ቀለበት ከሸጎጠችበት ጉያ እጇን ስዳ እየነካካች ፡ "መቼ እንደምንጋባ ንገረኝና ያመጣሁልህን ነገር አሳይሃለሁ።"

"እርሱን በኋላ እናርገው ይመናሹዩ ... ይኸውልሽ ታዲያ አውሬውን ለማደን ..."

"የጋብቻችንን ዕለት መናገር ያስፈራህ ለምንድነው እርሱን እንደርስበት የለ ? ወይስ አትወደኝም ማለት ነው?"

"እንደ እሱ ማለቴ አይደለም ። ደግሞ የምንጋባበትን ዕለት እኔም አንቺም ቀደም ብለን የወሰንነው መስሎኝ ። ተዚህ ምርት ስብሰባ በኋላ ተባብለን አልነበር?"

"ኡ…ገና እስተዚያ ድረስ ልንቆይ?" አለችው እንደ ማንጓጠጥ ብላ ። በጉያዋ ውስጥ የተሸጎጠ እጇን ግን ከነበረበት ቦታ አላወጣችውም ።

"ምንድን ነው እሱ? እስኪ ወዲህ በይው" አለና የእርሷን እጅ ተከትሎ የርሱም ወደ ጉያዋ ዘው አለ ።

"ዕረፍ እንጂ!"

"ለምንድነው የማርፈው?"

"እህ! እጅህን ከጡቴ አውጣው ። እ..." ማቅ እየተ ናነቃት ዐረፍተ ነገሩን አላስጨርስ አላት ።

ተጠግተው የተቀመጡበት ክምር ምንም እንኳ ከካፊያው ባያድናቸውም ለነርሱ ግን አልተሰማቸውም ። ነጎድጓድ እንደሌ አባርቆ ብርሃኑን ብልጭ ሲያደርገው ውብ ፊቷ እንደ መስተዋት ጠርቶ ከመቼውም የበለጠ አምሮ ላንጻፍታ ታየው። ስትሥቅ የሚጎረጉደው ጉንጯ ከዚህ ቀደም የማያውቀው ይመስል ብልጭ ካለው ነጎድጓድ ጋር ልቡን መታው ። እጁ ሳያስበው ያረፈበትን ጡቷን ጨበጥ አደረገው ። ነጐድጓዱ ለእነርሱ ፍቅርና ፈንጠዝያ የደስታ ከበሮ የሚደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልቅ መሰለው ።

"ኸረ እጅህን ሰውየ..."

"አላቅም ። ያመጣሽልኝ ዕቃና እጇ ያረፈበትም ጡት ሁለቱም የራሴ ናቸው ።"

"እንበ. ካልክ በቃ መሔዴ ነው ።"

"አታደርጊውም ።"

"እሺ ልቀቀኝ .... እኔ ራሴ ላሳይህ ..." እጇን እንደ ማላላት ሲል አፈትልካው እያስካካች ወደ እርሻው ሮጠች ። እርሱም በደስታ እየፈነደቀና እየሣቀ ተንደርድሮ ተከተላት ። በቡቃያው መሐል እየተሽለኮለከች አንዴ ወደ ግራ አንዴ ወደ ቀኝ እየታጠፈች እልያዝህ አለችው ። የነፋሱ ሽውታና የቅጠሉ መርገፍገፍ ለሚያሰሙት የደስታ ድምፅና የሣቅ ለዛ ጥሩ አጀብ ሆናቸው ። ግራ ቀኝ እየተሹለኮለከች እያስካካች በቡቃያው መኻል ሮጠች ።ግራ ቀኝ እየተሽሎከለከ እያስካካ ተከተላት ። በመሐሉ ነጓድጓድ አሁንም አንዳፍታ ብልጭ አለ ። ከብልጭታው ጋር የበለጠም ሰውነት በድንጋጤ ሽምቅቅ አለ ። ከርቀት የተከመረ ጥቁር አፈር ታየው ። የሩጫውን ፍጥነት ከበፊቱ እጥፍ አደረገው ።

"ይመናሹ ፡ ቂሚ! ይመናሹ ፡ ጉድጓድ ! ወጥመድ አለ ! ቁሚ! "ባለው ድምፅ ሁሉ ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ ድረስ ጮኸ ። በኃይል ሮጦ ደረሰባትና ተወንጭፎ ሊይዛት እጁን ዘረጋ ። የጨበጠው ግን ባዶ ሕዋ ነበር ። እጉድጓዱ ውስጥ ለአውሬው ማጥመጃ እተተከለው ሹል ጠርብ እንጨት ላይ ወደቀች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሰው ጫጪ ጨኙ

"እስቲ እንደማመጥ ወንድሞቼ ...." ባሻ ዳምጤ እጆቻቸውን እያጨበጨቡ የተሰበሰበውን ሕዝብ ጸጥ ለማሰኘት ሞከሩ። ሸንጎው ላይ የነበረው ሕዝብ ባንዴ ጸጥ ባይልም ቀስ እያለ ጫጫታው እየቀነሰ መጣ ። ከተሰበሰበው ሕዝብ ከፍ ብሎ ለመታየትና ይበልጥ ለመደመጥ ከትልቅ የወርካ ዛፍ ጥግ ከተሠራው የዕንጨት መቀመጫ ላይ ቆመው ንግግራቸውን ቀጠሉ — ባሻ ዳምጤ ።

ይህ የሆነው ራቅ ባለ አንድ የገጠር አካባቢ አብዮቱ እንደ ተቀሰቀሰ በነበሩት የመጀመሪያ ዓመታት ነው ።

"አብዛኞቻችሁ እንደምታውቁት ጭለማን ለብሶ ምሽትን ተገን አድርጎ እንደ አይጥ ከቀዳዳ ተሾልኮ እያደባ ወንጀል የሚፈጥምን ጥፋተኛ አጋልጦ ለማውጣት ከአውጫጭኝ የተሻለ መላ ከቶ የለንም ። እኛ ጥንትም በዘልማድ በአውጫጭኝ እንዲህ ግልጥ ብሎ የሚታየን ይቅርና ጭራሽ የተሰወረ ወንጀልን ገሃድ ስናወጣ ቆይተናል ። አምና በመስቀል የእንትትና ቤት ካለ ከሌለ ንብረቷ ጋር በእሳት ጋይቶ ሲወድም ከምድ ጃው በተነሣ ቃጠሎ ነው የጋየ ቢባል ፡ የለም ብለን በአውጫጭኝ ነው ያን ከይሲ ያጋለጥነ ። አርግጥ ለፎሊስ ጣሳወቁ ግድ ነው ። ውሎም አድሮም አይቀር ። አስከሬኑን ግን አይቀበር ማለቱ አልገባኝም ። ጦሩ ሆድቃውን ሸቅሽቆ ዘርግፎት እያየን በምን ሞተ ለማለት ነው


t.me/OLDBOOKSPDF

እሚመረመር? ይልቅ የወንድማችንን ሬሣ ተሸክመን ከምንን ከራተት ዛሬውኑ ይቀበርና ሳይውል ሳያድር አውጫጭኝ ይቀጥል" ብለው ንግግራቸውን አበቁ ።

ስጢም "ደግ ነው ...ይሁና...መልካም..." በሚል የስምምነት ቃላት እያጉረመረመ ረጭ አለ ።

የባሻዬን ቃል እንኳ የሚያዳምጥ በመንደሩ ጥቂት አይደለም ። ባሻዬ የሚል የቅጽል ስም የተሰጣቸው አቶ ዳምጤ ጎንጤ ምንም እንኳ በዕድሜ ከሚበልጧቸውም ከሚያንሷቸውም እንደሚጠሩበት የከበሬታ አንቱታ የሸመገሉ ባይሆንም ፤ ብዙ በረሃ አቋርጠው ፤ ከተማውንና ገጠሩንም አይተው እንደ ሰፈርተኛው አንድ ወጥ ሳይሆን የተዘበራረቀ ሕይወት የቀመሱና በመልካም ምግባራቸውም የሚወደዱ ስለነበሩ "አሜን" የሚላቸው ጥቂት አልነበረም። ንግግር ዐዋቂ በጣም ረጋ ያሉና የሚሠሩትንም ሥራ ሳይቸኩሉ የሚያከናውኑ ፤ የቤተክህነት ትምህርት የተማሩና ቅኔ በመጠኑ የተቀኙ ጨዋ ከሚባሉት የመንደራችን ሰዎች መሐል ትልቁን ሥፍራ የሚይዙ ናቸው ። ጊዜው መቼ እንደሆነ ባይታወቅም ለጥቂት ዓመታት በውትድርና እንዳገለገሉ ይናገራሉ ። ገና በ30 ዓመታቸው የፊት ለፊት ጸጉራቸው እየሸሸ በመሔዱና የተረፈውም ነጭ የቀላቀለ በመሆኑ ፤ ሽማግሌ ይምሰሉ እንጂ በጉልበትም ሆነ በአስተሳሰብ ጎልማሳ መሆናቸውን የማያውቅ የለም ። ዳምጤ ጐንጤ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ናቸው ። ሁለቱም ሕፃናት የተወለዱላቸው አሁን እቤት ካለችው ሚስታቸው ሳይሆን ከመጀመሪያዋ ሴት ነበር ። የመጀመሪያዋ ባለቤታቸው ሁለተኛውን ልጅ ስትገላገል በምጥ ምክንያት በመሞቷ ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ በፊት ሌላ አንዲት ወጣት ቆንጆ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስት አግብተዋል ። የእሁኗ ባለቤታቸው በዕድሜ ከእርሳ ቸው በጣም የምታንስ ጠጣትና ቆንጆ በመሆኗ የመንደሩ ጎረምሶች "የርሳቸው ባትሆን ኖሮ!" እያሉ የሚመኟት ነች ።

መንደሬው በባሻዬ ሐሳብ ተስማምቶ የዚያኑ ዕለት የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተከናወነ ። ሟቹን በጥሩና በመልካም ስም የሚያነሣው ባይኖርም በያረሰበት ድንገተኛ አሰቃቂ አደጋ ሁሉም ስለተነኩ በሚጠሉትም ፣ በሚወዱትም ፣ በሚንቁትም ፣ በሚያከብሩትም በሴቱም ፣ በወንዱም ተለቅሶ ለት ተቀበረ ። ከጥቂት የሩቅ ዘመዶች በቀር ትዳርም ሆነ አባት እናት ስላልነበረው ዕድርተኛው ከቤቱ በራፍ ድንኳን ጥሎ እንደ ቤተሰብ ሦስት ቀን ሙሉ አዘን አደረገ ።

በሦስተኛው ቀን ቤቱ ሲጠረግና ለቀስተኛው ሊበተን ሲል ቄስ አልታዬ ብድግ ብለው ፣ "በሉ ሁላችሁም ነፍስ ይማር በሉ ። የበደላችሁትም የበደላችሁም ይቅር ለግዜር በሉ። መቼም በዚህ ልክስክስ ጠባዩ ብዙዎቻችሁን አስቀ ይሞ ይሆናል ። ቢሆንም እንዲህ ዐይነት ከግዜር መንገድ የወጣ አደጋ ሊደርስበ ነ ልተገባ ነበር ። ከዚያች ልክስክስ ልማድ በቀር ሰውንና ሥራውን አክባሪ ወንድማችን ነበርና ባሻ ዳምጤ ከሚቴ የምትሉትን ያዙና ሕዋን ዐዋቂ ሳይባል ሁሉም አውጫጭኝ ወጥቶ ይህን አሠቃቂ ግድያ የፈጸመውን ወንጀለኛ አጋልጡት ። እግዜር ከእናንተ ጋር ይሁን" ብለው በያዙት መስቀል ግራና ቀኝ አማተቡ ።

በጸጥታ ሲያዳምጧቸው የቆዩት ሁሉ "አሜን!" አሉና አቀረቀሩ ።

ሟቹ ጣሰው በመንደርተኛው አጠራር "ሸማማው" የ29 ዓመት ጎረምሳና ወንደላጤ ነበር ። ጣሰው በሥራ ሰዓት እንደ ማንኛውም መንደሬ ብርቱና ጠንካራ ሥራ ወዳድ


t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር። ከሥራ ውጭ ቧልትና ቀልድ አጥብቆ ወዳድና በአሽሙር መሃለፍ የሚያውቅበት ነበር ። ይሁን እንጂ ቀልዱ በአብዛኛው በብልግና ስለነበረ ባለትዳሮችና ሽማግሌዎች አይወዱለትም ። በተለይ ግን በመንደሩ ባለትዳሮችንም ሆነ የደረሱ ልጃገረዶችን በማባለግ የታወቀ በመሆኑ በሴት ምክንያት ይሞታል የሚሉት አያሌ ነበሩ ። እንዲጠላም ያደረገው ጠባይ ይኸው ነበር ።

ባሰው ከመሞቱ ሁለት ምሽቶች ቀደም ብሎ እምና ቤት ተቃጥሎባት ከነበረችው ከሶዬ አዲስ አረቄ መሸጫ ቤት እየጠጣ ሲያመሽ ጎራ አለ ። ሶዬ ባልም ልጅም የሌላትና ከአረቄ ማውጣት በስተቀር መተዳደሪያ ስላልነበራት የአረቄ ንግድና መሸታ ሲከለከል እርሷን ግን ትተዋት ነበር ። ታዲያ በመንደሩ ካለእርሷ አረቄ የሚያወጣና የሚነግድ የለም ። ሠራተኛው አብዛኛው በምሽት እዚያች ቤት ውስጥ እየተገ ናኘ አረቄ ሲጠጣና ሲያውካካ ማምሸት የተለመደ እርጎት ነበር ። የዚያን ዕለት ምሽትም ከባሰው ሌላ በመንደሩ ዝናን ያተረፈ ጨዋና ዝምተኛ ፡ "ከተናደደ ግን የፈለገውን ከመፈጸም የሚመልሰው ምንም ነገር የለም" እየተባለ የሚወራለት የ24 ዓመቱ ወጣት እንዳዓለም ፡ ምንጊዜም ከዚያች አረቄ ቤት የማይጠፉት መምሬ አለታዬና የባሰው ተጎራባችና ጓደኛ ላጤው እስፋው እንዲሁም ሌሎች ነበሩ ። ሁሉም የየራሳቸውን ጨዋታ ሲያወጉ ቆይተው ድንገት በመሐሉ ቧልተኛው ባሰው ድምፁን ከፍ አድርጎ ፡ "እረ ማርያምን ምሽት ያደረገ ሰው በመንደራችን ተገኝቷል" አለ።

የማርያም ስም ሲነሣ መምሬ አለታዬ ቀና አሉና "እንዴት ማርያም? እም? ምን ማለትህ ነው?" አሉት ።

"የለ! ማርያም እኮ ብልግ ማርያም ራሷን ማለቴ

t.me/OLDBOOKSPDF

እያደለም ። ማርያምን የመሰለች እንጂ” አለ ባሰው እየሣቀ። ነገሩ የገባው አስፋውም አብሮት ሣቀ ።

በቅርቡ ውብ የሆነች ሚስት ያገባው እንዳዓለም አረቄውን በአንድ አፍ ጨልጠና ድምፁን አጥርቶ ፤ ለመሆኑ “የማርያም ባል ማነው?” ብሎ ጠየቀ ። በጠራራ ፀሐይም ሆነ በብርድ የማይለየው ካፖርት ኪስ ውስጥ የግራ እጁን እየዶለና በቀኝ እጁ በያዘው ዘንግ አፈር እየጫረ ።

“የማርያም ባልማ ዮሴፍ ነው ። ዮሴፍ አናጢው” አለ ባሰው አፉን የሸሙጥ አጣምሞ ።

የእንዳዓለም ፊት ድንገት ተለዋወጠ ። አሽሙሩ ለርሱ መሆኑ ገባው ። እንደ ተቀሩት የመንደሩ ነዋሪዎች ዋና መተዳደሪያው ግብርና ቢሆንም በትርፍ ጊዜው ወንበር ፤ ጠረጴዛ ፤ በርና መስኮት … የመሳሰሉትን የዕንጨት ሥራ ዎች ይሠራል ። በሠፈሩም አናጢ የሚያሻው ሥራ ሲፈጠር ቀድሞ የሚጠራው እርሱ ነው ። ታዲያ በባሰው አሽሙር “ዮሴፍ” የተባለው እርሱ ፤ “ማርያም” የተባለችው ደግሞ ሚስቱ መሆኗ ሲገባው ሰውነቱ በቁጣ ልውጥውጥ አለ ።

መምሬ አልታዩ ቧልቱ አላምር ብሏቸው “ሌላ ጨዋታ የለህም አንተ ሰው?” ብለው ሁኔታውን ሊያበርዱ ሞከሩ ።

ባሰው ግን ለጠቅ አረገና “አባቱ አይን መቼ ይጠማል? ወንድሜ እንዳዓለም እኮ ያገባት ምሽት እንኳን ያያትና ወሬዋንም የሰማ ይመረቃል ። እንዲህ አትምሰልዎት ፤ እኔ እንዲያው እግዜርን ባልፈራ …” ብሎ ሳይጨርስ እንዳዓለም ከመቀጽበት ብድግ አለ ።

የአረቄውን መለኪያ ባሰው ላይ ወርውሮ ቀኝ እጁ የጨበጠውን ዘንግ እየወዘወዘ ፤ “አንተ ሸማማ! ከዛሬ በኋላ ባለቤቴን ቀና ብለህ ማየት ይቅርና ስለ እርሷ እንኳ አወራህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲ.ሉ ብሰማ እንጀትህ ላይ ነው ጦሬን የምሸነትርልህ ። ሰማኝ! ከእንግዲህ ባለቤቱን በሚመለከት አንዲት ነገር ልሰማና ጦሬ የመጀመሪያ ደሚን ትቀባለች" እያለ መላ አካላቱ እየተንዘፈ ዘፈ ተቻኩሎ ወጣ ። የእንዱዓለምን ዛቻ በዋዛ የወሰደው የለም። የተናገረውን ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይል ሁሉም ያውቁ ስለነበረ ጣሰው የእንዱዓለም ሚስት ከዋለችበት ዝር እንዳይል አጥብቀው ይለምኑት ጀመር ። ይህ ወሬ ውሎ ሲያድር ከባሻ ዳምጤም ጆሮ ዘለቀ ።

ባሻ ዳምጤ ለሰው አያውሩት እንጂ ከሁለት ሳምንታት ቀደም ብሎ ያኘው ጣሰው ደፍሮአቸው የማያውቀውን ነውር ሠርቶባቸዋል ። መንደሬው ሁሉ ወጥቶ ሳለ ጣሰው ታሞ ስለነበረ በተባለው ቀን ከቤት ቀረ ። ያን ዕለት እንደ አጋጣሚ ባሻ ዳምጤ ዕቃ ረስተው ኖሮ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከጓሮ በኩል ጋቢ የለበሰ ሰው ሲወጣ አዩ። ግራ ተጋብተው እየተጣደፉ ከቤት ቢገቡ ሚስታቸው ጸጉሯ ተንጨፍሮ ፡ ሰውነቷ ተሞነጫጭሮ ፡ ፊቷ በጥፍር ተቧጦ አዩ ። ከፉም ደግም አልተናገሩ ። በሆዳቸው ቋጥረው የሚፈልጉትን ዕቃ ብቻ ይዘው ወደ ሥራቸው ተመለሱ ። ይህን ድርጊት ባሻ ዳምጤ በአእምሮአቸው ሲያብላሉ ይከረሙ እንጂ ለአንድም ሰው አልተነፈሱም ። ታዲያ እንዱዓለም እንዲያ ዛተበት የሚለውን ወሬ ሲሰሙ ሰውነታቸውን ነዘራቸው ። "አይምረውም!" አሉ ። ወሬውን ይዘውላቸው የመጡትን መምሬ አልታዩን ትኩ ብለው እያዩ ። "ካላረፈ ይበለው! ዋጋው ነው" አሉ ስለ ሚስታቸው ሲያስቡ እየዘገነናቸው ።

የመጀመሪያ አውጫጭኝ ስብሰባ ዕለት የደረሰች ነፍሰ ጡር ሴት ፡ እራስና ነፍስ ያላወቁ ሕፃናት ሲቀሩ ሁሉም

t.me/OLDBOOKSPDF

ልቅም ብለው ወጡ ። አውጫጭኙን በበላይነት እንዲመሩ ቀደም ብለው የተመረጡት አምስት ሽማግሌዎች ሰሞኑን ስለ ሰበሰቡት ማስረጃና ፍንጭ ሰጪ ዜናዎች ጥቂት ፈንጠር ብለው እርስ በርስ ከተወያዩ በኋላ ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ ተመለሱ ። ከአባላቱ አንዱ ባሻ ዳምጤ ከመካከላቸው ብቅ አሉና ከዋርካው ሥር ካለው የዕንጨት መቀመጫ ላይ ቆመው እጆቻቸውን በማጨብጨብ ጸጥታ እንዲሰፍን አድርገው ንግግራቸውን ቀጠሉ ።

"ወንድሞቼ ፡ እህቶቼ ፡ አባቶቼ ፡ እናቶቼ ፡ እንዲሁም ልጆቼ! ለአብዛኞቻችሁ እንግዳ እንዳልሆነ ሁሉ አውጫጭኝ በአንድ ማኅበረሰብ አጥፊን መንጥሮ የማውጫ ባሕላዊ ዘዴያችን ነው ። ጥንት አባቶቻችን እንደ ዛሬው የፖሊስና የፍርድ ቤቶች ሳይስፋፉ በፊት በአውጫጭኝ ወንጀለኛን በስውር ጥፋት የሚያደርስ አጥፊን ፡ ገሃድ በማውጣት ተገቢውን ፍርድ ይሰጡ ነበር ። ዛሬም እኛ ፈለጋቸውን ተከትለን በወንድማችን ላይ አሠቃቂ ግድያ የፈጠመውን ሰው አጋልጠን ለፍርድ ማቅረብ አለብን ። ማንነም ግቼ "በድሎኛል ፡ ጥለኛዬ ነው ፡ ባላጋራዎች ነን ፡ ዘልፎኛል" በሚል የምታውቀውን ይፋ ከማውጣት እንዳትቆጠብ ። እኛ የኮሚቴ አባላት ከመካከላችሁ ከአንዳንድ ሰዎች በግል በደረሰን ጥቆማና ማስረጃ መሠረት በጠሐፊያችን ተመዝግበው የሚገኙ ተጠርጣሪዎችና ለጥርጣሬው ድጋፍ የሚሆኑ ምክንያቶችም ከነጭብጥ ማስረጃዎች ይዘናል ። እናንተ ግን የእኛ ጥርጣሬና ማስረጃ ከመቅረቡ በፊት ጥቆማዎችና በአጋጣሚ ሆነ በክትትል ወደ ወንጀለኛው የሚያቀርበን ፍንጭ ያላችሁ ለጉባኤው አቅርቡ ። በተጨማሪ የማሳስበው ብዙ ጊዜ ሳንፈጅ የሥራ ቀናት ሳናጠፋ ጉዳያችንን ፈጥመን

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደየቤታችን እንድንገባ እያንዳንዳችሁ መልካም ጥረታች ሁን እንድታከሉበት ይሁን ።”

ባሻ ዳምጤ ንግግራቸውን ሲጨርሱ ጸጥ ብሎ የነበረው ሕዝብ ማንሾካሾኩን ቀጠለ ። ባሻዬ ንግግሩን ባይረኩበትም ወቅት ሆነ ካበቁም በኋላ ዐይናቸውን ከሕዝቡ ባሻገር ካለው ሕዋ ላይ ተክለው ጠልቀው ያስቡ ነበር ። ሚቹ ባለቤታቸውን መድፈሩን ከርሳቸውና ከሚስታቸው በቀር የሚያውቅ ማንም የለም ። እቤታቸው የሚያሳድጓት የእህታቸው ልጅም አልነበረችም ። የት ሔዳ እንደ ነበር ማን አስበውትም አያውቁ ። ዛሬ ማን አውጫጭኙ መሐል ከመሰል ልጆች ጓደኞቿ ጋር ፈዝዛ ቆማ ቢያይዋት ያን ዕለት የት ሔዳ እንደ ነበር ያስቡ ጀመር ። በሚቹ አማሚት መላ አካላታቸው ቢደነዝዝም አዘን እንኳ አልገባቸውም ። እርሳቸው “ይቅር ብዬ ትቼዋለሁ” ቢሉም ልባቸው ግን አብሮ ይቅር አላለውም ። ታዲያ በአማሟቱ እንጂ በሞቱ እንኳ አንዳችም አላዘኑም ...ከፍ እያለ የመጣው ጫጫታና ከተለያየ አቅጣጫ ስማቸውን የሚጠራ ድምፅ ሰምተው መለስ አሉ ። እጃቸውን አውጥተው ከሚጠሯቸው ሰዎች መሐል አያልነህን አይተው እንዲናገሩ ፈቀዱላቸው ።

“መቼም እንደ እኔ” ሲሉ ጀመሩ ጣታቸውን ወደላይ ቀስረው እየወዘወዙ። በዚህ ወንጀል የሚጠረጠር ከአንዱዓለም በቀር ማንም የለም ። እንዱዓለም ምሽቱን እንደ ብርቅ ነው የሚያየት ። ስንኳን ጣሰው እኛም ሽማግሌዎችና ማንም ጨዋ ቢያይበት አይወድም ። ከዚህ በቀር ግን ሚቹን ጣሰውን አረቄ ቤት ውስጥ “በጦር ዘክዝኬ እጥልሃለሁ” ብሎ ሲዝት ከዐሥር ሰው በላይ ነው የሰማው ። “ታዲያ ከዚህ የበለጠ ማን ተጠርጣሪ ይምጣ ?” ብለው ቁና ቁና እየተነፈሱ አቶ አያልነህ ንግግራቸውን አበቁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“እርግጥ ነው ፡ እርግጥ ነው ” የሚል የብዙ ሰዎች ድምፅ ከየአቅጣጫው ይሰማ ጀመር ። እንዱዓለም ማንንም ቀና ብሎ ሳያይ በእግሩ አውራ ጣት አፈሩን እየቆረቆረ እንዳቀረቀረ ቀረ ።

“ሐሳብ አለኝ!” በማለት ቂስ አልታዩ እንዲናገሩ እስኪፈቀድላቸው ሳይጠብቁ ንግግራቸውን በመቀጠል “ለመሆኑ የሞተበት ጦር የት እንዳለ አልታወቀም? በሠፈራችን ከበሬሁን በቀር ጦርና ቢላዋ የሚያበጅ አንጥረኛ የለም ። እስኪ እርሱ ጦርና ቢላዋ ለማን ለማን እንደበጀ ፡ እንደ ሸጠ ቢጠየቅ?”

“መልካም ሐሳብ ነው” አሉ ባሻ ዳምጤ ። ወደ በሬሁን መለስ አሉና ፡ “የቢላዋውን ተወው ። ሚቹ መቼም በቢላዋ አልሞተም ። ግን ጦር ለማን እንደ ሠራህና ማን ማን እንደ ገዛህ ብትናገር ።”

“ዐሥራ ሦስት ጦሮች ሠርቻለሁ ። በዚህ ዓመት ብቻ! ከነዚያ መሐል የሸጥኋቸው አምስቱን ነው ። ያደስኩላቸው ግን ብዙዎች ናቸው ። ጦር ከገዙኝ መሐል አንዱ ይኸው ተጠርጣሪ እንዱዓለም ነው ። እንዲያውም እንዱዓለም ጦሩን የገዛኝ ዛቻውን በሰነዘረበት ማግሥት ከግድያው ወንጀል አንድ ምሽት ቀደም ብሎ ነው” አለ በሬሁን በንግግሮቹ መሐል እየደጋገመ ከንፈሩን እየመጠጠ ።

“ለምን የእምነት ክህደት ቃሉን አይጠየቅም? እህም! እርሱ የተፈራ ለምን ነው! ሰውነቱን ከተናገረ ይኸ ሁሉ ውጣ ውረድ አያጥርም ኖሯል?” አሉ አቶ አያልነህ እጃቸውን አውጥተው ሳያስፈቅዱ ።

“ይቆዩ እንጂ አቶ አያልነህ ፡ ሥነ ሥርዓት ይኑረን ፡ እንዲናገሩ እኮ አልፈቀድሁሎትም” አሉና ባሻ ዳምጤ

t.me/OLDBOOKSPDF

በትድሚያ እጁን አውጥቶ ወደ ነበረው ወደ ሚቹ ማስጡ ኀደኛ ወደ እስፋው ጠቋሚ ጣታቸውን ቀስረው "ደግ እስቲ እንተ" አሉ ።

እስፋው በሚጣደፍና በሚንተባተብ ንግግሩ "እስቲ እቶ ማን ያህልሃል ጦር ገዝቶ እንደ ነበር አቶ በሪሁን ይጠየቅ" አለ ።

"ምክንያትህ?" አሉ ባሻዬ ።

"ምክንያቴማ ማን ያህልሃል ከሁለት ዓመት ጀምሮ የጣስው ባላጋራና ጠላት መሆኑን ዐውቃለሁ ። ከዚህም በቀር ባለፈው ዓመት በፍርድ ሸንጎ ከስሶ አንድ ወር አሳስሮታል ። ይህም አልበቃ ብሎት ፡ 'ከመንደሩ ካልወጣልኝ እኔ ከዚህ አልቀመጥም' ብሎ በብዙ ሽማግሌዎች ልመና ነው ነገሩ የበረደ ። ምሽቱንም በሰበብ አስባቡ ውጭ በወጣች ቁጥር 'ከጣስው ጋር ተገናኝተሽ ነው የምትመጪው' እያለ እየቀጠቀጠ ቢያስቸግራት የኅብረት ሱቅ እንኳ ሳይቀር ለዕቃ የምትልከው የእህቷን ልጅ ነው ።"

ባሻ ዳምጠ ሊናገሩ አፋቸውን እንደ ከፈቱ ከተመረጡት አምስት አባላት መሐል አንዱና የአውጫጭኝ ዋና ጸሐፊ የሆነው ማን ያህልሃል ነጠቅ አድርጎ ፡ "ምሽቴን የማስተዳድር እኔው ስለሆንኩ በትዳሬ የሚያገባው የለም ። ጦር ብገዛ ደግሞ ለሕይወቴ መጠበቂያ ነው ። ጦር የገዛ ሁሉ ይጠርጠር አልተባለም ። እንዲያውም በሪሁን ሳይጠየቅ እኔው ራሴ ልመልስልህና ባለፈው ወር አንድ ማለፊያ ጦር ገዝቻለሁ ። እንዲያውም ያማረ ዘንግ አበጅቼለት ከቤቴ ይገኛል" አለ ካለፍራቻ ።

"ልክ ነው!" አለ በሪሁን ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

"በሉ በጄ ። ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም ። እንዴ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠጥታ አርገን ተመካከሩ ። እኛ ሽማግሌዎች ቀደም ብሎ
የቀረበልንን ጥቆማ ከማሰማታችን በፊት በቆይታ የምንነጋገ
ረው አለን ። በመጀመሪያ ግን በለጠች ፡ ዳውድና በረደድ
እንያ፥ ወዲያ ጥላው ሥር ብቅ በሉ” አሉ ባሻ ዳምጤ ።

ምልዓተ ስብሰባው በተጠሩት ሰዎች ምክንያት ግራ
ተጋብቶ እርስ በርስ ተያየ ። ተጠሪዎቹ ግን ባለመደናገጥ
ፈገግ ብለው እየተጣደፉ ወደ ተጠሩበት ሔዱ ። አምስቱ
አባላትና የተጠሩት ሦስት ሰዎች ለሩብ ሰዓት ያህል ስለዘ
ገዩ ስብሰባው በፌሽኽት ታወከ ። ከዐሥራ አምስት ደቂቃ
ዎች በኋላ በለጠች ፡ ዳውድና በረደድ ተመልሰው ከስብሰባው
ተቀላቀሉ ። የዐሥራ አራትና የዐሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ
ያላቸው በለጠችና በረደድ ከተጠሩበት ጉዳይ ይልቅ በስብሰ
ባው የተዋከበ ጥያቄ አደናገራቸው ። በዕድሜ ጠና ያለው
በረደድ ግን እንዳችም ሳይሸበር ኩስተር ብሎ ቆመ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሽማግሌዎቹ ተመልሰው
ስፍራቸውን እስኪይዙ መላው ተሰብሳቢ ምን ይዘውልን
መጥተው ይሆን በማለት ጓጉቶ እንደወትሮው ሳያጨበጭብ
ጸጥ አለ ። ባሻ ዳምጤ እከፍታው ላይ ወጡና የያዙትን ቋጠሮ
በጥንቃቄ መፍታት ጀመሩ ። በመጀመሪያ አንድ የካፖርት
ዘለበት አውጥተው ለሕዝቡ እያዟዟሩ አሳዩ ። አንድ አፍታ
ሜሜታ ነገሠ ። ዘለበቱ በበጋም ሆነ በክረምት በቀትርም ሆነ
በምሽት ከላዩ የማይለየው የእንዱዓለም ካፖርት መቀነቻ
መሆኑን ሕፃን ሽማግሌው ያውቃል ። ባሻ ዳምጤ ጸጥታ
ካሰፈኑ በ ላ “ይህ ዘለበት የማን እንደሆነ ታውቃላችሁ?”
አሉ ።

ምልዓተ ስብሰባው በአንድ ድምፅ ፡ “አዎን የእንዱዓ
ለም ነው” አሉ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ባሻ ዳምጤም ለጠቅ አድርገው ፡ "ይህ ዘለበት የሟቹ አስከሬን ከወደቀበት ሥላሳ እርምጃ ያህል ራቅ ብሎ ያገኘው በረደድ ነው" አሉ ።

በረደድ ከመሐል ብቅ ብሎ ፡ "አስከሬኑ የተገኘ ዕለት ወደ ረፋዱ ብቻዬን ወንዝ ብቅ ብዬ ስመለስ ነው ያገኘሁት ። ሬሳው ወድቆ ከተገኘበት ሥፍራ ቢበዛ የእኔና የባሻ ዳምጤን ያህል እርቀት ቢኖረው ነው" አለ ።

"ያ ማለት ወደ ሥላሳ እርምጃ ማለት ነው" አሉ ባሻ ዳምጤ ።

ይህን ጊዜ ብቻ እንዱዓለም ቀና ብሎ፡ "ዘለበቱ የጠፋኝ ማሰው ከመሞቱ ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ከባሻዬ ጋር ስንጠጣ ያመሸንበት ዕለት ነው" በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ተናገረ ።

አቶ አያልነህ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በቁጣ "ይህን ሰው ዝም አሰኙት እንጂ ባሻ ዳምጤ! የጥበቃ ጓዶች ተመድበው ቢጠብቁትስ?" አሉ ።

ባሻ ዳምጤም "ደግ ነው ። ሁለት የጥበቃ ጓዶች ጥቂት ፈንጠር ብላችሁ ጠብቁት ። አንድም እንዳይናገር" አሉ ። ለጥቀውም ሁለተኛውን ቋጠሮ በቃጫ የተጠቀለለ ጦር ብቅ አደረጉ ። ጦሩ ሁለመናው በደም ከመነከሩ በቀር በዘንግ መግቢያው በኩል ሲታይ አዲስነቱ ያስታውቃል ።

"በስመአብወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ..."እግዝእትነ"..."አላህመነጅና...ላኢላህ ኢላላ" የሚል የድንጋጤ ድምፅ ከየአቅጣጫው ይሰማ ጀመር ።

"እንዴ ጸጥታ" አሉ ባሻ ዳምጤ "በሪሁን እስኪ ጠጋ በልና ይህን ጦር አስተውለው ። አዲስ አይደለምን? ደግሞስ ይህን ጦር ለማን እንደ ሸጥህ ታውቃለህ?" አሉ ።

በሪሁን በፍጥነት ወጥቶ ጦሩን ከተቀበለ በኋላ ዐይኑን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ፡ ፈጠጥ እንደ፡ ጠበብ ፡ ግንባሩን እንደ፡ ቋጠር ፡ እንደ፡ ፈታ እያደረገ አገለባብጦ እየና ቀና ብሎ "ጦሩ አዲስ ነው ። እንዲያውም ወይ መጨረሻው ግድም ካበጇኋቸው መሐል አንዱ ነው ። ግን ለአንዱዓለም የሸጥሁለት በትክክል ይህ መሆኑን ለማረጋገጥ ያዳግተኛል" አለ ።

"በጄ ይኸስ?" አሉ አንድ ታቹ ደም የነካው ዘንግ ከፍ አድርገው እያሳዩ ባሻ ዳምጤ ።

"እህም" አለ አስፋው እጁን እያወጣ ፡ "ይሄማ አንዱዓለም ጦር ሳይገዛ በፊት ለጦር የሚስማማ በትር ነው እያለ ሞራ እየቀባና አፈር ውስጥ እየቀበረ ሲያሽሞነሙነው የቆየው ዘንግ አይደለም እንዴ? እንዲያውም አረቄ ቤት ውስጥ የዛኑ ዕለት ይዞት ነበር እኮ!" አለ በመገረም ።

ባለ አረቄ ቤቷ ሰዮ "አዎን ልክ ነው" አለች ፡ ዝቅ ባለ ድምፅ ።

"እረ እኛም እናውቃለን" አለ ሌላ ወፍራም ድምፅ ።

"ዘንጉም የጠፋኝ ከዘለበቱ ጋር ..." ብሎ አንዱዓለም ንግግሩን ሳይጨርስ የጥበቃ ጓዶች እየጮሁ ዝም አሰኙት ።

ባሻዬ ፊታቸውን ከአንዱዓለም መለስ አድርገው "ጦሩን ከነዘንጉ ያገኙት ሁለቱ ሕፃናት ዳውድና በለጠች ናቸው ። ልጆች የት ናችሁ? እስኪ ወዲህ ብቅ በሉማ! ይህን ዘንግና ጦር ከየትና እንዴት ነው ያገኛችሁት?"

"ከወንዝ ነው" አለች በለጠች ።

"ወንዝ ውሃ ልንቀዳ ወርደን ነው" አለ ዳውድም ተደርቦ ።

"ለስንኬሎው መያዢያ ዕንጨት ስንፈልግ..." ብላ በለጠች ሳትጨርስ ዳውድ ጣልቃ ገባ ።

"ባሊውን ለሁለት የምንይዝበት ዱላ ስንፈልግ ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

ያገኘነው ። ሰንበሌጡ መሐል'' አለ በሚያንቃጭል ድምፅ ።

"ጦሩስ?" አሉ አቶ አያልነህ ።

"እውሃ ውስጥ በቃሚ ተጠቅሎ የቃሚው ሚዳ ሰንበሌጡ ያዘት ስለበው ..." ብሎ ደውድ ሳይጨርስ አቋረጣ ።

"ጦሩን ጎትቶ አወጣው" በማለት በለጡች ደመደመች ለት ።

"በቃችሁ ልጆች ። እግዜር ይባርካችሁ" አሉ ባሻ ዳምጤ ። ወደ ሕዝቡ መለስ ብለው ፡ "እንግዲህ እውነቱ እፍጦ የወጣ መሰለኝ ። ማስረጃውም እነሆ ። ፍርዱን ለፈራጆች እተዋለሁ" አሉ ከቆሙበት የዕንጨት መቀመጫ እየወረዱ ።

"ባሻዬ ይቆዩ እንጂ! የርሱን ቃል ሳንሰማ?" አሉ አቶ አያልነህ ።

"እዚሁ ሆኜ አዳምጣለሁ ፡ ይከመኝ እኮ!" አሉ ቆመውበት የነበረው መቀመጫ ላይ በረፍ እያሉ ።

"ቃልህን ስጥ ። የእምነት ክህደት ቃልህን አሰማ!"

"የምን ክህደት? የእምነት ቃሉን እንጂ! ከዚህ ሁሉ ማስረጃ በኋላ ክህደት አለ?"

"ይልቅ እንዴት እንደ ገደለው ያስረዳ!" የሚሉ የብዙ ሰዎች የተለያየ ድምፅ ከየአቅጣጫው ተሰንዘረ ።

አቶ አያልነህ ባሻዬ ቆመውበት በነበረው ቦታ ላይ ተተክተው "በል ተናገር አንተ" አሉ ወደ አንዱዓለም ዘወር ብለው ።

"በበኩሌ የምናገረው የለኝም ብዬ ነበር ። ማን መናገር ካለብኝ አድምጡኝ ። ወንድሞቼና እህቶቼ! በአንድ ቃል ይህን ሰው እኔ አልገደልሁትም ። ማን ባይሞት ኖሮ እርሱም አያርፍ፡ እኔም ከመግደል ወደ ኋላ አልልም ነበር ። ስለዚህም ማንም ገደለው ማን መሞቱን እፈልገው ነበርና በገዳይነት



t.me/OLDBOOKSPDF

ብወንጀል ቅር አልሰኝም ። እንዲህ ዐይነቱ ከንቱ ሰው ለመሞቱ እኔ ምክንያቱ ከሆንኩና አብሬው ብገደል የብዙዎ ችን ጠላት እንዲጠፋ ምክንያት ነኝና በጸጋ እቀበለዋለሁ ። ለሚበየንብኝ ፍርድ ዝግጁ ነኝ ። በተረፈ ወንድሞቼ ፡ እህቶቼ፡ አባቶቼና እናቶቼ የዚህ ሰው ነፍስ በእውነት አላችኋለሁ በእጄ አልጠፋም ።"

ምልዓተ ስብሰባው በአድናቆትና በመገረም ያጉረመ ርም ጀመረ ። አብዛኛው በንግግሩ ተነካ ። አዘነለትም ።

ጫጫታው ደርቶ ሰዉ እርስ በርሱ መደማመጥ እስኪያ ዳግተው ድረስ ጸጥታው ሲደፈርስ ከመሐል አንድ ያልታወቀ ድምፅ በጣም እየጮኸ ፡ "ደግ! በጥፋተኝነት ፡ ማለቱ በነፍስ ገዳይነት ወንጀል መከሰሱን ተቀብሎታል ። ግን አንዳንድ ጥያቄዎችን በፈቃደኝነት ቢመልስልን?" አለ ።

"የምን ጥያቄ?" አሉ አቶ አያልነህ ። ጫጫታው ቀስ እያለ ከሰመ ።

"አልገደልሁም ካልክ ጦርህን አምጥተህ ማሳየት ትች ላለህ?" አለ ያልታወቀው ድምፅ ።

"እንደ ብዙ ማስረጃዎቹ ሁሉ ከሥፍራው ተሰርቆ ካልተወሰደ አዎን ። ከራስጊዬ ግርግዳ ላይ ነበር የሻጥሁት ።"

"ደግ ቁልፍህን ለጥበቃ ጓዱ ስጠውና ካለ ይዞ ይምጣ" አለ አዲሱ ድምፅ ።

ቁልፉን ከመቀነቱ ፈትቶ ለጥበቃ ጓዱ ሰጠው ። ጓዱ እተላከበት ደርሶ እስኪመጣ በጫጫታው መሐል መምሬ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ፡ "ያለብዙ ጊዜ ባላጋራው የነበረ የተባለው ማን ያህልሃልስ የራሱን ጦር ይዞ እንዲመጣ ቢደረግ?" አሉ ።

ማንያህልሃል ቀና ብሎ "መምሬ አልታዩ ፡ ምነው



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዴህ እንደ ልጅ ያስባሉ? ጦሬን ቢያት እንኳ ከቤቴ ስወጣ አይቹዋለሁ ። ከመሰላችሁ ግን ይግ ፤ ባለቤቴ ሔዳ ታምጣው” አለ ።

“ያንተን ተወው! መምሬ እንጂ እኛ አላልንም” አሉ አቶ አያልነህ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መልዕክተኛው አንድ አዲስ ጦር ይዞ ከተፍ አለ ። የተሰበሰበው ሕዝብ ጦሩን ሲያይ በአድናቆት እያጉተመተመ ይህን ጥያቄ ያነሣውን ሰው ለማየት አዲሱ ድምፅ ወደ ተሰማበት አቅጣጫ ይንጠራራ ጀመር ።

አቶ አያልነህ እጃቸውን አጨብጭበው ፤ “ናማ ወዲህ ፤ ማን ነህ አንተ? ከየት የመጣህ ነህ?” ብለው ጠየቁ ።

“እኔ የወዲያኛው መንደር ሰው ነኝ ። ለገበያ እመሐል ከተማ ስሔድ እግረ መንገዴን ስብሰባ ባይ ምን ይሆን ብዬ ተጠጋሁ ። ጉዳዩ አጓጊ ሆኖብኝ ይኸው ቆሜ ቀረሁ” አለ እንግዳው ፤ ኩታውን ከአንገቱ ወደ አናቱ ከፍ እያደረገ ። አቶ አያልነህ በብዙ ማስረጃ የተረጋገጠውን ወንጀል እንዳልነበር የሚያደፈርስ ሰው በመምጣቱ ቅሬታቸው ከፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር ።

“እና የጦሩ ከቤቱ መገኘት ምን ለውጥ ያመጣል? በሌላ አዲስ ጦር ተጠቅሞስ እንደሆነ?” አሉ ።

እንግዳው ቀበል አርጎ ፤ “ለውጥ ያመጣል ማለትስ አይደለም እንዲያው ግር የተሰኘሁበት ነገር ቢገባኝ ብዬ ነው” አለ ።

አብዛኛው ሰው “ይጠይቅ ፤ ይህና ይዟል ። እስኪ የሚያመጣውን ለውጥ እንይ” አለ ።

“ጦሩን የሠራው ማን ነበር ስሙ ጠፋኝ ።”


t.me/OLDBOOKSPDF

"በሪሁን ነው ።" ሁሉም ጸጥ ብለው ማድመጥ ቀጠሉ።

"አቶ በሪሁን ፡ የጠፋህ ወይም የጎደለህ ጦር የለም?"

"ኧረ የለም ፡ ቅድም እንኳ ቆጥሬዋለሁ ።"

"የለም እንገደገና ቁጠረው ። እስኪ ቆይማ ፡ የተለወጠስ?"

"የተለወጠ? አዎን እሱን እንጃ ።"

"እስኪ እየውማ ።"

"በሪሁን ወደ ጎጆው ሔዶ ጦሮቹን ሲያገላብጥ ከቆየ በኋላ ትንፋሹ እጥር እጥር እያለ ላብ ግንባሩ ላይ ተንቸርፍፎ በት በእጁ ጦር ይዞ ሲሮጥ መጣና ፡

"አዎን የተቀየረ አለ ። ይኼ ...ይኼ አዲስ አይደለም ፡ ከዓመት በፊት የሠራሁት ነው" አለ ንግግሩ እየተንቀጠቀጠ።

"የማን እንደሆነ ታውቃለህ?" አለ እንግዳው ።

"አዎን የማን እንደሆነ ...እ..እ...እ..." ብሎ ሳይጨርስ አቶ አያልነህ ድንገት አቋረጡት ።

"ወንድሜን ባሻዬን አመመው ። እናንተ ዳምጤ ታሟል ። ወደቀ እኮ!" ብለው ጮሁ ። ይኸኔ የሁሉም ትኩረት ወደ ወርካው ሥር ተቀየረ ።

"ጠሐይ ብዙ መቷቸው ይሆናል ።"

"የለ ብዙ ስለ ተናገሩና ስለ ቆሙ ነው።"

"ከዚህ በፊት የሚጥል በሽታ አለባቸው እንዴ?"

"ለምን እቤት አይወስዱም?"

"ሐኪሙ የት ነው?" ሕዝቡ እርስ በርስ ሲንጫጫ አቶ አያልነህ ከፍ ብለው ቆመው እጃቸውን በማጨብጨብ ፡ "በሉ እንግዲህ ጎበዝ ባሻ ዳምጤ ከታመሙ ነገሩን ማከተም አንችልም ። ሁላችንም ደክሞናል። ነገሩ በይደር ይቆይና...."



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይጨርሱ እንግዳው አቋርጦ ፡ "መልካም ነው ጌታዬ! ግና እኔም የንገሩን መጨረሻ እንዳይ ቢፈቀድልኝና እዚሁ ባድር ። መቼም ከአሁን በኋላ ገበያም አልደርስ ። እግረ መንገዴንም አንዳንድ ሰዎችን ስለ ጉዳዩ እንዳነጋግር ፈቃድ ቢሰጠኝ ጀምሬ የነበረውን...."

እርሱንም አቶ አያልነህ አቋርጠው ፡ "መልካም ተፈቅዶልሃል ። ሑተታ አታብዛ ። ሁላችሁም ማለዳ እዚሁ እንድትገናኙ ይሁን ። ለእንግዳውም ማደሪያ ስጡት ። ጥያቄም ካላው ያሻውን ይጠይቅ" አሉ ።

በበነጋው ሰዉ ከትላንቱ አንድም ሳይቀንስ ግልብጥ ብሎ ወጣ ። ባሻ ዳምጤም ደህና አለመሆናቸው ከፊታቸው ሁኔታ ቢያስታውቅም ፡ በሁለት ጎረምሶች መሐል ተደግፈው ከወርካው ጥግ ቆሙ ። ትላንት እርሳቸው ቆመው ስብሰባውን ይመሩበት በነበረው ሥፍራ እንግዳው ሰው ወጣና እጆቹን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ጸጥታ በመጠየቅ ንግግር ማድረግ ጀመረ።

"ክቡራትና ክቡራን! ከሁሉ አስቀድሚ ማታ ስላደረጋችሁልኝ መስተንግዶ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ ። ይህ አውጫጭኛችሁ ፍሬያማ ሆኗል ። ወንጀለኛው በበቂ ማስረጃ ተጋልጧል ። ግን የሠራችሁት ስሕተት አለ ። አስከሬኑን ሳታስመረምሩ መቅበራችሁ ትክክል አይደለም ። ምክንያቱም የሐኪም ማስረጃ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው ። ለምሳሌ ጦርና ዘንጉ ላይ የተገኘው ደም በትክክል የሟቹ መሆኑ መረጋገጥ ይገባው ነበር ። በማስረጃነት የተገኙትም ንብረቶች በእጅ መጨባበጥ አልነበረባቸውም ። ወንጀሉ ሲፈጸም የሠፈረው የገዳዩ አሻራ ከብዙ ሰዎች አሻራ ጋር ስለሚደባለቅ ወንጀለኛውን ለመለየት ለጊዜውም ቢሆን ችግር ይፈጥራል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በተረፈ ግን ጎዳዩ ላተጠቀመበት ጦር ከነዘንጉ ሚቹ ያለፈበት መሣሪያ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። ከሁሉም በይበልጥ ግን ሚቹ የለበሰው ልብስ ላይና የጦር መሣሪያው ላይ የተገኙት ደሞች ከተመረመሩ በኋላ ይረጋገጣል ። የዚህ ወንጀል ተጠያቂ እጅግ ብልህ ማስረጃ ማጥፋትና በተጠርጣሪ ላይ የሐሰት ማረጋገጫ በመደራረብ ረቂቅ ዘዴ መጠቀም የሚችል ሰው ነው ። የጣሰውን ዛቻ መነሻ በማድረግ ዘወትር ከላዩ ላይ የማይለየውን የካፖርቱን ዘለበትና በትር በመጠጥ እስክር በመውሰድ እስከሬኑ ከተገኘበት አካባቢ በማኖር ዘንጉንም ለጦሩ መጠቀሚያ በማድረግ ተጠርጣሪውን ሙሉ ለሙሉ ወንጀለኛ መስሎ ለማቅረብ ችሏል ። ግን ይህ ዘንግና የካፖርቱ ዘለበት ከግድያው ወንጀል ጥቂት ቀደም ብሎ ከአንድ ሰው ጋር አለወትሮው ነፍሱን እስኪስት ሲጠጣ አምሽቶ በጋባዡ ደጋፊነት ከመጠጥ ቤቱ ሲወጣ ዘንጉና የካፖርቱ ዘለበት እንደ ነበር መቆየቱን ሰዪ ማታ አረጋግጣ ለች ። የዚያኑ ምሽት እቤቱ ሲገባ ዘንጉና ዘለበቱ አለመኖሩን ግን ሙሽራዋ ሚስቱ አረጋግጣልኛለች ። ታዲያ ጎዳዩ እኒህን ዘለበትና ፡ ጦርና ዘንግ ሰዎች በሚመላለሱበትና በቀላሉ ሊታዩ በሚችሉበት ሥፍራ እንዲገኙ ያደረገው ሆን ብሎ ነው ። ባይሆን ኖሮ ግን ለወንጀሉ የተጠቀመበትን ጦር ከወንዙ ውስጥ አርቆ በመወርወር መሰወር ይችል ነበር ። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ይህ ጎዳይ ከሚቹ ጋር ያለውን ቅራኔ እንኳንስ የሚያውቀውና የሚጠረጥረውም የለ ። በእንዲህ ዐይነት ያለዛቻ ቅሬታውን ይፋ ሳያወጣና በደም ፍላት ሚች ያደረሰበትን በደል ሳይናገር አምቆ የያዘ ደመ ቀዝቃዛ በቀልተኛ ነው ። ይሁን እንጂ ይህ አውጫጭኝ የሁሉንም መንደር የአስተሳሰብና ግምት ፡ ጥርጣሬና እምነት ሳይበታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቱን በአንድ ላይ ይዞ መቅረብ በመቻሉ ፡ ደህና አድርጎ የሚያውጠነጥን ከተገኘ ውስብስቡን ፍንጭ ወደ ትክክለኛው ፡ ወደ ተፈላጊው ምስፍራ መምራት የሚቻል ነው ። እዚህ ላይ ለመጥቀስ የምወደው ገዳይ የሠራቸውን ከፍተኛ ስሕተቶች ነው ። አንደኛው የተጠቀመበትን ጦር የተጠርጣሪው ለማስመሰል የተጠርጣሪውን ጦር ከሥፍራው መሰወር አለመቻሉ ሲሆን ፡ ሁለተኛው የበረሁን የጦሮች ቁጥር እንዳይቀንስ ሲል የተካውን የራሱን አሮጌ ጦር አዲስ ለማስመሰል ሲሞርድ ሞያውን ባለማወቁ ፡ ሙርዱ ከማስታወቁ በላይ የዘንጉን መግቢያ ቀዳዳ እንዳለ መተዉ ነው ። እነዚህ ስሕተቶች ባይሠሩ ኖሮ ምናልባት ዘሬ የተደረሰበት ወንጀል ከሁለትና ከሦስት ሳምንት ከዚያም በላይ ብዙ ጊዜ በፈጀ ነበር ። ትላንት በዚህ አውጫጭኝ ላይ ባልገኝና ስብሰባውን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በጥንቃቄ ባልከታተል ኖሮ የዚህን የረቀቀ ወንጀል ባለቤት ማጋለጥ ባዳገተ ነበር ። ምሽት ላይ በባሻ ሕመም ስብሰባው ሲበተን ጥቂት ጊዜ በማግኘቴና የዚህ መንደር ሕዝብና ሽማግሌዎችም ሙሉ ትብብር ስላደረጉልኝ ጥርጣሬዬን በማስረጃ መደገፍ ቻልኩ። በረሁን በግል በአዲሱ የተቀየረው አሮጌ ጦር የማን እንደሆነ ከገለጠልኝ በኋላ ነው ለግድያው ምክንያት የሆነውን ፡ ለቂም በቀል አነሣሽ የሆነውን ቁርሾ ማግኘት የቻልኩ ። ያቺ ከመጤፍ ያልተቈጠረችዋ ሕፃን ሚቾ ተሞነጫጭሮ ከእመቤቷ ቤት ጓዳ ሲወጣና ጌቶች በፊት ለፊት በር ሲገቡ እበራፋቸው ካሉት ጎተራዎች መሐል በፍራቻ ተደብቃ ባታይ ኖሮ ጉዳዩን ለግድያ እንዳነሣሣው ግልጽ ካለመሆኑም በቀር ማስረጃው በቂ ቢሆንም ትክክለኛው ገዳይ ፡ ገዳይነቱን በሙሉ ልብ ለመቀበል ግራ በገባ ነበር። ለማንኛውም



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንጀለኛው ሊያመልጥ አልቻለም ። ግን ለወይፈቱ እንደ ቁም ነገር ልብ በሉ ። አውጫጭኝ ወንጀለኛን ለማጋለጥና ወንጀልም እንዲቀንስ የሚረዳ ጠቃሚ ዘዴ ሆኖ ሲሠራበት ቢቆይም ፡ በእርሱ ላይ ብቻ ከመተማመን ለረቀቀ ለበሰለ ምርመራ አግባብ ላለው መምሪያ ቤት ማስታወቁ ይበጃል ። ምክንያቱም ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች አውጫጭኙን የሚራ መድረክ ሊያደርጉት ይችላሉ ። ወደ ነጥቡ ለመመለስ ጓድ በሪሁን " የተቀየረው አሮጌ ጦር የማን እንደሆነ ልታረጋግጥልን ትችላለህ?" አለ እንግዳው እግረ መንገዱን ባገኘው ፋታ በረጅሙ ተነፈሰና ።

"አዎን አረጋግጣለሁ ።"

"ማነሽ ...አንቺ ልጅ ...ደብሪቱ! ሟቹ እመቤትሽን ደፍሮ ሲወጣና ጌቶች ከእርሻ ሲመጡ በትክክል አይተሻል?"

"አዎን! ለምን እንደሆነ እንጃ አለወትሮዋቸው ከሰዓቱ ቀደም ብለው ከፊት ለፊት ካለው በር ሲገቡ አይቻለሁ" አለች እንባ በተናነቀው የሲቃ ድምፅ ።

"እሺ ደግ" እንግዳው ሰው አሁንም በረጅሙ ተነፈሰና ፊቱን ወደ በሪሁን መልሶ ፡ "ታዲያ ጦሩ የማን ነው?" ብሎ ጠየቀ ።

በሪሁን ከበፊቱ ለየት ባለና ዝግ ባለድምፅ ፡ "የባሻ ዳምጤ ነው" አለ ሁሉም በድንጋጤ ወደ ውስጥ "ህህእም" ብለው ተንፍሰው ከንፈራቸውን እየመጠጡ በአድናቆትና በአዘኔታ አንገታቸውን ደፍተው አጉተመተሙ ።

ለረጅም ጊዜ በዝምታ አቀርቅረው የቆዩት ባሻ ዳምጤ ቀና አሉና በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ፡ "ለመሆኑ አንተ ማነህ?" አሉት እንግዳውን በፈጠጠ ዐይን እያዩ ።

ድምፁን ከፍ አድርጎ "ፖሊስ" ብሎ መለሰ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ትፋንቻ

ፈሻሊያ እፊቱ ላይ ድቅን አለችበት። ወደታች የተገመደው ጸጉሯ ፡ ሲጨፈኑ የተቃረቡ ይመስል የጠበቡ ዐይኖቿ ፡ ደፍጠጥ ያለው አፍንጫዋ ፡ ወፍራም ከንፈሯ ፡ ነጭ ወተት የመሰሉት ጥርሶቿ ታዩት ። እያታው በዚህ አላበቃም ። መላ አካሏን በሐሳብ ሕሊናው ይቃኘው ገባ ። በአፍንጫዋና በጆሮዋ ላይ የተሰካው የማጭድና እራት የተለያዩ ርዝማኔ ዎች ያሉት የማዕዘን ቅርጽ ሎቲዎቿ በቁንጅናዋ ላይ ተደም ረው እስጊጠዋታል ። በእርጩሜ ተገርፎ ሰንበር እንዳወጣ ገላ የተኸርኮረኮረው ዕርቃን አካሏ ከፊትህ አልጠፋ አለው ። ለውጊያ እንዳጐጠጐጡ የጥጃ ቀንዶች ቀጥ ብለው የቆሙት ጡቶቿ ደረቱን ሲወጉት ተሰማው ። ጠንካራና ሸካራው እጇ ነጸጉሯ እንሶቶ ትከሻዋን ፡ ከዚያም ክንዷንና በክንዷ ላይ የጠለቀውን ወፍራም አንባር አልፎ ወገቧን ፡ ዳሌዋን እየዳበሰ ለኀፍረት መሸፈኛ ያህል ከወገቧ በታች እስከ ጉልበቷ ድረስ የተንጠለጠለውን የተገመደ ልጥ ዘልቆ ሲወርድ ታየው ። ሁሉም አሁን የሆነ ይመስል ሰውነቱ እየጋለና እየተንዘፈዘፈ የልቡ ምት ፍጥነትን እየጨመረ ትንፋሹ ቁና ቁና እየሆነ መጣ ።

ከጫጉላ ቤት ሲወጡ እርሷ ለድንግልናዋ ክብር ጸጉሯን የማር ሰፈፍ ተቀብታ ነጭ ሻሽ አሥራበት ፡ የቤተሰቦቿ ወገኖች የምሥራቹን ለመውሰድ መጥተው ዘፍነውና ጨፍ ረው በቤቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ እየዘረፉ ሲሔዱ ፡ በኋላም እርሷ በቤት ውስጥ ለአንድ ሳምንት ያህል ሳትወጣ ተሞሽራ ተቀምጣ ... የሚሆነው ሁሉ ታሰበው ። ለጥቆም በቤት



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥና በውጭ ሥራ ስታግዘውና ኋላም የምሒ ሰለት ከኮጆአቸው ማንዶ ባለው ረባዳ ሥፍራ ላይ ስታምጥ ፡ እርሱና ጓደኞቹ አራዷን ሳይቀርቡ ራቅ ብለው ከቆሙበት ሥፍራ እየተንቆራጠጠና ስለሚወለደው ሕፃን እያሰበ ወዲያ ወዲህ ሲል በኋላም በሀገሩ ወግ መሠረት በአሮጊቶች አዋላጅነት ተገላግላና እቤት ገብታ በተዘጋጀላት ቆጥ ላይ ስትጋደም አየ። "የቋም ቅገርት" አለ ለራሱ ። ከነፊሻልያ መንደር በኋደኛው በኢዲዛ ሥርግ ድግስ ላይ በርቀት የሚሰማውን የልጃገረዶችና የጐረምሶች ዘፈን ላለማዳመጥ ጆሮውን ከድኖ ከተቀመጠበት ብድግ አለና ቀስቱን ጀርባው ላይ አንግቶ ርቆ ሔደ ።

ኡፉንቻ የ24 ዓመት ፍርጥም ያለ ፡ የጋምቤላ ብሔረ ሰብ አባል ነው ። ሰውነቱ ግዙፍና ደንዳና ነው ። ትከሻው የሰፋና ደረቱም ያበጠ ነው ። ከርደድ ያለ ጸጉሩ ወደ ግንባሩ ግድግም እየጠበበ መጥቶ እፊት ለፊቱ ላይ ሾል ብሏል ። ከብልታቸው አካባቢ ነውርን ለመሸፈን ከሚጣለው ጨርቅ በስተቀር እንደ ወገኖቹ ሁሉ እሱም ራቁታም ነው ። ብቻ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚያ መንደር ስንጥቀው የሚያልፉትን የከተማ ሰዎች በማየትም ይሁን በሌላ ምክንያት ከአቡጀዲ የተሰሩ ቁምጣ መልበስ ጀምሯል። እግሮቹ ከመርዘማቸውና ጡንቻማ ከመሆናቸው የተነሣ ፡ አገር ከአገር ቢዞርባቸው ደክመኝን የሚያውቅ አይመስልም ። ጠንበለል ቁመናው በመንደሩ ካሉት ወንዶች ሁሉ የበለጠ ሞገስ ሰጥቶታል ። በጀግንነትም ቢሆን ከጎረምሶቹ የበለጠ የሚወራለት ነው ። አይንኮሉ ሰዶ ፡ ባዶ እጁን አይመለስም ። ቀስት አነጣጥሮ ስንዝሮ ዒላማውን ስቶ አያውቅም ። የሚበር ወፍ እንኳ ከሰማይ ላይ እንዳጠረደ ይነገርለታል ።

ፊሻልያም በመንደራቸው ውስጥ አሉ ከተባሉት ቆንጆ ጆች መሐል አንዷ ናት ። እንደ ተቀሩት ልጃገረዶች ሁሉ እያደገችና ለጋብቻ እየቀረበች ስትመጣ እየራቀችው ብትሔ ድም ከወንዶቹ መሐል አብልጣ ኡፉንቻን እንደምትወደው



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሁኔታዋ በግልጽ ይታወቅባታል ። የሚተዋወቁት ገና ነፍስ ሳያውቁ ከልጅነት ጅምር ነው ። በአንድ አካባቢ ተወልደው፣ አፈር ፈጭተው ፣ ጭቃ አቡክተው ያደጉ ናቸው ። እርሱና ጓደኞቹ ከኮረዶቹ ጋር ከብት እገዳ ውለው ፣ ሥራ ሥር ለቅመው ፣ እወንዝ ተንቦጫርቀውና ውሃ ተራጭተው ፣ ተሯሩጠውና ዘለው ደክሞአቸው ከትልቁ ዛፍ ሥር ዐረፍ ሲሉ አሩሩንቻ ቆሞ ወሬ ሲያወራና ሲቀልድ ማድመጥ ሁሉም ይወዱ ነበር ። ልጃገረዶቹም ከኀረምሶቹ መሐል እርሱን እንደሚመርጡ በልዩ ልዩ መንገድ ይገልጹ ነበር ። ግን የሱ ፍላጎት ዘወትር የሚያደላው ወደ ውቧ ፈሻልያ ነው።

በባልና ሚስት ጨዋታ እንኳ ፈሻልያ አጠገቡ በመቆም እንደምትፈቅደው ትገልጽለት ስለ ነበር ፣ ከመንደራቸው ውስጥ ሌላ ልጃገረድ አቅፎ አያውቅም ። ጨዋታው አብቅቶ ሁሉም ወደየቤታቸው ሲበተኑ ፈሻልያ በቁንጥጫ ጐንተል አድርጋው በመሮጥ ተከትሎ እንዲያባርራት ብዙ ጊዜ ትገፋፋው ነበር ። እርሱም አባሮ ይዞ ከልጆቹ ሁሉ ነጥሎ ከስቀረ በኋላ ወደ ነውር ባልተሸጋገረ የልጅ ፍቅር እንዲሁ

ሲሳሳሙ የሚያመሹባቸው ዕለታት ጥቂት አልነበሩም ። ነፍስ እያወቁ ሲመጡና የልጅነት ለዛና ጣዕም እየራቃቸው ሲሔድ ከልጃገረዶቹ ጋራ አብራ ፈሻልያም ገሸሽ ብትለውም ለርሱ የነበራት ግምት ግን ሊቀንስ ባለመቻሉ ዐልፎ ዐልፎ መገናኘታቸውን አላቋረጡም ። ይሁን እንጂ ሁኔታው ከመንደሩ ኀረምሶችና ልጃገረዶች ዐልፎም በአዛውንቶቹ ቅሬታን እያሳደረ በመምጣቱ እንደ ልባቸው መሆን አልቻሉም ። ልጃገረዶች እየሸሹና እየራቁት እርሱ ግን ፈሻልያን ለማግኘት ሲል ሊጠጋቸው የሚያደርገው ሙከራ ሳይሳከለት ቀርቶ ወደ ጐጆው በቅሬታ በተመለሰ ቍጥር እደጃፍ ደንጊያ ላይ ተቀምጠው ከቅል ፣ ከሸምበቆና ከገል የተሠራ ጋያቸውን እያጨሱ የሚጠብቁት እናቱ በኀዘን ኩርምት ይላሉ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የልጃቸውን የብስጭት መልክ እየተመለከቱ ፡ "ምነው ነጠላ አድርጎ የወለደህ ማሕፀኔ ከጥንቱ የተደፈነ በሆነ!" እያሉ የዐርባ ቀን ዕድላቸውን እየረገሙና ፈጣሪያቸውን እያማረሩ ያነባሉ ፡ የልጃቸውን ነጻነት አፍኖ ያስቀረው አብሯቸው የኖረው ኋላ ቀር ልማድ መሆኑን ሳያጤኑ ።

ፈሻልያም ብትሆን ከአያት ቅድማያት ተያይዞ የመጣው ባህል በሕሊናዋ ተቀርጾና ድፍን አድርቶ አፋንቻን እንዳትቀርበው ያግዳት እንጂ ስለርሱ ባሰበች ቁጥር ሰውነቷ በንዝን እየተሞላ ዐይኖቿ እንባ ያቀሩ ነበር ። በውስጧ የሚንቦገቦገው የፍቅሩ ነበልባል አልጠፋ በማለቱና በሌላ በኩል ደግሞ ካለእናት የቀረ ጐደሎ በመሆኑ ልታገባው እንደማትችል ባሰበች ቁጥር ብስጭት ይሰማታል ።

"ከሰው ልጆች ሁሉ የባሰ ጨቋኝ ለካስ ፈጣሪ ኖሯል ። እርሱ በሰውነቱ ምንም ሳይጐድለው የተፈጠረና ከወንዶች ሁሉ የበለጠ ጀግና ፡ ብልህና ውብ ሆኖ ሳለ እንደሌላው የሚመርጣትንና የሚመርጠውን እንዳያገባ እናት አልባ አድርጐ ያስቀመጠው ለምንድነው?" እያለች ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች ። ለእርሱ ካላት ከፍተኛ ፍቅር የተነሣ ምንም ዐይነት ነውር ብትፈጽም አያስፈራትም ነበር ። እንዲያውም አንድ ቀን በመንደሯ የተወራባትና የታማችበት የነውር ድርጊት እውነት ሊሆን ትንሽ ነበር የቀረው ።

ፈሻልያ ሥራ ሥር ለቅማ አፋንቻም አደንጕሎ የገደለ ውን ሚዳቋ በዱላ አንጠልጥሎ ፡ በትከሻው ላይ ተሸክሞ ሲመጣ እመንታው መንገድ ላይ ተገናኙ ። እንደ ተለመደው በአደን የተገኘው ሁሉ ተሰብስቦ በኅብረት ወደሚበላበት የመንደሩ ማዕከላዊ ሥፍራ ግዳዩን ሳያደርስ ፡ "ፈሻልያ እባክሽ እስቲ እዚህ እንቀመጥና ትንሽ እናውራ ፡ እኔም



t.me/OLDBOOKSPDF

እንቺም ሥራ ውሉን የደከመን ስለሆነ እግረ መንገዳችንን ዕረፍት ይሆነናል" አላትና ከመንገዱ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ረባዳ ሥፍራ በጣቱ ጠቆማት ። እርሷም ሳታመነታ ተከትላው የተሸከመችውን ሥራ ሥር ጣል አድርጋ ከጐኑ ዘፍ አለች ።

ጥቂት ዝም ብለው እንደ ተያዩ ፡ "ለምን ሸሸኸኝ ፈሻልያዬ?" ብሎ ሲፈሩ ሲቸር ጠየቃት ። መልስ ሳትሰጠው አቀርቅራ በግር ጥፍሮቿ አሸዋውን ጫር ጫር አደረገች ። "ስሚ እንጂ ፈሻልያ አትወጂኝም እንዴ?" አለና እጁን በዝግታ ከትከሻዋ ላይ አኖረው ።

ሰውነቷን መንጨቅ አድርጋ እንደ መራቅ አለችና "ብወድህ ባልወድህ ምን ፋይዳ አለው ?" ስትል ፍርጥም ብላ መለሰችለት ።

"እንዲያውም ነገሩን ማለቴ እንጂ ለትዳር እንደማላበቃሽ በውቀዋለሁ ።"

"ታዲያ ምን አስጠየቀህ?"

"ለሌላ ሳይሆን እንዲሁ ትወጂኝ እንደሆን ለማወቅ ነው ።"

"እንዲሁ ብወድህ ምን ያደርግልሃል?"

"ዝም ብሎ ደስ ይለኛል ።"

"እንዴት ዝም ብሎ? መውደድ እኮ ዋጋ ሲኖረው ነው"

"ልታሳዝኚኝ ብለሽ ነው እንጂ እወድሃለሁ ብትይኝ አሁን ምን ነበረበት ?"

"በእኔ ለምን ታዝናለህ ፡ በወለዱህ በእናትህና በአባትህ አዘን እንጂ ።"

ቃላትዋ ድርቅ ያሉ ይሁኑ እንጂ ስታወጣቸው ግን በትንንቅና በጭንቅ ነበር ። ኡፋንቻ የወረዛው ዐይኑ እንዳይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታደበት ቀና አለና በመጥለቅ ላይ ያለችውን ጀንበር ተመለከተ ።

ጥቂት በዝምታ እንደቆዩ "ኢባንታን ልታገቢ ነው ፡ አይደለም?" ብሎ ጠየቃት ።

"እኔ እኮ አልወደውም ። የእግሩ ቅጥነት ፡ እነጋገሩና ድምፁ ያስጠላኛል ።"

"አንቺ ብትወጂው ባትወጂው ወንድምሽ የሱን እኅት ኡቻያን ይወዳት የለ?" ሲላት መልስ ሳትሰጥ እንደ መናደድም እንደ ማዘንም ብላ ተንሥታ ልትሔድ ስትል በሁለት እጆቹ ጥርቅም አድርጎ ያዛትና ደረቱ ላይ ለጠፋት ።

እያጉተመተመች ትንሽ እንደ መታገል አለች ። ብቻ እቅፉ እየጠነከረ ሲመጣ የእርሷም ሰውነት ቀስ በቀስ እየጋለና እየተንቀጠቀጠ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ መጥቶ ገላዋን ለማስለቀቅ የምታደርገውን መፍጨርጨር ተወችው ። ከንፈሩ የእርሷን ሲነካው ሳታስበው እጆቿን አንሥታ እርሷም አቀፈችው ። ወዲያው እሷነቷን ከርሷ ይልቅ የርሱ አደረገችው ። ኢፋንቻ ግንባሯን እየሳመ ፡ አንገቷን እየደባበሰ ፡ እጆቹ በወገቧ ዙሪያ የታሰረውን ከሥር ልጥ የተገመደውን ሽፉን ገለጥ ሲያደርግ ልዩ ስሜት ነዘረው ።

ካሉበት ሥፍራ ጥቂት ራቅ ብሎ "ፊሻልያ" እያለ በተደጋጋሚ የሚጠራውን ድምፅ ከርሷ በፊት አስቀድሞ ያዳመጠው እርሱ ነበር ። ከመ ቅጽበት ብድግ ብሎ ግዳዩን እትከሻው ላይ ጣል አደረገና መለስ ብሎ ሳያያት በሌላ አቅጣጫ እየተጣደፈ ሔደ ። ፊሻልያም አቀርቅራ ጥቂት ከዘገየች በኋላ አሸዋውን ከገላዋ ላይ አራግፋና የተመሰቃቀለውን ልጥ ከጉልበቷ ላይ እያስተካከለች ወደሚጠራው ድምፅ እየሮጠች ሔደች ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ኡፋንቻ ፡ ፈሻልያን የሚማኅቱና ፍቅሯን የመወጣቱ ጉዳይ ግን ከዚያን ቀን ሙከራ ሊያልፍ አይችልም ። የትዳር ጉዳይ ለርሱ ከቀን ሕልምነት የማያልፍ ከንቱ ምኞት ነው ። ለዚህ ወግ ፡ ለዚህ ክብር ያልታደለ የወንድ ጐደሎ ነው ። እንደ ጓደኞቹ ሁሉ እንደ ልቡ በልጅነቱ ከመንደሩ ልጃገረዶች ጋር ያደገ ቢሆንም ለአቅመ አዳም ሲበቃ ግን የሚፈልጋትን ልጅ ወንድም አማክሮና ተወያይቶ ሚስት ማግባት አይችልም ። ለሚፈልጋት ሴት ወንድም በለውጡ የሚሰጠው እኅት ስለሌለው ለዚህ ወግ የመብት ዕድሉና ተስፋው ያከተመው ገና በልጅነቱ አባቱ ሲሞቱ ነው ።

አባቱ ባውዶ ራጋ በመንደራቸው የተከበሩ ትልቅ ሰው ነበሩ ። የዛሬ ዐሥር ዓመት ወጣት ሳለ በደረሰባቸው ጽኑ ሕመም የተነሣ ከዚህ ዓለም ሲለዩ ጎረቤት ተሯሩጦ ታላላቅ የተባሉ ሰዎች ተጠርተው እስኪሰበሰቡ ድረስ ኡፋንቻ ከጎጆአቸው ደጃፍ ላይ ተቀምጦ ሁኔታውን በአንክሮ እየተመለከተ በልጅ ጨቅላ አዕምሮው ስለ መጪው ሕይወቱ ያስብ ነበር ። በባህላቸው ደንብ ዐዋቂ ተሰብስቦ ሳይመጣ ለቅሶ አይጀመርምና ቢተዘመድ ሁሉ በኀዘን ተውጦ አቀርቅሮ አካባቢው ጭር ብሎ ነበር ። ጥቂት ዘግይቶ ታላላቅ ሰዎች ተሰብስበው ካበቁ በኋላ አንድ ጥይት ተተኩሶ ልቅሶው ሲጀመር የአባቱ ወንድም ከወዲያ ወዲህ በሰፊው ሜዳ ላይ እየሮጡ ስለ አባቱ ጀግንነት ፡ በጎ ምግባርና ትልቅነት እያወሱ ሲፎክሩ ባየ ጊዜ ዐይኖቹ በእንባ ተሞሉ ። ለቀስተኞቹ በተለመደው የኀዘን እንጉርጉሮ እያዜሙ ሲያለቅሱ የርሱም እንባ አልገታም ብሎ ዕርቃን ሥጋውን የቀረውን ጥቁሩን ገላውን እያጠበው ይወርድ ነበር ። ብቻ ይህ ሁሉ አባቱን ከሚሐዱበት የዘለዓለም ሥፍራ ሊያስቀራቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

አልቻለምና የአባቱ አስከሬን እንደ ደንቡ ዘይት ተቀብቶ እና በጨርቅ ተጠቅልሎ ተቀበረ ። በዚህም በአባቱ ግብዓተ መሬት የእርሱም ሕይወት ዓቢይ ገጽታ የጋብቻ መብት አብሮት ተቀበረ ። እናቱ ኢዮቤዩ ለአንድ ዓመት ያህል ካዘኑና የመታሰቢያቸውን ድግስ ካበሉ በኋላ ልጃቸውን ቁሞ ቀር ላለማድረግ የእርሳቸውን ቢጤ ፊት ባል ለማግኘት ብዙ ቢጥሩም አልተሳካላቸውም ። ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ኡፋንቻ ምንም እንኳ ለመንደሩ ልጃገረዶች የዐይን ማረፊያ ሆኖ ቢያድግም ያለ እንትት የቀረ በመሆኑ ሊያገቡት እንደማይችሉ በመገንዘባቸው ይቀርቡትና አብረውት ይጫወቱ የነበሩት ልጃገረዶች ሁሉ ከእርሱ ዕድሜ ጋር እያደጉና እየጐለመሱ በመጡ መጠን እርሱንም እየራቁት ሔዱ ። አንዳንድ ቀን ስለ ፈሻልያ ባሰበ ቁጥር ያን ዕለት ማታ ሊፈጽሙት የነበረው ነውር እፊቱ ላይ ድቅን ይልበታል ።

"እስቲ የዚያን ቀን ፈጽሜው ቢሆን ኖሮስ ምን የሚመጣ ነገር ነበር ? ያው እንደ ተለመደው የሠርግ ዕለት ማታ ለባሏ ድንግልናዋን የወሰድሁ እኔ መሆኔን ስትነግረው ሽማግሌ ልኮ ነው የሚከሰኝ ። ቤተሰቦቼም በደንቡ መሠረት አንድ ሠንጋ መቀጫ ከፍለው ሁሉም ያበቃ ነበር ። ሕይወቴን፡ ፍቅሬን ፡ ውዷን ፈሻልያን አግኝቼ እንኳን ሠንጋ ነፍሴንስ ብቀጣ ! እ...እም...የለ እንኳን አላደረግሁት !... ይህች ምስኪን እናቴና አጎቴ በምን አቅማቸው ነው ሠንጋ የሚቀጡት ። ያውም ለማይዘልቅ የፍቅር ሩካቤ! ዳሩስ ለአንድ ቀን ከፈሻልያ ጋር ብደሰት የሁልጊዜ ትዳር አይሆን!"

. እያለ ከራሱ ጋር ብዙ ተሟግቷል ።

ከዚያን ጊዜ በኋላ ፈሻልያን ሳያገኛት ብዙ ጊዜ ቢያልፈውም ስለ እርሷና ስለ ትዳር ውሎ ሲያድር ይብስ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውነቱ እየሚሸሸ ጣቅና ለዛው እየከዳው መሔድ ያዛል ። ከሁሉ የበለጠ የበገነው ግን ኢዲዛና ወንድሚ ሌሎች ወንድምና እኅት በሚያገቡበት ሥርግ ወንድሚ አድሩማም ከኢባም፡ታ እኅት ከኢቻዖ ጋር የጋብቻቸው ሥነ ሥርዓት እንደሚፈጸም ሰምቶ ነበር ። ሁሉም ሰሞኑን በመደዳ ሊያገቡ ነው ። አብሮ አደጐቹ አንድም ሳይቀሩ ። ውዷ ፈሻልያም እንደዚሁ ። ታዲያ ከእንግዲህ ወዲያ ያለው የኡፋንቻ ሕይወት ምን ሕይወት ነው ?

በድግሱ ሥፍራ ወንዶችና ሴቶቹ አሸዋ የሞላውን ቅል እያንከሻከሹና መሬቱን በዱላ እየመቱ እንደ እምቢልታ በአፍ የሚነፋውን የሙዚቃ መሣሪያ እየተጫወቱ ሲያዜሙና ሲጨፍሩ ፈሻልያ ብቻ ተደብራ ከአንድ ጥግ ተቀምጣ ታስብ ነበር ። በእንዲህ ዐይነት የሠርግ ቦታ ላይ ዘወትር የማይጠፋውና ሽብሸባውና ዜማ አወራረዱ የሚደነቅለት ኡፋንቻ ዛሬ ባለመኖሩ እንደ ዱሮው ሠርጉና ጨዋታው አልደምቅልሽ ብሏታል ። በእሷ ይባስ እንጂ የታዋቂው አቀንቃኝ የኡፋንቻ አለመኖር ሠርጉን እንዳቀዘቀዘው እዚያ የነበሩት ሁሉ ተሰምቷቸዋል ።

ጎረምሶች ሁለት ሦስት ጊዜ ፈልገው እንዲጠሩት ቢላኩም ሳይሳካላቸው በመቅረቱ "የት ሔደ?" በሚል ግራ ተጋብተው ተመልሰዋል ። ወጣቶቹ እራሳቸውን እንደ ምንም አሚሙቀው ጨዋታቸውን ቢቀጥሉም ፈሻልያ ግን አሁንም ከዳሱ ጥግ ብቻዋን ተጠግታ እንደ ተከዘች ታነባ ነበር ። በቅርቡ ሊያገባት ዝግጅቱን ያጠናቀቀው ኢባም፡ታና እኅቱ ኢቻዖ ሌቱን ሁሉ በሁኔታዋ ተደንቀው እየተንሾካሾኩ ሲያንጓጥጧት አመሹ ። ከዚህ ቀደም ከእኅት የለሹ ግማሽ ሰው ከኡፋንቻ ጋር ባልጋለች የሚለውን ሐሜት ደጋግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሰማው ኡባምታ ነገሩ እውነት አይደለም ብሎ ቸል ቢለ ውም ውስጡን በቅናት ከመብገን አልዳነም ። አድርጎትም ከሆነ ከሚከፍለኝ ሥንጋ በቀር ምንም አይሆንም በማለት እያሰበ በንዴት ይበግን ነበር ። በንዴት ጥቁር ፊቱ ይበልጡን ከሰል መሰለ ። የሚሆነው ጠፍቶት የፊሻልያን ወንድም ኡድሩሳን ጠርቶ አንድ ነገር በጆሮው ሹክ አለለት ። ኡድሩሳም ወደ ፊሻልያ ተጠግቶ አመልካች ጣቱን እየጠነቆ ለና ዐይኑን እያፈጠጠ አስጠነቀቃት ። ኡድሩሳ እኅቱ ፊሻልያ ኡባምታ ጋር ተፋቅረ መኖር ካልቻለችና ከጋብቻቸው በኋላ ትዳሩ ከፈረሰ እርሱም ከኡባምታ እኅት ከኢቻየ ጋር የሚመሠርተው ትዳር እንደሚፈርስ ያውቃል ። በባህላቸው ወንድ የው በለውጥ ያገባት ሚስቱ ካልተስማማችው ፊትቷት እኅቱን ማስመለስ ይችላልና ። ስለዚህ ነበር የፊሻልያ ሁኔታ ከኡባምታና ከእኅቱ ኢቻየ የበለጠ ኡድሩሳን ያስጨነቀው ።

ፊሻልያ በወንድሟ ማስጠንቀቂያ የተደናገጠችና በሥርጉ ጨዋታ ላይ ለመሳተፍ የምትሞክር መስላ ጥቂት ከዘገየች በኋላ ፡ ዕኩለ ሌሊት ገደማ ማንም ሳያያት ወጥታ ከኡፋንቻ ጋር ዘወትር ወደሚገናኙበት ዛፍ ስትሮጥ ሔደች ። እንደ ደረሰችም የምትፈልገውን ኡፋንቻን ግን አላገኘች ውም ። በምትኩ ዘወትር ከእሱ የማይለየውን ቀስቱን ግንዱ ላይ ተደግፎ አገኘችው ። እንኳንስ በሌሊት በውድቅት ጨለማ ይቅርና በቀንም የማይተወውን ቀስቱን ግንዱ ሥር ትቶ በአቅራቢያው አለመታየቱ የደግ እንዳልሆነ ታወቃት ።

"ኡፋንቻ ! ኡፋንቻ !" እያለች በድፍን ጨለማ ሚዳው ላይ እየተሯሯጠች ደጋግማ ተጣራች ። የገደል ማሚቶ የራሷን ድምፅ ሲያስተጋባው ከመስማት በስተቀር ምንም መልስ አላገኘችም ። በድንጋጤ እቆመችበት ሥፍራ ለጥቂት

t.me/OLDBOOKSPDF

ደቂቃዎች እንደ ተተከለ ድንጋይ ቀጥ ብላ ቆማ ቀረች ። መለስ ብላ ከዛፉ ሥር በዝግታ በርከክ አለችና የኡፋንቻን ቀስት በእጆቿ አጥብቃ ይዛ ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች ።

ኡባምታ የወደፊት ባለቤቱን ፊሻልያን ከሠርጉ መሐል ሲያጣት ከኡፋንቻ ጋር ተቃጥሯ ዘወትር ከሚገናኙበት ዛፍ ሥር ሔዳለች በማለት ጠርጥሮ እርሱም ቀስ ብሎ ወጣ ። የግማሽ ጨረቃ ብርሃን ፊቱን ሸንተረሩን ወለል አድርጐ ታል። እየተቻኮለ ከዛፉ አጠገብ እንደ ደረሰ ቅጠላ ቅጠል ተከልሎ የሚሆነውን ለማየት ወደ ዛፉ አካባቢ ተመለከተ ። እንደ ተጠራጠረውም ከትልቁ ዛፍ ፊት ፊሻልያን ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብላ ቆማ አያት ። ኡፋንቻን ግን በአካባቢው ሊያየው አልቻለም ። ጥቂት እንደቆየ ፊሻልያ ከዛፉ ጥግ ብርክክ ስትል ተመለከታት ። እርሱ ከማይታየው የግንዱ ሌላ አቅጣጫ ኡፋንቻ የተቀመጠ መሰለው ። እንዳጐነበሰች ብዙ ስትቆይ ከኡፋንቻ ጋር የተቃቀፉ መስሎት ሰውነቱ በንዴት ተለዋ ወጠ ።

"እነዚህን ወራዶች ማስደንገጥ አለብኝ" አለና ቀስቱን ከትከሻው ላይ አውርዶ ከፊሻልያ አናት በላይ ላለው ግንድ አነጣጠረ ።

ፊሻልያ እንባዋን አደራርቃ የኡፋንቻን ቀስት ከነበረ በት ሥፍራ አኑራ ከእንብርክኳ ተነሥታ ጭንቅላቷን ቀና ስታደርግ ለግንዱ የተነጣጠረው የኡባምታ ቀስት ከጆሮ ግንዷ ላይ ተሰካ ። በጣር ድምፅ "ኡፋንቻ!" አለችና በጀርባዋ ወደቀች ።

ኡፋንቻ ዘግየት ብሎ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ላይፈጸም በቻለ ነበረ ። እርሱ ግን ቀደም ብሎ ከአካባቢው ርቆ ሔዷል። የመንደሩ ጎረምሶችና ኮረዶች ሁሉ ሠርጉ ቤት ሲዘፍኑና


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲጨፍሩ ብቻውን ከመንደሩ ወጣ ብሎ እርሱና ፊሻልያ ይገናኙ ከነበረበት ዛፍ ሥር ተቀምጦ አሳቡን በሐሳቡ እያብላላ የባጥ የቆጡን ሲያወጣና ሲያወርድ አረፈደ ። በአንድ ወቅት ሙሉ የነበረችውን ግን ዛሬ እንደ እርሱ ሰውነት ለሁለት የተከፈለችውን ግማሽ ጨረቃ እያስተዋለ እራሱን በትላንት ፡ በዛሬና በነገ መሐል እየመላለሰ ይቃኘው ገባ ። ጨረቃዋ በጥቁር ደመና ውስጥ ተሸሽጋ ምድሩ ጨለማ ሲለብስ የርሱም ተስፋ እንዲሁ ሲጨልም ፡ ከዚያም ደመ ናው ከላይዋ ላይ እየተገፈፈ ውጋጋኗ ሲታይ የርሱም ልብ በብሩህ ተስፋ እየተሞላ ሲፈካ ቆየ ። በእንዲህ ዐይነት ሲጨነቅና ርቆ ሲያስብ ሳያውቀው ሌሊቱ ተጋመሰ ። ሐሳቡ ዘፈን ከሚዘፍንበት መንደሩ ወጥቶ በወሬ እንጂ በዐይኑ ወዳላየው ሩቅ አገር ዘመተ ። ሚስት ለማግባት በለውጡ እኅት እምጣ የማይባልበት ቦታ እንዳለ ታወሰው ። ዐልፎ ዐልፎ ብቅ የሚሉ ልብስ ለባሾችና አሞሌ ጨው ይዘው የሚመጡ ነጋዴዎች እንደ ፈለጉ ካለ ለውጥ ሊያገቡ እንደሚ ችሉ ሲነገር የነበረው ትዝ አለው ።

“በሰውነቱ ከየትኛውም የሰው ፍጡር አላንስም ። እንደ ማንም ወድጄና አፍቅሬ ፡ ሚስት አግብቼና ልጆች ወልጄ መኖር መቻል አለብኝ” አለና ተነሣ ። ከልጅነቱ ያልተለየው ጓደኛውን ቀስቱን ካስቀመጠበት ብድግ አድርጎ አየው ። በደጋኑ መሐል የፊሻልያ መልክ ብቅ አለበት ። ቀስቱን መልሶ ከነበረበት ዛፍ ሥር በጥንቃቄ አኖረውና አንዳንድ ወደ መንደሩ ለንግድ ልውውጥና ለሌላም ጉዳይ ብቅ የሚሉት የውጭ ሰዎች የሚመላለሱበትን ቀጭን መን ገድ ተከትሎ ወደማያውቀው አገር ጉዞ ጀመረ ። በውድቅት ሌሊት እሻቅቦ ሔደ ፡ ለእነ ዶዶዛ ሥርግ የሚዘፈነውን ዘፈን

t.me/OLDBOOKSPDF

በርቀት እያደመጠ ። ዘመዶቹን ሳያማክርና ሳይሰናበት ፡ ጨርቁን ማቁን ሳይል በእኩለ ሌሊት ሥልጣኑን እያሸተተ ወደማያውቀው አዲስ ዓለም አመራ ። አብሮት የኖረው አጉል ባህል የነፈገውን ነጻነት ፍለጋ !

t.me/OLDBOOKSPDF

# የካዛንችሱ ቀጠሮ

ድርጅቱ ሰፋ ያለ ነው ። የአስተዳደር ፡ የሒሳብ ክፍልና የመጋዘን ክፍሎች በእሱ ቢሮ አካባቢ ስለሚገኙ ከየክፍሎቹ ተጠሪዎች ሌላ ዐልፎ ዐልፎ ጥቂት ሠራተኞችን ያውቃል ። እራቅ ብሎ በሚገኘው በምርት ክፍል ግን ፡ ከክፍሉ ኃላፊ ከአቶ ደመወዝና ከጥቂት የምርት ጥራት ጥበቃ ሠራተኞች በቀር ብዙዎቹን ሠራተኞች አያውቃቸውም። የየክፍሉ ተጠሪዎቹንም ቢሆን ሊያውቃቸው የቻለው በሥራው ዘርፍ መሠረት ዘወትር ስለሚገናኛቸው ነው ። በተለይ በዚች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከትውውቅም ባሻገር ለግል ጉዳዩ ሳይቀር ልብ—ለልብ የሚግባባው ከአስተዳደር ኃላፊው ከአቶ አሰፋ ጐርፉ ጋር ብቻ ነው ።

አቶ ዘነበ ይባላል ። ዘነበ ረጋሳ ። ለመሥሪያ ቤቱ ገና እንግዳ ነው ። ቀድሞ ከነበረበት የሥራ ተቋም በሥራ እስኪያጅነት ተሹሞ ወደዚህ መሥሪያ ቤት ከመጣ ገና ሦስት ወር አልሞላውም ። ከቁመናው ረዘም ብሎ ቀጠን ያለና ዘወትር ሐሳብና ሥጋት የተጫኑት መሳይ ነው ። ግንባሩ እጅግም አይፈታ ። ዐይኖቹም ዐልፎ— ዐልፎ ጥልቅ ትካዜ ይነበብባቸዋል ። በል ሲለው ጥሩ ይጫወታል ፡ ወሬው ሁሉ አይጠገብም ። አንዳንዴ ግን መደዳውን ተለጉሞ መክረም ያስኘዋል ። አለባበሱም እንደዚያው ነው ። የነሸጠው ሰሞን የተወለወለ መስታወት መስሎ ይታይና ወዲያው ደግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙም ሳይሰነብት ከውሃ በተጣላች ኩሬ ውስጥ ተሸጉጦ ለሳምንታት ያህል ይዘልቃል ።

የወንድ ጓደኛ እጅግም አያበዛ ። የሴት ጓደኛም ቢሆን እርግፍ አርጎ ከተወ ሁለት ዓመት ዐልፎታል ። የሴት ልጅ ውበት በእሱ ዘንድ ቁመና ነው ፤ ለዐይን ለአፍንጫና ለቅላት ቁንጅናዎች እምብዛም ትኩረት አይሰጣቸውም ። ከሴት ልጅ አፈጣጠር ዘለግ ማለቷን በቅጡ ይወደዋል ። "ትቅላም ትጥቆርም ሴት ልጅ መዘዝ ማለት አለባት" ይላል መሰል ወሬ ሲነሣ ። የቆንጆ ቆንጆ ብለው ሰዎች የጠቆሙትን ፤ "ምን ዋጋ አላት! ቁመት ያንሳታል" ይላል በዐይኑ ከእናት እስከ ጫማዋ ይማትርና ። ደም ግባትም ቢሆን ለእሱ ምኑም አይደለም ። ብቻ የጉንጭ ነገር አይሆንለትም ። የሴት ልጅ ጉንጭ እንደ ሳንድዊች ግጥም ብሎ ፤ እንደ ማንጎ ፍሬ ቁልቁል ጥልጥል ካላለ ፤ በእሱ ዐይን የውበት ቁንጮውን አጥታለች ማለት ነው ። ጉንጬ ሰልካካ አጭር ሴት ምንም ታሚላ ምንም ይኑራት ዘነበን ካፈቀረች ወዮላት መሠቃየቷ ነው ።

ጠዋት ወደ ረፋዱ ላይ ነው ፤ እንደ ወትሮው ቢሮው ውስጥ አድረው የሱን ፊርማ የሚጠባበቁትን ልዩ ልዩ መዛግብትና ደብዳቤዎችን ሲያገላብጥ ያረፍድና ወደ አራት ሰዓት ገደማ እንዲት ከሸንጧ ረዘም ያለች ፖስታ ከጠረጴዛው በስተግራ ጠርዙ ላይ ተቀምጣ ያያል ። አንሥቶ አድራሻዋን ማንበብ ጀመረ ። "እ! — ማይ ጉድነስ" አለ ከሳምንት በፊት ከዋናው መሥሪያ ቤት የተላከችው ደብዳቤ መሆኗን ሲያረጋግጥ ። "ለዕድገት የሚበቁ የምስጉን ሠራተኞች ስም ዝርዝር ከሥራ ልምዳቸውና ከትምህርት ደረጃቸው መግለጫ ጋር ተያይዞ እንዲላክልን" የሚል እንደ ነበረ የደብዳቤውን

t.me/OLDBOOKSPDF

መልዕክት ከሰባት ቀን በፊት እንዳብቦታል ።

ፖስታዋን ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ጨምሮ በደወል ጥሪ ጸሐፊዋን ማኀደርን ይጠራታል ። ማኀደር አፍታም ሳትቆይ የቢሮውን በር ከፍታ ገባች ። "ማነሽ ፡ ማኀደር ያ የምስጉን ሠራተኞችን የአገልግሎት ዘመንና የትምህርት ደረጃ የሚገልጸው የስም ዝርዝር ሰነድ ተዘጋጅቶ አላለቀም እንዴ?!" ብሎ ጠየቃት ።

"አዎን አልቋል ፡ ከአስተዳደር ክፍል የመጣልኝ ገና ትላንት በመሆኑ ነው እስካሁንም ሊቆይ የቻለው ፡ ቆይ ላምጣው" ብላ ከቢሮው ወጣ እንዳለች የስልክ ጥሪ ተከታትሎ አቃጨለ ።

"ሀለው!" አለ ዘነበ የስልኩን የመነጋገሪያ እጀታ አንሥቶ ።

"አቶ ዘነበ ነዎት?" የሚል ቀልጣፋ ድምፅ በጆሮው ጥልቅ አለ ።

"አዎ ነኝ ።"

"እንደምናለህ ዘነበ? ክብረ አብ ነኝ ከዋናው መሥሪያ ቤት ። "

"አ! ጤና ይስጥልኝ — ጤና ይስጥልኝ! አቶ ክብረ አብ..."

የበኩሉን ሰላምታ በአክብሮት ካኀጉዳጉደ በኋላ ፡ "ዘነበ! በመዝገብ ቁጥር ኻያ አራት ስልሳ ዘጠኝ ፡ እዝባር ሰባ ሰባት የተጻፈው ፡ ለደሞዝ ዕድገት የምስጉን ሠራተኞችን የግልጋሎት ዘመንና የሥራ ልምድ በተደራጀ ሰነድ የሚጠይቅ ደብዳቤ አልደረሳችሁም እንዴ?"

"ደርሶናል! ደርሶናል! ሰነዱንም አጠናቅረን ወደ መጨረሱ ላይ ነን ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ታዲያ መቼ ልትልኩት ነው እስካሁን ያላጠናቀቃችሁት?”

“ከሰሞኑ ከሦስት— ከአራት ቀን በኋላ እንልከዋለን ። ኦልሬዲ አልቋል እኮ ።”

“ደህና! ከእንግዲህ ወዲያ ከሳምንት በኋላ ዘግይቶ ቢደርሰን ለእኛ ሥራ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ለሠራተኞቹ ሊሰጥ የታቀደው የደመወዝና የሥራ ዕድገት ዋጋ ያጣል ። ይህ ደግሞ ኃላፊነቱ ያንተው ስለሆነ ተጠያቂ ያደርግሃልና ቸልታ እንዳይኖር ” አለ አቶ ክብረአብ ቆምጨጭ ባለ የማስጠንቀቂያ ዐይነት አነጋገር ።

ዘነበ እሺታውን ለመግለጽ ዐይኖቹን ስለምለም አርጐ ፡ አሳዛኝ የፊቱን ቆዳ በመሸብሸብ “ደህና ግዴለም!” እንዳለ ማኅደር ፡ የሰነድ ጥራዝ በግራ እጇ ይዛ እቢሮው ትገባለች ።

የስልክ ንግግሩ እንዳበቃ ዘነበ ፊቱን ወደ ማኅደር ያዞርና ፡ “እሺ! እስቲ አምጭው ባክሽ!” ይላል በተሰላቸ እንደበት ማንባሩን ኮስተርተር አርጐ የቀኝ እጁን ወደ እሷ በመዘርጋት ።

ማኅደር ነጠር ፡ ነጠር በሚለው አካሔዷ ወደ ጠረጴዛው በመጠጋት ፡ “ይኸውና! ግን የተቀጠሩበትን የትምህርት ደረጃ በምሽትና በተልዕኮው ትምህርቶች ያሻሻሉ ሠራተኞች እንዲመዘገቡና ማስረጃቸውንም እንዲያቀርቡ በወጣው የውስጥ ማስታወቂያ መሠረት ፡ እስከ አሁን ዐሥራ ሰባት ሠራተኞች ተመዝግበው ፡ ማስረጃቸውን ያቀረቡት ዐሥራ አራቱ ብቻ ናቸው” አለች የተዘጋጀውን ጥራዝ ሰነድ እፊቱ እያቀረበችለት።

“ሦስት ሰዎች ማስረጃቸውን አላቀረቡም ማለት ነው?”

t.me/OLDBOOKSPDF

"እዎን"

"ይህና ከእንግዲህ ወዲያ ማንም ሰው ምንም ማስረጃ ቢያመጣ እንዳትቀበይ ።"

ማኅደር ፡ ዘነበ የነገራትን ትዕዛዝ በእሺታ ተቀብላ ከቢሮው እንደ ወጣች እራሷ ቢሮ በር ላይ አንዲት ከቁመቷ ዘለግ ፡ ከዳሌዋ ፈታ ያለች ሠራተኛ ቆማ አየች ።

"እኔን ነበር የፈለግሽው?" አለች ማኅደር እቢሮዋ በር ላይ ዘና ብላ የቆመችውን ረዥም ሴት ሽቅብ በማስተዋል ።

እዎን የትምህርት ማስረጃ ላደርስ ነበር የመጣሁት ።"

"እስከዛሬ የት ቆይተሽ ነው? አዝናለሁ ጊዜው አል ፏል።"

"እባክሽ! የእኔ እንኳን አይደለም ፡ ልጅቷ የወሊድ ፈቃድ ላይ ስለ ከረመች ፡ ገና ከትላንት ወዲያ ነው ሥራ ስትቀጥል ማስረጃ ማስፈለጉን የሰማችው ።"

"ታዲያ እሷ ሥራ ከቀጠለች አንቺ የምን መልእክተኛ ነሽ?"

"እሷ አስቸኳይ ሥራ ስለ ታዘዘች የክፍል ኃላፊዋ ልከውኝ ነው እኔ የመጣሁት ።"

"አየሽ! እኔ ከአሁን በኋላ ምንም ማስረጃ እንዳልቀበል ስለ ታዘዝኩ ምንም ልረዳሽ አልችልም ። እራሳችሁ ናችሁ ስትጓተቱ ሁሌ ዕድላችሁን የምታበላሹት ፡ ሶሪ! አዝናለሁ ።"

ማኅደር በእንግዳይቱ መልእክተኛ ላይ ከንፈሯን መጣ ፡ ዝንፍልፍል ገላዋን በሚያነጥር አኪያሔዷ እያውረገረገች ወደ ቢሮዋ ገባች ። "ሥራ አስኪያጁን ገብቼ ልለምናቸው?... ምናልባት ችግሩን ተረድተው ቢቀበሉኝ" አለች መልእክተ ኛዋ ተስፋ ሳትቆርጥ ወደ ማኅደር ቢሮ እንገቷን ገባ አድርጋ።

ማኅደር በማቅማማት ዐይነት አንገቷን ግራና ቀኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘንበል ቀና አድርጋ ፡ "መግባት እንኳን አይቻልም ነበር ። ግን እሺ ካሉሽ ሞክሪ" አለቻት ቁጡ ግንባሯን ፊቷ እያረገች።

መልዕክተኛዋ ሁለት ሦስት እርምጃ ተራምዳ እንደ መፍራትም እንደ መድፈርም እየታየባት የሥራ አስኪያጁን ቢሮ አንኳኳች ከፍታ ገባች ። አቶ ዘነበ የበሩን መከፈት ቢሰሙም ባለጉዳዩን ለማናገር ቀናም አላሉ ። መልዕክተኛይቱ ግን በአንድ በኩል ልቧ እየፈራ ፡ በሌላም 'እሺ ወይም እምቢ ነው ሌላ ምን ይመጣል!' በሚል ውስጣዊ ስሜት እራሷን እያደፋፈረች ቀና ብለው እስኪያናግሯት ጠበቀችው ።

ዘነበ የሚጽፈው ጉዳይ መቋጠሪያ አልባት ያገኘለት ይመስል ብዕሩን በመጫን አራት ነጥብ ያሰፍርና መጀመሪያ ከግንባሩ ፡ ቀጥሎም ከወገቡ ቀና ይላል ። ከወረቀት ጽሑፍ ላይ ተነቅለው በባለጉዳይዋ ሰውነት ላይ ያረፉት ዐይኖቹ በድንጋጤ ስሜት ፈጠው ቀሩ ። ድንገተኛ ስሜት በአእምሮው ውስጥ ተሯሯጠ ። እንደበቱም የአእምሮውን ደወል ተከትሎ በዝምታ ተጀቦነ ። ዐይኖቹ ግን ዐልፎ ዐልፎ የባለጉዳይዋን ጠንበለል ቁመና ለመለካት ከራስ ጸጉሯ እስከ ጫማዋ እየተንደረደሩ እርዝማኔን ከመመተር ባሻገር እራቅ አርገው የሚያስተውሉትም ሌላ የትዕይንት አካል እንደ ደራሽ ውሃ ከተፍ አለባቸው ።

ድንገት በከነፈበት የትዝታ አድማስ ውስጥ የሱዶቱን ለምለምን አነጋገራት ። የለምለም ጠንበለል ሰውነት በመቃብር ውስጥ በብዙ ሺህ የምስጥ ሠራዊት ታኝኮ ፡ ዕርቃኑ አፅሟን አፈትልካ ከመቃብር ስትወጣ ፡ በዐይኑ ሕሊናው ታየችው ። በአፅምሮው እይታ ውስጥ እያቆራረጠች ስትሮጥ፡ ሲከተላት ፡ ተመልሳ ከወጣችበት መቃብር ውስጥ ምስግ


t.me/OLDBOOKSPDF

አለች ። ተስፋም አልቆረጠ ። በሐሳብ የመቃብሯን ሐውልት ሰርስሮ ገባ ። በዘላለማዊ ቤቷ ውስጥ ጠይፍ ፣ ጠይፍ ብሎ ልብሱን ሲያወላልቅ ፣ ዓዕመ ገጽዋ ዳግም አፈትልኮ ከመቃብር ሲወጣ ሊከተላት ሲል ፣ ምስጦች እግሩን ሲጐትቱት ፣ እመር ብሎ ወጥቶ ሲያሳድዳት ፣ እሮጣ ሮጣ እቢሮው ውስጥ ግትር ስትል…ሁሉንም በዐይኑ ሕሊና ቅፅበት ያጻር ስና እቢሮው ውስጥ ወደ ቆመችው ባለጉዳይ ልቡናውን ይሰበስባል ።

ዘነበ ለዚህ ሁሉ የቅዠት ዓለም ያበቃው ፣ እቢሮ ውስጥ ያያት ባለጉዳይ ከሚች ፍቅረኛው ከለምለም ስብሐት ጋር መመሳሰሏ ነበር ። ይጋግሞ አስተዋላት ። ቁርጥ አንድ ሆኑበት ። በተለይ የቁመናዋና የጉንጮቿ ውበት የለምለም የምስል አሻራ መተኪያ ሆኖ ታየው ።

ዐይኖቹን ጨፍኖ በሁለት እጆቹ ፊቱን ካሻሸ በኋላ "ምን ነበር ጉዳይሽ? እምቄው እስቲ እሱን ወረቀት" አለ መደንገጧን አይቶ እንዳትፈራ ፈገግ በማለት ። ከእጇ የተቀበለውን ወረቀት የትምህርት ማስረጃ መሆኑን እንዳረጋገጠ "መልካም! ጊዜው እንኳን ዐልፎ ነበር ፣ እስቲ እኔው እንደሚሆን አረገዋለሁ ። ለመሆኑ የት ክፍል ነው የምትሠሪው?" ሲል ጠየቃት ዘና ባለ አነጋገር ፈገግ ብሎ ።

"ምርት ክፍል" አለች ጠንበለሏ ባለጉዳይ ድንጉጥ ፊቷን በፈገግታ እያፈካች ።

ዘነበ የፊቷን አወራረድ ፣ የወገቧን ጥበትና የዳሌዋን ዳገት ልቡ ካረፈበት ቁመናዋ ጋር እያነጻጸረ በዐይኑ ወረፍ አርጐ ጐበኛት ። በተለይ እንደ እንኮይ ድንቡሽ ባለው ጠባብ ፊቷ ግራና ቀኝ ሞላ ፣ ሞላ ያሉ ጉንጮቿን ሲመለከት የሱዶቱን ለምለምን አስናቀችው ። "ዳግማዊት" አለ በልቡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስም ሊያወጣላት እየከጀለ ። በአነጋገሩ መርበትበት እየታየ በት ። "ሥራ እንዴት ነው?" ሲል ጠየቃት ስሜቱን ሁሉ በሚያደርገው እንቅስቃሴ እየገለጸ ።

ባለጉዳይዋም ከወይ አፍ በምትፈጥረው ትኩስ ፈገግታ ጉንጮቿን ግራና ቀኝ እየቆለለች "ጥሩ ነው" ብላ ከቢሮው ለመውጣት ወደበሩ አመራች ።

የዘነበ ዐይኖች በረባዳው ሽንጧ ላይ ተተክለው እስከ በሩ ድረስ ሸኟት ። የቢሮውን መዝጊያ ከፊት አርጋ እንደ መውጣት ስትል ፡ "ማነሽ! እስቲ ቆይኝ አንዴ!" አለ ለራሱም እንግዳ በሆነበት ድምፅ ። ጉዳይ ኖሮት እንኳን አልነበረም መጥራቱ ። ተከትሏት የሔደው ዐይኑ እሷ ስትወጣ የመዝጊያ እንቅፋት እንዳይሆንታው አስቦ እንጂ ።

"አቤት!" አለች የከፈተችውን መዝጊያ በአንድ እጇ እንደ ያዘች ።

"ለመሆኑ ሥራሽ ነሽ አይደለም?" አለ ስሟን መጠየቁ ነበር ከትምህርት ማስረጃው ወረቀት ላይ አየት አርጎ ።

"አዎን!" አለች ፈገግ ስትል ፍርጥም ከሚሉት ጉን ጮቿ አንዱን ወደ እሱ ዞር በማድረግ ።

"መልካም ፡ አትጥፊ እንግዲህ" አለ እሱም የይድረስ ይድረስ ፈገግታውን ጀሮው ድረስ እያስነካው ።

ዘነበ እንግዳይቱን ጠንበለል ከሸኘ በኋላ ለማማሽ ሰዓት ያህል ከስሜት ፡ ከፍቅር ፡ ከትዝታና ከተስፋ ጋር ሲመከር ይቆይና ሚችቱን ለምለም ስብሐትን በሥራሽ ሐኮስ ለመተ ካት ወስኖ ፡ ውሳኔውን በቁርጠኝነት ዝግጅት ያጸድቀዋል ።

ይህ ሁሉ ከሆነ ኻያ ቀን ቢያልፈው ነው ። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ሥራሽን ለማናገር ያላውጠነጠነው ዘዴ የለም ። ምስጢሩን ለመጠበቅ ሲል እቢሮው ድረስ አስጠርቶ ወይም

t.me/OLDBOOKSPDF

እሥራ መደቧ ድረስ ሔዶ ሊያናግራት አልሞከረም ። ከሁለት ሳምንታት በፊት ግን በሥራ ጉዳይ አስታኮ በእፕሬተሯ አማካኝነት በውስጥ ስልክ አነጋግሯታል ። እንዲያውም በዕድገት ሪፖርቱ ውስጥ በቀደምት ከታጩት ምስጉን ሠራተኞች ጐን ስሟን ለበላይ መሥሪያ ቤት እንዳስተላለፈም የነገራትና የቤት የስልክ አድራሻዋንም የተቀበላት ያኔ ነው ።

"ሀለው!" አለ የደሞዝና የሥራ ዕድገት ለድርጅቱ ሠራተኞች በደረሰ በሳምንቱ ስልክ ደውሎ ። ሥራሽ ከጐረ ቤት ተጠርታ ቀረበች ።

"እንኳን ደስ ያለሽ!" አላት በተፍታታ አነጋገር።

"በአምላክህ!"

"አዲሱ የሥራ መደብ ተስማማሽ?"

"ምንም አይል! እየለመድኩት ነው ። ያኔ ስትነግረኝ እኮ አላመንኩም ነበር ። መቼም ምስጋናዬ የላቀ ነው ።"

"ምን እባክሽ ዛሬ ጊዜ ለሰው ውለታ መፈጸም እራስን እንደ መቅበር ሆኗል ።"

"እንዴት?"

"አዬ! በስልክ አውርቼ እጨርሰዋለሁ ብለሽ ነው? ባይሆን ቀጠሮ ወስደን ብንነጋገር ሳይሻል አይቀርም ።"

"ይሻላል?"

"አዎን! ሌላም ብዙ የማነጋግርሽ ቁም ነገር ስላለ መገናኘቱ ደህና መሰለኝ ።"

"ጥሩ ፣ ግን መቼ?"

"ቅዳሜ አይመችሽም?"

"የመቼው ቅዳሜ?"

"አሁን የፊታችን ቅዳሜ ።"

"ቦታውስ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ለምን የገበያ አዳራሹ ጋ…ማለት ሱፐር ማርኬት ጋ አልጠብቅሽም?…ብዙ ያርቅሃል እንዴ ከሰፈርሽ?…የት አካባቢ ነው ያለሽው?”

“ያለሁት እንኳን ባምቢስ ፡ ከምሥራቅ ገበያ ወረድ ብሎ ነው ። ብዙም አያርቀኝ ፡ እመጣለሁ…ግን በስንት ሰዓት?”

“ስምንት ሰዓት ላይ አይመችሽም?”

ከሥራ በስድስት ሰዓት ወጥቼ ፡ ቤት ደርሼና ምሳ በልቼ እስከመጣ ለስምንት ሰዓት ቀጠሮ ለመድረስ በቂ ጊዜ አይኖረኝም ።”

“እንግዲያው ዘጠኝ ሰዓት ላይ እናድርገዋ?”

“ደህና ፡ ይሁን ።”

“አደራ እንዳትቀሪ!”

“ግዴለም ። ብቻ ሰዓት ይከበር ።”

“አይዞሽ ለእሱ አትስጊ ፡ እኪ?”

“እሺ በል ፡ ቻው!”

“ቻው! ደህና ቆይኝ ።”

ዘነበ ስልኩን ጨርሶ ስልኩን እንደ ዘጋ የቅዳሜውን ፕሮግራም ማብሰልሰል ጀመረ ። እምቡጥ ፍቅሩ የጉመራ ተስፋን አብርቶለት ፡ በዚያም ውስጥ የስራሽ ቁመና እየተመዘዘ ከሽንጡ ላይ ሲጠመጠም ፡ በጉመዣ ሕሊናው አሻግሮ አስተዋለው ። ሞላ ያሉት ጉንጮቿ የፊቷን አወራድ ግራና ቀኝ ደግፈውት ፡ ከመሐል ትኩሳቷም ፊገግታዋ እያበራ ሲደምቅ፡ ነገረ ሥራዋን በሐሳብ ዘገን አርጐ በምኞት አላመጠው። ከለምለም ሞት ወዲህ ከአእምሮው የሸሸው የትዳር ፍላጐትም እንደገና ተቀጣጥሎ ማለፊያ የጋብቻ ውጥን በልቡ ውስጥ ሥሩን ተከለበት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቅዳሜ በቀጠሮው ሰዓት መኪናውን እየነዳ ጉዞውን ወደ ካዛንቺስ አመራ ። ከመገናኛው ሰፍራ ራቅ ብሎ መኪናውን ካቆመ በኋላ አሻግሮ የሱፐር ማርኬትን አቅራቢያ በዐይኑ ያስስ ገባ ። ዐይኖቹ ተሽቀዳድመው ከአንዲት ወጣት ሴት ላይ ዐረፉ ። አጠር ቀጠን ማለቷን እንደለየ በታክሲ ተሳፍራ ሔደች ። ከሩቅ የሒልተን ሆቴልን አጥር ተደግፋ ከቆመችው ወፍራም ሴትዮና ወዲያና ወዲህ ከሚተላለፉት መኪናዎች በቀር በአካባቢው ጨርሶ የሥራሽ ጠምበለል ቂመና ጠፋ ። ዳግም ዐይኖቹን ለፍለጋ ሸኛቸው ። የለችም ።

ዘጠኝ ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ሆነ ። ከሥፍራው ዝር የምትል የሚያውቃት ሴት ጠፋች ። በልቡ ማቆጥቆጥ የጀመረውን ብሽቀት በብርቱ ትዕግሥት አፍኖት መጠባበቁን ቀጠለ ። ከሴቶችም ፡ ከወንዶችም ፡ ከወጣቶችም ፡ ከጐልማሶችም አንዳንድ መንገደኞች በአካባቢው ሲያልፉ ወይ በታክሲና በአውቶቡስ ከፌርማታው ታሳፍረው ሲሔዱ የዐይኖቹ ማረፊያ ከመሆናቸው በቀር ፡ የናፈቃት ወጣት በአካል አልቀረብ አለች ። ሒያጁም ፡ መጭውም ብዙ ሳይቆይ ሥፍራውን ይለቃል ። ከሒልተን ሆቴል አጥር ሥር ቆማ ያያት ሴትዮ ግን አሁንም እንደ ቆመች ነው ።

ብዙም ሳይቆይ ከአፍሪካ አዳራሽ በኩል ከሚያወጣው መንገድ ወደ ሱፐር ማርኬት ታጥፋ የመንገዱን ጥግ በመያዝ ወደ እሱ አቅጣጫ የምትመጣ ፡ ቀጠን ዘለግ ያለች ወጣት ብቅ አለች ። ድፍር ዐይኖቹ ተወንጭፈው ጉብ አሉባት ። ወዲያው "እፍ!···ስቱፒድ!" አለ ዐሥራ አምስት ደቂቃ ሙሉ ጠብቆ ገና አሁን ብቅ በማለቷ ። ሽቅብ የወጣ ቁመናዋን አሻግሮ በዐይኑ ማተረው ። ከሩቅ መልኳን አይቶ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲለዩ ግን ጨርሶ አልቻለም ። ጉጉቱ ባሰበት ። እንገቷን ያሩ አድርጋና ጥቁር ቆዳ ጃኬት ከአናቷ ላይ ጣል አርጋ ነበር የምትራመደው ። ፀሐይ እንዳይመታት መሆኑ ገባው ። የቁመናዋ ነገር ግን አሁንም በዐይኑ ላይ ይምዘገዘጋል ።

ወደ እሱው አቅጣጫ እየተራመደች አጠገቡ ልትደርስ አንድ ሀርባ ሜትር ያህል ሲቀራት የጻሴዋ ስፋት ቀድሞ የሚያውቀውን ምስል አልያዝልህ አለው ። መዘዝ ያለ ቁመናዋ የሚያውቀውን ዐይነት ቢሆንም ፡ የደም ግንቦ መሳይ ጉንጮቿ ግን በቦታቸው የሉም። "አይ…ከዐይኔ ይሆናል" አለ በአውራ ጣቱ ዐይኖቹን እያሸ ። ዳግም ጥርጣሬው ቢንርበት "ለአንድ ቀን አይደል ቢሮዬ መጥታ ያየኋት? ከዚያ ወዲህ በስልክ እንጂ በአካል መቼ ተገናኝተን እናውቃ ለን?" አለ እራሱን በእራሱ በመጠየቅ ፡ "ከዐይኔ ነው" የሚለውን መጽናኛውን ሊያጠናክር ።

በቀረበችው ቁጥር ግን ጨርሶ የማያውቃት እየሆነች በት መጣች ። ራመድ ፡ ቀና ነበር አኪያሒዷ ። ቀና የምትለው ሁለት—ሦስቱ ተራምዳ ስለነበር ፊቷን አተኩሮ ለማየት አላመቻቸውም። ወደ እሱ ስትቀርብ አፍጥጦ ተመለከ ታት ። በእርግጥም የቀጠራት ጉንጨ ቆንጂቷ ጠንበለል አልነበረችም ። ሌላ ጠንበለል ፡ ፊተ ሰልካካ ፡ የማትነድፍ ፡ የምትስብ ብቻ ሆነችበት ። "ዱሮም ይኸው ነው!" አለ ሲጋራውን አውጥቶ እያቀጣጠለ ። ከሩቅ አይቶት ያሳሳተው ቁመና ግን በጉን ዐልፎት ሔደ።

በልቡ "ላንዷም ለሁሌም"አለና አሻግሮ ወደ ቀጠ ሮው ማዕከል ዐይኖቹን ወረወረ ። የናፈቃት ወጣት ግን ጨርሶ የውሃ ሽታ ሆነችበት ። ከሱፐር ማርኬት ፊት ለፊት ከመንገዱ በስቲያ ፡ የሒልተን ሆቴልን የአጥር ግድግዳ


t.me/OLDBOOKSPDF

ተደግፋ የቆመችው ወፍራም ሴት ግን ፡ ለዐይን ማረፊያ እንደ ሰቀሉት ፎቶግራፍ ፡ ከቦታው አልጠፋ አለች ።

ንጉሤት መላ ሰውነቱን እያንዘፈዘፈው መኪናውን አስነ ሥቶ ወደ ሱፐር ማርኬት በዝግታ መጠጋት ጀመረ ። ዐይኖቹ ከየአቅጣጫው የሚመጡ ሰዎችን እየፈተሹ ሲያዘግም "ዘነበ!" የሚል ድምፅ ከበስተቀኝ በኩል ካለው ግድግዳ ሥር ተሰማው ። መኪናውን ቆም አርጐ ከአንገቱ ዘወር ሲል ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ቆማ ያያት ወፍራም ሴት ከፈገግታ ጋራ ወደ እሱ መምጣት ጀመረች ።

"የት ታውቀኛለች?" አለ በልቡ ፡ ስትራመድ እንከስ እንከስ ማለቷን እያስተዋለ ። ያውቃት እንደሆነ ሊያስታውስ ሞከረ ። ግን ጨርሶ ትዝ አልልህ አለችው ። "ሥራሽ እክል ገጥሚት እንደማትመጣ ልትነግረኝ የላከቻት መልእክተኛ ትሆን ?" አለ ግምቱን በጥያቄ እያብላላና ሆዱን ባር ባር እያለው ።

"ምነው ባክህ ግማሽ ሰዓት ሙሉ ታስጠብቀኛለህ?" አለች—እጇን ለሰላምታ በመኪናው መስኮት እየሰደደች ። በአክብሮት ጨበጣት ፡ ጉዳዩ ተአምር እየሆነበት ። ወደ መኪናው መስኮት አንገቷን ዘንበል አርጋ በድጋሚ ፡ "ምነው አረፈድክ?" አለች ። ፈገግ እንደ ማለት ይቃጣትና በፊቱ ላይ የግርታ መንፈስ ስታይ ደግሞ መልሳ ፊቷን ኮስተር—ፊታ ታደርገዋለች ። የማያውቃት ሴት የምታው ቀው ሆና ብትገጥመው ጭራሽ ግራ ገብቶት በዝምታ ተዋጠ።

"እንዴት ተናደድኩ መሰለህ! ደግሞ ሰዓት ይከበር ብዬ አስጠንቅቄህ ነበር የተቃጠርን ዕለት ። ትዕግሥቴ አልቆ ልክ ልሔድ ስል ነው የመጣኸው" ስትለው ምስቅልቅል ተአምር በሕሊናው ተወራጨበት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማነሽ አንቺ?" አለ እንደ መገረም ፡ እንደ መሣቅም ፡ እንደ መቆጣትም እየቃጣው ።

"እንዴ! ማንነቴ ጠፋህ እንዴ?...በእርግጥ ሦስት— አራቴ ያነጋገርከኝ በስልክ ስለሆነ በመልክ አንተ ላታውቀኝ ትችላለህ ። እኔ ግን የመሥሪያ ቤታችን ኃላፊ ስለ ሆንክ ከመጣህ ጀምሮ አውቅሃለሁ ። ደግሞም የውለታህ ጉዳይ ስለከበደኝና የምነግርሽ ቁም ነገር አለ ስላልከኝ እንጂ ስለቀጠርከኝ ብቻ የመጣሁ ሰው አይደለሁም" አለችው ወደኋላዋ እንደ መራመድ እየቃጣት ።

"ምን አስቆጣሽ የእኔ እህት? ማንነትሽን አጥቼው እኮ ነው ። ካንቺጋ ቀጠሮ ያለኝ አልመሰለኝም ።"

"እ!—ታዲያ ምን ፍለጋ መጣህ እዚህ? እኔስ ግማሽ ሰዓት ሙሉ ፀሐይ ልሞቅ ነዋ እዚህ የተገተርኩት? ቀጠሮ የለንም? የምትገርም ወራዳ ነህ ግን ።"

"ማ—እኔ?...ማነው ወራዳው?"

"አዎ ፡ አንተ እራስህ!"

"የማነሽ ጨምላቃ?"

"እረ አንተ ራስህ የማነህ ጨምላቃ? ልክስክስ!"

"ሴትዮ ክብርሽን ጠብቂ! የቀጠረሽ ሰው ካለ እሱን ፈልጊ ። ከእኔጋ ቀጠሮ የለሽም ...አላበድኩም አንቺን የምቀጥረው—ባለጊ!"

ሴትዮዋ በቁጣና በድፍረት ዘነበን ደጋግማ ስትሰድበው ትዕግሥቱ እንዳሞሌ ጨው እየሟሟ ሔዶ በንዴት መላው ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ ። 'ባስታርድ!' ብሎ ከመኪናው ወርዶ ሊያጋጫት ያስብና በቅብዝብዝ አፏ ሎሚ የምታዋርደው መሆኑን ሲያስተውል ደግሞ ወዲያው ሐሳቡን ይለውጣል ። ድንገተኛ ኃፍረት አዕምሮውን ቢዘነጥለው ፡ የመኪና



t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ሞተር እስንሥቶ ከውርደት እጋጣሚው ለመሸሽ ፈለገ ። እሱ ሳያውቃት እሷ የምታውቀው መሆኑ ወዲያው ስለ ከነከነው ማንነቷን ማወቁና የት እንደምታውቀው ማረጋገጡ አስፈላጊ እንደሆነ እምነት ያድርበታል።

"ትውውቃችን የት ነው? ምን አለ ስምሽን ብትነግ ሪኝ?"

"ስሜን አላጠኸውም ፡ ያጣኸው ሌላ ነገር ነው ።"

"ምንድነው ያጣሁት?"

"ያጣኸውማ የፈለከውን ነው ፡ ፊቱኑ በሀይሉን ብንተዋ ወቅ ኖሮ ባልተሳሳትክ ነበር ።"

"ምንድነው ስሕተቱ?"

"መች አጣኸውና!...ዐይኑ— ግቡ ሆኜ ባታገኘኝ ቀጠ ሮህን ትክድ?"

"እንዴ! መቼ ነው የተቃጠርነው? ግልጽ አርገሽ ተናገሪ ።"

"የአራት ቀን ቀጠሮ ተረሳና! እሮብ ለት በ18 00 11 የደወልከው ማንጋ ነው?"

"ኦ! በእርግጥ በዚያ ቁጥር ሥራሽ ሐጐስ የምትባል አውቃለሁ ፡ እሷጋ ደውዬ ነበር ። ልካሽ ከሆነ መልእክቱን ንገሪኝ ። በተረፈ ስለእሷ ባትጠይቂኝ ደህና ነው ።"

"ስለማን ነው የማልጠይቅህ?"

"ስለሥራሽ ።"

"እቂ—ቂ—ቂ—ቂ ጉድ እኮ ነው! ምናለ ባታሥቀኝ?"

"ምን የሚያሥቅ ነገር አለ ፡ ታውቂያት የለም?"

"እኔስ አውቃታለሁ እንዳንተ አልካድኳትም ።"

"እንደማውቃት ታውቀኛለች ፡ እንደምታውቀኝ አው ቃታለሁ ።እንተ ግን እንደምታውቅህ አታውቃትም ለማለት



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ።"

"ሴትዮ ጤነኛም አይደለሽ? ፊት ለፊት ተናገሪ ። የነገረችሽ ነገር ካለ ልወቀው ፣ አለዚያ መሔዶ ነው ።"

"እቂ—ቂ—ቂ—ሥራሽን መች አወቅኩትና ፣ አላወቅ ኩትም እኮ!"

"ባውቃትማ ነው የደወልኩበትን ቀንና የስልክ ቁጥ ሯን ስትነግረኝ ስሟን የጠራሁልሽ ።"

"እኔንስ ታውቀኛለህ?"

"የእኔ እህት ለቀልድ ጊዜ የለኝም ። እስካሁን የቀለድ ሽው ይበቃል!"

"ግዴለህም! እንካ ይኸን መታወቂያ ተመልከተው ።"

ዘነበ እቆመችበት ጥጓት ሊሔድ የመኪናውን ሞተር እንዳስነሣ የሰጠችውን መታወቂያ ተመለከተው ። "ሥራሽ ሐጐስ" ይላል ስሟ የፎቶግራፉም ምስል የእሷው ነው ። በሚሠራበት ድርጅት ውስጥ በምርት ክፍል እንደምትሠራ ጭምር ከመታወቂያው ላይ አንብቦ "የአሁኑ የሥራ መደብሽ የት ነው?" ሲል ጠየቃት ።

በአስተያየቷና በአነጋገሯ እንደ ማፌዝ እያለች ፣ "በአ ዲሱ የሥራ ዕድገት ከምርት ክፍል ተቀይሬ በጥሬ ዕቃ ማደራጃ ክፍል በኃላፊነት መመደቤን መች አጣኸውና! ለነገሩማ ለዕድገቴ ባለውለታ ነኝ ትል የለ?" አለችው ።

ብሽቀትና ግራ መጋባት እየተቀባበሉ ያቆዩት ጕልማሳ እመኪናው ውስጥ እንዳለ ዐይኖቹን አፍጦ ደጋግሞ የሴትዮ ዋን መልክና የፎቶግራፉን ምስል ሲያስተያይ ይቆይና ፣ "ስሚ! ስሚ! የትምህርት ማስረጃሽን እቢሮዬ ይዛ የመጣ ችው ማናት?" ሲል ጠየቃት ማስረጃውን ይዛ የመጣችው ጠንበለል ሴት ትዝ እያለችው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

''የቱን የትምህርት ማስረጃ?''

''በማታ ትምህርት ያሻሻልሽውን የትምህርት ደረጃ የሚገልጽ ደብዳቤ ለደሞዝና የሥራ ዕድገቱ በቅድሚያ አላቀረብሽም?''

''እምም!...እንዲህ ነው ነገሩ? እሱንማ ታፈሰች ናት እቢሮህ ድረስ ይዛልህ የመጣችው ። እሷ መስየህ ኖሯላ በሆነው ባልሆነው እያስታከክ በስልክ ስታባብለኝ ከርመህ ለቅሌት ቀጠሮህ ያበቃኸኝ? ...ወይ ጉድ! ታፈሰችን ጉም ዥሮ ሥራሽን ማባበል? እሷም እንደ እኔው እርም ትሁንብህ! ታፈሰች እንዲህ በቀላሉ አትታፈስም ። የሞቀ ትዳር ያላት ናት ።''



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሰደረው

ሰባት ሰዓት ከኻያ የተቀበላትን ፖስታ በቀኝ እጁ እንጠል ጥሎ ወደ መኝታ ክፍሉ (ዶርሚቶሪ) በፍጥነት አመራ። ፖስታይቱ የተሻሸች፣ የተጐሳቆለች ናት፣ ብዙ ሰዎች በላብ እጆቻቸው እየተቀባበሉ እሱ ዘንድ ያደረሷት ወይነት።

ቀና እያደረገ ያያታል። ሁለት ሦስቴ ይራመድና መሳሳ ቷና መቆሸሿ አስገርሞት ዙሪያ ገባዋን እያስተዋለ ፍጥነቱን ጨመረ። ጥቂት እንደ ተራመደ ወደ ፊቱ አስጠግቶ "የተንገላ ታች ፖስታ" አለ በልቡ፤ ከመተሻሸቷ ብዛት ሸቅብ ሲይዛት ቅሽር ማለቷ ቀርቶ እንደ ጨርቅ ዝልፍልፍ ብትልበት ። በጥንቃቄ አያያዙን አሳመረ ፤ ሊንከባከባት ያችን፣ የተሻሸች ፖስታ።

እመኝታ ክፍሉ እንደ ገባ ወንበር ላይ ተቀምጦ አድራሻዋን ደጋግሞ አነበበው። ለረዥም ጊዜ ሲናፍቃት የነበረችው የወላጆቹ ደብዳቤ ኖራለች። የእጅ ጽሑፉም የታናሽ ወንድሙ የጋሹ እንደሆነ በፊደል አጣጣሉ በአንዴ ዐወቀ። "የምሥራች በይኛ አቦ!" አለ ፖስታይቱን ከመክ ፈቱ በፊት መልዕክቷን ለማወቅ ስሜቱ እየተጣደፈበት።

ወዲያው እንደ ብልት አውጭ ሰተር፣ ሰተር አድርጐ ፖስታይቱን ቀደደና አለፍ፣ አለፍ እያለ ማንበቡን ተያያዘው።

"ውድ ልጄ!" ይላል ከሁለተኛው አንቀጽ በታች ትንሽ ዝቅ ብሎ። "ውድ ልጄ ዓለሙ…የኛን ነገር ተወው።



t.me/OLDBOOKSPDF

የኛ ነገር አይጸጽተንም። የሚጸጽተን፣ ይልቁንም የሚያሳዝነን ያንተው ጉዳይ ነው ። የወይፈኑ ተስፋችን ማረፊያ አይደለህ? ...እንደ ወትሮው በየወሩ የወረቀት መግዣ ታህል እንኳ ገንዘብ ልንልክልህ ባለመቻላችን ብርቱ ኀዘን ተሰምቶናል። በጎዳር ወር የጻፍከው ደብዳቤ ደርሶናል። ከዛሬ፣ ነገ እያልክ የኛን ጤንነት፣ የኛን እርዳታ እንደማትጠብቅ እናውቃለን። ታዲያ ምን እናድርግ ልጄ! እግዜር ሸሸን እንጂ እኛ አልሸሸንህም። አውድማችን በነጥፍ ነው ዕርዳታችን መቋረጡ። ማዕዳችን በራቆት። ለወትሮው በየወሩ የምንልክልህ፣ ከከብቶቻችን አላብ፣ አሊያም እህል ሸጠን ከምናገኘው ገንዘብ እንደሆነ አንተም ታውቀዋለህ። ዛሬ ያ ሁሉ የለም። ስድስቱንም ላሞች ከነኰርማዎቻቸው ድርቅ ጨርሷቸዋል። ከያ ሁሉ ከብት አንድ ጥማድ በሬ እንኳን አልተረፈንም። ከበረቱ የተረፈን አንድ ወፈን ብቻ ቀርቷል። የሙዳይ ልጅ። ጫጉት። እንደ ኦው ያ ከምር ሻኛው ያለ አይምሰልህ። እየሟሸሸ አልቋል። ያ ጫንቃው፣ ያ ድፍን አካላቱ፣ ተመጦ፣ ተመጦ አገዳው ነው የቀረ። ባላየህ ሥጋም እንደ ዋዛ ሲከዳ! ... እሱንስ እንደ ሌሎቹ አልሞኘም። ሞት ሳይሠርቀኝ ያወጣውን ያህል ሸጬ እልክልሃለሁ። ሌላው ቀሪ ነው፣ ባይሆን አንተ ተማር እንጂ!

“ልጄ ዓለሙ፣ አክስትህን ማንያህሉ ከነልጆቿ ዐርፋለች። እርምህን አውጣ። ግን ብዙ አትዘን። ተላመድነው። እኛጋ ኀዘን ቀርቷል። ቀብር ውሎ ቀብር ማምሸት፣ ቀብር ሔዶ ቀብር መቅረት ተላምደናል። እንደ ወትሮው የሞተን የሚያቃብር፣ የቆመን የሚያረዳዳና የሚያደጋግፈው ዕድራችን እንኳ ፈርሷል። የተረፈችን ብትኖር ይችው ማኅበራችን ናት። በእሷ በኩል ተስፋችንን ሁሉ ከወገን ነው የምንጠ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብቅ። እና ላከስትህም ሞት ብዙ አትዘን። እዩራ...እንዲያ ብለህ እንዳታዝን። ልጁ መቻል ነው። ለስንቱ ይታዘናል ብለህ!

"ልጁ ዓለሙ! አንተስ ትምርቱ እንደምን አረገህ? ... በርታ! ብቻ እንዲያ ብለህ ትምርት ቤቱ ሲዘጋ ወዲህ እንዳትመጣ። እኛ ምናልባት ችግሩ ከጠና ቀያችንን ለቀን ሳንሔድ አንቀርም። ለዚያውም ብርታቱን ካገኘን አይደል?.. .ቀያችን የተረገመ ሁኗል። የድርቅ እሳት የበላው፡ የማይታረስ፡ የማያበቅል። ማሳዎችና ጕተራዎቻችን መቀበሪያ ሆነው ምን ቀዬ አለን ብለህ?...ሌላ ቀዬ ሌላ ግድም መፈለግ እንጂ። እስከ ዛሬም እዩህ መከረማችን ደመና አታሎን ነው። ሰማይ ዋሾ ሆኖብን። ለየህ ነው መሔዳችን የማይቀር። እንዳታዝን፡ ሆድህ እንዲባባ አይደለም ይህን ሁሉ መጣፌ። ሁሉንም ነገር በጊዜ ቁርጡን ዐውቀህ፡ አንጀትህን ጠበቅ አርገህ እንድትማር ብዬ እንጂ!

"ተማር!...ተማር! ልጁ ዓለሙ፡ ተማር፡ አንተ እንኳን ተማር እንጂ። ከእንግዲህማ ዐውቀዋለሁ መቼም ያለ ሐሳብ አትዘልቀውም። የእኛ ነገር እያሳሰበህ ብቻ ጥረህ ተጣጥረህ ተስፋችንን ጨብጥ። ዋ! ልጁ ምክሬን አትዘንጋ። እጁ ቢሸሽህ መንፈሴ እንዳይሸሽህ። ይቺ አንድ ዓመት እማይደለች የቀረችህ? አሞትህን ቋጥረህ ጨርሳት። ለተማረ ሰው እኮ ጊዜው ደግ ነው። ሌላው ቢቀር መንግሥት ቀለብህን ማደሪያህን ችሎ በነጻ ያስተምርህ የለም? በእኛ ጊዜ የገበሬ ልጅ ይኸን ሁሉ ድጋፍ መች አየና!

"ሰማህ ዓለሙ ታናሽ ወንድምህ ጋሹ ጥሩ ይጥፋል፡ ገና ከልጅነቱ ጕበዝ ነው" ትል እማልነበር አንተ እንኳ! ይኸው ይህን ደብዳቤ የማስጥፈው እሱኑ ነው። እረጋ ብሎ ሲያዳም



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠኝ ባለየህ! …ብቻ ምን ያደርጋል፤ ትምርቱን አቋረጠብኝ እንጂ። ያኔ መከራ ያልሠራኝ ሥራ አለ ብለህ? 'አባዬ! አባዬ! ወንድም ጋሼን አስተምረህ ፤ አስተምረህ ፤ የእኔ ጊዜ ግን ዝናቡ አቆመብን ። እግዜር አይወደኝም ማለት ነው!' ይለኛል ነጋ ጠባ ። መቼም አፉ እሳት ነው ፤ ታውቃለህ ። ትምህርት እንደ መውደዱ አልቀናውም ። ምን ያታወቃል እግዜር ካለ አንተው ትደርስለት ይሆናል ። እሱንም ፤ እንተንም የዚያ ሰው ካላችሁ ። አደራ! አደራ! እስከ ወዲያኛው አስተምረው …"

ዓለሙ የአባቱን የአደራ ደብዳቤ እንብቦ ሲጨርስ ከጠረጴዛው ወለል ላይ ግንባሩን ለትሞ ተንሰቀሰቀ። ጥልቅ የአባት፣ የቤተሰብና የወገን ሰቆቃ ሕሊናውን ሠርሥሮት ገባ። የወላጅ የዘመድ ፍቅሩ፣ ይልቁንም የአባቱ አያዛህ ባይነት፣ በረኃብ ቃጠሎ እየሟሸሸ እየሟሸሸ ሲሔድ በዐይነ ሕሊና ታየው። የሞት ኩስታራ ግንባር የእናቱን ርኅሩኅ እንጀት ሲቆርጠው፣ የለጋስ አባቱን መዳፍ የትቢያ ምስጦች ሲፈተፍቱት፣ አሞራው ሲረባረብ፣ እታባ እህቱ እወንዝ ወርዳ ባዶ እንስራ አዝላ ስትመለስ …የዘመዶቹ ሰቀቀን ሁሉ ጦር ሆኖ አዕምሮውን ወጋው። ዘመድ አዝማድ በዐይኖቹ ላይ ተግተለተሉበት፣ የናፈቀ ስሜቱን እየቆነጠጡት። ከዚያ ግትልትል ስቃያቸው ጋር በሐሳብ ተስተናገዱለት፣ ኀዘና ቸው ፤ ሰቆቃቸው ፤ ዋይታቸው ፤ እሪታቸው ፤ እረኃባቸው ፤ ጥማቸው፣ ድርቅ ካራቆተው አውድማ ጋር አብሮ ሆኖ።

የዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ያለው የታናሽ ወንድሙ የጋሹ አስተዋይነት፣ ያ ተጫዋችነት፣ ያ ጣቂታነት፣ እየበረደ… እየበረደ ለዐመል ቃህል እንኳ ከንፈር በማያስገልጥ ድባብ ውስጥ ሲያዘግም፣ የጣር ሕይወት ባልጠና ጉልበቱ እየታገ ዘች ፤ ከሞት መንጋጋ ለማፈትለክ ስትፍጨረጨር ፤ እረኃብ

t.me/OLDBOOKSPDF

እርጨቱሟ ደባ ሲያግዷት ...የዓለሙ የናፈቀ ሕሊና ሁሉንም በእርቀት አስተዋለ።

"ምን ሆንሃል! አለው የዱሮ ጓደኛው አሸብር፣ ዓለሙን ሲንሰቀሰቅ አይቶት። መልስም አልሰጠው። ብቻ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ተንሥቶ ወደ አልጋው አመራ። "ምንድነው ነገሩ? ለምን አትነግረኝም ዓለሙ?" አሸብር ደግሞ ጠየቀው። የጭንቀት እንባ እሬቱ ላይ እየኰለኰለ። የዓለሙ ልሳን ግን እራሷን ሸሽጋ መልሱንም ሸሽገች ፡ እንባ ፊታ እንዳያገኝ ፡ በላይ በላዩ እንዲወርድ።

አሸብር ግራ ገብቶት ደርቆ እንደ ቆመ ፡ ዓለሙ ከማንባሩ ዘቅዘቅ አለና ሔዶ አልጋው ላይ በደረቱ እረብ አለ።

"ዓለሙ! ዓለሙ!" አለው አሸብር ወደ አልጋው በርከክ ብሎ። "ደብዳቤውን ላንብበው?"

"ውሰድ፣ አንብበው። ለስድስት ወር እርቆኝ የነበረው የቤተሰብ ደብዳቤ ዛሬ ማንነቴን ሊያወጋኝ መጣ። ዕቅጬን፣ ቁርጡን እንዳውቀው። ልቤ እንዲሁ ቀድሞውንም ፈርቶ ኋል። የትካዜ ጽልመት ሲያጠላብኝ የከረመው ይህንኑ ሊያሳየኝ ኖሯል? በጤናው የአባቴ ደብዳቤ እንደማይጠፋ መች አጣሁት። ቢከፋው ድምፁን አጠፋ፣ ቢርበው እጁን ሸሸገኝ፣ ያንን ለጋስ እጅ አራሽ ቆፋሪውን።"

"በቃህ ዓለሙ፣ እንደ ደብዳቤውን እስካነብ ጠብቀኝ ።"

"እም፣ ዛሬ እኔ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ለመሆን በቅቻለሁ። በአባቴ ወዝ ተማርኩ፣ ወዙ ተንኖ፣ በሥጋውም ተማርኩ፣ ሥጋው ሳሳ፣ አሁን ዓፅሙን ላከልኝ። የወደፊት ብሩህ ተስፋ በእኔ በልጁ ላይ ጥሎ፣ ተምሬ እንዳስተምር፣ ሠርቼ እንድለመልም፣ ከቀዬው እንዳልደርስ እሱ ከተራበበት። አዲስ ቀዬ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንድፈጥር፣ የሚታረስ፣ የሚለማ። የበኩሉን፣ ያቅሟን እንድ ፈጽሞ 'ተማር! ተማር!' ነው የደብዳቤው መልክት ። 'ወንድምህን አስተምር!' ይላል የመሠረተ ትምህርቱ አባቴ እንኳን የትምህርትን ጥቅም ዐውቆ ። ወገንን ለማገልገል ከቤተሰብ ለመጀመር አልታደልኩም ። ያባቴ ሕይወት ያጠራጥረኛል ። ያች የደገፈችኝ ሕይወት ፤ በልታ ያበላችኝ ፤ በልቼ ሳላበላት እሞራ ሊቀጥፏት ነው ። ማን አላትና ያለኔ?"

"ዓለሙ! ዓለሙ! ኀሊስ፣ ምናለ እንደዉ ብታዳምጠኝ!"

"ተስፋችንን ሁሉ ከወገን ነው የምንጠብቅ" አለኝ እኮ አባቴ ። ሕቅ...ሕቅ...እንባ...እንባ...እንባ...

እሸብር የዓለሙ አነጋገር እየከነከነው ደብዳቤውን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ በቁሙ ማንበብ ጀመረ። እያንዳን ዱን እንቀጽ ባነበበ ቁጥር በዓለሙ አዕምሮ ውስጥ የተፈጠ ረው የኀዘን ስሜት በእሱም ሕሊና ውስጥ ይቀጣጠል ገባ። ወዲያው ደብዳቤውን አንብቦ እንደ ጨረሰ ለጥቂት ደቂቃ ዎች ተክዞና ወደ ዓለሙ አልጋ ተጠግቶ፣ "ብዙ ማዘን አያሻህም ዓለሙ! ናፍቀሃቸው እንደ ነበር ፤ ሲሚስተሩን ያለ ዕርዳታ ተቸግረህ እንደ ጨረስክ በእርግጥ ዐውቃለሁ። ሰሞኑን ለአንድ ወር ዕረፍት እንኳ ለምን ወደ አገር ቤት እንዳልሔድክ ብትደብቀኝም ከሁኔታህ ገብቶኛል። አይዞህ ለመሔድ ከፈለግህ መጓጓዣህን እኔው እችላለሁ። ቢያንሰኝ እንኳ ከልጆች እናሰባስባለን" አለው ለስለስ ባለ የማጽናኛ አነጋገር።

ዓለሙ በወዶ ዘማችነት ወደ ወሎ ለመሔድ ማቀዱን ለዩኒቨርስቲው አስታውቆ ጊዜያዊ የስንብት ደብዳቤ እመጣ። ከእሸብርና ከሌሎችም ጓደኞቹ በተሰበሰበለት ገን ዘብ ወደ አገር ቤት ሲጓዝ ከውሃ መያዣው የላስቲክ ኰዳ


t.me/OLDBOOKSPDF

በቀር ያንጠለጠለው አንድም ቦርሳ ወይንም ሻንጣ አልነበረ ውም። በሁለት ቀን ጉዞ የቃሉን፣ የደሴ ዙሪያንና የአምባሰ ልን አውራጃዎች ተሻግሮ፣ በየጁ አውራጃ ውስጥ መርሳ ከተማ ደረሰ። ከአውቶቡስ እንደ ወረደም ወዲያው ብዙም ሳይቆይ ቀሪውን የእግር መንገድ በአቋራጭ እያሳበረ ከሦስ ትና ከአራት ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ከጨሬ ሶዶማ እናት አባቱ መንደር ገባ።

ቀዩው ጭር ብሏል። ፀሐይም የቀን ጠራራዋን መሰሰት ጀምራ ብርሃኗን ድንግዝግዝ አርጋለች። ዓለሙን የናፈቀው የውሻና የከብት ጩኸት እንኳ በአካባቢው ጸጥታ ውስጥ ዝር አልል አለ። ዐልፎ ዐልፎ በየቤቱ ደጃፍ ላይ ቁጭ ቁጭ ካሉ አሮጊቶች በቀር እንደ ወትሮው ውር ውር የሚል ጐረምሳና ጐብዛዝት በአካባቢው አልታይህ አሉት። ብዙዎቹ የመንደ ሬው ቤቶች በራቸው ከፍቱን ሆኖ፣ ከጨፈቃ የተሠሩ የግቢ አጥሮቻቸው ተመነቃቅረውና ፈርሰው ሲመለከት ሞት አድብቶ ገብቶ መንደርተኞቹን እያሉበት አፍኖ ያስቀረ ዐይነት ሆኖ ተሰማው።

ጉጉቱ ወደ ቤቱ ነው። ወደ ወላጆቹ። አባቱን፣ እናቱን፣ እታባን፣ ጋሹን፣ ማሚ ሕፃኑን ጭምር ዐቅፎ መሳም። ናፍቆቱን መወጣት፣ እይዟችሁ ማለት። ከዚያም እያበረታታ እንደ ምንም አውቶቡስ ተራ ወስዶ በያዛት ገንዘብ በማሳፈር ወደ መጠለያ ጣቢያ ማድረስ። ይህ ነበር ልቡ የቸኮለበት ቁም ነገር።

ወደ ቤቱ በቀረበ ቁጥር በሚያስተውላቸው ሙታን የቤት እንስሳት ከፍተኛ የሞት ወረራ በመንደሬው ሕዝብ ላይ እንደ ዘመተ ተረዳ። እርምጃው ግን እየጨመረ ነው። ጠደፍ፣ ጠደፍ፣ ወደ ግራም ወደ ቀኝም እየት፣ እየት፣ ግን እና



t.me/OLDBOOKSPDF

መንደር።

ከወላጆቹ ቤት ወረድ ብላ ከምትገኘው ከአጎቱ ቤት የአጥር ግቢ አጠገብ ደረሰ። "አባይ ጽጌ!" አለ ወዲያው፣ የአጎቱን ሚስት መጣራቱ ነበር። እረጭ ባለ ጸጥታ ውስጥ የእራሱ ጥሪ ተምዘግዝጐ እየወፈረ...እየወፈረ ቢያስተጋባ እንዳች መቅሰፍት የወረደ ያህል መልሶ እራሱን አስደነገጠው። በፍርሃትና በድንጋጤ የሚብረከረኩ እግሮቹን ባለ ችው ጉልበት እያጽናና ወደ ወላጆቹ ቤት ፊጥኖ ገሠገሠ።

ግቢው ወለል ብሏል። ይኸን ጊዜ ለወትሮው መደቡ ላይ አባቱና ጋሹ አንዳንዴም እህቱም ጭምር ሲጫወቱ ያመሹ ነበር። አሁን ግን ማንም ሰው እደጅ የለም። የቤቱ በርና መስኮቶቹ እንደ ተከፈቱ ናቸው። ሁሉ ነገር ተለዋወጠ ቢት፣ ዓለሙ ተጨነቀ ።"አባዬ!" አለ ወደ በሩ መዝጊያ ተጠግቶ። የራሱ ድምፅ ከቤት የውስጥ ግድግዳ ድምፅ ላይ ነጥሮ መልሶ እራሱን ጠራው። "አባዬ...ዬ...ዬ" የእናው ቤት መስተንግዶ ደግሞ ደጋግሞ በዓለሙ ድምፅ ላይ ጮኸበት። ሁለት ሦስት እርምጃ ከበሩ መዝጊያ ወደ ኋላው አፈገፈገና ወደ ኋላም፣ ወደ ፊትም፣ ወደጐንም ግቢውን በዐይኖቹ ፈተሸ። ወዲያው ልቡናውን ወደ ቤቱ ውስጥ ቢወረውር፣ አድብቶ የገባ የሞት ጐምላላ አባቱን፣ እናቱን፣ ወንድሞቹንና እህቱን እስኪጠግብ በልቶ እመደብ ላይ የተንጋለለ መስሎ ታየው።

የፈጠጡ ዐይኖቹ አንዴ ወደ ቤት፣ አንዴ ወደ ማድ ቤት፣ አንዳንዴም አሻግረው ወደ ጀምበር መሹለኪያ እየተን ከራተቱ የማይነጥፉ የእንባ ምንጮች ሆነው ቀሩ። ባናት ባናቱ ማንባት፣ እንባ...እንባ። ድምፅ የሌለው እዬዬ።

ጥቂት ቆይቶም ሐሞቱን ሰብስብ አርጐ ወደ ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመግባት ወደ በሩ ተጠጋ። ግን ድፍን ጨለማ መዝገጊያ ሆኖ አገደው። በመጀመሪያው የጉዞ ቀን ደሴ ከተማ ባደረበት ሌሊት የኤሌትሪክ መብራት በመጥፋቱ ለሻማ መለኰሻ የገዛትን ክብሪት አስታውሶ ከኪሱ በርብሮ አወጣት።

በግራ እጁ ያንጠለጠላትን የውሃ ኮዳ በሩ ላይ አስቀምጦ ክብሪቱን ለኮሰ። በመጀመሪያው የክብሪት ብርሃን አሻግሮ የቤቱን አድማስ ሁሉ ቃኘ። አንድ ፎቶግራፍ ከፊት ለፊት ግድግዳው ላይ ተሰቅሏል። የማን ምስል እንደሆነ ሳይለየው ክብሪቷ ተጠፋና ዳግም ጨለማ እቅመበት ይሸፍነዋል።

"ኳ...ኳ...ኳ..." አደረገው የክብሪቱን ማጥን በክብሪቱ ሰንጨት ለመጫር ። አልሆነለትም ። የመጫሪያው ስንጥሮች ባሩዳቸውን እያሸተቱት እልም ማለት ብቻ ሆነ። አንዳንዶቹ የክብሪት ሰንጨቶች በብልጭታቸው ጨለማውን ገለጥለጥ ያረጉና ተመልሰው ቦታ ይለቁለታል። በስድስተኛው የክብ ራት ጭረት ቤቱ ወገግ ይላል።

ዓለሙ፡ በለኮሰው የክብሪት ብርሃን እየተመራ ቀድሞ ያየውን ፎቶግራፍ ያስተውል ገባ ። የእናቱ ኖሯል። 'የእታባ!' የሚል ድምፅ አሰማ። የናፈቁ ዐይኖቹን ከእናቱ ምስል ላይ ሳይነቅል ብርሃን ተሸንፎ ዳግም ጨለማው በቤቱ ውስጥ ግጥም አለ። ደግሞ ጫረ፡ እራሱንም ቤቱንም ከጨለ ማው ለማላቀቅ። አንዴ ጠፍታ አንዴ በራችለት። ስምንተ ኛዋ ክብሪት መሆኗ ነው። ወዲያው ጠደፍ፡ ጠደፍ ብሎ ፋኖሱን ከሚሰቀልበት ግድግዳ ላይ ሊፈልግ ወደ ጓዳ ገባ። ከበስተቀኝ ካለው ግድግዳ ላይ መጀመሪያ ያባቱን ቀጥሎም የእናቱን ፎቶግራፍ ራቅ ራቅ ብለው ተሰቅለው ያያል።

የናፈቁ ዐይኖቹ የፋኖሱን ነገር እረሱት። የክብሪቷንም ዕድሜ ዘንግተው በአባትና በእናት ምስል ላይ ብቻ ይንከራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቱ ገቡ። የአባቱ ግንባር፣ የአባቱ ጢም፣ የአባቱ አፍንጫ፣ የአባቱ ዐይኖች፣ ‘‘ተማር ልጄ!’’ ሆነ ቋንቋው፣ በኀለሙ መንፈስ ውስጥ ሰርገው ገብተው እኒያን የእንባ ምንጮች ሊያደፈርሱ። አደፈረሱት። የእንባ ጓሎች በጉንጮቹ ላይ ተንደረደሩ። ዱብ...ዱብ...በድፍን ጨለማ ውስጥ ለቅሶ።

ክብሪቱን ለዘጠነኛ ጊዜ ጫረ፣ በብርሃን እየተመራ ፋኖሱን ፈልጎ ለመለኮስ። በራለት። በሦስቱም ማዕዘናት ከማድግዳው ላይ አጣው። በአራተኛው በኩል ከቆጡ ሥር ባሉት ማንጠልጠያዎች ላይ ሲፈልግ ክብሪቷ ጠፋችበት።

በትዕግሥት ሌላ የክብሪት ዕንጨት አውጥቶ ጫረ ። ተቀጣጠለችለት። በቆጡ ሥር ባሉት መስቀያዎች ላይ ሁሉ መፈለጉን ቀጥሎ በመውጫው በኩል ዐይኖቹን ወደታች ሲያዘቀዝቅ ከታችኛው መደብ ላይ ተንጋሎ ያገኘዋል። አፍታም ሳይቆይ የበራችው ክብሪት እንዳትጠፋ ተጠንቅቆ ፋኖሱን ለኮሰው።

ዓለሙ ወላጅ ቤተሰቡን አጥቶ፣ በዚያ አና ቤት ውስጥ ኀዘንና ምሬትን፣ ትዝታና ናፍቆትን፣ ጭንቀትንና ሥጋትን፣ ተከናንቦ ዐልፎ ዐልፎ በሚያፈልቃት ተስፋ ዕረፍት እያደረገ፣ ሌሊቱን ያለ ዕንቅልፍ በትካዜ ተሻገረው።

በማግሥቱ ጠዋት የዋላጆቹን ቤት ዘግቶ፣ የተወለደባትን ምድር እየረገመ፣ መንደሩን ለቆ ወደ መርሳ ከተማ የሚያደርሰውን መንገድ በእግሩ ተያያዘው።

‘‘የኔ አባት?’’ አለ ከመንደሩ ወጣ ብሎ ኮረብታማው ዳገት ላይ ሲደርስ አንድ አዛውንት አግኝቶ።

‘‘አቤት ልጄ፣ አናገርከኝ?’’ አሉት።

‘‘አዎ! ያገሬው ሰው የት ሔደ? ምነው እንደ ወትሮው ሰው አላይ በቀዬው?’’



t.me/OLDBOOKSPDF

“እዬ ልጄ ከየት ነው የመጣኸው? ያለቀው አለቀ። ቀሪውም የበረታ የበረታው እግሩ ወደ መራው አዝግሚል።”

“የዚያ ማዶ መንደር ሰዎች ወዴት ይሆን የሔዱ?”

“ምን አቅጣጫ አለው ብለህ? እግር ወደ ጣለው መሔድ እንጂ! ብዙዎቹ ግን በያ — ታቹን ወደ ውርጌሳ ነው ያዘገሙ። አንዳንዱም በየህ ወደ መርሳ ነው የወጣ፡ ሁለት ቀን ሆናቸው እኮ ቀየውን መልቀቅ ከጀመሩ። ለመሆኑ ከያ መንደር ማንን ታውቃለህ? ማንን ፈልገህ ኑሯል?”

“አቶ አሰበን ያውቁታል?”

“አሰበ — አሰበ?”

“አሰበ ደጉ።”

“አሰበ ደኸ የኛ? የሺበሺ ደጉ ወንድም?”

“አዎ የአብዬ ሺበሺ ታናሽ ወንድም።”

“እኮ — የዚያች የሚችታ የማን ያህሌ ወንድም እማ ይደል? አዬ! አፈር በበላሁ፣ እሱማ እኮ ወደ ውርጌሳ ነው ቤተሰቡን ይዞ ታቹን ያመራ። አንተስ ወዴት መሔድህ ነው?”

“ወደ መርሳ።”

“እንግዲያውማ መርሳ ከዘለክ ባቶቢስ ቅደማቸው፣ ከውርጊሳ መንገድ ታገኛቸው ይሆናል።”

ዓለሙ አዛውንቱ የነገሩትን ሁሉ ከልቡ አድምጦ መርሳ ከተማ በመሔድ በአውቶቡስ ተሳፍሮ ወደ ውርጌሳ ጉዞ ቀጠለ።

አውቶቡሱ ወደ ውርጌሳ ይበራል። የዓለሙ ልብ ግን የኋሊት ተመልሶ ያደገባትን መንደር በሐሳቡ ይጐትታል። እትብቱ የተቀበረባትን፣ ልጅ ሆኖ ጭቃ ያቦካባትን፣ እሸት የበላባትን...ያችን...ያችን መንደር ያለቀጠሮ እንደ ዘመዶቹ


t.me/OLDBOOKSPDF

ጥኋት መሔዱን እያስተዋለ የባባውን እንጀቱን መልሶ አባባው።

በአውቶቡስ ውስጥ ሆኖ ግራና ቀኝ ፀልፎ ፀልፎ የእግር መንገደኞች ማየቱ አልቀረም። በተጓዘ ቁጥር ግን ሕፃናት ታዝለው፣ የደከሙ አረጋውያን ተደግፈው፣ አንዳንዶቹም በየዛፉ ሥር ዐረፍ እንዳሉ የሚያቸው ስደተኞች ቁጥር እየበረከተ በመሔዱ፣ ከአውቶቡስ ወርዶ ወላጆቹን ለመፈለግ ሐሳብ አደረበት።

ብዙም ሳይቆይ አውቶቡሱን አስቁሞ ይወርድና ከሚያዘግሙ ስደተኞች መኻል ተቀላቅሎ የአባቱን፣ የአጐቱንና የእናቱን ስም እየጠራ ማጠያየቅ ጀመረ። ጨርሶ 'እናውቃቸዋለን' የሚል ሰው ጠፋ። አንድ የመንደሩን ባልቴት አግኝቶ ሲጠይቅ የእሱ ወላጆች ቀደም ብለው መንዛቸውን ነግረውት በሩጫ ወደፊት ገሠገሠ።

ጥቂት በተጓዘ ቁጥር ድካሙ እየበረታበት ሔደ። ትላንት ጠዋት ውሎ ፣ ጠሙን ያደረው አንጀት ፣ የእግር መንገድ ያላሸቀው ጉልበት፣ ኀዘን ያቃጠለው ልቡናው... ሁሉም ተነባብረው መላ ሰውነቱን አደነዘዙት። እንደ ስደተኞቹ እሱም ተዳከመ። ተስፋ ግን አልቆረጠም። ያጠያይቃል፣ የእናት አባቱን ስም እየጠራ።

ብዙም ሳይቆይ የመንደሩን ሰዎች በርከትከት ብለው አግኝቶ ስለ ወላጆቹ ቢጠይቃቸው፣ ከእያሌ ሰዎች ጋር ታቹን በእቋራጭ የእግር መንገድ እንደ ሔዱ ስለ ነገሩት ፣ አቅጣጫውን ለውጦ ተስፋ በሰበሰበው ጉልበት በጥድፊያ ይገሠግሣል። እረጭ ባለ ጠራራ ላቡን እየጠረገ ብዙ ተጓዘ።

አንድ አዛውንት ራቅ ብለው ከዛፍ ጥላ ሥር ተንጋለው ያይና በፍጥነት ወደ እሳቸው ያመራል። ከሩቅ ሲያያቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ቈመናቸው ፡ ራስ በራነታቸው የአባቱን ምስለ ያዘለት ።

"አባዬ! አንተ ኖረሃልና እዚህ የወደቅህ?" አለ እንደ ማሽለብ ያላቸውን አባቱን በግራ እጁ ከአንገታቸው ደገፍ ቀና አድርጎ።

"እቶ አሰበ ዐይናቸውን ገልጠው ልጃቸውን እንዳዩት ድንገት ሰውነታቸው ይወራጫል። ለመናገር፣ ለመተንፈስ ከአንደበታቸው ያምጡና መልሰው ይውጡታል። ወዲያው ትንፋሻቸውን ሰብስብ አርገው የልጃቸውን ስም ጠሩ።

"ዓለሙ!"

"አቤት አባዬ!"

"አዬ ልጄ! ምን አመጣህ? አትምጣ ብዬህ አማልነበር በደብዳቤ?...አንተ እንኳ ላትተርፍ ነው መምጣትህ?"

"እኔ ምን እሆናለሁ ብለህ ነው አባዬ!"

"ልጄ ምኔን ልስጥህ ታዲያ ከመጣህ?...እንግዳዬ ነበ ርክ እሱማ! እስቲ ኪሴን ዳብስ፣ ጥሬ ብታገኝ፣ መንገዱን ታግዝሃለች።"

ዓለሙ በአባቱ ደረት ላይ ግንባሩን ጥሎ ተንሰቀሰቀ። የነፈረ አንጀቱን መልሶ አነፈረው። ወዲያው የልጃቸውን ለቅሶ ያስተዋሉት አረጋዊ ልሳናቸውን አነቃቅተው "አዬ — ልጄ! መቻል ነው እንጂ፣ ከሆነ ምን ይደረጋል! ይልቅ ከበረታህ ይህን ግድም ለቀህ ጥፋ። እግርህ እስከቻለ በጊዜ ገሥግሥ። ከሰው ተቀላቅለህ አንተ እንኳ ብትተርፍ። ከሰው የዋለ ሰው ይሆናል። ይልቅ ጉልበትህ ሳይሚሽሽ ቶሎ ፍጠን። የእኔ ነገር እንደሁ አብቅቷል።"

"የለም አባዬ አላበቃም። እንካ ይቺን ውሃ ተጎንጭና እንደ ምንም እመንገድ ዳር ደግፌ ላድርስህ። እሚያልፍ መኪና አይጠፋም። በእሱ እንሔዳለን። ገንዘብ ይዤያለሁ


t.me/OLDBOOKSPDF

እኮ!...ይቺን ውሃ እንደ ምንም ተጉንጭ፡ እንደበትክን ትከፍትልሃለች። ታበረታሃለች። ጉሽ አባዬ እሺ በለኝ።”

አቶ አሰበ በልጃቸው ክንድ ላይ የተንተራሰ ጭንቅላታ ቸውን ወደ ጐን ዘንበል አድርገው፡ “አዬ ልጄ! እታለም እንዲያማይደል የሞተች!”

“እታብ ሞተች?”

“እህሳ!...ሁለት ቀን ውሃ ሳትቀምስ ከርማ፡ ከ የሀ ታች ማነው ስሙ...መንደር ስንደርስ ሰው ውሃ ሰጥቶን እሱን ቀምሳ እኮ ነው የሞተች!”

“እማዬስ?”

“እሷ ማሚንና ጋሹን ይዛ ሔዳለች። ከቻልክ ድረስ ባት። ትረዳታለህ። ትንሹን ልጅ እንኳን ብትይዝላት። የእኔን ነገር ተወው አብቅቷል።”

ዓለሙ በክንዱ እቅፍ የተንጋለሉት የአባቱ ሰውነት ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘው ሲሔድ ተሰማው። “አባዬ! አባዬ!” አለ ዐይኖቹን በአባቱ ዐይኖች ላይ ተክሎ። እንደዋዛ፤ እየጫወተው ከእቅፉ ውስጥ የአባቱን ሕይወት፡ ሞት ሰረቀው ፡ በድናቸውን ትቶለት ።

የነፈረው አንጀቱ ይብስ ነፈረ። የሙት አባቱን ዐይኖች በዐይኑ እያስተዋለ በእውን ይቃኘ ገባ። ሕይወትን፡ ተፈጥሮን መኮነን። ከአፈሩ ቆንጠር ያረግና መልሶ ይረጨዋል... የአንጀት ውስጥ እዬዬ! የማይተፉት፡ የማይውጡት የልብ ውስጥ ነበልባል። እዚያው ነዶ እዚያው የሚያቃጥል። ማልቀስ...ማልቀስ...ማልቀስ...

ዓለሙ ብቻውን ሲያነባ ቆይቶ፡ ልቦናው መለስ ሲል ለት የአባቱን በድን ገላ አፈር ጭሮ ያለብስና እናቱና ወንድሙ ጋ ለማድረስ ጉዞውን ይቀጥላል።

t.me/OLDBOOKSPDF

በጠራራ ፀሐይ ኀዘንና ድካም ያለዘዘው ጉልበት፣ ነፍስን ያህል ትልቅ ዕቃ ተሸክሞ የታቻለውን ያህል ፈጥኖ ተራመደ። የራስን አንጠልጥሎ የሌላን ነፍስ ለማገገዝ፡ የእና ትና የወንድምን የጠወለገ ሕይወት ጨርሶ ሳይደርቅ ለመር ዳት፡ ነፍስን በነፍስ ለማትረፍ፡ ሥቃይን በሥቃይ ለማስወ ገድ ...እናም...ሕይወትን በሕይወት ለማለምለም የዓለሙ ጉልበት በተቻለው ዐቅም ተግተረተረ።

ረባዳውን ምድር ሀልፎ ከረብታማውን ዳገት ሲያያዝ ሰውነቱ ተዝለፈለፈ። ያ — ጉልበት፣ የራሱን አንጠልጥሎ ለሰው ሕይወት አደርስ ባዩ፡ መልሶ እራሱ ጠወለገ። ድካም ብርክን ወልዶ፡ ብርክን ይዞ፡ የወለል የድንጋይ ድጋፍን ይጠይቅ ገባ፡ የዓለሙን ተስፋ ትቢያ ሊጥል። ትግል፡ ከራስ ጋር ትግል፡ የሔድ አልሔድም ዐይነት። ዳገት እያዳላ ድካምን ሲከበው፣ ነፍስ ለነፍስ እሪ ስትል፡ አፋፍ አልቆ ሜዳው ታየ።

እራቅ ብሎ በሜዳው ላይ ሰዎች ጥንድ፣ ጥንድ ሆነው አንዳንዱም ተበታትነው፡ ዐልፎ ዐልፎም እጅብ እንዳሉ ሲያዘግሙ፡ የሚወዛወዙ እንጂ የሚራመዱ አይመስሉም።

ዓለሙ የሰው ዘር በማየቱ ተስፋው ደግሞ ፈካለት። እናቱን፡ ጋሹንና ማሚን የማግኘት ምኞት ቀርቦ ታየው። ተስፋ ያንቃቃው ጉልበት በጉጉት እየታገዘ ፈጣን እርምጃ ፈጠረለት።

ብዙዎቹ ስደተኞች እርቀው ሲጓዙ አንዳንዶቹ ከኋላ ተንጠባጥበዋል። ዓለሙ ግን ወደ እነሱ መሔዱን ትቶ ከቁጥቋጦው አካባቢ ቁጭ፣ ቁጭ ወዳሉት ሰዎች አመራ።

በየቁጥቋጦው ሥር እየዞረ አያቸው፡ ብዙዎቹን ያውቃ ቸዋል። የመንደሩ ሰዎች ናቸው፡ ግን እንዳቸውም ለሚያናግ


t.me/OLDBOOKSPDF

ራቸው መልስ አልሰጡትም። ከፊሎቹ ተኝተው፣ ግማሾቹ ደግሞ በተቀመጡበት ተኮራምተው ሁሉም የየግል የውስጥ ሕመማቸውን ያዳምጣሉ። ከትንሹም ከትልቁም እየተጠጋ ሊያነጋግራቸው ሞከረ። መልስ የሚሰጠው ልሳን ግን ጨርሶ አላገኘም። ብቻ በደከመ ዐይኑ እንደሚያያቸው መልሰው ያዩታል። ተኝተው ወደሚያቃስቱት ዘወር አለ። የሚወራጩም አሉ። ቋቅ የሚላቸውም አሉ። በርከክ ብሎ አንዱን ሲደግፍ፣ ሌላው ተወራጭቶ፣ ተወራጭቶ እንዳወዳደቁ ጸጥ ሲል፣ ወደ እሱ ሲያመራ ከወዲያ ተቀምጦ የነበረው እንዳሸለበው ፍንግል ሲል ተራ በተራ የሕይወትን ሽንፈት ጐበኘ።

ወዲያው ብድግ ብሎ በሙታን ወገኖቹ መኻል ዐይኑን ፈታሽ አድርጐ ይዘዋወር ገባ። የሞትን ድግስ በዐይኖቹ እንባ ሲታዘብ ቆይቶ ድንገት "እንዴ — እማዬ!" አለ ከሌሎቹ ሁሉ ወደ ኋላ ፈንጠር ብለው የወደቁትን እናት አይቶ። ሕፃን ልጅ ታቅፈዋል ዓለሙ ፈጥኖ ሕፃኑን ከእናቱ ጉያ ፈልቅቆ አነሣው። ማሚ ኖሯል። ያልተባረከ ሕፃን ደሙ ረግቷል።

ዓለሙ የእኅቱን፣ የአባቱን፣ የእናቱንና የሕፃን ወንድሙን ሞት ተራ በተራ ቆጥሮ፣ ታናሽ ወንድሙን ጋሹን ብቻ ይፈልግ ገባ። በመንገድ ከአጋጠሙት ስደተኞች መኻል ሁሉ ፈለገው። ነገር ግን አላገኘውም። አንድ የሚያውቃቸው አረጋዊ አግኝቶ "ወደ ውርጌሳ ቀድሟል" ያሉትን በመከተል ወደፊት ገሠገሠ። በዛሉት እግሮቹ ሲራመድ እዚያና እዚህ የመርገጡን ያህል፣ ሐሳቡም ወዲያ ወዲህ ይወራጫል። "ጋሹ እንኳ በተረፈኝ" አለ አባቱ በደብዳቤ "...እስከ ወዲያኛው አስተምረው..." ያሉት የአደራ ቃል ድንገት ትዝ ብሎት።

የመከራው መንገደኛ በሕይወት ሞት እስትንፋስ ሕዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳቱ፡ ያንገዘየ ተስፋን ብቻ እየጐመገጉ ከውርጌሳ ከተማ የመጠለያ ማቢያ ይደርሳል። አቧራ የጠጣው ልብሱና የተን ጨባረረ ጸጉሩ፣ በዐሐይ ንዳድና በለቅሶ የበለዘው ፊቱ፣ ከዚያ የጣር አረማመድ ጋራ የዓለሙን ገጽታ በድርቅ ከተጐዱት ወገኖች ጋር አመሳሰለው።

ከማቢያ እንደ ደረሰ እያሌ ስደተኞች አውቶቡስ ላይ ሲሳፈሩ አይቶ ቀሪውን የቢተሰብ ተስፋ ከጋሹ ሕይወት ላይ እየጓጓ በዝግታ ወደ ሕዝቡ አመራ።

አንድ ቡናማ ሸሚዝ ለብሶ፣ ነጭ ኮፍያ ከአናቱ ላይ ጣል ያደረገ ሰው ዓለሙን አተኩሮ ከተመለከተው በኋላ ጠጋ ብሎት፣ "አንተም ወደ ሠፈራ ማቢያ...ለመሔድ እያሰብክ ነው?" ሲል ጠየቀው እያቅማማ። ዓለሙ በቋመናውም ሆነ በአለባበሱ ከተቀሩት መንገደኞች ለየት ስላለበት ጥርጣሬ አድሮበት ነው።

"አዎ..."አለው ዓለሙ አንገቱን እንደ ሰበረ። "ዘመዶቼን ፍለጋ።"

"በዚህ አካባቢ አልነበርክም ማለት ነው?"

"የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበርኩ። እና..."ሲል ተናግሮ ለመጨረስ አልቻለም። ሲቃ ተናነቀው።

ሰውዬውም ሊያስጨርሰው የፈለገ አይመስልም። የዓለሙ የኀዘን እስትንፋስ ወዲያው በደም ሥሩ ተሠራጨበት። እንደ መሳል ብሎ ጉሮሮውን ከጠራረገ በኋላ፣ "...ውጣ፣ እዚያኛው አውቶቡስ ላይ" አለው በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።

ዓለሙ ከተደረደሩት ሰባት አውቶቡሶች ወንድሙ በአንደኛው ውስጥ ሊሆን እንደሚችል ተስፋ ጥሎ ሰውዬው ወደ ጠቆመው አውቶቡስ ላይ ሔዶ ተሳፈረ።

ጥቂት ቆይቶም የመጀመሪያ ዕርዳታ የሕክምና ሰጭ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዎች ነጫጭ ኮት እንዳጠለቁ ሁለት ሁለት ሆነው በየአውቶ ቡስ ላይ ከወጡ በኋላ፣ ስደተኞቹን የያዙት አውቶቡሶች ኋላና ፊት ተከታትለው ወደ ደሴ አመሩ።

ከውርጌሳ የተነሡት አውቶቡሶች በኢሉባቡር ክፍለ ሀገር፣ በጋምቤላ አውራጃና በፔርቤንጐ የሠፈራ ጣቢያ እስኪደርሱ ጉዟቸውን ቀጠሉ። በሚያርፉበትም ጣቢያ ሕፃን ሽማግሌው በስሜት እየወጣ ይቀበላቸዋል። ምግቡንም መጠጡንም ያቀርብላቸዋል። ሐኪሞችም አንዳንድ ሕመም ተኞችን ለመርዳት ተፍ ተፍ ይላሉ። ባብተው የሚያባቡ ገጾችን ሲመለከቱ አላስችል ያላቸው ሴቶችም ፊታቸውን በነጠላቸው ጋርደው ያነባሉ።

በፔርቤንጐ ራቅ ፡ ራቅ ብለው የተቆረቆሩና በሚገባ የተደራጁ ሌሎች የሠፈራ መንደሮች ቢኖሩም ፡ እነ ዓለሙ ያረፉበት መንደር ግን በቅርብ ጊዜ በባለሞያዎች ተቀይሶ ገና በመዘጋጀት ላይ ያለ አዲስ የሠፈራ መንደር ነበር ።

ከአዲሶቹ ሠፋሪዎች ከፊሎቹ በረድፍ በረድፍ በዕቅድ በተሠሩት ቤቶች እንዲያርፉ ሲደረግ ቀሪዎቹ ደግሞ በጅምር ላይ ያሉት ቤቶች እስኪጠናቀቁ በየድንኳኑ እንዲያርፉ ተደረገ ።

ዓለሙ በሠፈራው የሕክምና ማዕከል ለአምስት ቀናት ሲረዳ ቆይቶ በስድስተኛው ቀን ላይ ተሽሎት መበርታት ይጀምራል ። ከሕመሙ የተሻለው ቢሆንም መንፈሱ ግን አሁንም የጋሹን አድራሻ በማብሰልሰል ሳይጨነቅ አልቀ ረም።

በሰባተኛው ቀን ጠዋት ከድንኳኑ በር ላይ ተቀምጦ በአቅራቢያው የሚያልፉትን ሰዎች ሁሉ እየጠራ የወንድ ሙን ጉዳይ ሲያጠያይቅ ቢያረፍድም ፡ "እናውቀዋለን ወይም



t.me/OLDBOOKSPDF

እዚህ ቦታ ነው” የሚለው ሰው ግን ጨርሶ አላጋጠመውም ። ከምሳም በኋላ ከመኝታው እየተግተረተረ ወደ በሩ ተጠግቶ እንደ ጠዋቱ አላፊ አግዳሚውን ሲያናግር ዋለ ። አዲስ ነገር ግን አሁንም አላገጠመውም ። ጥቂት በቆየ ቁጥር ይበልጥ ጭንቀትና ሥጋት እየወረረው ሔዶ በጥልቅ ምሬት ተንሰቀሰቀ ።

ጊዜው መሸትሸት ሲል ዓለሙ የሕክምና መርፌውን እተኛበት ይወጋና ሐኪም ያዘዘለትን ሽርባ እንደ ነገሩ ቀማምሶ ጥቅልል ብሎ ይተኛል ። የለበሳት አንሶላ ፊቱን ብትጋርደውም ሐሳቡ ግን እንደ ወትሮው እርቆ ነጒዶ ፣ ጋሹን ሊያስስ ፣ ሊያፈላልግ ። መጭት መትረፉን በዐይነ ሕሊና ሊያብላላ ።

ጉበዝ ሰማችሁ! አንድ መልእክት አለን ። እንዴ ወደዚህ አድምጡኝ” አለ በአንድ በጣቢያው የተመደበ የመንግሥት ሠራተኛ ከድንኳኑ በር ላይ ቆሞ ። ዓለሙ የተሸፈነበትን አንሶላ ገልጦ ልቦናውን ወደ ሰውየው አሠማራ ።

“በነገው ዕለት የምግብ ማብሰያ ቤቶች ስለምንሠራ የበረቱና ከአቅማቸው ጠና ያሉ ከየድንኳኑ አንዳንድ ሰዎችን ለሥራው እንዲረዱን እንፈልጋለን ። የሰው ኃይል ስላነሰን ነው እንጂ በእውነቱ ጉልበታችሁ እስኪጠና ሁላችሁም ብታገግሙ ደስታችን ነው። ስለዚህ እባካችሁ አንድ ሰው ከእናንተ ሻል እላለሁ የሚል ምስማር እንኳ ቢያቀብል።”

“የት ግድም ነው?” አሉ አንድ ከበሩ አካባቢ ጋደም ያሉ አዛውንት ።

“እዚህ ታች! ከእህል መጋዘኑ ወረድ ብሎ” ሲል መለሰላቸው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምናለ ታዲያ! ይግእዬ ፡ ይግ ፡ ይግ ። እኔ እበረታለሁ ። ማልጄ እዚያው ነኝ ። የእናንተው ነኝ ። የእናንተን ውለታ እግዜር ይክፈለው እንጂ ይሞ ለዚሁ ኑሯል ። እኔ ብርቱ ነኝ ። አሁን አካላቱም ጠና ብሏል" አሉ እዛውንቱ ከወገባቸው ብድግ ብለው ።

ከዓለሙ መኝታ ፊት ለፊት ፡ ከድንኳኑ መስኮት ሥር የሚገኝ አንድ ከሲታ ጐልማሳም ፡ "እያ — ዝቄ ምን ማለትዎ ነው ፡ ከእርሶ እኔ አልሻልም? ...እኔ ነኝ ከዚህ ድንኳን ሔጄ እምሠራ ፡ እርሶ ተኝተው ያርፉዱ ፡ ማለዳ እንዳይነሡ ፡ ገና ነዎት ። ዕረፍት ያስፈልግዎታል አላሎትም ሐኪም?...እኔ ነኝ የምሔድ ፡ ማያለም እበረታለሁ" አለና ብርቱነቱን ለማሳየት ሽንቀጥ ፡ ቁጢጥ አለ ።

እዛውንቱም መልሰው ፡ "የለም — አዬ! አንተ ጎዘን ፡ በርከቶብሃል ። አንጀትህ በምን ዐቅሙ ይችለውና" አሉት ።

"የለም — የለም! የኒህ ሰዎች ውለታ ከብዶኛል ፡ እግዜርን! እኔ ነኝ ሔጄ እምረዳው ፡ እሊያ መንፈሴ እሺ አይለኝም ። እርስዎ ዕድሜዎትም ገፋ ብሏል ። ይልቅ ይመርቁልን እነህን ሰዎች ። ጸሎትዎን እግዚያሔር ይሰማ ዋል ..."

ዓለሙ ለሥራ ትብብር "እኔ እሻል ፡ እኔ እሻል" እያለ ከእሱ በዕድሜ ጠና ያሉ የረኃብ ግልቱዎች ሲተዛዘኑ አይቶ "እኔ ነኝ ሒያጅ! አብዬም እርሶም አባቴም ገና ያንጀታችሁ ቁስል አልጠገገም ፡ እኔ እሻላለሁ ፡ ደግ ነኝ ፡ ብቻ ማለዳ እንድነቃ ቀሰቅሱኝ" አለ ከተንጋለለበት ቀና ፡ ብድግ ብሎ በክርኑ በመመርኮዝ ።

እዛውንቱ ሽብሽብ ያለ ግንባራቸውን ፊካ አድርገው "እንደ ልጄ አንተ በምን ዐቅምህ ፡ በሽተኛ ማይደለህ? ገና


t.me/OLDBOOKSPDF

መርፌህን መች ጨረስክና?"

ዓለሙ ቀበል አርጎ "ድኛለሁ እኮ  አባቴ! አሁን ደህና ነኝ።" መርፌው የዛሬው የመጨረሻዬ መስሎኛል ። አሁን በጉ ነኝ ፡ በርትቻለሁ" አለ ።

"ቁርጥማቱ አለቀቀኝም ስትል እማልነበር ፡ ቅድም መርፌ ሊወጋህ ለመጣው ሐኪም?" አለ ከድንኳኑ መስኮት ሥር ጋደም ያለው ጉልማሳ አንገቱን ወደ ዓለሙ እግሮች ሰበር አርጎ ።

ዓለሙ "እይ! አሁን ለቆኛል ። ምሽት ላይ እንጂ እሱም ቢሆን ቀን ቀን አይሰማኝም" አለና በተቻለው ሁሉ እራሱን ከሌሎቹ ብርቱ አርጎ ለማለዳ የቤት ሥራ እራሱን መረጠ ።

"እዩ ልጄ! ለየህ ለቁርጥማቱ እኮ ወዲያ ወዲህ ቢሉበት ነው የሚሻለው ። እቺን ሰባት ቀን ተኝተህ እማይደል የከረምክ? እራሱ በሽታ ነው ። እስቲ አሁን በየህ በነፋሻው ወዲያ ወዲህ በልበት ። ደጁ እኮ ጠሐይ መስሏል ፡ ሰዉ እሳት እየሞቀ" አሉት አባውንቱ ወደ ዓለሙ ጠጋ ብለው እንዲነሣ ደገፍ እያረጉት ።

ዓለሙ ተነሥቶ በእግሩ ወዲያ — ወዲህ ማለቱ ፡ አንድም ወንድሙን ለመፈለግ ፡ አንድም ለቁርጥማቱ እንደ ሚበጀው አምኖ የለበሳትን አንሶላ እንደ ተከናነበ በዝግታ ከድንኳኑ ወጣ ።

በየድንኳኑ አካባቢ የሚንቀለቀሉ የእሳት ምድጃዎች ዙሪያ ሰዎች ተኮልኩለው ሲሞቁ አየና እሱ ካለበት ድንኳን ፊንጠር ብሎ እሳት ከሚሞቁት ሰዎች ተቀላቀለ። ከወዲያም ፡ ከወዲህም ፡ ከፊት ለፊቱም ከጐኑም ሊታዩት የሚችሉትን ልጅ ልጆችን በዐይኑ እየመረጠ በእሳቱ ውጋጋን ውስጥ ማንነታቸውን ያሰላስል ገባ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

እፍታም ሳይቆይ ከተቀመጠበት ተነሣና እራት ወዳሉት ድንኳኖች በማዝገም በርከት ያሉ ሰዎች ተሰባስበው ከሚጨዋወቱበት ጠጋ ብሎ ተቀመጠ ። ወዲያው እኒያ ዐይኖቹ ምሪቻቸውን ቀጠሉ ። ማንነትን በሚያይዋቸው ልጆች ፊት ላይ እያፈላለጉ ጥቂት ሲባዝኑ ይቆዩና ተስፋ መቁረጥ ሲሸታቸው ከእንባቸው ፈንጠቅ አርገው ወደ ኳክብት ይበራሉ ፡ እኒያ የእንባ ምንጮች!

በጨወታ መኻል “ተመስገን ማለት ነው! ተመስገን! ተመስገን!” አሉ አንዲት ወይዘሮ የታቀፉትን ሕፃን ዐይን ዐይኑን እያዩ ። ወዲያው ወሬያቸውን ከተል አድርገው “አሁን ...ከዚያች ድንኳን በታች እሳት የሚሞቁት ልጆች የገጠማቸው ዕድል ፡ ዕድል ነው? ያንዳቸውም ወላጆች እኮ የሉም ። የአንዳንዱን ዕድል ሲያዩትስ አለሁ አያሰኝም” አሉ ሴት ወይዘሮዋ አዘኔታ በተመላበት አነጋገር ።

ዓለሙ በሴትዮዋ አነጋገር ተረበሸ ። ያለ እናት ፡ ያለ አባት ዕድሉ ወደ መራው የተሰደደው ታናሽ ወንድሙ ጋሹ በዐይኑ ላይ ድቅን አለ ። ጨሬ ሰይማን ድርቅ ሳያደርቃት በፊት ፡ በዶጉ አዝመራ ጊዜ በአባቱ እሸት ተቀማጥሎ ያደገው ያ የዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ያለው ታናሽ ወንድሙ ፡ ከነጥብቆው በረሃብ ኩርምት ብሎ ሲያነባ በዐይኑ ላይ ተመላለሰበት ።

“እማዬ! እኒያ ልጆች ከየት እንደ መጡ ያውቃሉ?” አለ ዓለሙ ወደ ሴትዮዋ አንገቱን ዘወር አርጎ

“ከየት እንደ መጡ እንኳን አላውቅም ። ባንድ አውቶቡስ ስለ መጣን ግን ወላጆቻቸው እንደ ሞቱ ሲያወሩ ሰምቻለሁ” አሉ ።

ዓለሙ ወዲያው ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ተሰብስበው እሳት ወደሚሞቁት ልጆች አመራ ። ከኋላቸው ቆሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ በአንድ አስተዋላቸው ። አንዳንዶቹም የተቀመጡበት ጉንጫቸውን በጉልበቶቻቸው ላይ ደገፍ አድርገው እሳት እሳቱን ያያሉ ። አንዳንዶቹም ኩርምት ያሉበት ያንቀላፋሉ ። ዓለሙ በእሳቱ ውጋጋን እየተመራ የሁሉንም መልክ መረ መረ ። የሁሉም ፊት ግን ምጥጥ ብሎ ጣረ ሞት በመምሰሉ አንዱን ከአንዱ በቅጡ ሊለይ አልቻለም ። ይሁን እንጂ ከሁሉም ይልቅ ከዳር የተቀመጠው ልጅ የፊቱን አወራረድ የሚያውቀውን የጋሹን ዐይነት ሆነበት ።

ወደ ልጁ ተጠግቶ እፊቱ በርከክ አለና "ጋሹ!" አለው። በእርግጥም ጋሹ ኖሯል ። ጋሹ ግን ሰውነቱን ብቻ ሳይሆን አዕምሮውም ጭምር ተኰሳቁሎ ነበርና ከገጠመው ድንጋጤ በቀላሉ ሊመለስ አልቻለም ።

ይሁን እንጂ ፡ የዓለሙን ድምፅ በተደጋጋሚ ሲሰማ መለስ ባለ ልቦናው ፡ "ወንድም ጋሼነህ?" አለ ዐይኖቹ እንባ እያረገዙና የገጠጠ ፊቱን ለለቅሶ እያጨማደደ ።

"አዎን ፡ ወንድም ጋሼ ነኝ ፡ የሸንኮሬ ልጅ ፡ የእታለማሁ ወንድም ፡ ያንተው የጋሻዬ ወንድም ነኝ ። አሁንስ አወከኝ?" አለው እንደ ማባበል እጆቹን እየዘረጋ ለት።

ጋሹም እንደ መሸሸ ካለበት መለስ ይልና በዓለሙ ደረት ላይ ተስፈንጥሮ ተጣበቀ ። የሁለቱም ዐይኖች ያረገዙትን እንባ በጉንጮቻቸው ላይ አንደረደሩት ። የእንባ ዘለላ ዎች በዐይኖቻቸው ሽፋን እየተጨመቁ ቁልቁል ፈሰሱ ።

ጥቂት እንደ ቆዩም ጋሹም ጭንቅላቱን ከዓለሙ አንገት ሥር ወጣ አድርጎ፡ "ወንድም ጋሼ! ወንድም ጋሼ! እታባ እኮ ሞተች" አለው ።

"አዎን ዐውቂያለሁ" አለ ዓለሙ ደግሞ የጋሹን


t.me/OLDBOOKSPDF

ሎንቅላት ወደ እንገቱ እያጣበቀ ። አፍታም ሳይቆይ ጋሹ እንደገና ፊቱን ቀና አድርጐ "አባዬምኮ ሞቷል!" አለና ተንሰቀሰቀ ።

"ወንድም ጋሼ! ሸንኮሬም እኮ ትሞታለች! ማን ያበላታል! እንደ ራባት… እንደ ራባት… ማሚም ይሞታል!" ጋሹ በለቅሶ ላይ ለቅሶ ከፋኝ አነባ ። ጥልቅ ስሜት እንዘፈዘፈው ።

ዓለሙ የታናሽ ወንድሙ ሁኔታ ኀዘኑን ሁሉ ቀስቅሶበት አብሮት ተንሰቀሰቀ ።

ዓለሙ የወንድሙን የከፋ ለቅሶ እስተውሎ አብሮ ከማልቀስ ይልቅ ሊያጽናናው ሞከረ ። "ሁሉንም እኮ ዐውቂዋለሁ ጋሻዬ! እታልቅስ እንጂ ፡ እኔንም እታሳዝነኝ — እሞትብሃለሁኮ! እሺ?"

ጋሹ ወዲያው ለቅሶውን ቁርጥ አርጐ ፡ "ወንድም ጋሼ! እናንተም ጋ አዲሳባ ዝናብ የለም? ዝናብ የለም? እህል የለም?" አለ ጋሻዬ ።

"ሞልቷል እንዳፈር ነው"

"ታዲያ ለምን መጣህ አንተ እዚህ?"

"አንተን ፍለጋ!"

"እኔ እዚህ መሆኔን ማን ነገረህ?"

"በኋላ እነግርሃለሁ ፡ ብቻ አንተ አታልቅስ እንጂ!"

"እሺ ፡ እንዲያውም ሳለቅስ ፡ ሳለቅስ ፡ ሆዴን ያመኛል ። ደሞ ሐኪሙ እንዳታለቅስ ብሎኛል ። አላለቅስም ።"

ዓለሙና ጋሹ ስለ ወላጆቻቸው እያነሡ ብዙ ተነጋገሩ ። በተለይ ጋሹ ከቤት ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ያጋጠመውን ታሪክ ሁሉ በልጅ እንደበቱ ለዓለሙ አወራለት ። ዓለሙ ይህ ሁሉ ሲሆን እኅቱን ያህል ብርቱ ሰው ፡ እናቱን ያህል ቻይ ፡ ተራ በተራ ሲሞቱ ያንን የረኃብና የጥም ጉዞ ችሎ ጋሹ መትረፉ ፡ እምር ሆነበት ።

"ጋሻዬ! አባዬና እማዬ ሲሞቱ አንተ እንዴት ቻለህ ተረፍክ? እንዲያውም ከትልቅ ሰው ልጅን ነው በጣም የሚርበው ፡ አይደለም?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አባዬ እኮ ምንም አልበላም ፤ ውሃም ስናገኝ ፤ ጥሬም ስናገኝ ለእኔና ለእታባ ነበር የሚሰጠን ። በኋላም አልበላም ሲል ፤ አልበላም ሲል እኪሱ የነበረችውን ብቄላ እኔ ኪሴ ጨመረልኝና እኛን ሒዱ ብሎ ዛፍ ሥር ተኛ ። በየመንገዱ ስንለምን ፤ ስንለምን በኋላ ሽንኩሬም ለእኔ ብቻ ስትሰጥ ፤ ስትሰጥ እሷ ምንም አልበላችም ። እኔን ለሰዎች ሰጠችኝና እመጣለሁ ብላ እታላኝ ቀረች ። ላመጡኝ ሰዎችም ምን እንደ ነገረቻቸው አላውቅም ፤ በጆሮአቸው ነግራቸው ነው እኔን እታላኝ የቀረችው ማማኒንም አሞት ነበር ።"

ጋሼ ያየውን ፤ የገጠመውንና ያለፈበትን የሰቆቃ ሕይወት ሁሉ ለወንድሙ ሲነግረው አምሽቶ ሌሊቱን በዓለሙ ድንኳን ውስጥ አብሮት አደረ ።

በሠፈረው ጣቢያ ውስጥ ሌላ ሁለት ፤ ሦስት ቀናት ዐለፉ ። ዓለሙም የወደፊት ሕይወቱን ጋሼን ከመንከባከብ ኃላፊነቱ ጋር እንደምን እንደሚዘልቀው ያብሰለስል ገባ ። በተለይ የዕረፍት ጊዜው አልቆ የሁለተኛው ሴሚስተር መክፈቻ መድረሱን ሲያስብ ሕሊናው ይበልጥ ይረበሽ ጀመር። "ተማር ልጄ!" የሚለውን የአባቱን ምክር ፤ ጥርሱን ነክሶ በመማር ሊወጣው ይወስንና የጋሼን ጉዳይ ሲያስብ ደግሞ መልሶ ጭንቀት ውስጥ ይዘፈቃል ።

ከብዙ የሐሳብ ውጣ ውረድ በኋላ ለመመረቅ የቀረችውን የአንድ ሴሚስተር ትምህርት ተጣጥሮ በመጨረስ ወንድሙን በተራው የማስተማሩን ግዴታ መወጣት እንዳለበት ያምናል ። በሰፈረው ለሚገኙት የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ሠራተኞችም ችግሩን አማከረ ። የሁሉም አስተያየት ግን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመልሶ በወቅቱ ትምህርቱን እንዲቀጥል ያሳደረበትን ግፊት ሳያመነታ ተቀበለው ።

"ጋሼ!" አለው አንድ ቀን ጠዋት ጥልቅ በሆነ ትካዜ ጉዳዩን ለወንድሙ ለማስረዳት ። "አባዬ እኔን ለማስተማር ምን ያህል እንደ ደከመ ታውቃለህ ። ግን እስከዚህ ደረጃ ተምሬ አሁን ከማቋርጥ አዲስ አበባ ሔጄ እንደ ምንም


t.me/OLDBOOKSPDF

መፈፈረስ አለብኝ ።'' ጋሹ ፊቱን ኮስተር ፡ ፊቱ አረገና ''እኔንም ይዘኸኝ ትሔዳለህ?'' አለው ።

''እይ ጋሹ አንተ ማንጋ ትቀመጣለህ? አዲስ አበባ ዘመድ የለን ። እኔ ዩኒቨርስቲው ውስጥ መንግሥት ያኖረ ኛል። አንተ ግን የምትኖርበት አንድ ዘመድ እንኳ ስለሌለህ የምትበላው አታገኝምና እዚህ ቆርተህ እኔ እስክምፈርስ ጠብቀኝ ።''

''እንደ እማዬ ልታታልለኝ! እምቢየው ። አብሬህ እሔዳለሁ ። አዲስ አበባ እየለመንኩ እበላለሁ ። ደሞ...ደሞ... መንግሥት አንተን ብቻ ነው የሚያኖረው? እኔንም ያኖረ ኛል፣ ጥለኸኝ አትሒድ ።''

''ተው እንጂ ጋሻዬ! መንግሥት እኮ እዚህም አለ ። እንኝህ የምታያቸው እህል የሚሰጡህ ፡ የታመሙትን የሚያክ ሙት ሰዎች ፡ መንግሥት አንተንና እንዳንተ የተቸገሩትን ሁሉ እንዲረዱ የመደባቸው ሰዎች ናቸው ። ያዲሳባም ሕዝብ እዚህ ያለው ችግረኛ ሁሉ ከችግሩ ተላቆ እንደገና ተቋቁሞ ራሱን እንዲችል ጉበዝ ሠራተኛና አምራች እንዲሆን ያለውን ሁሉ በመንግሥት በኩል እያወጣ እየላከ ነው ። መለመን አያስፈልግህም ፡ ሁሉ ነገር እዚሁ ድረስ ይመጣል ፡ እሺ?''

''እምቢዬው! እኔ መማር ነው የምፈልገው ። አባዬ እንድትማር ብሎኛል ። አንተን እንኳን ተማር ብሎህ አልነበረም ያን ደብዳቤ ለአንተ ስጽፍለት ። እሱ ቢኖር ኖሮ እማር ነበር ።''

ጋሹ የአባቱን ትዝታ ደጋግሞ በማስታወስ ትዝታቸው ወደ እዩዩ መራው ። ድምፁን በጥብቆው ሜዳ አፍኖ ተንሰቀሰቀ ። ዓለሙም የጋሹ እንባ ኩለል ብሎ ሲወርድ አይቶ አብሮት ተንሰቀሰቀ ። ወዲያው ትንፋሹን ዋጥ አረገና


t.me/OLDBOOKSPDF

በእንባ የረጠቡ ጉንጮቹን እየጠራረገ ጋሹን ማባበል ጀመረ።

"ጋሹ! ጋሹ! በቃ አታልቅስ! እኔን አታሳዝነኝ ብዬህ የለም? ተው ኋላ እሞትብሃለሁ!"

"እሺ አላለቅስም በቃ ።"

"በል ፊትህን ጥረግ ።"

ጋሹ እድፍ ባቆረፈዳት ጥብቆው ፊቱን ጠረገና ቲማቲም የመሰሉ ዐይኖቹን ወደ መሬት ተከለ ።

"ጋሻዬ ፡ ሁለተኛ ታለቅሳለህ?"

"እሞትብሃለሁ አትበለኝ!"

"እሺ ሁለተኛ አልልህም ። ሞት እኮ ቀርቷል ፡ እኔም አንተም አንሞትም ። እኔም ትምህርቴን ጨርሼ ፡ አንተም ተምረህ አድገህ ገና ብዙ ሥራ እንሠራለን ።"

"እ...እ...እኔን ማ...ማን ያስተምረኛል አባዬ ሞቶ የለም?"

"እንዴ! አይዞህ መንግሥት ያስተምርሃል ። አሁን ይኸ ሁሉ ችግረኛ ሰው የደከመ ሰውነቱ ሲያገግም ፡ እንደገና መሥራት ሲችል እዚሁ ትም/ቤት ይከፈታል ። ትልልቆች እንኳን መሠረተ ትምህርት ይቀጥላሉ ። ከዚያ በቃ! እየተማሩ መሥራት ፡ እየሠሩ መማር ነው ። ያኔ አንተ በደንብ ተምረህ ታድጋለህ ። ትልቅ ሰው ትሆንና ብትፈልግ እንደነኚህ ሰዎች ሐኪም ብትፈልግ ደሞ አይሮፕላን አብራሪ ትሆናለህ ። ብቻ አንተ አታልቅስ ፡ እሺ! በል አሁን እኔ እዛች ቆርቆሮ ቤት ሰዎቹ ጋ ደርሼ እስከመጣ ፊትህን ታጥበህ ቆየኝ ።"

ዓለሙ ያለበትን ሁኔታና የገጠመውን ችግር ሁሉ በሥፍራው ለተመደቡት የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ሠራተኞች በቅድሚያ ያሳወቀ ቢሆንም ፡ አሁን ግን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመሔድ መፈለጉንና የትራስፖ


t.me/OLDBOOKSPDF

ርትም ችግር እንዳለበት አስረድቶ በማግሥቱ ጠዋት ወደ አዲስ አበባ የሚሔድ የድርጅቱ መኪና እንዳለ ተነግሮት በቀጠሮ ወደ ድንኳኑ ተመለሰ ።

ለጉዞ የተነሣው ወጣት መዋያውንና ማምሻውን ባይተዋር ወንድሙን ሲመክርና ሲያባብል አሳልፎ በማግሥቱ ጠዋት ማልዶ ነቅቶ ጋሹን በብሩህ የወይፊት ተስፋ ሊሰናበት

ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው ።

"ጋሹ! ጋሹ! ተነሥ! ተነሥ!" አለው ጉንጮቹን እየዳበሰው ።

ጋሹ ከእንቅልፉ ብንን ከማለቱ "ጥለኸኝ ልትሔድ?" አለ እንደ ማልቀስ እየቃጣው ።

ዓለሙ እሚመልሰውን አጣ ። ብቻ ዝምታን ቋንቋው አርጐ በተከፋ ስሜቱ የጋሹን መራር ስሜት ያነጋግር ገባ ። ማየት ፡ መተያየት ፡ ቋንቋ በሌለበት ትካዜ ማነጋገር ። ግንባርን አፋጦ መንፈስን ከመንፈስ ማከራከር ፡ ከተቀላጠፈ የትካዜ ቋንቋ ። የሁለቱም ዐይኖች በስሜት ዋኙ ፡ በእንባ ተንከሩ ።

ዓለሙ ወዲያው ልቦናውን ኮስተር —ቆጣ አርጐ ፡ በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ ፡ "ጋሻዬ ፡ ልጅነህ ። ግን እንደ ልጅ አትሁን ። የምልህን ነገር ስማኝ ። በማልቀስ የሚሆን ነገር የለም ፡ ቢያንስ ይቺ ዓመት እስክታልቅ መለያየታችን ግድ ነው። ምነው እስከ ዛሬ አዲሳባ ስማር ተለያይተን አይደል ያሳለፍነው?" ይለዋል ቆንጠጥ ባለ አነጋገር ።

"ያኔማ ብቻዬን አልነበርኩም።"

"አሁንስ ይኸ ሁሉ ሰው አብሮህ አይደል ያለው? ቆይ እኔ እዚህ ቀርቼ እስከ ዛሬ የተደከመበት ትምህርት ይቅር ነው የምትለው? አልማር?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሱማ አባዬ ተማር ብሎሃል ።"

"ታዲያ ለምን ሔጀ እንዳልማር ታደርገኛለህ? ዶቹ ዓመት እስከታልቅ እዚሁ ብትቆየኝ ምናለ? ደብዳቤ እጽፍል ሃለሁ ። ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ችግር አይገጥምህም ። አታስብ ፡ እሺ?"

"እሺ ፡ እስከ መንገድ እንኳ አብሬህ ልሒድና እመለሳ ለሁ ።"

"የት ድረስ ትሔዳለህ? እኔ የምሔደው እኮ በመኪና ነው ።"

"ታዲያ ...በቃ...አልሸኝህም ማለት ነው?"

ዓለሙ የሙት ልጅ የሆነውን ጨቅላ ወንድሙን ለሕዝብ አደራ ጥሎ ብሩህ የወደፊት ተስፋ እየታየው አልቅሶ ተሰናበተው ። የጋሹን የገረጡ ጉንጮች ጭምቅ አርጐ ስሞ ከቶዮታ መኪና ላይ ሲሳፈር ይታይበት የነበረው ስሜት በአጠገቡ የነበሩትን የመንግሥት ሠራተኞች ጭምር የወገን ስሜታቸውንና ሰብአዊ ርኅራኄያቸውን ኰንትሎ ኀዘኔታን አጐረፈባቸው ።

ከሠፈራው ጣቢያ የተነሣችው ቶዮታ መኪና ዓለሙ ንና ሌሎች አራት የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ሠራተኞ ችን እንደ ያዘች ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ አዲስ አበባ ገባች ።

"ዩኒቨርስቲው ድረስ እናድርስህ?" አለው መኪናዋን የሚነዳው ሹፌር ወደ ዓለሙ ዞር ብሎ ። ዓለሙ እሺታውን ገልጾ የሰዎቹን ትብብር እያደነቀ ሲጓዝ ፡ "መቼ ነው ምዝገባችሁ?" ሲል ከጐኑ የተቀመጠው አንዱ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ጠየቀው ።

"እሱ ነው ሥጋት ላይ የጣለኝ ፡ ቀኑን አላስታውስ ውም። ዐልፎ ሊሆንም ይችላል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የመመዝገቢያው ቀን ካለፈ አይመዘግቡህም ማለት ነው?"

"አዎን! እንደ ካለፈኝ ያው...ከዓመት በኋላ በተመሳ ሳይ ሴሚስተር ላይ ነው መመዝገብ የምችለው ።"

"ችግር ገጥሞት የሚዘገይ ተማሪም በአስተያየት አይቀበሉም?"

"ፕሮግራማቸው ጥብቅ ነው ። ስለዚህ ሁሉ ተማሪ በወቅቱ እየተገኘ ይመዘገባል ። ከዚያ ውስጥ የወጣ ተማሪ ግን ያው አንድ ዓመት ይቀጣል ።"

ቶዬታዋ በዩኒቨርስቲው የስድስት ኪሎ ካምፓስ በር ላይ እንደ ደረሰች ዓለሙ አንዱን የክፍል ጓደኛውን አይቶ "ቆይ እስቲ ያንን ልጅ የምዝገባውን ቀን ልጠይቀው" አለና ቀኑን እስኪያረጋግጥ እንዲጠብቁት ነግሯቸው ከመኪናዋ ወረደ ። ወዲያው ፈጥኖ ወደ ጓደኛው ተጠጋና የምዝገባውን ማለቂያ ቀን ጠየቀው ።

"አ ዛሬ ሁለተኛ ቀኑ ነው ምዝገባው ካለፈ ። የት ቆይተህ ነው እስከ ዛሬ?" አለው በመገረም አስተያየት ዓለሙን ከላይ እስከ ታች እየቃኘው ።

አንዳች ድንጋጤ በዓለሙ ሕሊና ውስጥ ተፍለቀለቀ ። በሁለት እጆቹ ጭንቅላቱን ይዞ መሬት ፡ መሬት እያየ ከኋላው ወደ ቆመችው ቶዬታ ተመለሰ ።

"እሺ...መቼ ነው?...ምን አለህ?" ሲሉ ጠየቁት በመኪናዋ አብረውት የመጡት አራቱም ሠራተኞች ከመኪናዋ ውስጥ በመስኮት አሰፍስፈው ።

"አ...አ...ዐልፏል ፡ ዐልፏል አለኝ!" አለ ዓለሙ ፡ የገረጣው ፊቱ እየወዛ እየወዛ ሔዶ ላብ ችፍ...ችፍ እያለበት ።

"ዲዛስተር!..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማያውቅ ድንክስ!..."

መልሱን ለመስማት በመስኮት ያቆበቆቡት አራቱም ሠራተኞች የተሰማቸውን ብሽቀት በቁጣ እስትንፋስ ያገል ጹና ወዲያው በማጽናናት የሚረዳበትን መንገድ እንደሚፈልጉ ከነገሩት በኋላ ፡ የስልክ አድራሻና ሀርባ ብር አውጥተው ሰጡት ።

ያቺ ሕይወት ፡ ያቺ ነፍስ ፡ ተጕሳቁላ ፡ ተንገላታ ፡ ከድርቅ መንደር የአባትን የአደራ ዘር ተቀብላ ፡ በአዲስ መንደር የአዲስ ሕይወት ችግኝ ተክላ ፡ ለምልማ እንድታለመልም ፡ ብዙ ተንከላወሰች ። የአባት ቃል ጠብ እንዳይል ፡ አዝላ ልትዘልቅ አደራዋን ፡ ገፍታ ፡ ገፍታ ከበር ላይ ትክዝ አለች ላይቀርላት ።

"ሀለው!" አለ ዓለሙ በማግሥቱ ጠዋት ሦስት ተኩል ላይ ስልክ ደውሎ ።

"አቤት ማን ልበል"

"እቶ ተካበ ይኖራሉ? ዓለሙ ነኝ ።"

"አ! ዓለሙ...አዎን ነኝ ፡ ተካበ ነኝ ። እሺ እንዴት ሆንክ?"

"ተመዘገብኩ! መደበኛው የምዝገባ ቀን ኖሯል ያለፈብኝ ። የሬጅስትሬሽን በመቀጫ ክፍያ የሚካሔደው የመጨረሻው ቀን ምዝገባ ገና ዛሬ ነው የሚያልቀው ..."



t.me/OLDBOOKSPDF

# ወጥመድ የገባ ወጥመድ

ቅዳሜ በቀትር ሰዓት ላይ ከቤቷ ወጥታ የደረሰችበት ሳይታወቅ ባሏንና ዘመዶቿን'ምን ዋጣት?' እያሰኘች ሲያስጨንቃቸው የከረመው የወ/ሮ ስንዱ ጉዳይ ለፖሊስ መርማሪዎች አስቃቂ ዜናን ይዞ ከቀረበ ሰነበተ ።

የ28 ዓመት ዕድሜ ያላትና የአቶ አዳሙ የሕግ ባለቤት የሆነችው ልጅ እግር ወይዘሮ ፡ ባልታወቀና ፍንጩ ባልተጨበጠ ሁኔታ ከቤተሰቧና ከአካባቢው በመሠወሯ 'የት ገባች?' ያሰኝ የነበረው ጥያቄ ውሎ አድሮ 'ማን ገደላት?' ወደሚል የወንጀል ምርመራ መነሻ ተሸጋግሯል ።

በወንድ እንደበቱ እሪታውን እያቀለጠ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ሒዶ ፡ «እሪ የሰው ያለህ! . . . ዘመዶቼን ለመጠየቅ ድሬዳዋ ብሔድ የልጆቼ እናት ጠፍታ ቆየችኝ ፡ ልጆቼ ያለእናት ቀሩብኝ ። የደረሰችበትን አፋልጉኝ . . . » የሚል አቤቱታ ይዞ የቀረበው የሕግ ባሏ አቶ አዳሙ እንኳ ባልታወቀ ሰው ተገድላ በሸራ የተጠቀለለ አስከሬኗ አልባሌ ቦታ ተጥሎ መገኘቱን እንደ ሰማ በድንጋጤ ሕሊናውን እስከ መሳት ደርሶ ነበር ። እያደርም ቢሆን በብርቱ ኀዘን ከፉኛ በመቃጠል በኑሮው ላይ የመንፈስ ሰላም እንዳጣ ነው ።

ጉዳዩን ለማጥናት የተቋቋመው የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቡድን በሻምበል ሲራክ እየተመራ ጠቃሚ የፍንጭ መረጃዎችን በየአቅጣጫው ለመቃረም ትጋት በተሞላበት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሦልትና በረቀቀ ዘዴ ሥራውን ማጣደፉን ተያይዞታል ።

በአፍንጫው በር ከሚገኘው ድልድይ ወደ ደጃች ውቤ መንደር ከሚያወጣው መንገድ በስተግራ ከወንዙ ዳርቻ በሚገኝ ጉድባ ውስጥ በደም የተነከረውን ሸራና ብርድልብስ ከሚችቷ አስከሬን ጋር እንደ ተጠቀለለ አይቶ ለአካባቢው ቀበሌ ማኅበር ጽ ቤት ያስታወቀው አንድ የ11 ዓመት የመንደሬው ወጣት ነበር ። ጉዳዩ ለወንጀል መርማሪው ቡድን ከተገለጸ ወዲህ ወጣቱ የሚያውቀውን ሁሉ እንዲናገር በልዩ ልዩ የምርመራ ስልቶች ሳይጠየቅ አልቀረም ። ይሁን እንጂ የወጣቱን ቃል ተቀብሎ ከመመዝገብና ከአስከሬኑ ጋር በተገኙት ቁሳቁሶችና ከሐኪም ምርመራ በተገኙት መረጃ ዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ጥናቱን ከመቀጠል ባሻገር የወንጀ ሉን ተጠያቂዎች ለማወቅ በጭራሽ አልተቻለም ።

ከሐኪም የተገኘው የምርመራ ውጤት ወ/ሮ ስንዱ ስለት ባለው መሣሪያ ከደረቷ ላይ በመወጋቷ የግራ ሣንባዋ ክፉኛ መቁሰሉን ከማመልከቱም በላይ፡ በግንባሯና በጉን ጮቿ ላይ የተገኘው ነጠብጣብ የደረቀ ደምም በዐይነቱ የሌላ ሰው እንደሆነና በሌላው የሰውነቷ አካባቢና በሸራው ላይ ተጨማልቆ የተገኘው ደም ግን የእራሷ የሟችቷ እንደሆነም ጭምር ያመለክታል ። የወንጀል ምርመራ ክፍሉም ባደረገው የአሻራ ምርመራ የአንድ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው የመዳፍ አሻራን ለመመዝገብ ችሏል ። ታዲያ « የማን አሻራ ይሆን? ማን ይሆን የገደላት ? » ይህ ነበር የወንጀል ምርመራው ዓቢይ የመነሻና የመድረሻ የጥናት ጥያቄ ።

ከአስከሬኑ ጋር በተገኘው በሟችቱ የእጅ ቦርሳም ውስጥ በብጣሽ ወረቀት ላይ ተጽፎ የተገኘው የማስታወሻ መልዕክት ለምርመራው ጠቃሚ መረጃን እንደሚያስጨብጥ


t.me/OLDBOOKSPDF

ተገመተ ። ማስታወሻው በአንድ ማንነቱ ባልታወቀ ሰው የተጻፈና እሱም በአንድ ዕለት ቅዳሜ ወ ሮ ስንዱ ባለቤቷ በማያውቀው ሁኔታ እቤቱ እንድትመጣ የሚገልጽ የምስጢር መልዕክት የነበረው ነው ። ወ ሮ ስንዱ ማስታወሻውን ወደ ጻፈላት ሰውዬ ቤት እንድትሔድ በምስጢር የተጠየቀችበት ዕለትና ከቤቷ ወጥታ የቀረችበት ዕለት ተመሳሳዩ በመሆኑ ማስታወሻውን የጻፈላትን ሰው ለይቶ ማወቁ ስለ ወንጀሉ አፈጻጸም ጠቃሚ መረጃን ያስገኛል የሚል እምነት በሰፊው አሳደረ ። ታዲያ ሰውዬው ማን ይሆን? እንዴ ምንስ ሊገኝ ይችላል?

ሚችቷ ከለበሰችው ኮት የጎን ኪስ ውስጥ ባለዘንግ የበር ቁልፍም ተገኝቷል ።

የመርማሪው ቡድኑ የደም ፡ የአሻራ ፡ የማስታወሻውን ወረቀትና የቁልፉን የመረጃ ሰጭነት መነሻ በማድረግ ምርመራውን ከግብ ለማድረስ ጥረቱን በልዩ ልዩ ስልት ያቀላጥፍ ገባ።

የፍንጭ መነሻዎችን ለማደርጀት የወንጀል መርማሪውን ቡድን ስለ ሚችቷ ሊታወቁ የሚገባቸውን ነገሮች ሁሉ በባለቤቷ ፡ በዘመዶቿና በጓደኞቿ በኩል ለማወቅ እንደ ሁኔታው ዘዴ በተሞላበት መንገድ ሁሉንም እየጠራ ይጠይቅ ጀመር ። በተለይ የሚችቷ ባለቤት አቶ አዳሙ ስለ ሚስቱ ቀደም ሲል ጀምሮ የሚያውቀውን ሁሉ እንዲያስረዳ የመርማሪው ቡድን ጻሐፊ ሻምበል ሲራክ ደጋግመው ማቢያ ድረስ እያስጠሩ ጠየቁት ።

«. . . ስማህ ስለእሷ የሚያስፈልጉን መረጃዎች ስሟን የትውልድ ቦታዋን ፡ ዕድሜዋንና የምትሠራበትን መ ቤትና የመሳሰሉትን ማወቅ ብቻ አይደለም። ፍላጎቷ ፡ ስሜቷ ፡


t.me/OLDBOOKSPDF

ከሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት ፡ ጓደኞቿንና ሌሎችም እሷን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችም ሁሉ ፡ በወግ ተለቅመው ከተጠኑ ለምርመራችን ትልቅ ጠቀሜታ ሊሰጡ ይችላሉ ። በአንተ ግምት እዚህ ግባ የማይባል ነገር ወይም አንተ ቅድም ዋጋ የላቸውም ያልካቸው ጉዳዮች ለእኛ ተለቅመውና ተጨ ምቀው ነው የባለቤትህን ጉዳይ ለማወቅ የፍንጭ መረቡን ሊዘረጉልን የሚችሉት ። ስለዚህ ለጠየኩህ ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢውን መልስ ከሰጠኸኝ መልሶችህ በሌሎች አቅጣጫ ዎች ከምናሽታቸውና ከምንቃርማቸው መረጃዎች ጋር በሚ ያያዙበት ሁኔታ ተያይዘው የምርመራውን እርምጃ ያፋጥኑል ናል ። ገባህ?» አሉ የወንጀል ምርመራው ኃላፊ ሻምበል በእንክሮ ወደ አቶ አዳሙ እያስተዋሉ ።

« ሻምበል ፡ ወዳጆቿንና ዘመዶቿን እርሶ እንዳሉት ተናገርኩ ፡ ጠላቶቿን ግን . . . እኔ የማውቀው ጠላት የላትም » አለ አዳሙም ለስለስ ባለ አነጋገር ኀዘን ያጨለ መው ስሜት እፊቱ ላይ እየታየበት ።

« በቅርቡ እሷ ያስቀየመችው ወይም እሷን ያስቀየማት ወይም ደግሞ በማንኛውም ሁኔታ የተጣላችው ወይም የምትጠላው ሰው የለም? »

«እንዴ መጣላትማ መቀያየምማ ያለ ነው ። ከኔም ከእራሴም ጋር እንኳ የምንጣላበት ብዙ አጋጣሚ አለ ።»

« ብዙ ጊዜ የምትጣሉት በምንድነው?»

« በትዳር ጉዳይ ፡ በንብረት አያያዝ . . . ደሞ ይኸ በእኔና በእሷ መካል ያለ ጉዳይ ነው ፡ ለእናንተ ምን ይረባችኋል? »

« ግዴለም እሱን እንመለስበታለን ። አንተ የሕግ ባሏ እንደ መሆንህ ባሳለፋችሁት ስድስት የትዳር ዓመታት ውስጥ


t.me/OLDBOOKSPDF

መቼም መጣላት ያለ ነውና ስትጣሉ እሷ የምትወስደው እርምጃ ምንድነው ?»

«ታኩርፋለች ፡ መቼም ኩርፊያዋ እንዲህ አይምሰላችሁ ።»

« አንተስ ብዙዉን ጊዜ የምትወስዳቸው እርምጃዎች ምንድናቸው? መቼም የእሷ ጥፋቶች ያበሳጩህ ይሆናል ፡ ያኔ ምንድነው የምታደርገው ? »

«ማ! እኔ ...— እኔ ጫፏን ነክቼው አላውቅም ።» እወቅሳታለሁ ፡ እመክራታለሁ ፡ ከሰማች ሰማች ። ካልሰማችም መቼስ ምን አደርጋለሁ ፡ ልጆቼን አቅፌ ጥቅልል ነው።»

“ከመጋባታችሁ በፊት ከአንተ ሌላ ያፈቅራት የነበረ ወይም ታፈቅረው የነበረ ሰው አለ? ካለስ ማን ይባላል?”

“አይ ከእኔስ ሌላ ማንንም አታፈቅርም ። የሚያፈቅራት ሰው ይኑር አይኑር ግን እማውቀው ነገር የለም ።”

“ከአንተ ሌላ አለማፍቀሯን በምን አወቅህ?”

“እንዴ! እንዴት አላውቅም? ሚስቴ አይደለችም እንዴ? አብሬያት እየኖርኩ ፡ ወልደን ፡ ተዋልደን? ይኸን ያህል ስኖር ስሜቷን ማወቅ ያቅተኝ እንዴ?”

“እንግዲያው ስሜቷን ማወቅ ከቻልክና አንተን ብቻ እንደምታፈቅር እርግጠኛ ከሆንክ ፡ እሷ የምትጠላውንም ሰው ከዘመድም ሆነ ከባዳ ልታውቅ ትችላለህ ማለት ነዋ?”

“አዎ! አዎ! ስሜቷን በደንብ ነው የማውቀው ...”

ሻምበል ሲራክ ስለ ሚትቷ የቀድሞ ይዞታ በግልጽ ከሚታወቁት ጉዳዮች የተለየ አዲስ የመረጃ ፍንጭን በመስጠት አቶ አዳሙ ሊረዳን ይችላል ብለው የገመቱት ፍሬ ሳያስገኝ ቀረ ።

ምርመራው እንደ ቀጠለ ጥቂት ቀናት ዐለፉ ። በመርማሪው ቡድን ዘንድ የወ/ሮ ስንዱን ገዳይ በውል ለይቶ ለማወቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

በልዩ ልዩ አቅጣጫ ተገቢው ጥረት ሁሉ ቢደረግም እንኳን ወንጀለኛውንና የወንጀሉን አፈጻጸም ሁኔታ አጣርቶ ማወቁ አስቸጋሪና የማይደፈር ሆነ ።

በተለይ አስከሬኑ ወንጀሉ በተፈጸመበት ሥፍራ የተገኘ ባለመሆኑ ፣ ከወንጀሉ መፈጸሚያ አካባቢዎች ሊገኙ ይችሉ የነበሩትን ፍንጭ ሰጭ የአካባቢ መረጃዎች እንኳ ለማግኘት አልተቻለም ። ወ ሮ ስንዱ የት ቦታ ተገደለች? በዱር ወይም በመንገድና በገላጣ ቦታ ላይ ወንጀሉ እንዳልተፈጸመ አስከ ሬኑ በጥንቃቄና ዝግጅት ባለው ሁኔታ ከመጣሉ በቀላሉ ለመገመት ይቻላል ። ይህ ካልሆነና ግድያው በቤት ውስጥ ወይም በግቢ ውስጥ ወይም ደግሞ በሌላ በተመሳሳይ ሠዋሪ ሥፍራ ለማወቅ የተፈጸመ ከሆነ ደግሞ በማን ቤትና ግቢ እንደ ተፈጸመ ለማወቅ አለመቻሉ ፣ ከቤቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የወንጀለኛውን ወይም የወንጀለኞቹን ማንነት ለማ ወቅ የሚቻልበትንም ሁኔታ አዳፍኖታል ።

ይሁን እንጂ ፣ የወንጀል መርማሪው ቡድን ያለ ምንም ተስፋ መቁረጥ እያንዳንዳቸውን ከአስከሬኑ ጋር የተገኙትን ቁሳቁሶች ሁሉ በጥንቃቄና በጥልቀት ትኩረት ሰጥቶ ማጥና ቱን ቀጠለ ። በዚህም በሟችቷ የኮት ኪስ ውስጥ የተገኘው ባለዘንግ የበር ቁልፍ በእርግጥ የሟችቷ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ አቶ አዳሙ ተጠርቶ ተጠየቀ ።

"አቶ አዳሙ ይህንን ቁልፍ ታውቀዋለህ?" ሻምበል ሲራክ ነበር ይህንን ጥያቄ ለአቶ አዳሙ ያቀረበው ።

አቶ አዳሙ ቁልፉን በእጁ ቀበል አረገና አንድ ሁለቴ አገላብጦ ከተመለከተው በኋላ ፣ "አላውቀውም " የሚል፡ መልስ ሰጠ ።

«ከዚህ ቁልፍ ጋር የሚመሳሰል ሌላ ቁልፍ በባለቤትህ


t.me/OLDBOOKSPDF

እጅ አይተህ ታውቃለህ?»

«እቢጋ የነበሩት ቁልፎች ሁሉ እኔምጋ አሉ ። የበርም ሆነ የግጥን ቁልፎቻችን ከዚህ ለየት ያሉ ናቸው ። ይህን ያህል የረዘመ ባለ ዘንግ ቁልፍ ሁሉታችንም ኖሮንም ተጠቅመንም አናውቅም ።»

«ከእንተም ሆነ ከባለቤትህ ጓደኞች ወይም ከጐረቤትም ሆነ ከዘመድ የዚህን ዐይነት ቁልፍ ያለው ሰው ታውቃለህ? »

«እኔ እንጃ ! ከዘመድም ሆነ ከጐረቤት እኔ የማውቀው የለም ። ግርማ የሚባል ጓደኛዬ ግን እንደዚህ ዘለግ ያለ የበር ቁልፍ እንዳለው ዐውቃለሁ ። እንዲያውም እርግጠኛ ባልሆንም የዚህ ቁልፍ ቁመትና ቅርፁ ከግርማ ቁልፍ ጋር የሚመሳሰል ይመስለኛል ። »

ከአስከሬኑ ጋር የተገኘው ቁልፍ የሚችሏ ንብረት እንዳይደለ አቶ አዳሙ በሰጠው ቃል በመረጋገጡ የምርመራው ትኩረት በጽኑ በቁልፉ ላይ ዐርፎ ከአቶ ግርማ የመዝጊያ ቁልፍ ጋር በምስጢር ሲመሳከር በእርግጥም ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ ሆኖ ተገኘ ።

አቶ ግርማ ከሚችሏ የኮት ኪስ ውስጥ የተገኘውን ቁልፍ የእራሱ እንደሆነ ቢያምንም በወንጀሉ ተጠያቂ እንዳይደለ ለመግለጽ « የጠፋብኝ መስሎኝ ነበር ። ምናልባት አዳሙን ወደ ድሬዳዋ ለመሸኘት እቤቴ የሔድኩ ዕለት እዛው ረስቼው ሚችሏ ያገኘችውና እኪሷ ያስቀመጠችው ይሆናል » የሚል መልስ ሰጠ ።

በወንጀሉ ምርመራ የተሠማሩት ፖሊሶች የአቶ ግርማ መልስ ስላጠራጠራቸው ፤ በእሱ ላይ ምርመራውን ጠንከር አርገው ገፉበት ። በልዩ ልዩ አቅጣጫ የተገኙትን መረጃዎች የማመሳከሩና የማገናዘቡ ረቂቅ የምርመራ ስልትም ቀጥሎ


t.me/OLDBOOKSPDF

በአስከሬኑ ላይ የተገኙት አሻራዎች ከአቶ ግርማ የመዳፍ አሻራዎች ጋር ተመሳሳይነት ሲያሳዩ በሚችቱ ግንባርና ጉንጮቹ ላይ ተንጠባጥቦ የተገኘው ደም ግን ፡ በሀይትቱ ከአቶ ግረማ ደም የተለየ ሆኖ ተገኘ

ማንነቱ ባልታወቀ ሰው ተጽፎ ወ ሮ ስንዱ እንደ ወጣች በቀረችበት ዕለት እቤቱ እንድትመጣ በምስጢር ቀጠሮ የሚገልጸውና ከሚችቱ ቦርሳ ውስጥ የተገኘው ማስታወሻ የአቶ ግርማ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሁኔታው ሳይነገ ረው በማስታወሻው ላይ የሚገኙትን ቃላትና ሐረጋት ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ሌላ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ በእጅ ጽሑፍ እንዲገለ በጥ ተደረገ ።

በእጁ ጽሑፍ ምርመራው አብዛኞቹ በማስታወሻው ላይ የሠፈሩት ፊደላት የጽሑፍ አጣጣል ጋር ተመሳሳይነት ሲያሳዩ ሁለት ፊደሎች በተለያየ ቃላት ውስጥ የተለያየ አጣጣልን የያዙና ሦስቱ ደግሞ የእሱን አጣጣል የተከተሉ ሆነው በአቀማመጣቸው ግን በአንዳንድ ቦታዎች መጠነኛ ልዩነት ያለባቸው ሆነው ተገኙ ።

የአሻራውና የእጅ ጽሑፉ ምርመራ ውጤት መርማሪውን ቡድን በአቶ ግርማ ላይ ያደረበትን ጥርጣሬ እጅግ ከፍ ሲያደርገው በደም ምርመራው የተገኘው ውጤት ግን፡ በወንጀሉ ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ሌላም ሰው እንደሚኖር ተጨማሪና አዲስ ጥርጣሬን ፈጠረ ።

ጥልቅ ምርመራዎች ደረጃ በደረጃ በስፋትና በረቀቀ ቴክኒክ ይቀላጠፉ ገቡ። እያደር ግን አቶ ግርማ ስለ ወ/ሮ ስንዱ አሟሟት የሚያውቀውን ብቻ አስረድቶ የወንጀሉ ፈጻሚ አለመሆኑን ገለጸ ። -

እንደ አቶ ግርማ አባባል ወንጀሉ የተፈጸመው እራሱ ቤት


t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖ የወንጀሉ ፈጻሚ ወይም ፈጻሚዎች ግን ሌሎች ናቸው ። እራሱም በጭራሽ አያውቃቸውም ። በእራስ ቤት ውስጥ ስው ተገድሎ ጉዳዩን ሳያውቁት መቅረት እንዴት ሊሆን ይችላል? ለፖሊሶች ግራ ያጋባ ነበር ።

«እስከሬኑን በሸራ ጠቅልዬ የጣልኩት እኔ ነኝ » ብሎ ጀመረ ፡ አቶ ግርማ የሚያውቀውን ሲያብራራ ። « የወንጀሉ አፈጻጸም ግን ለእኔውም ባዳ ነው ። አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰንዱ ከሕይወት ወደ ሞት ተሸጋግሯ ስላገኘኋት የአሟሟቷ ጉዳይ እጅግ ምስጢራዊና ተአምራዊ ሆኖብኛል ። አዳሙ ድሬዳዋ በሔደ በሦስተኛ ቀኑ ቅዳሜ ቀትር ላይ ሰንዱ ድንገት እቤቴ መጣች ። ያለወትሮዋ ለምን እንደ መጣች ባላውቅም ፡« ልጠይቅህ ነው » ስላለችኝ ጉዳዩን ችላ ብዬ ከመስተንግዶ ጋር እጫወታት ጀመር ።

« ወዲያው ልክ ከቀኑ 8 ሰዓት ከ30 ላይ ስልክ ከድሬዳዋ ተደወለ ። ደዋዩ አዳሙ ስለነበር ለጊዜው ደነገጥኩ ። መደንገጤን እንዳያውቅ ተገነናንቼ ላናግረው ሞከርኩ ። አዳሙን ከድሬዳዋ የመጋረጃ ጨርቅ ይዞልኝ እንዲመጣ ነግሬው ስለ ነበር ፡በአጋጣሚ ድሬዳዋ እንደሚቆይና የመጋረ ጃውንም ጨርቅ በሚያምነው ሰው በኩል የላከልኝ መሆኑን ነግሮኝ በዚሁ ስልኩን ዘጋሁ ።

« በግምት ዘጠኝ ሰዓት ከኻያ አካባቢ በድጋሚ ስልክ ተደወለ ። ደዋዩ ጨርቁን እንዲሰጠኝ አዳሙ የላከው መልዕክተኛ ነበር ። ስሜን ጠርቶ ጨርቁን ወዲያው ሔጄ እንድቀበለው ባቡር ጣቢያ በሩ ላይ ለምልክት ቢጫ ባርኔጣ አድርጎ እንደሚጠብቀኝ ነገረኝ ። እኔ እንኳን ሰንዱን ባዶ ቤት ጥያት ለመሔድ ስላልፈለግሁ በወቅቱ ልመጣ እንደማልችል ለመልክተኛው ብነግረውም ፡ ከአንድ ሰዓት

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ወይ ደብረ ዘይት በአውቶቡስ እንደሚሔድና ሌላ ጊዜም በጭራሽ ላገኘው እንደማልችል አስታወቀኝ ። በጉዳዩ አጣዳፊነት ስንዱን እቤት ትቻት ሰበር ወይ ባቡር ጣቢያ ሔድኩኝ ።

« . . . ይገርማችኋል ! አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፊዴሮቹን ይዤ እቤቴ ስመለስ ስንዱ በአልጋዬ ላይ በደም ተበክላ አገኘኋት ። ቆልፌው የሔድኩት በር ስመለስም እንደ ተቆለፈ ነበር ። ብቻ ምን ሰይጣን እንደገባ አላውቅም በዝግ ቤት ውስጥ በደም ተጨማልቃ አገኘኋት ። ሁኔታውን ለማመን ስላዳገተኝ መስኮቶቼንና ክርኒሶቼን ሳይቀር ፈተሽኩ ። ሁሉም እንደ ነበረው ዝግ ነው ። እንደ ነበረችው ያላገኘኋት ስንዱን ብቻ ነበር ። አገላብጬ ሰውነቷን አየሁት። ከደረቷ በቀር ሌላው ሰውነቷ አልቆሰለም ።

« ነዘንም ድንጋጤም መንፈሴን ስላዋከቡት ለጊዜው የማደርገውን አላውቅም ነበር ። ቀኑ እየመሸ ሲሔድ ምንም እንኳን የወንጀሉ ፈጻሚ ባልሆንም ከተጠያቂነት ለመዳን የምችልበትን ዘዴ ማብሰልሰል ጀመርኩኝ ። የመጣልኝ ሐሳብ የወንጀሉን ደብዛ ከቤቴ ማራቅ ነበር ። አስከሬኑን ከነቦርሳዋ በደም በተነከረው ብርድ ልብስና በሸራ ጠቅልዬ ወደቆ የተገኘበት ሥፍራ ሌሊቱን በጭንቃቄ ለመጣል ችያለሁ ። በተረፈ በፍጹም የወንጀሉ ፈጻሚ አይደለሁም ። ከደሙ ንጹሕ ነኝ ።»

ቃሉ ምን ያህል እውነተኛ እንደሆነ ባይታወቅም አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአቶ ግርማ ቤት ፡ አቶ ግርማ በሌለበት ሁኔታ የሟችቱ ሕይወት ማለፉ ሆን ብሎ በተዘጋጀና በተቀናበረ ሁኔታ ወንጀሉ እንደ ተፈጸመ በመርማሪዎች ዘንድ ብርቱ ግምትን አሳደረ ። ምናልባትም የወ ሮ ስንዱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገዳይ በወቅቱ አቶ ግርማ ቤት የምትገኝ መሆኗን ያወቀና አቶ ግርማም የመጋረጃ ጨርቁን ለመቀበል ወደ ባቡር ጣቢያ መሔዱን ሀውቆ ፣ እግር ጠብቆ አደጋ ያደረሰ የቅርብ ዐዋቂ ሰው እንደሚኖር ከፍተኛ ጥርጣሬ ፈጠረ ። ጥርጣሬው በምርመራ ሲብላላ የወንጀሉን ምስጢራዊ አፈጻጸም እያገላው ከመምጣቱ በቀር ወንጀለኛውን በይፋ የሚያሳውቅ ምንም ማስረጃ አልተገኘም ።

አቶ ግርማ ባቡር ጣቢያ ሲሔድ እግር ጠብቆ ገብቶ አደጋ ያደረሰ ሰው ካለ የተቆለፈውን ቤት እንዴት ከፍቶ ሊገባ ቻለ? ወንጀሉን ከፈጸመስ በኋላ እንደ ምን ቤቱን እንደ ነበረ ቆልፎ ሊሔድ ቻለ? ከመዝጊያው ቁልፎች አንዱ በሌላ ሰው እጅ የሚገኝበት ሁኔታ እንዳለ አቶ ግርማ በብርቱ ተጠየቀ ። መዝጊያው ከተሠራ ጀምሮ ያሉት ሁለት ቁልፎች ብቻ እንደ ሆኑና ከነሱም ውስጥ አንዱ በእጁ የሚገኘውና ሌላው ከሚችቱ ኮት ኪስ ውስጥ የተገኘው መሆኑን ደጋግሞ ከመናገር በቀር አቶ ግርማ አዲስና ያልታወቀ ምስጢር ሊያወጣ አልቻለም ። እንግዲያው ማን ከፍቶ ገብቶ ገደላት? አሁንም ፖሊሶችን ግራ ያጋባ ነበር ።

ወ/ሮ ስንዱ ራሷን ገድላ ይሆን? እንደ ምንስ እራሷን በስለት ልትጠፋ ትችላለች? አዲስ ጥርጣሬ ቢፈጠርም ከሚችቱ ፊት ላይ የሌላ ሰው ደም መገኘቱ ጥርጣሬውን ወዲያውኑ አከሸፈው ። እንግዲያው የወንጀሉ ፈጻሚ እራሱ አቶ ግርማ ሆኖ ምስጢሩን ለመጠበቅ የፈጠረው ዝባዝንኬ መሆን አለበት የሚለው የቆየ ጥርጣሬ ዳግም አገርሽቶ በመርማሪው ቡድን ዘንድ በቅጡ ይብላላ ጀመር ።

በሚች ፊት ላይ የተገኘው የሌላ ሰው ደምም ፣ ምንም እንኳን የአቶ ግርማ ባይሆንም ዞሮ ዞሮ ሌላ ግብረ አበር ሊኖር



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚችል ከመጠቆሙ በቀር የአቶ ግርማን ንጽሕና ሊያረጋግጥ አይችልም ። ስለዚህም በአቶ ግርማ ላይ ምርመራው ያለማሰለስ በከፍተኛ ደረጃ ቀጠለ ።

አቶ ግርማ ፡ «መጋረጃውን ባቡር ጣቢያ የሰጠኝ መልዕክተኛ በአለባበሱ የጠበኩት አልነበረም » ማለቱና «መልዕክተኛው ዐሥር ብር ተቀበለው በሎኛል አዳሙ ብሎ ከተቀበለኝ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት በመሔድ ፋንታ ወደ አራት ኪሎ መጣፈሩ ፡ በማግሥቱም ጠዋት አራት ኪሎ ባንክ ቤቱ ፊት ለፊት መንገዱ ዳር ቆሞ አይቸዋለሁ» ማለቱ ምርመራውን በአዲስ አቅጣጫ ለማራመድ አዲስ መቆና ጠጫ ሆኖ አገለገለ ።

በመልዕክተኛው ላይ የታየው ዋሾነት ከምን መጣ? በሐሰት ወደ ደብረ ዘይት እሔዳለሁ ብሎ አቶ ግርማን በጥድፊያ ወደ ባቡር ጣቢያ ሔዶ ጨርቁን እንዲቀበለው ያደረገበትስ ምክንያት ምንድነው? እነዚህ ጥያቄዎች ናቸው ጉዳዩን የምስጢር ቋጠሮ እንዳለበት አርገው ብርቱ ጥናትን የጠየቁት ።

በዚህም በአንድ በኩል መልዕክተኛውን በአቶ ግርማ አማካኝነት በሥውር ፈልጎ ማግኘት ፡ በሌላ በኩል ደግሞ መልዕክተኛው ተገኝቶ ለምርመራ እስኪቀርብ ድረስ አቶ አዳሙን በዐይነ ቁራኛ መጠበቅና መልዕክተኛው ሲገኝም አቶ አዳሙን ጠርቶ ቃሉን እንዲሰጥ ማድረግ የመርማሪው ቡድን አጣዳፊና መንታ ተግባራት ሆኑ።

አቶ አዳሙ በዐይነ ቁራኛ እየተጠበቀና መልዕክተኛ ውም ሊገኝ ይችላል ተብሎ በሚገመትበት አካባቢ ሁሉ ቀንም ሆነ ምሽት በስውር ሲፈለግ ሁለት ሳምንታት አለፉ ።

ልክ በ17ኛ ቀኑ መልዕክተኛው ቅድስት ማርያም


t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተክርስቲያን አካባቢ መንገድ ሲያቋርጥ ተገኝቶ ተይዞ ለምርመራ ቀረበ ። አቶ አዳሙን ቀድሞውንም ጠርቶ መጠየቁ የታሰበ ቢሆንም በተለይ ከመልዕክተኛው የተገኙት አዳዲስ መረጃዎች ተፈላጊነቱን እጅግ አበረቱት ።

አዳዲስ መረጃዎች መመንጨት ጀምረው ፣ ደረጃ በደረጃ ምርመራው መቋጠሪያ ዕልባት ወደሚያገኝበት ግቡ በፍጥነት ተራመደ ። የወንጀሉን ምስጢራዊነት በይፋ የገታ ቃልም በመጨረሻው ላይ በአቶ አዳሙ አንደበት ይግተለተል ገባ ።

«...በእርግጥም ድሬዳዋ ለመሔድ ሐሳብ ነበረኝ ። ሆኖም ግን የባለቤቱና የጓደኛዬ የግርማ ሽረባ ሊያስኬደኝ ቀርቶ ሰላም ሊሰጠኝ አልቻለም ። ሰላም! . . . ሰላም ካጣሁ ዓመት አልፎኛል ። የአዕምሮዬ ሰላም መደፍረስ የጀመረው ስንዱ በእንቅልፍ ልቧ ደጋግማ የግርማን ስም መጥራት ከጀመረች ወዲህ ነው ። በተፈጥሮዋ በእውን ያወጋችውን በቅዠት መድገሙ አብሯት ያደገ መሆኑን ወላጆቿም ይናገራሉ ።

« ከተጋባን ጊዜ አንሥቶ በእንቅልፍ ልቧ የምትናገረውን ዘወትር እንድነግራት ትወተውተኝ ነበር ። እኔም በቅን ልቤ እስከ አምና ድረስ ከአንደበቷ የሰማሁትን ሁሉ ከመንገሬ በቀር የደበቅኋት ነገር አልነበረም ። ከአምና ወዲህ ግን የገዛ ጓደኛዬ ባልተለመደና ባልጠበቅሁት መንገድ የባለቤቴ የቅዠት ጓደኛ እየሆነ በመምጣቱ ፤ የሰማሁትን በልቤ ቀብሬ በምስጢር ስታዘብና ስገረም ቆየሁ ።ይህ በባለቤቴና በጓደኛዬ ላይ የተፈጠረው የመጀመሪያው ውስጣዊ ጥላቻዬ ምንጭ ነበር ።

« በዚህ ብቻ አላበቃም ። ልቤን ውስጥ ውስጡን


t.me/OLDBOOKSPDF

እያቃጠለ ስላም የነሣኝ ሴላም ስውር ደባ ገጠመኝ ። ብዙ ጊዜ ከሥራ መልስ እቤት ሳለሁ ። ስልክ ይደውልና ስልኩን እንሥቼ «ሀሎ ! » ወይም «እቤት !» እንዳልኩ ወዲያው ስልኩ ይዘጋብኛል ። ይህ ተደጋግሞ ሲገጥመኝ ጥርጣሬዬ በጣም አደገ ። ስንዱ ስልኩን ባነሣች ጊዜ ግን ፈጽሞ ይህ ዐይነቱ ነገር ገጥሟት አያውቅም ።

« አንድ ቀን እንደ ተለመደው ስልክ ተደወለ። ስንዱ አልነበረችም ። ወዲያው የስልኩን የመነጋገሪያ እጀታ እንሥቼ ምንም ምላሽ ሳልሰጥ ጆሮዬ ላይ ይቅኝ ደዋዩ እስኪናገር ጠበቅሁት ። ፈጥኖ የፈለገውን ሰው ሊጠራ ወይም ድምፁን ሊያሰማ አልቻለም ። እኔ ድምፄን ሳላሰማ የእሱን ድምፅ ለመስማት እንዳደባሁ ፡ እሱም ድምፁን ሸሽጎኝ የእኔን ድምፅ ቀድሞ ለመስማት በዝምታ ጥቂት እንደ ቆየ «ማን ልበል?» የሚል ጥያቄ አመለጠው ። መልስም አልሰጠሁት ፡ ድምፁ ግን የማውቀው የግርማ ነበረ ። ወዲያው ዝምታዬን እንዳወቀ ስልኩን ዘጋው ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ለአንድ ወር ያህል በዚህ ዐይነቱ መንገድ እቤቴ ስልክ ደውሎ አያውቅም ። ምናልባት እኔ በሌለሁበት ደውሎ ሊሆን ይችላል ። እርግጠኛ አይደለሁም ።

« ውስጥ ውስጡን እየገነተርኩ መገንተሬን ሳላሳውቅ ፡ ሥውር ግንኙነታቸውን ወጥመዴ ውስጥ ለማስገባት ዘዴ ሳብሰለስል አያሌ ቀናት ዐለፉ ። ባደረኩት ከፍተኛ ጥንቃቄ ስንዱም ሆነች ግርማ መጠርጠሬን እናዳልጠረጠሩ የኋላ ኋላ ባዘጋጀሁላቸው ወጥመድ አረጋግጫለሁ ።

«ከአንድ ወር በኋላ ያ ተጣርቶ ድርግም የሚለው የኮንትሮባንድ የስልክ ጥሪ ተመልሶ መጣ ። እኔ ባለሁበት ስንዱ የስልኩን እጀታ እንዳነሣች ‘አይቻለኝም!’ ብላ ስል


t.me/OLDBOOKSPDF

ኩን መዝጋቷን ልቤ እያወቀ የመጠቋቆሚያ ዘዴ አርገው ተጠቀሙበት ። ስልክ እንደሚጮህ እኔ ካለሁኝ 'አይቻለኝም !' የሚል መልስ መስጠቷ ' አዳሙ ' አለና ማውራት አንችልም ስልኩን ዝጋው ማለት እንደሆነ ለክትትል የተሠማራው ንቁ ልቤ መረዳት አላዳገተውም ።

«በሌላም ቀን ስልኩን እንዳነሣሁት ጆሮዬ ላይ ድር ማም ማለቱ እንደገና ገጥሞኛል ። እሷም ብትሆን እኔ በአቅራቢያዋ ካለሁ 'አይቻለኝም' ብላ ስልኩን መዝጋት ፣ እራቅ ካልኩ ወይም መኝታ ቤትም ከሆንኩ ደግሞ ባጭሩ በሹክሹክታ ማናገር ጥበብ አርጋ ደጋገመችው ። ልቤ ያውቀዋል ፣ ማወቁን ግን ሁለቱም አያውቁትም ።

« ግርማ በቤት እያስደወለ ስንዱ ስትቀርብለት እራሱ የሚያነጋግርበትንም ጥበብ ተጠቅሟል ። ሁሉንም ስለማወ ቀው ስውር የበቀል ወጥመዱን ማመቻቸቱ ብቻ የተግባር ምርጫዬ ሆኖ በአዕምሮዬ ተወጠነ ።

«ግርማን በጓደኝነቱ እንደ ተለመደው እኔው ቤት ምሳ ወይም እራት ጋብዘነው ወይም እሱ ቤት ተጋብዘን በምናሳል ፋቸው የጭውውት ጊዜያት ከስንዱ ጋር በስውር መልዕክት የሚለዋወጡበትም ጥበብ ተደጋግሞ ተከሥቶልኛል ።

«በአዕምሮዬ ተብላልቶ የከረረውን ወጥመድ በድርጊት መዘርጋት የጀመርኩት ድሬዳዋ ለመሔድ የነበረኝን የቀድሞ ፍላጐት ለስንዱም ሆነ ለጓደኞቼ ሁሉ በቅድሚያ በማሳወቅና በማስጠራት ነበር ። የእኔ ድሬዳዋ መሔድ ስንዱንም ሆነ ግርማን እንደሚያስደስታቸው ዐውቃለሁ ። ቀኑ እስኪደርስ ግን ደስታ አልነፈግኋቸውም ። በተስፋ ረኩበት ።

«እሱም ሆነ እሷ፣ የእኔን ወደ ድሬዳዋ መሔድ በጉጉት እየጠበቁና ሐሳቢንም እንዳልቀየር የዘመድ ጥየቃን እስፈላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጊንት በሆነው ባልሆነው እያስታከኩ ሲያስተምሩኝ ቆይተው የወጥመዷ ሁለተኛው የእርምጃ ቀን ደረሰ ።

«ረቡዕ ጠዋት ለሐሙስ የባቡር ጉዞ ከስንዱ ጋር አብረን ባቡር ጣቢያ ሔደን ቲኬት ቆርጠን መጣን ። ለግርማ በእርግጥም ድሬዳዋ መሔዷን ያለምንም ጥርጣሬ እንዲያውቅና እንዲረዳ ቲኬቱን ማሳየት ስለ ነበረብኝ ፡ የኸው ደቻለኝ ዘንድ በዕለቱ ለእራት እቤቱ እንዲመጣ አስቀድሜ በጠራሁት መሠረት ሰዓቱን ጠብቆ መጣልኝ።

«እራት እየበላን ሳለን፡ ከድሬዳዋ ምን እንዲመጣለት ጠየቅሁት ። ይህ ሦስተኛው ለወጥመዷ አስፈላጊ የሆነውን ጉዳይ የሚያመቻች ተግባሬ ነበር ። ‘ የመጋረጃ ጨርቅ ጉሽ ! አደራህን እንዳትረሳ ’ አለኝ ፡ የሚያላምጠውን ጉርሻ በውሃ እያወራረደ። ‘እንግዲያውስ ከመኝታ ልብስህና ከአልጋ መብራትህ ቀለም ጋር የሚስማማ ቀይ የመጋረጃ ጨርቅ ላምጣልሃ?’ አልኩት ፡ የአፌንም የልቤንም አዋህጄ መናገሬ ነበር ። አልገባውም ። ደማቅ ቀለም እንደማይሻና እንደማይወድ ብቻ ነገረኝ ።

« ገበታው ተነሥቶ ሥፍራውን ጨዋታና የቢራ ጠርሙሶች እንደ ተኩት የቆረጥኩትን ቲኬት እንደ ቀልድ ለማሳየት ዕድል አገኘሁ ። ግርማ ቲኬቱን በሚገባ አየው ። የመሔዷን ዋስትና አየው ማለት ነው ። ላይ ላዩን በጨዋታ ብሥቅም ውስጥ ውስጡን ግን በልቤ እበግናለሁ ። እሱም በልቡ ‘እዚያው ያስቀርህ !’ የሚለኝ ይመስለኛል ። ብቻ በልቡ እንደሚረግመኝ በልቤ እረግመዋለሁ ።

« በዚያ የጨዋታ ምሽት ስንዱ ወዳጇን ፡ እኔም ጠላቴን ፡ እሷ ከአንጀቷ ፡ እኔ ከአንገቴ ስናጫውተውና ስናስተናግደው ቆይተን ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ እኔ ተሰናብቼው ፡ እሷ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደኅና እደር ! ብላው ግርማን ሸኘነው ። በልቡ ለአዋሽ በረሃ እንደ ተመኘኝ ፡ እኔም ለወጥመዱ መረብ ተመኘሁት ።

«ከደጅ ግርማን ሸኝተን ስንመለስ እኔ ወደ ሳሎን ቤት ሳመራ ስንዱ ሻንጣዬን ልታዘጋጅ ወደ መኝታ ቤት ገባች ። የጀመርኩትን በብርጭቆ የተቀዳ ቢራ ጨርሼ ሌላ ለመድገም የጠርሙስ መክፈቻውን መፈለግ ጀመርኩኝ ። ከጠረጴዛው ላይ ባጣው በወንበሮቹና በወለሉ ላይ ሳይቀር አጉንብሼ ፈለኩት። አላገኘሁትም ። ቀና ስል ከስልኩ መቀመጫ አጠገብ ካለው ወንበር ላይ የስንዱን ኮት ተሰቅሎ አየሁት ። ቀደም ሲል ጨዋታው በደራበት ሰዓት ለብሳው ስለነበር ምናልባት እኪሷ ውስጥ ከትታው ይሆናል በሚል ወደኮቱ አመራሁ ።

«በግራ የኮቱን ኪሷ ውስጥ እጄን ከተትኩ ። ጣቶቼ መክፈቻውን ሳይሆን ብጣሽ ወረቀት ይዘው ወጡ ። ወረቀቷ ተጣጥፋለች ። ገላልጬ በላይዋ ላይ የተጻፈውን ማስታወሻ ማንበብ ጀመርኩ ።

«ከማስታወሻው አናት ላይ የስንዱ ስም ተጽፏል ። ከበስተቀኝ ጠርዙ ላይ ቀን ተጽፏል ። ከሥር ያለውን ዋና መልዕክት ቆይ — — ገልብጬ ስላስቀረሁት አሁንም ድረስ የገለበጥኩትን ማስታወሻ በኪሴ ይዤዋለሁ . . . ላንብብላችሁ ።

' ስንዱዬ ቀደም ሲል እንደ ሰማሁትና አንቺም ትናንት በስልክ እንደ ነገርሽኝ አዳሙ ነገውኑ ወደ ድሬዳዋ የሚሔድ ከሆነ እንደ ተነጋገርነው ቅዳሜ በ፰ ሰዓት እኔው ቤት የምንገናኝበት ቀጠሮ የጸና ይሆናል። ይህም ምናልባት ለእራት እቤታችሁ ስመጣ በቃል ለመነጋገር አዳሙ ዕድል ያልሰጠን


t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲሆን በሚል የተጻፈ ማስታወሻ ነው ። ለመነጋገር ከቻልን ግን እንደ ሁኔታው የቀጠሮውን ቀን ልንለውጠው እንችላለን ። ለማንኛውም ላልሔድ እችላለሁ ብለው፣ል ላልሽኝ እኔም ሆንኩ አንቺ ለመሔድ በወጠነው ሐሳብ እንዲጸና መገናኛቱን በዘዴ እንቀጥላለን ። ምናልባት ትዳሜ እኩል ንጥ ሞኝ በ፰ ሰዓት ኢቤት ለመድረስ ካልቻልኩ ገብተሽ እንድትጠብቂኝ አንዱን የቤቱን የበር ቁልፍ እመጸ ጻጃ ቤታችሁ መስኮት ላይ በአበቦቹ ማሳ ሥር አስቀምጠዋለሁ ' የሚል ነው ።

« ወዲያውኑ አንብቤ እንደ ጨረስኩ ማስታወሻውን ለመገልበጥና የተቀመጠችውንም የግርማን ቁልፍ ለማየት ብዕርና ወረቀት ይዤ መጻጃው ክፍል ገባሁ ። ቁልፉን አስቀምጠላታል ። እንሥቹ ኢኪሴ ከተትኩና በፍጥነት መልዕክቱን ይኸው እንደምታዩት ጽፌ ለማስቀረት ችያለሁ።

« ቁልፏ ለ፡ ጥመደ ልትጠቅመኝ ስለምትችል ኢኪሴ እንደ ተውኳት በማስታወሻው ላይ ቁልፍ ስለማስቀመጡ የሚገልጸውን ሠ ነዕክት ብቻ ደልዤ በማጥፋት ወረቀቷን እንደ ነበረች አጣጥፌ እኮቷ ኪስ ውስጥ መለስኩት ።

« በማግሥቱ ጠዋት እኔን ለመሸኘት ስንዱም ግርማም አብረውኝ ባቡር ጣቢያ ተገኝተዋል ። ሁለቱንም ስሚ ስስናበታቸው ልገልጸው የማልችለው አንዳች ስሜት ሰውነቱን ነዘረኝ ። ያ! የምንከባከበው ትዳሬ ፣ ያ ልጆቼ የሚቦርቁበት ቤቱ እንደ ፈራረሰ ሆኖ ተሰማኝ ። ነፍሴ በውስጠ ሕመም እሪ እንዳለች ባቡር ላይ ተሣፈርኩ ።

« በደረሰብኝ ሥውር በደል በቁጭት እየጋየሁና እንዳን

t.me/OLDBOOKSPDF

ደ፟ም ሕፃናት ልጆቼን በሐሳብ እያጫወትኩ ፡ ብዙ መንገደ ኞች በጫኑነው ባቡር ላይ ባይተዋር ሆኜ ደብረዘይት ደረስኩ ። አፍታም አልቆየሁ ። ባቡሩ እንደ ቆመ የያዝኳትን አንድ ሻንጣ አንጠልጥዬ ወረድኩ ።

« በውጥኔም መሠረት በአውቶቡስ ተመልሼ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወጥመዴ እስኪሳካ ድረስ ልጆቼ ባሉበት ከተማ ከልጆቼ ተለይቼ ፡ ቤት እያለኝ እንደሌለኝ ሆኜ እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ተጠንቅቄ ቆየሁኝ።

« ዓርብ ዕለት ለእኔ ከፍተኛ የሥራ ቀን ነበር ። ግርማ የፈለገውን የመጋረጃ ጨርቅ እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ መግዛት ነበረብኝ ። ከኪሴ የያዝኳትንም ቁልፍ የሚተካ ሌላ መሰል ቁልፍ ማሠራትም ነበረብኝ ። ሁለቱንም አስፈላጊ ነገሮች በመርካቶ ገበያ አከናወንኳቸው ። የቀረኝ ዋና ተግባር ለወጥመዴ ቅንብር የሚያግዘኝ ሰው ማግኘት ነበር ።

« ለዚሁ ሁሉ ምስጢር መጋለጥ ምክንያት የሆነኝን ይኸን መልዕክተኛ ያገኘሁት ዓርብ ማታ ነው ። ከድሬዳዋ እንደ ተላከ መስሎ መጋረጃውን በማቀበል በትክክልና በማያስጠረጥር ሁኔታ እንዲያገለግለኝ በ50 ብር ክፍያ ተዋዋልኩት ።

«ሌላው ለወጥመዴ የሚያስፈልግ ተግባር ፡ ስንዱ ቅዳሜ በቀጠሮዋ ሰዓት ግርማ ቤት ስትገባ በግልጽ ለማየት የምችልበትን ሥፍራ መምረጥ ነበር ። ከግርማ ቤት አካባቢ ሱቆች ፡ ሻይ ቤት ፡ ግሮሰሪና ቡና ቤትም ይገኛሉ ። ከሁሉም ግን ግሮሰሪው ለከለላ አመቺ በመሆኑ ከሌሎቹ ይበልጥ በእርቀት የግርማን ቤት በግልጽ ለማየት በፊት ለፊት አቅጣጫ በመገኘቱ ፡ ተደግፎ በመቆም ወደ ውጭ ለማየት ባንኮኒው በበሩ ትክክል


t.me/OLDBOOKSPDF

የሚገኝ በመሆኑና በክፍያ ስልክ ለመደወል የሚቻልበትም ቤት በመሆኑ ከሱቆቹ ፡ ከሻይ ቤቱና ከቡና ቤቱ ይልቅ መረጥኩት ። ይህንንም በጥንቃቄ ተዘዋውሬ የፈጸምኩት በዛው በዓርብ ዕለቱ ምሽት ነበር ።

« ቅዳሜ በቀትር ላይ ከግሮማ ቤት ፊት ለፊት እራቅ ብሎ ከሚገኘው ግሮሰሪ ገባሁ ። ይኸ መዘዞኛ መልዕክተኛም አብሮኝ ነበር ። ከመርከቶ የተገዛው የመጋረጃ ጨርቅም በማንጠልጠያ ላስቲክ ውስጥ ተጠቅሎ እንደ ተያዘ ነው ። በበሩ ትክክል ባንኮኒ ላይ ተደግፈን ያዘዝነውን ቢራ እየጠጣን አሻግረን ወደ ግሮማ ቤት ስንመለከት 8 ሰዓት ሆነ። የ ግሮማና የስንዱ የኮንትሮባንድ የቀጠሮ ሰዓት የደረሰ በመሆኑ ዐይኖቹን አሻግሬ ከግሮማ በር ላይ ሳልነቅል 5 ደቂቃ ዐለፈ ። 10 ደቂቃም ተከተለ ።

ስንዱ ቡኒ ኮቷን ለብሳ ከታክሲ ወርዳ ወደ ግሮማ ቤት ስታመራ ታየችኝ ። ከመጋባታችን በፊት ወደ ወላጆቿ ቤት ስትገባና ስትወጣ በፍቅር ዐይን እጠብቃት የነበረው የቀድሞ ትዝታ ትውስ ብሎኝ ዐይኖቼ እንባ አቀረሩ ። ያኔስ ስትገባም ስትወጣም በዐይኔ መከተሌ ላገባት አስቤ ነበር ። አሁን ግን ልቀብራት ወስኜ ነው ።

« ዐይኔ እያየ በሩ ተከፍቶላት ግሮማ ቤት ጥልቅ አለች ። ወጥመዱ ውስጥ ገባች ማለት ነው ። ጥቂት ቆይቼ እግሮማ ቤት ስልክ ደወልኩ ። ልክ ድሬዳዋ ያለሁ በማስመሰል የሩቅ ሰላምታዬን አዥጐደጐድኩለት ። የፈለገውንም የመጋረጃ ጨርቅ ገዝቼ በሰው እንደ ላኩለትና በአድራሻው ይውሰዱ እንደሚሰጠውም ነግሬው ስልኩን ዘጋሁ ። በስልኩ ውስጥ ግን ስንዱ አልጋ ላይ ተዘርግታ በሐሳብ ትታየኛለች ።

« ከአንድ ሰዓት በኋላ አብሮኝ የነበረው ይኸ መልዕክተኛ ልክ ለእናንተ እንደ ዘከዘከው ግሮማ ቤት ስልክ ይውሰዱ ከድሬዳዋ



t.me/OLDBOOKSPDF

በዓርብ ማታው ባቡር እንደ መጣ በመምሰልና አስቸኳይ የእደራ መልዕክት እንዳለውም በመሆን እንዲነግር አደረኩ ። ወዲያው ስልኩን እንደ ዘጋም ለግርማ በሰጠው አስቸኳይ ቀጠሮ መሠረት ወደ ባቡር ጣቢያ ዉሬቹን ይዞ በፍጥነት በታክሲ ገሠገሠ ። እኔ ግን እዛው ሆኜ የግርማን ከቤቱ መውጣትና ወደ ባቡር ጣቢያ መሔድ እስካረጋግጥ ቆይቼ ከቤቱ ልክ ወጥቶ ሲሔድ ወደ ቤቱ አመራሁ ።

« በሩጋ ስደርስ የግርማንም ፡ በማስመሰል ያሠራሁትን የራሴንም ቁልፎች ከኪሴ አወጣሁ ። በተለይ መርኀቶ ሔጄ በጥንቃቄ ያሠራኋትን ተመሳሳይ ቁልፍ ለመፈተን ፡ መጀመ ሪያ በሩን በዷው ለመክፈት ሞከርኩ ። ለጊዜው እንደ መንከስ አለችና ወዲያው ከፈተችልኝ ።

« ሰንዱ አልጋው ላይ ተንጋላ መጽሔት ታነባለች ። ባልጠበቀችው ሁኔታ እኔን እንዳየችኝ በድንጋጤ ሀመደ. ቡን አለ ። ቦርሳዋ ከአልጋው አጠገብ ባለው ወንበር ላይ ተንጠልጥሏል ። የተቆራረጡ ቡርቱካኖች ከቤላዋ ጋር ማሀን ላይ ተቀምጠዋል ። የተከፈቱ የቢራ ጠርሙሶችም ይገኛሉ ። እነሱንም ፡ ወለሉንም በጠቅላላ መኝታ ቤቱን በዐይኔ እየቃኘሁ ስንጐራደድ ቆይቼ ወደ ሰንዱ ዘወር አልኩ ።

« ሳልጠይቃት መለፍለፍ ጀመረች ። እንዴ ግርማ አታሳት እንደ መጣች ፡ እንዴም ደግሞ አስገድዶ እንዳመ ጣት ፡ እርስ በርሱ በተሳከረና በተምታታ አነጋገር ስትቀባጥር ሁሉ አልተናገርኳትም ። ‘ምን ሆነህ ተመለስክ?’ አለችኝ የእኔ ጉዞ እንዳሳሰባትም ሆና ። ልሳኔ በንዴትና በብሽቀት ተቆልፎ ስለ ነበር አሁንም አልተናገርኩም ። የባጥ የቆጡን እያወራች ጥቂት እንደ ቆየች ፡ የማውቀውን የአንድ ዓመት የምስጢር ሥራዋን እንደማላውቅ አርጋ ከወጥመዱ ለማም



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጥ በሐሰት እንደ ልጅ ታባብለኝ ጀመር ።

« ከህዶቷ ፣ የማጭበርበሪያ ንግግሯና የማስመሰል መቅለስለሷ የተቃጠለ አንጀቴን ይብስ አጋየው ። ያ — አታላይ ምላሷ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ መቅጠፉን አላፈረበትም ። ንዴቴ ትዕግሥቴን ፈንቅሎ የቅዠቱን ፣ የስልኩን የኮንትሮባንድ ጥሪውንና ከኪሷ ያገኘሁትን የግርማን የማስታወሻ ጉድ ሳይቀር የማውቀው መሆኔን ግልጥልጥ አድርጌ ብጠቅስላት፡ ድንጋጤዋ ወይ ንዴትና ወይ ቁጣ ተለውጦ ሳታውቀው በጥፊ አፍንጫዬ ላይ መታችኝ ። አፍንጫዬ ደማ። ልብ — አርጉ መጀመሪያ የደማሁት እኔ ነኝ ።

« እተንጋለለችበት ሆና እኔም እቆምኩበት ሆኜ ስንተናነቅ ከአፍንጫዬ የሚወርደው ደም እራቷ ላይ ይንጠባጠብ ነበር ። በእናንተ ምርመራ ከራቷ ላይ ደርቆ የተገኘው ደም በዐይነቱ ከእንተ ደም ጋር ተመሳስሏል ብላችሁ ተጨማሪ ማስረጃ ያደረጋችሁትም በእርግጥም ትክክል ነው ። ምንጩ በእሷ ጥፊ የወረደኝ የነስር ደም ነበር ።

« በሁሉም አቅጣጫ የፈጸመችውን ሥውር ብልግና ማወቄ ጥፊን ብቻ ሳይሆን እጥንት የሚነካ ስድብም አስከትሎብኝ ነበር ። በስድብ ወንድነቴን እንኳሰሰችው ፤ ተጠየፈችው ። ለእኔ ለልጆቿ አባት ያላትን የውስጥ ንቀት ከግርማ ብርታት ጋር አወዳድራ በዚያ በሾህ ምላሷ መንፈሴን ወጋችው ። በንዴት አዕምሮዬ ሰከረ ። ትዕግሥቴም ተሟጠጠ።

« በአንድ ፊት ጭካኔዋ ፤ በሌላም ፊት ልጆቼ ተራ በተራ ዐይኔ ላይ ድቅን እያሉ እልሄን ወደ ለቀሶ መሩት ። እሷም ብትሆን የነፍረት ንዴቷ የተስፋ መቁረጥ እልህን ዘርቶባት እኔ እንደማንባው እያነባች . . . እንደ ተናንቅን

t.me/OLDBOOKSPDF

እኩል የብርቱካን መቁረጫ ቢላዋ ከማህኑ ላይ አነሣን ።

« ጉልበት አላት ። በአንድ እጇ ጉሮሮዬን አንቃ በሌላ እጇ እኩል ያነሣነውን ቢላዋ አጥብቃ እንደ ያዘች ጥቂት ስንታገል ቆይተን የሞት ሞቷን የቢላዋውን ስለት ደረቷ ላይ ተክልኩት።

« ለጊዜው ከብርቱ ጉልበቷ ትንቅንቅ ተገላገልኩ ። እፎይታ ግን አላገኘሁም ። መንፈሴ ይበልጥ ተረበሸ ። በጣር ጩኸቷ ውስጥ የልጆቼን ጫጫታ ሰማሁት ። እነሱን የወጋሁ ያህል ተሰማኝ ። በእርግጥም እንደ ወጋኋቸው ዛሬ ነው የታወቀኝ ።

« ጣር አብቅቶ ሕይወቷ እንዳለፈ እኪሴ የነበረውን የግርማን ቁልፍ እኮቷ ኪስ ውስጥ ጨምሬላት ባሠራሁት ተመሳሳይ ቁልፍ ቤቱን እንደ ነበር ዘግቼ ወጣሁ።

« ወጥመዴ በወንጀል ከተበከለም በኋላ እንደ ቀድሞው ጥንቃቄ አልተጓደለኝም ። ማታውኑ ከዚህ መናጢ መልዕክተኛ ጋር አራት ኪሎ ቀጠሮ ስለ ነበረን እዚያው ሒጄ 50 ብሩን ሰጥቸው ተለያየን ።

« ሌሊቱን በተከራየሁት ሆቴል የልጆቼን ጩኸት እየቃዠሁ አድሬ በማግሥቱ እሑድ እንደ ተለመደው ድሬዳዋ ያለሁ በማስመሰል ወደ ቤት ስልክ ደወልኩ ። ሠራተኛዋ የስንዱን እንደ ወጣች መቅረት ነገረችኝ ። ሰኞንም ካለሁበት ሆቴል ሳልለቅ ደግሜ ደወልኩኝ ። የቀድሞው መልስ ተሰጠኝ ።

«ከባቡር እንደ ወረደ በመምሰል ማክሰኞ ማታ እቤቴ ገብቼ እሮብ ጠዋት ለእናንተ አቤት አልኩኝ ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

# ዱር ያበበ ፍቅር

በጉብላክ የሠፈረ አካባቢ ከሚገኘው የሻንቅሎች መንደር አንድ የዐሥራ አራት ዓመት ወጣት በቀኝ እጁ ቀሩ ፤ በግራ እጁ ቀስትና ደጋኑን እንደ ጨበጠ ከመንደሩ በስተሰሜን ወደ ሚገኘው ጫካ በሩጫ ገሠገሠ ። ብዙም ሳይቆይ ከዳንጉር ተራራ ግርጌ ከበስተምሥራቅ በኩል ወደ ደቡብ ከሚፈሰው የጉብላክ ወንዝ ደርሶ ከውሃው ዳርቻ ላይ ከሚገኘው ተረተር ላይ ወጣ።

አካባቢውን በዐይኑ ማሰስ ጀመረ ። የወራጅ ውሃ ኳኳቴና ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ብቻ ታየው ። ድንገት አንድ ሐሳብ መጥቶለት ወደ ዲንባ መንደር ለማየት ሞከረ ። ከፊቱ ያለው ጥቅጥቅ ደን ግን ከለላ ሆኖ እይታውን ጋረደበት ። ቅብዝብዝ ዐይኖቹ በርቀት አሻግረው ለዐሐይ ደረቱን ከሰጠው የበላይ ተራራ ላይ ዐረፉ ። ያ ግዙፍ ተራራ አድማሱን አግድም ለጥጦ ሰማዩን የተሸከመ መስሎ ተወዝፏል ። ድቅድቅ ደመና ከተራራው ጫፍ ላይ ተጀንጅኖ ሲታይ ተራራው ሰማዩን የሚደግፍበት የመሸከሚያ ጉዝጓዝ ይመስላል ። ሽባቦ ይህን ሁሉ አስተውሎ ሕሊናውን ሰበሰበና ጥቁር ፊቱን ቅጭም አርጎ ባቅራቢያው የወንዙን ዳርቻዎች መቃኘት ጀመረ ። የናፈቃት ወጣት ግን አልታይ አለችው ።

ጥቂት ቆይቶም የታመቀ ትንፋሹን ከእንደበቱ አስወጣና ቆጣ ባለ ድምፅ ፡ "ዲዲጋ — ፉዲዳ ከንዳቴ?" አለ እፉን

t.me/OLDBOOKSPDF

በፈታበት የሻንቅልኛ ቋንቋ ። "ልጅቲ የት ጠፋች?" ማለቱ ነበር ። አከታትሎም "ያርሚያ!" ሲል ተጣራ ። ምላሽ ግን የለም ። ድምፁን ከፍ አርጎ በድጋሚ ተጣራ ።

ወዲያው "ሽባቦ!" የሚል የስም ጥሪ ምላሽ ከበስተቀኝ በኩል ካለው ጨፌያማ ጉድባ ውስጥ ሰማ ። ስሙን የጠራ ችው ያርሚያ እንደ ሆነች ከድምጿ በመረዳቱ ደስታ በሕሊ ናው ጎረፈበት ። አፍታም ሳይቆይ በቀኝ እጁ የያዛትን ትራ ባሽረጣት ግልድም መቀነት ውስጥ ሽጦ ቁልቁለቱን በፍጥ ነት ተንደርድሮ ወረደ ።

ያርሚያ ፡ በትከሻዋ ላይ አጋድማ በያዘችው የሽመል ሜፎች ላይ ፡ ኋላና ፊት ተቋጥረው በተንጠለጠሉ ሁለት አቃፊ መረቦች ፡ የውሃ ቅሎቿን ተሸክማ ከምንጩ ዳርቻ ብቅ ስትል አያት ። ተንደርድሮ በደረቷ ላይ ተጣበቀ ። እሷም የውሃ መሸከሚያዋን መረብ ሳታውቀው ከንቅሎቹ እጭቃው ላይ ጥላ በሽባቦ እቅፍ ውስጥ በስሜት ትላወስ ጀመር ። የሳማትን ያህል ደጋግማ ሳመችው ፡ ያቀፋትን ያህል አቅፋ አሻሸችው ። ቀና ብላ የሚያብረቀርቀውን ፊቱን ታይና ከትከት ብላ ትሥቃለች ። መቼም ደስታዋን በሣቅ መግለጽ የተለመደ ጠባይዋ ነው ። ፀሐይ በመታችው ቁልል ጡቶቿ የደረቱን ቅዝቃዜ እየተረተረች ትኩስ ሙቀቷን ስትመግበው ጥቂት ትቆይና ዘወር ብላ ወደ ወደቁት ቅሎች ታጎነብሳለች። የቀዳችው ውሃ የተደፋ ቢሆንም ቅሎቹ ግን አልተሰበሩም። የተንጋለሉትን ቅሎች አንሥታ ቀና ስትል ፡ "ታይሚ ጊንዲካ" አላት ። "የቅርሜት መረቦች የተቋጠሩበትን የሽመል መሸከሚያ ስጭኝ" ማለቱ ነው ፡ ውሃዋን እስከት ቀዳ ሊያዝላት አስቦ ።

ያርሚያ ፡ መሸከሚያዋን ለሽባቦ ሰጥታው ወደ ምንጩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስትመለስ እሱም ተከትሏት ወረደ ። "ሸባቦ! አንግሽሚያ" አለችው ። እንደ ተለመደው "ዝፈንልኝ" ማለቷ ነው ። እሱ ግን ከገደሉ ሥር የሚፍለቀለቀውን የምንጭ ውሃ አወራረድ ትኩ ብሎ እያየ እቆመበት በትካዜ ተዋጠ ። ለጊዜው መተከዙን ባታይም ውሃዋን እየቀዳች ዘወትር የሚዘፍንላትንና የምትወደውን ዜማ አስቀድማ እራሷ ማንጐራጐር ጀመረች ፡ ለዛ ባለው ዜማ ። "ወይወረድሺልማ ባቡእ ወይወረድሺልማ..." እያለች አዝማቹን ደጋገመችው ። "አባቱ ከእናቱ ጋር ለምንድነው የምትባላው?" የሚል ፍች አለው ። ከግጥሙ መልዕክት ይልቅ ዜማው ይማርካታል።

ሸባቦ እንደ ወትሮው አብሯት አለማንጐራጐሩን አይታ በኩርፊያ ጸጥ አለች ። ወዲያው በቀኝ እጇ ማጅራቱን እያከከ "እሺ አባትሽ ምን አሉ?" አላት ጸጥ ብላ ከምንጩ ውሃውን እየቀዳች ሳለች ። መልስም አልሰጠችው ። ኩርፊያዋ ግን ከመቅዕበት በኀዘን መንፈስ ተለወጠ ። ደጋግሞ ጠየቃት ። ልትናገር ከአንገቷ ቀና ትልና መልሳ በዝምታ ታቀረቅራለች።

ጥቂት ቆይታም ፍርሃት በሸበበው አፍ እየተርበተበተች " — በ — ባ — ባቡእ — — — እ — እ — አባቴ" ትልና ማግባሯን ሳትጨርስ ተመልሳ ዝምታ ውስጥ ትሰጥማለች ። ሸባቦም በእሷና በእሱ ጉዳይ መክረሚያውን ስላተረበው የጋብቻ ጥያቄ አባቷ እስከፊ ውሳኔ ላይ እንደ ደረሱ ከሁኔታዋ በመረዳቱ ሕሊናው በኀዘን ተሞልቶ ልሳኑ በዝምታ ተዋጠ ። እንድ ሁለቴ ተራመደና ከያርሚያ ፊት ለፊት ካለው ድንጋይ ላይ ተቀምጦ በትካዜ ዐይኖቹን ወደ ወንዙ ወረወረ ። ያርሚያም የሸባቦ መጨነቅ ይበልጥ ስላስጨነቃት እንባ ያጋቱ ዐይኖቿን ጨምቃ ከአንገቷ ቀና አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያው በባህላቸው መሠረት አባቷ ለታላቅ ወንድሟ ለታጌ በሚስትነት የምትሰጥ ሴት ልጅ ከነሽባቦ ቤተ ዘመድ ባለመገኘቱ ፡ ያርሚያን ያለልዋጭ ለሽባቦ ለመዳር ፈቃደኛ እንዳልሆኑና ፡ ማዶ ከዲባጢ መንደር ያሉት አቶ አገሉ ግን ለያርሚያ ወንድም ለታጌ በሚስትነት የሚሰጡት መዲን የምትባል ሴት ልጅ ስላላቸው የመዲን ወንድም ባሹ ያርሚያን ፡ የያርሚያን ወንድም ታጌ ደግሞ መዲንን በማግባት ዝምድናን ለመፍጠር ሁለቱ ቤተሰቦች መስማማታቸውን ለሽባቦ ነገረችው ።

ያርሚያ የምትወደውንና አብሮአደግ ፍቅረኛዋን ሽባቦን ለማግባት ያላት የረዥም ጊዜ ጉጉት በባህል ወግና ልማድ መጨናገፉን ደጋግማ በማብሰልሰል እተቀመጠችበት ስቅቅ ብላ አለቀሰች ። ወዲያው የላላ ግልድሟን ጠበቅ አርጋ በመሸበብ ሔዳ እሽባቦ ጭኖች ላይ ተቀመጠች ። ጉንጮቹን እያሻሸችና ዐይን ዐይኑን እያየች ፡ "ሽባቦ ማንኑሽ ያሉት አጐትህ ሴት ልጅ አላቸው እማይደል እንዴ?" ስትል ጠየቀችው ።

"አዎ! አጐቴማ ሴት ልጅ አለችው ። ግን ሚስቱ ስላረገዘች የሚወለደው ልጅ ወንድ ይሁን ሴት ሳይታወቅ ትልቋን ልጁን ለማንም አልሰጥም ብሏል" አላት ።

"ለምን?" ስትል ጠየቀችው ለጌጥ በቤሳ ምላጭ በጉንጮቿ ላይ ተተልትላ የተሸለመችውን የጠባሳ ንብብር (ሞቅታ) እያከከች ።

"እንዴ! እሱማ ሚስቱ ወንድ ልጅ ከወለደች ኋላ ልጁ ሲያድግ እህቱን ካልሰጠ ለልጁ ሚስት የሚሰጣቸው ቤተ ዘመድ ስለማያገኝ ነዋ!"

"ታዲያ ገና ለሚወለደው ልጅ መጠባበቂያ ናት ማለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው?"

"እህሳ! ለኔው ጉዳይ ሲል አባቴ ጠይቆት እንኳ ነበር ። ግን እሺ አላለውም ።"

"በቃ እንግዲህ እኔና አንተ ተለያይተን መቅረታችን ነው?"

"አይ! ለምን? እረ አይቦሽ ግዴለም! አንድ ዘዴ እኮ አለኝ በኋላ እነግርሻለሁ ። ብቻ አንቺ ቆራጥ ሁኚ" ብሏት በቅል የቀዳችውን ውሃ በመረቡ ቅርጫት ላይ አስቀምጠ የመሸከሚያውን ሽመል ትከሻዋ ላይ ካደረገላት በኋላ ቀስትና ድጋኑን አንሥቶ ዳገቱን እየወጣ ወጡ ።

አቀበቱንና ጨሌፌያማውን ምድር ተሻግረው ወደ መንደራቸው እስኪዘልቁ ሽባቦ እንደ ዘዴ ባቀረበው ሐሳብ ሳይስማሙ ቀርተው ረጋ ባለ መንፈስ የተጀመረው ውይይት ቀስ በቀስ ወደ ክርክር አመራ ።

"ሌላ መላ ይሆናል የምትይው ሐሳብ ካለሽ ንገሪኝ ። አለዚያ እኔ በነገርኩሽ ሐሳብ መስማማት አለብሽ!" አለ ሽባቦ እያደረ ንግግሩ ሁሉ በቁጣ እየታጀበ ። ያርሚያ ግን ጭራሽ መልስም ነፈገችው ። ዝምታ ብቻ ። ደግሞ ደጋግሞ ጉተጉታት ። እንሒድ እንብረር ነው ሐሳቡ ። ቀየውን ጥሎ መጥፋት ! መንደሩን ትቶ መኮብለል ! ያርሚያ ግን ልቧ ድፍረት ስላጣ አልተዋጠላትም ።

ወዲያው በመኻላቸው ጸጥታ ገብቶ ያለ ንግግር በዝምታ ወደ መንደራቸው ተቃረቡ ። ሽባቦ ያላትን ሁሉ እሺ የምትለውና የመከራትን ሁሉ የምትቀበለው ወጣት ፡ ዛሬ ላስከፊ ችግራቸው ዘዴ ብሎ ያቀረበውን ሐሳብ ባለመቀበሏ በእሷ ላይ ያለው እምነት ሁሉ ወደ ጥርጣሬ ተለወጠበት ። ስለ እሱ የነበራት ያ ብርቱ ፍቅር እንኳ በልቧ ውስጥ መኖሩን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከፋኝ ተጠራጠረ ።

እንቅፋት የሆነበትን የባህል ማነቆ በሀመስ ሊቋቋመው የመጠነው ሐሳብ በያርሚያ ፈቃደኛ አለመሆን ዋጋ እንዳጣ ሲረዳ ሕሊናውን ለተስፋ መቁረጥ ተሸናፊ አረገው ።

የሽባቦ መበሳጨትና በመኻላቸው የተፈጠረው አለመግባባት የያርሚያን እንጀት መልሶ አባባው ። በእርጋታ የተሻለ መፍትሔ እንዲፈልግ ጠየቀችው ። መልስም አልሰጣት ። "ሽባቦ ተናገር እንጂ!" አለችው በቀኝ እጇ ትከሻውን መታ አርጋ ። አሁንም አቀርቅሮ ከመራመድ በቀር ከአንደበቱ ቃል አልወጣም ። እንደ ቁጣም ፡ እንደ ልመናም አካሒዷን ቆም አድርጋ አፈጠጠችበት ። በእሱ በኩል አዲስ ነገር አልተፈጠረም ። አቀርቅሮ መራመድ ብቻ ።

ቀስ በቀስ በዐይኖቿ ላይ የእንባ ቸፍችፍታዎች መመንጨት ጀመሩ ። "ለምን አትናገርም?" የተሸከመችውን ባለማንጠልጠያ የሽመል ዘንግ ትከሻዋ ላይ እያመቻቸች ጮኸችበት ።

"ምን ዋጋ አለው የእኔ መናገር! አንቺ እንደሁ የማውቅሽ ያርሚያ — የድሮዋ ያርሚያ አይደለሽም ፡ ተለውጠሻል" አላት ራሱን እየነቀነቀ ።

ለቅሶዋ እያደር በአናት በአናቱ እየባሰ ሔዶ ንግግሯ ሁሉ በተለየ ድምፅ ቁርጥ ቁርጥ ይል ጀመር ። ለእሱ ያላትን ፍቅር ሁሉ ደጋግማ ገለጸችለት ። እሱ ግን አልመሰለውም ። ከዐይኖቹ እንባ ባይፈሱትም ፡ በልቡ ግን ከእሷ ቀድሞ አልቅሷል ።

እሷም የእሱን ጥርጣሬ ለማስወገድ ፡ እሱም የተከፋበትን ስሜት ለመግለጽ እንደ በለሆሳስ አንዳንዴም በቁጣ እየተነጋገሩ ወደ መንደሩ ሲጠጉ የጥይት ተኩስ ተሰማ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታያለሽ እናንተ ግቢ ?" ሽባቦ እጇን ዘርግቶ ያንግጠ ቆመ ።

"ምን ! — ምን ! ምንድነው እሱ ?" መልሳ ጠየቀ ችው።

"አባትሽ ናቸው እኮ አከታትለው ሦስቱንም ጥይት ወደ ሰማይ የተኮሱት ። ማን ሞቶባቸው ይሆን ?"

ያርሚያ ደነገጠች ። በባህላቸው ወደ ሰማይ ሦስት ጊዜ በማከታተል የሚተኮሰው የቅርብ ዘመድ ሲሞት ብቻ እንደ ሆነ ስለምታውቅ በቤተሰቧ ላይ የሞት አደጋ የደረሰበት ሰው እንዳለ ተረዳች ። አፍታም ሳትቆይ በፍጥነት እየተራመደች ለቅሶዋን ማሰማት ጀመረች ። የጕረንን ድምፅ ከአንደበቷ እየወጣ በፍጥነት ወደ ቤቷ ገሠገሠች ።

በያርሚያ ሁኔታና በመንደርተኛው የለቅሶ ትርምስ የተደናገጠው ሽባቦ ከኋላዋ ተከትሏት እግቢው አጥር ጋ ሲደርስ ከበስተጓሮ ካለው የበቆሎ እርሻ ውስጥ ገብቶ በአጥሩ ቀዳዳ ወደ ኀዘንተኞቹ ያስተውል ገባ ። ቢያዝንም ፣ ቢከፋም በሆዱ ከመቃጠልና ቆሽቱን ከማሳረር በቀር ለቅሶ እሚሉ የማያውቀው ወጣት ፣ በነያርሚያ ግቢ ሴቶች እየበረከቱ ፣ ምስቅልቅል የለቅሶ ዜማ እየደመቀና እሪታው እየተሳለ ሲሔድ እንጀቱ ከፉኛ ተላውሶ በዐይኖቹ እንባ ቀደመው ።

ሽባቦ በማግሥቱ ጠዋት እንደ ተለመደው እወንዝ ወርዶ ያርሚያን ውሃ ልትቀዳ ስትመጣ ከሩቅ አያት ። ያ የሚያብረቀርቀው ጥቁር የፊቷ ገጽታ ወዙን አጥቶና የዐይና ሽፋኑ ተጕረብርቦ ፣ በጨሌ ጌጥ ይደምቅ የነበረው ጸጉሯ ጭፍርር ብሎና ወፍራም ከንፈሯ ተነፋፍቶ በርቀት ሲያስተ ውላት ከፉኛ አንጀቱን በላችው ። እንባው ባይቀድመውም የቆሽቱ እሳት ቀደመው ፣ ውስጥ ውስጡን የሚጋይበት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከምንጩ ዳር ካለው ሰንበሌጥ ውስጥ ወደ እሷ ብቅ ሲል የርሚያ እንደ ወትሮው በፈገግታ ሳይሆን ከመሪር ለቅሶ ጋር ተስፈንጥሮ በደረቱ ላይ ተጣበቀች ። ለቅሶዋ ወዲያው ባያባራም እየደር የፍቅራቸው አፍላ ስሜት በደም ሥሯ ተፍለቅልቆ ኀዘኗን ገለጸባት ። እንደ ወትሮው እሷ በእሱ ፣ እሱም በእሷ እቆመበት እንደ ሻማ ቀለጡ ። እንዳቸው በአንዳቸው እቅፍ ውስጥ እየዋኙ እርስ በእርስ የሰውነታቸ ውን የስሜት ትኩሳት ሲጋሩ ቆዩና ከምንጩ ዳር ተቀመጡ ።

"ለመሆኑ የእናትሽ ገዳዮች እነማን እንደሆኑ ታውቀ ቃል ?" ሲል ጠየቃት በእንባ የረጠቡ ጉንጮቿን በመዳፉ እየጠረገላት ።

"አባቴ ያውቃቸዋል ። ወንድሜ እንኳ አብሯቸው ኖሮ ስለ ነበር በወሬ ወሬ ሰዎች ነግረውት ነው ያወቃቸው ፣ ያልመሃል ነው ያሉት እሉ ።"

"ከያልመሃል ድረስ ሆን ብለው ለበቀል ሲሉ ነው የመጡት ማለት ነው ?"

"አዎን እኔ ሕፃን ሆኜ እናቴ ታማ አባቴ ያልመሃል ያሉት ጠንቋይ ጋ ወስዶ ካዳናት በኋላ ፣ ስመለስ እናቴን ሊቀሙት ተኩስ የከፈቱበትን ሁለት ጉረምሶች ገድሏቸው ነው እናቴን ይዞ አምልጦ የመጣው ። ከዚያ ወዲህ የሟቾቹ ወንድሞች እዚህ ድረስ እየመጡ አባቴን ሊገድሉ ብዙ ጊዜ ይሞክሩ እንደ ነባር ሲያወሩ ሰምቻለሁ ።

"ታዲያ ይህንን እያወቁ እናትሽ እንዴት ብቻቸውን ማገዶ ሰበ . ሔዱ ?"

"ብቻዋን አይደለም የሔደችው ። ከጐረቤታችን ከካ ንቱ እናት ጋር ነበር የሔዱት ። እሳቸውን አስፈራርተው ነው እናቴን ገድለዋት ያመለጡት" አለችና ተንሰቀሰቀች ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሸባቦ እፊቷ በርከክ ብሎ እንባዋን እየጠረገ ሊያጽናናት ሞከረ ።

"ወንድሜ ቃጊም እኮ ብቻውን ነው ለብቀላ ትናንትና ወጉ የሔደው ።"

"የልመሃል ?"

"አዎን ። አባቴ ከአጎቴ ጋ ዝናርና ጥይት እስኪመጣልኝ ቆየኝና አብረን እንሔዳለን ፣ ያለበቂ ጥይት ለበቀል መውጣት አደጋ ነው ብሎት ነበር ። እሱ ግን ደሚን ሳላጠራ አንድ ቀን እቤቴ አላድርም ብሎ ጠመንጃውን አንግቶ ሔደ።"

የርሚያ ወንድም ቃጊ የእናቱን ሞት ሊበቀል መንደሩን ጥሎ ወደ ያልመሃል ከገሠገሠም ወዲህ ሸባቦና ያርሚያ እወንዝ እየተገናኙ እንደ ተለመደው ሲጨዋወቱ ማሳለፋቸው አልቀረም ።

አንድ ቀን ጠዋት ያርሚያ እምንጭ ወርዳ ሸባቦን ስንበሌጥ ላይ በጀርባው ተንጋሎ አገኘችው ። መቼም እንደ ልማዱ ከሰላምታ በፊት ስሙን ጠርታ ደረቱ ላይ መጠምጠም ይቀናታል ። የእሷን ሙቀት ለእሱ ፣ የእሱን ሙቀት ለእሷ እንደ ወትሮው በመተሻሸት ተካፈሉት ። የወጣትነት እፍላ ስሜታቸው ደቂቃ በደቂቃ እየጨመረ ሔዶ እንደ ተቃቀፉ ከስንበሌጡ ላይ ኸርዋ ብለው ተዘረጉ ። ጥቂት ቆይቶም በስሜት የተጨፈኑ ዐይኖቻቸውን ገልጠው ከአንገታቸው ቀና ይሉና ዐይን ለዐይን ሲጋጠሙ በዕፍረት እሱ በእሷ ፣ እሷም በእሱ በየጉያዎቻቸው ሥር ሽጉጥ — ሽጉጥ ይላሉ ። ሙቀታቸው እየጨመረ እየጨመረ ሲሔድ ፣ የቀዝቃዛው ስንበሌጥ እርጥበት እየነዘራቸው አንዳቸው በአንዳቸው ሰውነት ውስጥ ለመግባት የሚፍጨረጨሩ ይመስል በጠበቁ እቅፎቻቸው እንደ ተናነቁ አንድ ሁለቴ ተገላበጡ ።

እንገቷ ከአንገቱ ፣ ጡቶቿ ከደረቱ ፣ እምብርቷ ከእምብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርቱና ጭኖቿ ከጭኖቹ ጋር መሳ ለመሳ ገጥመው የሰሚታቸውን እፍላ ትኩሳት እያጋጋሉ የዓላማቸውን እሽት ለመጀመሪያ ጊዜ ቀጠፉት ።

እካል ከአካል ጋር ትንንቁ አበታ ። እፏ በግራው ፡ እሱ በቀኙ ከንድ ለከንድ ተንተርሰው እተንጋለሉበት እሮይታን ተላበሱ ። በስሜት እርካታ የሰከነው የውስጥ ገላቸው ሙቀት እየከሰመ ሔደና የሰንበሌጡ ቅዝቃዜ ካሽለበበት እሮይታ ቀሰቀሳቸው ።

ወዲያው ተያጋግፈው ተነሡና ከፊት ለፊታቸው ካለው ቋጥኝ ላይ ወጥተው ጐን ለጐን እንደ ተቀመጡ ፡ "ሽባቦ ሳልነግርህ!" አለችው ያርሚያ ያጠፈችውን እግሯን ሽርተት አርጋ ጭኗን በምራቋ እያበሰች ።

"ምንድነው እሱ?" ሽባቦ ወሬዋን ለመስማት በጉጉት ጠየቃት ።

"አቶ አገሉ ከልጃቸው ከባሹ ጋር ለወቀሳ እቤት መጥተው ነበር ፡ ትናንት ከዚህ ውሃ ቀድቼ ስሔድ አባቴ ለምን ቆየች ብሎ ተቆጣኝ ። ከአንተ ጋር እዚህ እየተገናኘን እንደምንጫወት ሁሉ አቶ አገሉ ነግረውት አባቴ ሁለተኛ እንዳይደገም ብሎ አስጠንቅቆኛል ።"

"አቶ አገሉ ምን አገባቸው?"

"አባቴ ለልጃቸው ለባሹ ሊድረኝ እያደለም እንዴ የተስማማው! የልጃቸው እጮኛ ሆኜ እንዴት አያገባቸው?"

"ታዲያ ባሹ አንቺን ያገባል ማለት ነዋ?"

"እኔ ምን ዐውቄ!"

"እንዴ — እንዴት ምን ዐውቄ? የምታገቢውን አታውቂም?"

"የሚድረኝ አባቴ ነው ፡ እሱ ደግሞ ለባሹ ሊድረኝ ነው የሚፈልገው ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንቺስ ባሽን ማግባት ትፈልጊያለሽ?"

"አልፈልግም! እንኳን ላገባው በዐይኔም ማየት አልፈልግም!"

"ማንን ማግባት ነው የምትፈልጊው?"

"እ! …" ትከሻዋን ነቅንቅ አርጋ በዕፍረት አቀረቀረች።

"ተናገሪ እንጂ!"

"እንተን አልኩህ? በቃ ዝም በለኝ!" የዕፍረት ቁጣ ተቆጣችው ።

ሸባቦ ቀድሞውኑ እንደምትወደው ቢያውቅም ፡ በዚህ ሁኔታ ለእሱ ያላትን ምርጫ ስትነግረው ደስ አለውና ልቡ በኩራት ተሞላ ። እተቀመጠበት ደረቱን ነፍቶ ወደ ኋላው ለጠጥ ሲል በጣቶቹ ቆንጥጦ የተደገፈበት እንኳር ኮረት ተፈንቅሎ ከቋጥኙ ላይ ተንሸራቶ ወደ ምድር ወደቀ ።

ኪር — ኪር — ኪር ብላ ማቀች ያርሚያ ልትደግፈው ዘላ እየወረደች ፡ ሳታስበው እዛው ቀረች ። እተኛበት ተኟታበት ፡ ተቃቀፉ ፡ ያንን እፍላ ስሜታቸውን ዳግም አጉምርተው ሊመገቡት ።

በዚያ ለምለም ሣር ላይ ሁለት አካል በአንድነት ፡ አንድ አካል በሁለትነት በትቅፍቅፍ ማጎደር ውስጥ በስሜት ተጣምረው በአካል ተላወሱ ።

በድንገት ሳያስቡት ከበስተግርጌያቸው በኩል የተወነጨፈ ቀስት የሰንበሌጡን አገዳ እያንካከተና ቅጠላቅጠሉን እየበጣጠሰ ዐልፎ ከራስጌያቸው በኩል ቋጥቋጦው ላይ ተሸንቀረ ። ሸባቦ ያርሚያ ፡ ከተኛችበት እንዳትነሣ በግራ እጁ ወደ ምድር እየተጫናትና በዐይኖቹ አካባቢውን እየፈተሸ እመር ብሎ ተንበረከከ ። ወዲያው ቋጥኙ ሥር ጠዋት


t.me/OLDBOOKSPDF

ያስቀመጠውን ቀስትና ደጋን በእንብርክኩ እየዳኸ ሔዶ
አነሣውና ወደ ያርሚያ ተመለሰ ። ያርሚያ ደንግጣለች ።
"ተነሽ ፤ እዚያ ገደል ሥር ካለው ጢሻ ውስጥ እንደበቅ"
አላት በአንድ እጁ እየጐተታትና በሌላ እጁ ቀስትና ደጋኑን
አጥብቆ እንደ ያዘ ።

"ታያለሽ? ያ! ባሹ አይደለም አድፍጦ ወደ ሰንበሌጡ
የሚራመደው?" አለ ሽባቦ በሹክሹክታ ድምፅ ለያርሚያ
ከፊቷ ያለውን የተጐነጐነ ሐረግ እየገለጠላት ።

"አዎ ! እሱ እራሱ ነው" ስትል መለሰች ።

"ተመልከቺ ይኸንን ቀስት በግንባሩ ላይ ስተክለው!"
በርከክ ብሎ አነጣጠረ ።

"ተው! ተው! መግደሉ ምን ይጠቅመናል!" የያዘውን
ቀስትና ደጋን የሙጢኝ ጨብጣበት ተቆጣችው ።

ገፍትሯት ቀስቱን ወደ ባሹ አነጣጥሮ ሊያስፈነጥር
ቢሞክርም የያርሚያን ጉልበት ግን አልቻለውም ። የቀስቱን
ማስፈንጠሪያ ጅማት ከደጋኑ ጋር አጥብቃ ይዛ ሽባቦን
ከማንፍል እርምጃው ልታግደው ተጣጣረች ።

"ወደሽዋል ማለት ነው ?"

"ማንን ?"

"ባሹን ።"

"ብወደውማ ኖሮ ሁለተኛ ከአንተ ጋር እንዳልገጥም
ትናንት የስምታ ማስጠንቀቂያ ተነግሮኝ ዛሬ አብሬህ ባልተገ
ኘሁ ነበር ።"

"ግዴለም ፤ ዛሬ ጉዱ ይለያል ! እጁን ማርኬ እፊትሽ
አመጣዋለሁ ፤ ልቀቂኝ !"

"ለምን ሳያየን አንጠፋበትም ---በዚህ በኩል ?"

"በጭራሽ ከኋላው ሳያየኝ ቀስቱን ነጥቄ ባዶ እጁን

t.me/OLDBOOKSPDF

እፊትሽ አመጣውና ከሁለታችን የምትመርጭውን ፊት ለፊት ትናገሪያለሽ ። እንቺ እዚሁ ቆይኝ ።”

ሽባቦ ቀስቱን በደጋኑ መኻል ለመኻል በማስፈንጠሪያው ጅማት ላይ ወጥሮ ዝግ ባለ እረማመድ አጐንብሶ ችምችም ወዳለው ስንበሌጥ ውስጥ ገባ ። ባሹን ቀድሞ ያየው ቦታ ላይ አጣው ። እቅጣጫውን ቀይሮ ኮሽ ወዳለበት ሁሉ ይፈልገው ጀመር ። በተረጋገጠው ስንበሌጥ ውስጥ ቁልቁል ወደ ምንጩ የሚያመራ የእግር ፋና ተመልክቶ ፡ እሱኑ ተከትሎ እያደባ ወረደ ።

“ያርሚያን የት አረከት?” አለ ባሹ በደጋኑ ማስፈንጠሪያ የወጠረውን ቀስት ጫፉን በሽባቦ ማጅራት ላይ ፈጥኖ በመደገን ።

“ስለ እሷ ምን አግብቶህ ትጠይቀኛለህ?”

“እንዴት አያገባኝም የአባቱን ቃል ከአባቷ ፡ እህቱን ከወንድሟ አስማምቼ ያጨኋት መሆኔን ሳትሰማ ቀርተህ ነው ወይስ ተዘንግቶህ? ለመሆኑ ከእጮኛዬ ጋር እንድትጓዝ የፈቀደልህ የትኛው አይዞህ ባይ ነው?”

“አንተ እራስህ ከፍቅረኛዬ ጋር እንዳንጫወት መረበሽህ ማንን ተማምነህ ነው ?” በጉርምስና ስሜት በከርከር ይናጨ ገበ ።

“መረበሽ ቀርቶ መግደልም እንዳለ ሳታውቀው ቀርተህ ነው ?” ባሹ ወደፊት አለፍ ብሎ ከሽባቦ ፊት ለፊት ቆመና የቀስት ማስፈንጠሪያውን ጅማት ከደጋኑ ላይ አጥብቆ በመወጠር በደረቱ ላይ ደገነበት ።

“በያዝከው ቀስት ሒድና የጲባጤን ጅማሬ ግደል !”

“ያርሚያን ለማግኘት አንተን መግደል አያሻኝም !”

“እኔ ካልሞትኩ ያርሚያ የኔው ነች ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ለአንተ ማን ሰጥቶህ ማን ፈቀደልህ ?”

“እራሱ ፈቅዷልኝ ! ስለምትወደኝ የኔው ናት ፡ እንዳንተ የማትወደኝን ልጅ አልቋምጥም !”

“ማንን ነው የማትወደው ?”

“አንተን!”

“ትምጣና እሬት ትናገር ! እኔን ጠልታ አንተን ከፈቀረች ለአባቱ ነግሬ የጋብቻው ስምምነት ይፈርሳል ። አባቷ የእኔን ዘር ፈልገው እንጂ ዘር ፈልጌ አላጨኋትም ።”

ሽባቦ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያርሚያን ተጣራ ። ወዲያው ከነበረችበት ጢሻ ውስጥ ወጥታ የሰንበሌጡን አገዳ ግራና ቀኝ እያንጋለለች በዝግታ ወደነሱ ተጠጋች ።

ባሹ በሽባቦ ደረት ላይ የደገነውን ቀስትና ድጋን አንሥቶ ፡ ቀስቱን በጀርባው ላይ ካንገተው የቀስት መያዣው ኮረጆ ውስጥ ከከተተና ድጋኑን በትከሻው ላይ ካነገበ በኋላ ከሁለቱ ምርጫዋ ለማን እንደሆነ በቁጣ ጠየቃት ።

ያርሚያ ጭራሽ መልስም አልሰጠች ። ግንባሯን ወደ መሬት አቀርቅራ በጸጥታ እንባዋን ታዘንበው ጀመር ።

“ተናገሪ እንጂ !” ባሹ ዐይኑን አፍጥጦ ጮኸባት ።

“ተው እንጂ አትቆጣት ፡ አታስፈራራት !” ሸባቦ ባሹን እየገላመጠው ያርሚያን ያባብላት ገባ ።

“አይዞሽ ያርሚያ ንገሪው ። ደሞ እንባሽን ጥረጊ ፡ ምን ያስለቅስሻል ?” አገጯዋን ደገፍ አርጎ እንባዋን ጠራረገላት ።

“የእኔ መውደድ ምን ዋጋ አለው ፡ ዘመዶቼ የተስማሙት ለእሱ ሊድሩኝ አይደለም ?”

“ዘመዶችሽ አንቺ ሳትፈልጊ ነው አማላጅ ለአባቱ የላኩት ?” ባሹ ቅር እያለው የተስፋ መቁረጥ ጥያቄውን አቀረበላት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያስ ?" ያርሚያ ገላጋይ መልሷን ለባሹ ገለጸች ለት ።

"አንቺ ወደድሽም ጠላሽ አባትሽ እንደሁ ለእኔ መዳራቸው አይቀር … ግዴለም !" ባሹ በንዴት እልህ እየተናነቀው ያርሚያና ሽባቦን እቆሙበት ትተቻቸው ታቹን ወደ ዲባጤ በሚያደርሰው መንገድ ወንዙን ተሻግሮ ሔደ ።

ከያልመሃል የታጉን እሬሳ ይዘው የመጡት ሦስት ፖሊሶች ጉብላክ እሮቢት ሠፈር እንደ ደረሱ መንደርተኛውን በማጠያየቅ ወደነያርሚያ ቤት አመሩ ።

"ይህን ሰው ያውቁታል ?" ከፖሊሶቹ አንዱ ዐሥር አለቃ በጨርቅ የተሸፈነውን የአስከሬኑን ፊት ገለጥ አርጐ የያርሚያን አባት ጠየቃቸው ። የያርሚያ አባት ደነገጡ ። ዐሥር አለቃው የጠየቃቸው ምን እንደሆነ ባይገባቸውም የልጃቸውን እሬሳ በደም ተነክሮ ሲያዩት በጦር እንደ ተወጋ ነብር እቆሙበት ሰውነታቸው ተሸማቀቀ ። "አማርኛ አያውቁም እንዴ ?" አለ ፈንጠር ብሎ የቆመው አንዱ ፖሊስ ።

የያርሚያ አባት ፖሊሶቹ ለጠየቋቸው ሁሉ ምንም መልስ ሳይሰጡ ፣ እንገታቸውን ደፍተው ወደ ቤት ገቡና ጠመንጃቸውን እያቀባበሉ ወደ ደጃፍ ተመልሰው ወጡ ።

ዐሥር አለቃው ሽጉጡን ፣ ሁለቱ ፖሊሶች ጠመንጃቸውን በፍጥነት አቀባብለው በያርሚያ አባት ላይ ደገኑ ። ኀዘንተኛው አባውንት ባቀባበሉት ጠመንጃ ወደ ሰማይ እንደ ተኰሱ ዐሥር አለቃው ከመቅጽበት ከእጃቸው ላይ ጠመንጃውን መንጭቆ በመውሰድ በቁጣ አፈጠጠባቸው ።

የያርሚያ አባት በቋንቋቸው መልሰው ከመጮህና እሪ ከማለት በቀር ከፖሊሶቹ ጋር የሚያግባባቸው አንድም ቃል አልተነፈሱም ። ወዲያው የተኰሱን ድምፅ የሰማው መንደር

t.me/OLDBOOKSPDF

ተኛ ሁሉ ተግተልትሎ ተሰበሰበ ።

"ቆንቃ አያቆም ፡ ቆንቃ አያቆም" አለ አንድ አማርኛ በመጠኑ የሚናገር የብሔረሰቡ ነዋሪ ።

"ለምንድነው የተኮሱት ?" ከፖሊሶቹ አንዱ ሰውዬውን ጠየቀው ።

"ባህል ኖ ፡ ሰው ሲሞት ወደ ሰማይ ኢንተኩሳለን ?"

"ለዚህ ልጅ ምኑ ናቸው ?"

"የቱ ?" ሰውዬው የታጌን አሬሳ አየት አረገና "አ — አ! ሊጁ ኖ" ሲል መልስ ሰጠ ።

"እንዲያው እስቲ በቋንቋቸው ንገራቸው ። ይህ ልጅ በያልመሃል በረሃ ብዙ የሻንቅላ ነዋሪዎች ጨርሶ ደረቱ ላይ ቆስሎ እንደ ወደቀ ደረስንበት ። እኛ እንዳገኘነው አድራሻውን ብቻ ነግሮን የጠቡን መንስኤ ሳያስረዳን ነው ወዲያው ነፍሱ ያረፈችው ። ስለዚህ ግጭቱ በምን እንደ ተፈጠረ ዘመዶቹ የሚያውቁትን እንዲነግሩን ብለን ነው የመጣነውና አባቱ ከሆኑ እስቲ ይህንኑ አስረድተህ ጠይቃቸው ?"

ትርጁማኑ የተባለውን ሁሉ በሻንቅልኛ ቋንቋ ለያርሚያ አባት ካስረዳና ከጠየቀ በኋላ ፡ የሰጡትን መልስ ለፖሊሶቹ ነገረ ። ፖሊሶቹ የጠቡን ምንጭ እስከ ተቻላቸው ለመረዳት የሚያሻቸውን ሁሉ ከጠየቁና ካዳመጡ በኋላ የታጌን አስከሬን ለዘመዶቹ ትተው በመጡበት ተመልሰው ሔዱ ።

ታጌ ከሞተ ኻያ ቀን አለፈው ። ሽባቡና ያርሚያም ከባሹ ቤተዘመድ በሚመጣው ወቀሳ ሕሊናቸው ሰላም ይጣ እንጂ እንደ ቀድሞው አሁንም እወንዝ መገናኘታቸው አልቀረም ። በተለይ ያርሚያ ከሽባቦ ባለመራቋና የሽምግልናውን የጋብቻ ስምምነት ባለማክበሯ በመንደሬው አረጋውያን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘንድ ተጠላች ። ወስላታና ስድ ተደርጋ ተቆጠረች ። ወቀሳና ቅጣት ከዘመዶቿም ሆነ ከባዳ ዘወትር የሚቀርብላት ምሷ ሆነ። ከሸባቦ በቀር የፍላጐቷ ደጋፊ ጠፋ ። አሽሙር ሽሙጥም በዛባት ። እያደር ይህ ሁሉ የባህል ጥቃት ሕሊናዋን አቆሰለው ። በተስፋ መቁረጥ የፍላጐቷ ባዳ ወደ መሆኑ ተጠጋች ።

ሸባቦ እወንዝ የሚመጣው ወደ ረፋዱ ላይ እንደሆነ ብታውቅም አንድ ቀን ያርሚያ ከወትሮዋ እጅግ ማልዳ የውሃ መቅጃዋን ቅሎች የቅርጫት መረቦች በተቋጠሩበት የሸመል መሸከሚያ ላይ አንጠልጥላ እወንዝ ወረደች ። ከወትሮው በተለየ የአካባቢው የተፈጥሮ ውበት ማረካት ። የፏፏቴው ፏኸትና የአዕዋፍ ዝማሬ እርስ በእርሱ ተቀናጅቶ ውበት ያለው ልዩ ዜማ ፈጠረላት ። በዚያ ለዛ ባለው የተፈጥሮ ዜማና ልዩ ቃና ባለው የአበቦች መዓዛ ውስጥ ሸባቦን ወዲያው ብታገኘው እንዴት ደስ ባላት ነበር ። ግን በጣም ዘገየባት ። ከፏፌው መኻል ቆማ ጥቂት እንዳሰበች አንድ ሐሳብ ፈልቆላት ወዲያው ጥቅጥቅ ወዳለት አበቦች ለመድረስ ተረተሩን በሩጫ ወጣችው ።

"ያርሚያ!" ሲል ተጣራ ሸባቦ ልክ ከምንፏ፡ አፋፍ እንደ ደረሰና የውሃ ቅሎቿን ተቀምጠው እንዳየ ። እሷ ግን የለችም ። ደጋግሞ ስሟን ቢጣራም ጥቅጥቅ ያለው ጫካ ድምፁን ውጦ አስቀረው ። ከወዲያም ከወዲህም ተሯሩጦ በየጢሻው ፈለጋት ። አላገኛትም ። ተመልሶ ከምንፏ፡ ዳር ካለው ሰንበሌጥ ውስጥ ሮጦ ምስግ አለ ። ያርሚያ ግን ጭራሽ ከዐይኑ አልገባ አለች ።

ቢፏንቀው ከምንፏ፡ ዐለፍ ብሎ ከወርካው ዛፍ ሥር ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ይተክዝ ገባ ። የዲባጤ መንደርተኞች


t.me/OLDBOOKSPDF

በጥልፊያ የታወቁ መሆናቸው ትዝ ቢለው ከፋ ሥጋት መልሶ መላልሶ ናላውን በጠበጠው ። "እም! ተጠልፉ መሆን አለበት!" አለ በሆዱ ፣ ባሽ ከንጓደኞቹ ማልዶ ከምንጩ ዳር በማድፈጥ ጠልፎ እንደ ወሰዷት ገምቶ ።

ግምቱን ደግሞ ደጋግሞ በሐሳቡ እያብላላ አሻግሮ ወደ ተረተሩ መመልከት ጀመረ ። ለወትሮው ከተረተሩ ላይ ቸምቸም ብለው የሚታዩት አበቦችና ቅጠላ ቅጠሎች ዛሬ ምስቅልቅል ብለውና ተበጣጥሰው ሲመለከት በጥልፊያው ሳቢያ የትረምሶች ግርግር በሥፍራው እንደ ነበር ተረድቶ የቀድሞ ጥርጣሬው ይበልጥ በልቡ ውስጥ ሥር ሰደደ ።

ወዲያው ተነሥቶ ተንኰራደደና ተመልሶ እነበረበት ድንጋይ ላይ ተቀመጠ ። ያርሚያን የማግኘትና በእፍላ ትዳር አብሯት የመኖር ተስፋው ያከተመ መስሎ ስለ ታየው ጭንቀቱ በድንገት እልህ ዘራበት ። የሚመካበት የፍቅሩ ባልንጀራ ከመዳፉ ተመንጭቃ እንደ ተወሰደች ያህል ክፉኛ ስሜቱን ነካችው ።

ለመጨረሻ ጊዜ "ያርሚያ!" ሲል ተጣራ ወደ ዲባጤ መንደር ለመዝመት ወስኖ ። እፍታም አልቆየ በሥጋቱ ላይ ድንጋጤ ተጨመረበት ። በቁጤማ የተቋጠረ እቅፍ አበባ ትከሻው ላይ ነጥሮ መሬት ወደቀ ። ሽቅብ ቀና ከማለቱ ያርሚያ ከወርካው ላይ ዘላ አጠገቡ ዱብ አለች ። የደነገጠ ልቡ ገና በቅጡ ሳይረጋጋ እተንጋለለችበት ተወርውሮ አቀፋት ። እንደ ወትሮው መገላበጥ ፣ መንከባለል ፣ ግለታቸው እስኪሰክን ድረስ ።

ተደጋግፈው እንደ ተነሡ ያርሚያ ቀጥፋ ያዘጋጀችውን በቁጤማ የተቋጠረ የአበባ ዕቅፍ ከወደቀበት አንሥታ እሽትሽት አርጋ እሽባቦ እግር ላይ በተነችው ። ሲጋብዟቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

የአባቷን ፈቃድ ማግኘቷን ማብሠሯ ነበር ። ሽባበም ከሁኔታዋ በእንዴ ተረዳ ። በእጆቹ መዳፎች ግራና ቀኝ ጉንጮቿን ደግፍ አርጐ በደስታ የፈካ ፊቷን እያስተዋለ ስለ አባቷ መፍቀድ በዝርዝር እንድታስረዳ ጉተጐታት ።

“እሀ! እሺ እንዴት ፈቀዱ?”

“እንደምታውቀው አባቴ ፊትም ለአንተ ከልክሎ ለባሹ ሊድረኝ የነበረው በለውጡ ወንድሜ ታጊ የባሹን ታላቅ እህት መዲናን ለማግባት እንዲችል ነበር ። አሁን ታጌ ከሞተ ወዲህ ግን ሌላ ወንድ ልጅ ስለሌለው ከእንግዲህ የፈቀድሽውን ልታገቢ ትችያለሽ አላስገድድሽም አለኝ” አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# እንቶኔህ

ወደ መነጋገቱ ላይ ነው ። ከምሥራቅ በኩል ሰማዩን ደግፎ አድማሱን ያካለለው ጋራ በአናቱ ላይ አሾልኮ ለጋውን የፀሐይ ጮራ ለከተማው ለማቀበል ገና በጉጉት ይጠባበቃል። ሌሊቱን ነግሦ የቆየው ጸጥታ ቦታውን ለቀኑ ሁካታ ለመልቀቅ የሚፈልግ አይመስልም ። ከወደ ደጋማው ምድር ቁልቁል የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር እንደ ባለጉዳይ ከወዲያ ወዲህ እያለ ባቅሙ ጸጥታን ሊያደፈርስ ይጥራል ። ወይ ፍንክች! ከተማይቱ እንዲሁ በጸጥታ መዳፍ ተጠፍራለች ።

በየማዕዘናቱ ካሉት ፋብሪካዎች ጥቁር ጭስ እየተጥመለመለ ይወጣና ድብዝዝ ባለው የጨረቃ ውጋጋን ውስጥ እያለፈ ወደ ሰማይ ይበተናል ። በሌሊት ፈረቃ የተመደቡት የፋብሪካ ሠራተኞች እየገፉ በመጣው ሌሊት እየተጻከሙና እንቅልፍም እየተጫጫናቸው ሲሠሩ ነፍስና ሥጋቸው ይሟገታል ። ለጸጥታ ጥበቃ የተሠማሩ ፖሊሶችና በየሥፍራው ያሉ ዘበኞችም ቆቅ ሆነው ካሳለፉት ምሽት ተላቀው እፎይ ብለው ለመተኛት የሌሊቱን መንጋት እየተጠባበቁ በያሉበት በድካምና በእንቅልፍ ያፋሽጋሉ ።

ቀሪው የከተማው ነዋሪ ሕዝብ እረጭ ብሎ ተኝቷል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንቅልፍ በየቤቱ ገብቶ በእያንዳንዱ ሕይወት ውስጥ ተንዘራፍጧል ። አንዲት ነፍስ ብቻ የእንቅልፍ ክርን አልረታትም። አልጋ በያዘ ሥጋ ውስጥ ተወሽቃ በብርቱ ሥራ ተጠምዳለች። እንደ ፋብሪካ ሠራተኞቹና እንደ ዘበኞቹ በድካም አትንገላጀጅም ። ይንጋ — አይንጋ ጉዳይዋ አይደለም ። ብቻ ሥራዋን ፡ ብርቱ ሥራዋን ማጣደፍ ።

ቀስ በቀስ ከነፋሱ ሽውታ ጋር ሌሎችም ኮሽታዎች ጸጥታውን ይጋፉት ጀመር ። ምሽት ማዛቱን ለቆ ሲሔድ በሥፍራው የቀን ብርሃን ተተካና ለሥራ ወዲያና ወዲህ ውር— ውር የሚሉ ሰዎች መታየት ጀመሩ ።

ያቺ ነፍስ ፡ እሷም ብትሆን ፋታ በሌለው የአእምሮ ሥራ ተጠምዳ አይኑጋ የለም ኑጋላት ። ከዋክብት በኅህ ውጋጋን ተጋርደው ምሽት ከተማውን ተሰናብቶ እስኪጓዝ ፡ በትንሿ ዛኒጋባ ቤት ውስጥ ጭንቀትን አርግዛ ጭንቀትን ስታምጥ የነጋላት ነፍስ የአንተነህ ነፍስ ነበረች ። አንተነህ በሻህ ውረድ ።

በዚያ ጥቁር ጽልመቱ ሲኮራ ሲጀንን ቆይቶ በዘበኞች እግዚዎታ ከተማውን ለቆ የሔደው ምሽት ለአንተነህ የምጥ ሌሊት ነበር ። ዕረፍት በሌለው የሐሳብ ሥራ የሚታደርበት ወይኑት ፡ ብርቱ ሥራ ፡ ያውም የአዕምሮ ። ጭንቀትን ለመናድ መላን በሐሳብ ሲገነባ ፡ መልሰው ሲያፈርሱ ፡ በድጋሚ ሲክቡ ፡ ደግሞ እንደገና የካቡትን ሲንዱ ያለ እንቅልፍ የሚታደርበት አሰልቺ የሌሊት ሥራ ።

አንተነህ በዚያ ዝርግ ጀርባው ታጣፊ አልጋው ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተዘርግቶ ምሽቱ በሌሊት ፡ ሌሊቱ በንጋት እስኪተካና እስኪረካከብ ድረስ ለአንድ አፍታ እንኳ እንቅልፍ የሚሉ በዐይኑ አልዞረም ። በሐሳብ መርፌና ክር የመላ ቅንጭብጭ ቢምችን ሲሰፋና ሲያያይዝ ይሆናል ብሎ የወጠነውን በስሌት ሲጥፍና ሲቀጣጥል ፡ ያ ቀውላላ ሌሊት እጥር ቁጥር ብሎ ሳያስበው ጭልጥ አለ ። ውጥኑን በሐሳብ ሲያበጃጅ ሌቱን ሙሉ ቢፈጅም ገና ምንም ዐይነት የረባ መቋጫ ላይ አልደረሰም ።

እተንጋለለበት ሆኖ ቀንም እንደሌሊቱ ያህንኑ ውትብትብ የሐሳብ ዝባዝንኪ በልኩ ሲያብላላ ቢውል ምርጫው ነበር ። ሆኖም ግን የሌሊቱን ባይተዋር ጸጥታ የቀኑ የመኪና ጭት ጥሩምባና ሁካታ ስለ ነጠቀው ፡ ተነሥቶ ወደ ውጭ ለመሔድ ዝግጅቱን ቀጠለ ።

“እንደምን አደርክ እንተንየ?” አሉት እናቱ እመት ያሰለፍ ። በእጃቸው ቁርስ መሳያ ይዘዋል ። ተገቢውን መልስ ሰጥቶ ጠረጴዛው ላይ የቀረበለትን ምግብ አትኩሮ እያስተዋለ ያለወትሯቸው ከአጠገቡ ቁጭ ያሉትን የእናቱን ሁኔታ ያሰላስል ገባ ።

“ዛሬ ደግሞ ምን ሊታወሩልኝ ይሆን?” አለ በልቡ የሰሞኑን የመንደር ወሬ እያስታወሰ ። እናቱ ከቁርስ ጋር አጣምረው ነገር ባረገዘ ሆዱ ነገር ሊጨምሩለት ሆን ብለው ማለዳው እንደ መጡ ተረዳ ።

“ዛሬ አብረን ነው እንዴ ቁርስ የምንበላው?” እናቱን ጠየቀ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

“አይደለም ። ልነግርህ የፈለኩት ጉዳይ ስላለ ነው እዚሁ ቁጭ ማለቴ ፤ መቼም አንተ የሰው ነገር አትሰማ!” አሉና ዘወትር የአዕምሮው በሽታ የነበረውን ነገር ቀስቁሰው ለዘብና ቆጣ በሚል አነጋገራቸው ያወጉት ጀመር ።

ያስለፍ ነገራቸው ብርቱ ነው ። እንኳንስ ቁም ነገር ጨዋታም አይዋጥላቸው ። በአቅራቢያው ቀርቶ ራቅ ካለ መንደርም በእኩይ ጠባያቸው የማያውቃቸውና በክፉ የማያነሣቸው ሰው የለም ። በክፋትና በተንኮል ፤ በቅናትና በምቀኝነት በየቀየው ዘልቀው ትዳር ያፈረሱ ፤ ወንዶች ያሜረሱ ፤ ልበ—ርጉም ወይዘሮ ተደርገው በሰፈሩ ይታማሉ። በመልክ የሚያውቋቸው የሩቅ መንደረተኞች እንኳ ስማቸውንና ባሕርያቸውን ልቅም አርገው ያውቃሉ ።

“እመት ያስለፍ .....” ሲባል “የቷ? — ያቺ ተንኮሏ?” መባሉ የተለመደ የመንደሬው አነጋገር ሆኗል ።

ታዲያ እመት ያስለፍ እንኳን ከባዳ ከሥጋ ዘመዶቻቸ ውም አይስማሙ ። ከልጆቻቸውም ጋር ቢሆን ያው ናቸው ። በተለይ ከትልቁ ልጃቸው ከአንተነህ ጋር ብርቱ ጭቅጭቅና ንዝንዝ ከጀመሩ ይኸው ሁለት ዓመት አልፏቸዋል ።

ያኔ ገና የአንተነህና የጽዮን ፍቅር በትኩስነቱ መድራት ሲጀምር የእመት ያስለፍ ቅናትም አብሮ ጀመረ ። ለእራሱ ለአንተነህ እንኳ ከጽዮን ጋር ያሳለፈው የፍቅር ጊዜያት ከዳር እስከዳር በእናቱ ቅናት መታጀቡ ትውስ ሲለው በጣም ይገርመዋል ። እሱ ጽዮንን ማፍቀር ሲጀምር እናቱም ያኔውኑ እሱን መጥላት ሲጀምሩ ፤ ፍቅራቸው ሲደራ የእናቱም ጥላቻ በቅናት እየጐለበተ ሲሔድ፤ እሱና እሷ የፍቅራቸውን ዓመት


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያከብሩ የእናትዬውም ቅናት ዓመቱ ታስቦ ሲውል…ያለ ፈው ሁሉ ትዝ ይለውና ለጊዜው እንደ መገረም ብሎ ኋላ ግን ዞሮ ዞሮ እወትሮው ብስጭት ውስጥ ይዘፈቃል ።

ያኔ በጅምሩ ሰሞን በእናትና ልጅ አምሳል ቅናትና ፍቅር ማብግብ ገጥመው በይሩ መሬክት ላይ ሳሉ ፤ ፍቅር ጽንነቱን ገልጾ የቅናትን ልሳን በእንበጢተኝነት ከረታ ወዲህ እናትና ልጅ ተቆራርጠው ቀሩ ።

"አይሆንም አልኩሽ? አይሆንም …እወዳታለሁ ፤ እም ናታለሁ ፤ በጭራሽ አልርቃትም ።" ከአምና ጀምሮ እናትና ልጅን አቆራርጦ ያስቀረ የፍቅር አማርኛ ። ከዚያማ ምኑ ቅጡ፡ እንደ ሐኪም ትዕዛዝ በቀን ሦስቴ እርግማኑ ፤ ስድቡ ፤ የስለቱ እግዚኦታ ፤ የመካረው ጋጋታ የእንተነህ የብዙ ወራት ባላንጣዎች ነበሩ ።

ምንም ይግጠመው ምንም ፤ እንተነህ ፤ እንተነህ ነው፤ ጽዮንም ጽዮን ናት ፤ ፍቅር ደግሞ ሁለቱንም ሆኗል ። እሷ ለእሱ ፤ እሱ ለእሷ የአንድ ነፍስ የአካል ዝንጣፊ እንዲሆኑ ያህል ጥቃትን ችለው ፍቅራቸውን አደረጁት ። የመንደሬው የአሉባልታ እሾህ ፤ የእናትየው የቅናት ወረንጦ እያደር ብስጭት ውስጥ ይጨምራቸው እንጂ ሊያለያያቸው ግን በጭራሽ አልቻለም ።

እንተነህና ጽዮን ገና ከጮርቃነታቸው አፈር ፈጭ ተው ፤ ጭቃ አቡክተው ማደጋቸውን ድፍን መንደሩ የሚያ ውቀው ቢሆንም ፤ ፍቅር በሚሉት መንቻካ ሰንሰለት መተሳሰራቸው ግን ነፍስ ካወቀ ወዲህ የመጣ መሆኑን ከአንዳንዶቹ በቀር ብዙዎች አያውቁትም ።

"የልጅ ፍቅር ያመናቅር" ይላሉ አንዳንዶች ሊያንኳስ ሷቸው ሲፈልጉ ። አንዳንዶቹም መዋደዳቸውስ ደግ ነበር ፤


t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኑ ሳጂን የሰሙ ጊዜ "ጉድ ይፈላል እንጂ! ይላሉ ። ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ አይደል? ሳጂን ገረመው አለመስማታቸው እንጂ ቢሰሙስ ልጃቸውን ከቤት አስወጥተው ያባርሯት ነበር።" አስተዋይ ነን ባዮች ሁሉ የመሰላቸውን ወሬ ሲያስኳኩ አያሌ ወራት አልፈዋል ።

እንተነህና ጽዮን በመጀመሪያው የፍቅር ዓመታቸው ሁሉንም ነገር በትዕግሥት ችለው አሳልፈው ነበር ። ዘንድሮ ግን ትዕግሥት የማይችለው አስከፊ መከራ የፈጥኝ አስሮ ያንገላታቸዋል ። አንዱን ሲሉት አንዱ ፣ አልረጋ ያለ ችግር የሥጋት ሠራዊቱን አሽቆጥቁጦ የላከባቸው ዘንድሮ ነው ። ዘንድሮ ፣ ከወትሮው የባሰ ቀውጢ መከራ ዐይኑን አፍጥጦ ከእሱም ሆነ ከእሷ ቤተሰብ ክፉኛ ተጭኗቸዋል ።

በሁለቱም ልቦና ውስጥ ሥጋት ሐሳብ ጭንቀት ደቂቃ በደቂቃ ይላወሳል ። እንዳይተኙ ፣ እንቅልፍ የሚሉ በዐይናቸው እንዳይዞር ። ለዚህ ነበር እንተነህ ሌሊቱን ከሐሳብ ጋር ትግል ገጥሞ የነጋለት ። ታዲያ ያን ያህል ሌሊቱን ሲያስብ ሲያሰላስል ቢያድርም ተጨምቆ ጠብ ያለ ቁራጭ ብልሃት እንኳ ያገኝ አይመስልም ። ብቻ ቢሆንም ባይሆንም አንድ ነገር ሳያዘጋጅ አልቀረም ። ክፉኛ መሸበሩ ግን አሁንም ግንባሩ ላይ ይነበባል ።

እመት ያስለፍ ማልደው እመኝታ ክፍሉ ድረስ መጥተው ያቀረቡለት ሐሳብ ተቀባይነትን አላገኘም ። በግነዋል ። በመለማመጥም ፣ በማስፈራራትም እንዲቀበላቸው የዋተቱት ሁሉ በልጃቸው አሻፈረኝ ባይነት ከንቱ ሆኖ ቀርቷል ። ጽዮን አትሆንህም ተዋት! ከነባችሁ እንደማይገጥም ሁነኛ ዐዋቂ ነግሮኛል ። ብትረሳት ነው የሚበጅህ ፣ ኋላ ነገሬሃለሁ ፣ ልባርግ! የሚለው እምብርት ሐሳባቸው በስላ እምቢታ


t.me/OLDBOOKSPDF

ተቆርጦ ተደምድሟል ።

"በቃ አሻፈረኝ ማለትህ ነው?"

"አዎ ፣ እንዲያውም ከቁጥጥራችን ውጭ ሆና አርግዛለች ።"

"ኧ! ምን ... ምን?"

"አርግዛለች!"

"ከማን?"

"ከእኔው ።"

"እውነትክን ነው? እስቲ ወላዲት አምላክን ክለኝ!"

"እንዴ ነግሬሻለሁ ።"

እመት ያሰለፍ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ። ዘራቸውን አረገሙት ። መፈጠራቸውን ጠሉት ። የተፀነሰውን የልጃቸውን ልጅ ሳይቀር በእናቱ በጽዮን ማሕፀን ውስጥ እንዳለ ውሃ ሆኖ እንዲቀር ልሳናቸው የፈቀደውን ያህል ጮኸው ተሳሉ ። ምስኪኗን ጽዮንንም ጭምር ለሞት እየተመኙ ለፈጣሪ አሳቀቧት ። ጥቂት ቆይተው እንባቸው ጐረድ ፣ እልሃቸው በረድ ሲል ትንፋሻቸውን ዋጥ ፣ ለቅሷቸውን እምቅ አረጉና አንተነህ የጽዮንን እርግዝና እንዲክድ ደግመው ደጋግመው ገዘቱት ።

አንተነህ ፣ አሻፈረኝ ባይነቱን ጭንቅ ባለው ድምፅ ከአንደበቱ ተንፍሶ የታሸገ ፖስታ ከመኝታው ትራስ ሥር አነሣና እናቱን ብቻቸውን ትቷቸው ምንጥቅ ብሎ ከቤት ወጣ። በሕሊናው የምትታየው ጽዮን ናት ። የጽዮን ምስል ድረስልኝ ያለው ይመስል ዐይኖቹ እንባ እያቀረሩ በፍጥነት የግቢውን በር ተራምዶ ወጣ ።

በአንተነህ ሕሊና ውስጥ የምትገላበጠው ጽዮን የዛሬን አያርገው እንጂ በልጅነቷ በትሑት ጠባይዋና በቤት ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥራዋ በዐዋቂዎች ዘንድ የተመሰገነች ወጣት ነበረች ። ያኔ እንኳን በአባቷ በሳጂን ገረመው ፣ በሚያውቃት መንደርተኛ ሁሉ ነጋ — ጠባ እንዳልተመረቀች ዘንድሮ አርግዛ መታየቷ አይ የቤት ነገር! ያላሰኘው የለም ። በተለይ ልጅን ቀጥቶ በማሳደግ ሀገር ያመሰገናቸው ሳጂን ከጽዮን ያልጠበቁትን ነገር በማየታቸው ነፍሳቸው ሲአል እንደ ወረደች ፣ ሥጋቸው ኃፍረትና ውርደት እንደ ነካው አርገው ቆጥረውታል ።

ሲመስላቸው የሰው ነገር የማይሰሙት ሳጂን ዛሬ የሰው ወሬ ረታቸው ። ያኔ "ምን ጐደለሽ? ምን ላርግልሽ?" እያሉ በአባትነት ፍቅራቸው እንዳልተንከባከቧት ሁሉ ፣ ዛሬ ለዐይናቸውም ማየት ጠልተዋታል ። ለዚህ ነው መከረሚያውን ስድብ ፣ ዘለፋ ፣ ጥፊ ፣ ቁጣ ነጋ ጠባ በጽዮን ላይ የሚያከናውኑት ተግባራቸው ሆኖ የሰነበተው ።

ሳጂን ሌላው ቀርቶ ከማን እንዳረገዘች እንኳ ሊያውቁ አለመቻላቸው ዘወትር ያበሳጫቸዋል ። "ከማነው...?" ለሚለው ጥያቄያቸው የምትሰነዝረው መልስ አጭርና መልሶ እሳቸውን እርር — ብግን የሚያደርግ ፣ "ከነፋስ!" የሚል ነበር የጽዮን የዘወትርና የማይለዋወጥ መልስ ። ያ ሁሉ ብስጭታቸው ውስጥ ውስጡን ያለቅጥ ተጠራቅሞ ሌሊቱን እንቅልፍ ነሥቷቸው አደረ ። ማልደውም አልበረደላቸው ። ጊዜው እየረፈደ ሲሔድም ያለቅጥ መንፈሳቸው እየተረበሸ ሰውነታቸውን ያንዘፈዝፈው ገባ ። ወዲያው "ጽዮን!" ብለው ወደ ጓዳ ተጣሩ ። እጃቸው ይንቀጠቀጣል ። ዐይኖቻቸው ተጉረጥርጠው ጣር እንደ ያዘው ሕመምተኛ ጣሪያ — ጣሪያውን ያማትራሉ ።

ጭንቀት ፣ ሥጋትና ብስጭት ፣ ሰላም ካጣ አዕምሮ ጋር አካላቷን እየሸረሸረና ውበቷን ቀስ በቀስ እየፈገፈገ ኩስምን

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ያረጋት ጉብል እየተንቀጠቀጠችና ልቧ በፍርሃት እየዳዳ አባቷ ወደ ጠሯት ክፍል መጣች ። በዐይኗ እንባ ግጥም እንዳለ ነው ። እንደ ፈጠመቀችው ወደ አባቷ ቀና ብላ አየችና ። ከጊዜ ወዲህ እየገጠሙ የመጡት ጉንጮቿ ከዐይኖቿ የሚረግፉትን የእንባ ዃሎች እንደ በረዶ አሸዋ ጠጥተው ሲጠግቡ የተረፉትን ቁልቁል ያፈሱታል ።

ሳጂን በፉርቅ መሳይ የሚጠራርጉትን ሽጉጣቸውን እፍን አርገው በቀኝ እጃቸው ከያዙ በኋላ ወደ ግንባሯ ያቅነው ፡ "ዛሬ የኔም የአንቺም የመፈረሻ ቀን ነው ። ነፍስሽ ነፍሴን ይዛ ሲኦል ልትወርድ ተቃርባለች ..." አሉና በቁጣ አፈጠጡባት ። እጃቸው አሁንም ይንቀጠቀጣል ። ዐይኖቻቸውም መንቀረጥረጡን አላቋረጠም ። የእሷም ዐይኖች ቢሆኑ ሽጉጥ አባቷ ወደ ፊበቡት ሽጉጥ ላይ ተተክለዋል ። ይሁን እንጂ ዐይኖቿ ያለማቋረጥ በሚያመነጩት እንባ በመጋረጃቸው ሁሉም ነገር የሚታያት ድብዝዝ ብሎ ነው ። በእንባ መስታወት ውስጥ ዐልፎ የሚታይ ሽጉጥ ምን እንደሚመስል የሚያውቁት እሷና ሕሊናዋ ብቻ ናቸው ። ጭምቅ አርጋ እንባዋን ትንድና በሥጋት ያየችውን እይታ ሳትጠግብ መልሶ ሌላ እንባ ከዐይኗ መንጭቶ እይታዋን ያደበዝዘዋል ። የሚንቀጠቀጠው የአባቷ እጅ አንዳንዴ ሁለት እየሆነባት ፡ አንዳንዴም ጥቁር ቦት ጫማ እየመሰላት በጭንቀት ወረርሽኝ ስትሠቃይ ትልቅ ፊሽት በጆሮዋ ጥልቅ አለ ።

"ስማሽ? አንቺን ነውኮ ፡ መልሺልኝ እንጂ!" እልህ ያጐረነነው ድምፃቸው ከአንደበታቸው ፈንቅሎ ሲወጣ ጉሮሯቸው ላይ በተወተፈ ፊርቅ የታነቁ ይመስላሉ ። "ሲ... ሲኦል ሳንወርድ በፊት ከማን እንዳረገዝሽ ንገሪኝ? ... ንገሪኝ ነው የምለው ማነው እሱ?" የሚንቀጠቀጠው እጃቸው


t.me/OLDBOOKSPDF

ሽጉጡን አጥብቆ ያዘ ።

ጽዮን ከዐይኗ ይበልጥ ጆሮዋ ተሠቃየ ። ጆሮዋም እንደ ዐይኗ ቢያንባ ኖሮ ፊቷ ሽቱም በደበዘዘላት ነበር ። በሥጋት ይተኮሳል ብላ ከምትጠብቀው የሽጉጥ ድምፅ ባላነሰ የአባቷ ፊሽክት አሁንም አሁንም ጆሮዋ ላይ እያንባረቀ ይንዘራ ታል። ከዐቅሙ በላይ ጭንቀትን መሸከም ያልቻለው አዕም ሮዋ ጆሮዋን እያንቋሮና ምላሷን ሸብቦ ፡ ለዐይኖቿ ብርቱ ለቅሶን ፡ ለልቧ ፈጣን ትርታን አዘዘና ለራሱ ደንዝዞ ጭልጥ አለ ።

ሳጂን ተስፋ ቆረጡ ። "ሲኦል ለመውረድ ያንቺ መልስ አያሻኝም! ... የጐደፈው ስሜ በሲኦል እሳት ይታጠባል!" አሉና የሽጉጣቸውን መጠበቂያ አላቀው ሌባ ጣታቸውን በምላጩ ላይ አኖሩት ። የሚንቀጠቀጥ ጣታቸው ምላጩን ለመሳብ እንደጎና ለመልቀቅ ደግሞ ለመሳቢን እየታቀጣ ፡ የልባቸውን ውሳኔ ሲጠባበቅ ይቆይና ከማንም ታርግዝ ከማንም የዲቃላዋን አባት ማወቁ በሲኦል ቤት ለውጥ እንደሌለው ሕሊናቸው ፈርዶ ፡ ሳትሞት የሞተችውን ሕይ ወት ገላግለው ለመገላገል እንዳሰቡ አንድ ሰው ዘሎ እቤት ገባ።

"አንተነህ!" አለች ጽዮን ሰውነቷ እንደ ሽምቅቅ እንደ ፈታ እያለ ። ድምጿ የለቅሶ ቅልቅል ዐይነት ነበር ። ሕቅታ የበዛበት ። አንተነህ ከምትር ያለ ሰውነቱን ቅንጥስ አርጐ እሳጂን ጉልበት ላይ ወደቀ ።

"ምንድነው ጉዳዩ ፡ ምን ልትፈጥር መጣህ?" የሚጉረ ጠረጥ ዐይናቸውን ቁልቁል ወደ አንተነህ ተክለው በጥያቄ ተቆጡት ።

"ይማሩኝ ሳጂን ፡ ይቅር ይበሉኝ!" ነፍስ ካወቀ ወዲህ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንባ ነዝረው የማያውቁት ያንተነህ ዐይኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ። ጽዋንም ከአንተነህ ጉን አስቀ እግር ላይ ወደቀች ። የእሷም ዐይኖች ቢሆኑ እንባ የማመን ፈት ተግባራቸውን ያበልጥ በትጋት ተያያዙት ።

ሳጂን እቶሙበት ደንገዘው ቀሩ ። ልባቸውን በአንድ ፈት የሲአል መስተንግዶ እየጠራው በሌላም በኩል ከእግራቸው ሥር የሚዘንበው የሁለቱ ወጣቶች እንባ እየቀጠቀጠው የፍርድና የምሕረት ብያኔ መሚገቻ ሆኖ መኻል ቤት ይዋዥቅ ገባ ። "..የ... የሲአል መንገደኛ ነኝ ፣ የእናንተን አቤቱታ የምሰማበት ጊዜ የለኝም ። እግሬን ልቀቁ!" ሲሉ ሳጂን ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ ዋዣቂው ልባቸው ያዘዛቸውን በፌዠኸት ተናገሩ ።

ያንን አጥፍቶ ልጥፉ ባዩን ልባቸውን የኋላ ኋላ እንዳት ወፍራም የእንባ እንክብል ገሠጻቸው ። አንተነህ ግንባሩን የደፋበት የሳጂን የግራ እግር ሹራብ አያስ የእንባ ወራጆችን ጠጥቶ ሲጠግብ ገላጋይዋ የእንባ ጠብታ ሹራቡን ዘልቃ የእግራቸውን መታጠፊያ ለማራስና ለማቀዝቀዝ በመብቃቷ የሲአል መንገደኛው ልብ ወደ ምድር ተመለሰ ። በድንገት የሳጂን ጉርጥርጥ ዐይኖች ወዛ ወዛ እያሉ ሒደው በተራቸው የእንባ ኩሬ ሆኑ ።

ሳጂን እንባቸውን በክንዳቸው ጠረግ ጠረግ አረጉና ፊታቸውን አራት ፣ ግንባራቸውን ስለት ፊጥረውበት "ተነሡ! ምንድነው ነገሩ ... የመጣህበትን ጉዳዩን ንገረኝ" አሉ ወደ አንተነህ እያተኮሩ ።

አንተነህ የተጨበጠ አካሉን በአቋቋሙ እያቀና እንደ ፊኛ ያበጠውን ፊቱን ወደ ሳጂን ቀና አርጐ መልሶ አቀረቀረ። እሚናገረው ጠፋበት ። ምን እንደሚል ፣ ምንስ ለመናገር


t.me/OLDBOOKSPDF

የትኛውን ቃል እንደሚያስቀድም ለጊዜው ማገናዘቡ ቶስ ኗት ጸጥ ብሎ ቆመ ። "እኮ ምንድነው ጉዳዩ? አትናገርም እንዴ የመጣህበትን? " አሉ ሳጂን አሁንም ከውስጥ የበቀለ ርንራኂያቸውን ያብቀው ውጫቸውን ቱቡ በማስመሰል ። እንተነህ ቀና ብሎ አያቸውና ከደረት ኪሱ የታሸገ ፖስታ አውጥቶ ሰጥቷቸው በሩን ለቆ ወጣ ።

ሳጂን ከእንተነህ የተቀበሉትን ፖስታ ቀደው ደብዳቤ ውን ሁለት ሦስቴ ደጋግመው አነበቡት ። አዲስ መንፈስ ከደም ሥራቸው የሚንቆረቆር ይመስላል ። ፊካ ያለ ገጽታ ከፊታቸው ላይ ተንጸባርቆ የጽዮንን የፌዘ ለመ ልቡና የተሰሩ ጭላንጭል ፈነጠቀበት ።

"ደግ! ... ማለፊያ! ታዲያ የደበቅሽኝ ለዚህ ኖሯል? ፊቱኑ ልትነግሪኝ ሲገባ ... አጥፍተሽ ልታጠፊኝ ነበር ። በየት ፡ በየት እንዲህ ያለውን ነገር እንደ ፈጸማችሁት ባይገባኝም ብቻ እንተነህ መሆኑ ደግ ነው ። ባልወልደውም እንደ ልጄ ያሳደኩት የጐረቤት ልጅ ነው ። ጥሩ ልጅ መሆኑንም ዐውቃለሁ ፡ ነገሩ እንዲህ ከሆነ እሱ መሆኑ ቅር አይለኝም ። አብሮሽ ሊዘልቅ የሚችል እውነተኛ ባልንጀራሽ እንደሆነ ከጽሑፉም ፡ ከሁኔታውም ዐውቂያለሁ ። ወግና ደንቡ መደፈሩ እንጂ መቼም እንዴ ከሆነ ምን ይደረጋል!... በአሁኑ ጊዜያችሁ እራሳችሁን ችላችሁ በትዳር ጐጆ እስክት ወጡ የእኔ እርዳታ እንደሚያስፈልጋችሁ ዐውቃለሁ ። ለማና ቸውም ሁሉታችሁ ባላችሁበት የአባትነቴን የምመክራችሁ ብዙ ነገር አለና መክረሚያውን እንዲያውም እሑድ ዕለት እዚህ እንዲመጣ ንገሪው ። ምሳም እንጋብዘዋለን ። በተረፈ ከእንግዲህ ብዙም አትሥጊ ፡ አሁን ሒጂና ፊትሽን ታጠቢ " አሏት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሰለቲ ዓርብ ፡ ግዜው እኩለ ሌሊት ላይ ነው ። እንተነህ በጀርባው አልጋው ላይ ተንጋልሏል ። ዐይኖቹ የእንትልና ሲሳይ ትንፋሾቻቸው ሽቶብ ማሪያው ላይ ይንከራተታሉ ። በአቅራቢያው ማንም ሰው የለም ። ብቻውን አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ሆኖ በአዕምሮው የሚርመሰመሰውን ያዳምጣል። እንጽዮን ቤት የታየው የአባትና ልጅ ትንቅንቅ ሥጋት ውስጥ ጥሎታል ። ሳጂን በጽዮን ግንባር ላይ ሽጉጣቸውን ደቅነው ያፈጠጡት ከእርግዝናዋ ጋር በተያያዘ ጉዳይ እንደሆነ ሲያውቅም አደናፈራቸውና ጭካኔያቸው እጅግ ዘግንኖታል ። እሱ ለሳጂን ሥጋታውን ሰጥቶ ከሔደ በኋላ እምን ደረጃ ላይ እንደ ደረሱ አያውቅም ። ሳጂን በጦር ሜዳ ፡ ቆራጥ ደፋርና ጨካኝ ስለ መሆናቸው የሚወራውን አስታውሶ ይህንኑ ጭካኔ በልጃቸው ላይ ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይሉ አርጎ ቈጠረ ።

"በጽዮን ላይ ሽጉጥ? ... እንዴት — እንዴት ይሆናል" በማለት በቅዠት ዐይነት አነጋገር ድምፁን ዝቅ አርጎ አማተበ ። "በእኔው ጣጣ ሞተች አይደል?" በዐይነ ሕሊናው የጽዮን ግንባር በጥይት ሲተረተር ታየውና ዘግንኖት ሽምቅቅ አለ ። የፊጥኝ ተጨባብጠው የነበሩትን የእጆቹን መዳፎች አላቆ በግራ እጁ ላይ ያለችውን ሰዓት ተመለከተና በረዥሙ ተነፈሰ ። በልቡ የሚንቀለቀለውን የጭንቀት እሳት መልሶ መላልሶ ስለ ፈጀው የታመቀ ሥቃዩን የተፋው እየመሰለው ደግሞ ደጋግሞ ይተነፍሳል ። በጭራሽ ጋብ ሊልለት አልቻለም ።

ከተንጋለለበት ተነሥቶ ሲንቆራጠጥ ጥቂት ቆየና ከቤቱ ወጥቶ በግቢው መኻል ላይ ካለው የዋንዛ ግንድ ላይ ተደግፎ ቆመ ። የነፋሻው አየር ቅዝቃዜ ለጊዜው ቢያረካውም ሕሊናው ግን አሁንም ጤና አላገኘም ። በውድቅት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌሊት ከራሱ ልቦና ጋር ንዝንዙን ተያያዘው ። ብስጭት ከወዲያ ወዲህ ያወዛውዘዋል ። እራሱን በራሱ በጥያቄ እያፋጠጠ እንጉሉን በንዴት ያተራምሰው ገባ ። ጭው ባለ የሐሳብ ገደል ውስጥ ሰምጦ ቀረ ።

ወዲያው "ድም ... ድም" የሚል ድምፅ ከሐሳቡ ቀሰቀሰውና ዐይኖቹን ወዲያና ወዲህ ቢያውማራ ምንነቱን የማይለየው ነገር ውልብ ብሎ ተሰወረበት ። እንተንሀም ድንጋጤም አልሰጠውም ። ነገሩን ችላ ብሎ ቀድሞ ወደ ነበረበት የሐሳብ ሥራዊት ተቀላቀለ ።

እፍታም ሳይቆይ የማቢው በር በጣም ተንኳኳ ። ጠመንጃ የያዙ ሰዎችም በአጥር ዱብ ዱብ እያሉ ዘለው ይገቡ ጀመር ። እንተንህ በዚህ ውድቅት ሌሊት ምንም ይመጣል ብሎ ስላልገመተ ድንጋጤው እቶመበት በድን አደረገው ። "ቁም ! እንዳትንቀሳቀስ !" የሚል ከባድ ጩኸት እንደ መብረቅ ጆሮውን ሰንጥቆት ገባ ። ለካስ ፖሊሶች ኖረዋል ። ፈጥነው በመጠጋት የሰደፍ ዱላቸውን ካሳረፉበት በኋላ መላ አካላቱን ይፈትሹት ጀመር ። ነገር ግን ምንም አላገኙበትም ።

"አንተ እዚህ እሱን ጠብቀው ፤ ሌሎቻችሁ ማቢውን ፈትሹ" አለ ከፖሊሶቹ አንዱ ። ወዲያው በየጉራንጉሩ ማቢው ይታሰስ ገባ ። ብዙም ሳይቆይ ከማድ ቤቱ አጠገብ ካለው አጥር ሥር በጆንያ የተጠቀለሉ ልዩ ልዩ የመለዋወጫ ዕቃዎች ተገኙ ። "ይኸውና ተገኝቷል ! መደበቁ ነበር?" አለ በጆንያ የተሞሉትን ዕቃዎች ያገኘው ወታደር ።

ግርግሩ ከእንቅልፍ የቀሰቀሳቸው እመት ያሰለፍ ልጃቸውንና ተያዘ የተባለውን ዕቃ ከፖሊሶች ጋር ሲመለከቱ ነገሩ እንደ ሕልም ሆነባቸው ። ወዲያውኑ የጉዳዩን ምንነት


t.me/OLDBOOKSPDF

ጠይቀው ሳይረዱ ፖሊሶቹ እንተነህንና ዕቃውን በላንድሮ
ቨር መኪናቸው ጭነው ወደ ጣቢያ ሔዱ ።

በማግሥቱ ጠዋት ጽዮን አባቷ ያዘጋጁትን የእሑድ ዕለት ቀጠሮ ለመንገር ወደ እንተነህ ቤት ሔደች ። እንዳሰበችው እንተነህን አላገኘችውም ። እንዲያውም ያልጠበቀችው የስድብና የእርግማን መዓት ገጠማት ። እመት ያሰለፍ አራስ ነብር ሆነው "አንቺ ገሬ ! ገሬ  የገሬ ዘር ፡ ሐጅ ጥፊ ከዚህ ! ነፍስሽን ያጥፋውና ..." ብለው ጽዮንን አሳቀው መለሷት ።

ከእንተነህ ቤት ቆሌዋ ተገፎ የተመለሰችው ጽዮን ክፉኛ በመደንገጧ አዕምሮዋ ተረበሸ ። እቤታቸው ጓሮ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። በተጐሳቆለው ሕሊናዋ ላይ ብርቱ ድንጋጤና ምሬር ያለ ኀዘን ተጨምሮበት ጤንነቷን አደፈረሰው ። አጥወለወላት ። ደግሞ ደጋግሞ አስመለሳትና አዞሯት ጥቅልል ብላ ወደቀች ።

ጽዮን የእንተነህን መታሰር የሰማችው ታማ አልጋ ላይ በወደቀች በሦስተኛው ቀኗ ነበር ። በተለይ መታሰሩን ከሰማች ወዲህ በየቀኑ ሕመሟ እየጠናባት እንጂ እየተሻላት አልሔደም ። የመንደር ሐኪም ካንዴም ሁለቴ ተጠርቶ ሕክምና ቢያደርግላትም ለጊዜው ሻል ይላትና መልሶ ያገረሽባታል ። ሕመሟ ምን እንደሆነ ተለይቶ ባይታወቅም የእንተነህ መታሰር መንፈሷን እንዳናጋው ግን ወላጆቿ አበክረው ዐውቀዋል ። እያደር ቋንቋዋ ሁሉ የእንተነህን ስም መጥራት ብቻ ሆነ ።

ሳጂን ገረመው ፡ የእንተነህ መታሰር በጽዮን ላይ ያስከተለውን ጉዳት በማስተዋል ክሱን ለመከታተልና ከተቻለም ዋስ ሆነው ለማስፈታት ፖሊስ ጣቢያ መመላለሱን ተያያዙት። ሆኖም ግን እንተነህ የታሰረበት ጉዳይ በዋስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሬታት እንደማያበቃው ተነግሯቸው ጥረታቸው ብዙም አልቀጠለ። የሬያት የመለዋወጫ ዕቃ መጋዘኑን ለብዙ ጊዜያት ሲያራቁት የቆየ ሌባ እንደሆነ የተነገራቸው ሳጂን ፡ ጉዳዩ ሊሆን እንደማይችል ቢታወቃቸውም ፡ ከአንተነህ ግቢ በውድቅት ሌሊት የተገኘውንና በኤግዚቢት የቀረበውን ዕቃ ሲመለከቱ ብርቱ ጥርጣሬ ላይ ሳይወድቁ አልቀሩም ።

እንተነህ እስር ቤት እንዳለ ሁለት ወራት አለፈው ። "ይቺ ገሬ ናት ልጄን ጻፉ ውስጥ የጨመረችው" የሚሉት እናቱ እንኳ አዘውትረው ጽዮንን ዐልፎ ዐልፎም እራሱን እንተነህን ከማማረርና ከመርገም በስተቀር ለመጠየቅ ማቢያ እሚሉ ዝርም ብለው አያውቁ ። የፈረደባት ጽዮን ነበረች አልጋዋ ላይ ሆና በየወቅቱ ምግብ እንዲሔድለት ወላጆቿን እየወተወተች የምታስልክለት ።

ጽዮን ፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ሕመሟ እየበረታባት እንጂ እየተሻላት አልሔደም ። እንደ ከዋክብት እርቀው የሚናፍቋት የእንተነህ ዐይኖች የሕሊና ዕረፍት እየነሷት ሕመሟን ይበልጥ እያባባሱት ሔዱ ። እንደ ምንም ተግተርትራ ፖሊስ ማቢያ ድረስ ሔዳ ልትጠይቀው በልቧ ትከጅልና ከአልጋዋ ለመውረድ ስትጣጣር አዙሯት ትወድቃለች ። እያደር በበሽታ ላይ ሐሳብ ፡ በዚያ ላይ ደግሞ የወሊድ ጊዜዋ መቃረብ ሁሉም ተደራርበው የረገፈ ሰውነቷን ይብስ አረገፉት ።

የእንተነህ ጉዳይ ለማቢያው የምርመራ ቡድን መላቅጡን ያጣ ችግር በመፍጠሩ ሌሎች አስተማማኝ መረጃዎች እስኪገኙ ድረስ እስር ቤት እንዲቆይ ተደርጓል ። እስር ቤትም ሆኖ ያንኑ የጽዮንን ጉዳይ በማብሰልሰል ሳይጨነቅ አልቀረም። ለአባቷ ምስጢር የያዘውን ደብዳቤ ከሰጠ ወዲህ



t.me/OLDBOOKSPDF

በንጽዮን ቤት ምን እንደተፈጠረ ለብዙ ሳምንታት አላወቀም ነበር ። ያ ሁሉ በልፎ በጾኑ ሕመም ላይ መገኘቷንና በየዕለቱም እየጠናባት መሔዱን መስማት የጀመረው ባለፈው ሳምንታት እስረኛና ጠያቂ እንዲገናኙ ከተፈቀደ ወዲህ ነው። ሰሞኑን ግን በየቀኑ ምግብ እየያዙላት የሚመጡት የጽዮን ታናሽ ወንድሞችም እስከነአካቴያቸው ስለቀሩ ፤ ምንጊዜና ሐሳቡ ጠጥሮ ሕሊናው ይበልጥ ሰላም አጥቷል ።

እስር ቤቱ ከውስጥ ጨለምለም ብሏል ። እንተነህ ከማዕዘን በኩል የማድግዳውን ጥግ ይዞ አንገቱን ደፍቶ ተቀምጧል ። አንዳንድ እስረኞች ካርታ ሲጫወቱ አንዳንዶቹ ደግሞ ሐሳብ እንደሌለባቸው ሁሉ ጧ. ባለ እንቅልፍ ውስጥ ያንኮራፉሉ ። ቀልድ የሚያወሩም አሉ ። ጥርሱን የሚፋቅም ይገኛል ። እንተነህ ግን በሐሳብ ውጣ ውረድ ውስጥ ይማስናል ።

"ወንድም ! ወንድም !" አለው እንተነህን አንድ ከሆስፒታል ሕመሙ ተሽሎት ዛሬ ጠዋት የመጣ እስረኛ ።

እንተነህ ከነበረበት ትካዜ ልቡን መለስ አርጎ "አቤት! አናገርከኝ?" አለው ።

"ምን ሆንሃል ታስባለህ እንዴ?...አይዞህ አትጨነቅ ፤ መታሰር እንደሁ ያለ ነው !" አለው ገመምተኛው እስረኛ ሊያጽናናው ትከሻውን መታ መታ እያረገው ።

"አይ...እንዲያው ዝምብዬ ነው ።" ባጭሩ መለሰለት።

"ታዲያ ለምን ዝም ትላለህ? እንጫወት እንጂ ፤ ካልተጫወቱ እኮ እስር ቤት ውስጥ ጊዜው አይሔድም " አለና ወዲያው ከተል አርጎ ፤ "ደግሞም እንተዋወቅ ፤ እኔ ሽመታው እባላለሁ ... አንተስ?"

እንተነህ ፤ ገመምተኛው እስረኛ የጠየቀውን ሁሉ


t.me/OLDBOOKSPDF

ፊጽሞ ተመልሶ ሊያቀረቅር ሲከጅለው ፡ "የእኔን ስም ስምተህ አታውቅም? ስሜን ድፍን ከተማው ያውቀዋል ... መቼም ይኸ ሙያዬ ያላስተዋወቀኝ ሰው የለም" አለ ሽመታው ኩምትር ያለ ፊቱን ፈካ አድርጎ ።

"ምንድነው ሙያህ?" አንተነህ ጠየቀው ።

"ሌብነት ነዋ! እንዴት ስሜን እንኳን አልሰማህም?"

"በእርግጥ ስምህን እዚህ ማቤያ ከመጣሁ ፖሊሶች እየደነቁ ስለ ሠሯኸቸው ሥራዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ ። አንተ መሆንክን ግን በጭራሽ አላውቅም ነበር ።"

ሽመታው "አዎን — አዎን! በሌብነት ብዙ ታሪክ አለኝ" አለና የፈጸማቸውን የሥርቆት ሥራዎች እንደ ጀብዱ ለማውራት ደረቱን ኩራ ፡ ጩልጩል ዐይኖቹን ፈካ አረገ ። "በዚህ ከተማ ያልሰረቅኩት ቴጃር የለም ። በተለይ ከቴጃር መስረቅ ቀላል ነው ። ብዙ ጊዜ የሚያስቸግሩኝ የመንግሥት መ ቢሮችና ድርጅቶች ብቻ ናቸው ። ብዙ ጊዜ ታስሬ ስፈታ አንድም ቀን እንኳ ከቴጃር ስሰርቅ የተያዝኩበት አጋጣሚ የለም ..." ብሎ ወሬውን በስፊው ለመተረክ አቀማመጡን አሣመረ ።

አንተነህ በዚህ ዐይነቱ ጨዋታ ቢገፋበት በመጠኑ የሚያዝናናው መስሎ ስለ ታየው የሽመታውን ወሬ በጥሞና ይከታተል ጀመር ። ሽመታው በሌብነት ሥምሪት ውስጥ ካጋጠሙት ድንቅ ሁኔታዎች መካል ጥቂቶቹን እየመረጠ ሲያወራለት ቆይቶ የአንተነህን ልብ ከፋኛ ያስደነገጠውን የመለዋወጫ ዕቃ ሥርቆት ታሪክ ጀመረለት ።

"...አ! ብዙ ነው ። ግን ምን የሌባ ነገር መያዝ በሚገባው ሳይያዝ በቀላል ነገር ነው ፖሊሶች እጅ የሚገባው። አንዴ ትዝ ይለኛል እንደ ለመድኩት ከፋይት መጋዘን


t.me/OLDBOOKSPDF

ያዘና ዋጋ ያላቸው የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎችን በድንጋይ አግበስብሼ እንደ ወጣሁ ያላሰብኩት የነዚህ ሉጂዎች (ፖሊስ ሶች) ላንድሮቨር እፊቴ ድቅን ማለት!'' ሲል እንተኑነህ ሀይኑን አፍጥጦ ከተቀመጠበት ሊነሣ ምንም አልቀረውም ።

ወዲያው መጨረሻውን ለመስማት እንደ ምንም ራሱን ተቈጣጠረና ፡ "እሺ ከዚያስ ፡ እንዴት አመለጥክ?" አለው ለወሬው እድናቆት ያለም በማስመሰል ።

"...ከዚያማ ምኑ ቅጡ! ዕቃዬን እንዳልጥል አንኳን ፡ እንዳለ ተሸክሜ ፊት ለፊት ባሉት መንደሮች ውስጥ ሽመጠጥኩ ። ላንድሮቨሯ ወደ እኔ እስክትጠመዘዝ ርቄ ሔጄ ነበር ። ግን ምን ያደርጋል ፡ ዘወር ስል ቲጢ ፖር ደርሳለች ። ወለም ዘለም ሳልል እፊት ለፊቴ ካለው የሰው ግቢ ዕቃውን ከነጆንያው ወረወርኩና እኔም ተንጠልጥዬ ዘልዬ ገባሁ ። ይገርምሃል በዚያው ውድቅት ሌሊት እግቢው ውስጥ አንድ ሰውዬ ዛፍ ተደግፎ ቆሞ ጸሎት ነው መሰለኝ አቀርቅሮ ይደግማል ። እሱን ሰውዬ ብታየው እኮ...መቼም እሱ ያልጸደቀ በዚች ምድር ላይ ማንም ሰው አይጸድቅም ። ብቻ እሱን ሳየው አሁንስ አለቀልኝ አልኩና ዕቃዬን እዛው ትቼ ወደ ሌላ ግቢ ስዘል...እየው ግንቡ ላይ የተተከለው የጠርሙስ ስብርባሪ የቆራረጠኝ እስካሁን ጠባሳው አለ ፡ ጠሲን ይቦት ይሒድና ከዛሬም እኔ ያን ሰፈር አልወደውም።"

"ለምን አትወደውም?"

"እእ...መጥፎ የነፍጠኛ ሠፈር ነው ። በተለይ አንድ የፈጣኝ ዶራሽ ፖሊስ ጡረተኛ አለ ። እንደ በጭለማ ሽጉጥ መዘውብኝ አምልጫቸዋለሁ...እርጉም ሰውዬ! እኔ ስለ እሳቸው ብዙ ሰምቻለሁ ፡ ሳጂን ማን ነበር ስማቸው እንኳ..."

"ሳጂን ገረመው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎ! ታውቃቸዋለህ?...የተረገሙ ሰውዬ! እንዲያውም ትናንት ሆስፒታል ውስጥ ሲያለቅሱ አይቻቸዋለሁ ፤ ሰው ሞቶባቸው ነው መሰለኝ...የዚያ ሰፈር ሠራተኛ አንድ አልተረፋም ግልብጥ ብሎ መጥቷል..."

"የሞተው ሰው ማን እንደሆነ ታውቃለህ?"

"እኔ እንጃ! ስሙም ሲያወሩ አልሰማሁ ፤ ለራሴ ጠባቂዬ ፖሊስ መፈናፈኛም አልሰጠኝ ። በመስኮት ነው ሲለቀስ ከሩቅ ያየሁት ። መቼም ያው የሳቸው ቤተሰብ ወይም የቅርብ ዘመድ መሆን አለበት የሞተው ። እረ እሳቸውንም ይዟቸው በሔደ!"

ንዴት ሥጋትና ጭንቀት በላይ በላዩ እየፈራረቀበት የመጣው አንተነህ ዘሎ በሁለት እጆቹ ሽመታውን አነቀው ።

"ሰውዬ! ጤነኛ አማይደለህ? እረ ልቀቀኝ!"

"ያንተ መዘዝ ነው ለዚህ ሁሉ ..."

"እኔ ምን አጥፍቼ? ኋ...ኋላ አንድ ነገር ብሆን...ዳፋ እንዳልሆንብህ!"

"ሳ...ሳጅን ገረመው አለቀሱ አልከኝ? ጽዮን...ጽ... ጽዮን ሞተች ማለት ነዋ!"

"የቷ ናት ጽዮን?"

አንተነህ እልህ ይተናነቀዋል ። በዚያ ውድቅት ሌሊት የሰይፍ ዱላ የቀመሰበት ፤ ተይዞ የታሰረበት ምስጢር ሁሉ ወለል ብሎ በሀይኑ ላይ ሀረፈ ። በመታሰሩ ምክንያት ሳያስታምማት ፤ ሳይደግፋትና እንደ ወትሮው እይዞሽ ሳይላት ቀርቶ በብስጭትና አስታማሚ ባጣ በሽታ ምስኪኗ ጽዮን እንደ ሞተችም ሕሊናው ለመረዳት ችሏል ።

ከሦስት የኀዘን ምሽቶች በኋላ በአራተኛው ቀን ላይ አንተነህ ከእስር ቤት ተፈቶ ወደ ቤቱ ሲያመራ በምድር ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

የቀረው አንድም ዘመድና አፍቃሪ እንደሌለው እየተሰማው ነበር ። ለምን ወደ ቤቱ እንደሚሔድ አያውቅም ። የሚጠብቀው ሰው ፡ የሚናፍቀው ዘመድ የለውም ። ለእሱ ዓለሙም ፡ ዘመዱም ፡ እጮኛውም ፡ መጽናኛውም ጽዮን ነበረች ። እሷ ደግሞ ሳትሰናበተው ብቻውን ጥላው ለሞት ተሸንፋለች ። ጽዮን ታማ እንዷት ቀን እንኳን ሳይጠይቃትና ሳያጫውታት በሩቅ እንደ ናፈቀችው ሕይወቷ ማለፉን ደግሞ ደጋግሞ ያስታውስና እመንገድ ላይ እንዳለ እንባው ግጥም ይላል ። ወዲያው ደግሞ እናቱ እመት ያሰለፉ የጽዮን መሞት ምን ያህል እንደሚያስደስታቸው ይገምትና በተራው እሳቸውን ለክፉ ያሳቅላል ።

ኅዘን ያጠላበት ወጣት ጭር ባለ ቀትር መንደሩን አቋርጦ እመኖሪያ ግቢው እስኪገባ የሚያውቀው አንድም ሰው አልገጠመውም ። ግቢው ወለል ብሎ እንደ ተከፈተ በሩን ተራመደና ፈንጠር ብላ ከጥግ ወደምትገኘው ባኒጋላ ቤት አመራ ።

በቤቷ ውስጥ ምንም ነገር የለም ። ያቺ ታጣፊ አልጋው፡ ጠረጴዛው ፡ የመጻሕፍት መደርደሪያውና ሳጥኖቹ ሁሉ የሉም። አነስተኛ ድብዳብ መሳይ ምንጣፍ ብቻ ከበስተቀኝ በኩል ግድግዳው ሥር ተነጥፋለች ። ባይተዋርነት ልቡናውን እያሸበረው ውትፍ ያለ ሆዱን አጠፈና እድብዳቧ ላይ በደረቱ ተዘረጋ ።

ሆዱ ተርቧል ፡ ግን አልተሰማውም ። ውሃም ጠምቶ ታል ፡ ግን ትዝም አላለው ። የሰሞኑ እራስ ምታትም እንዳለ ነው ፡ እሱም ቢሆን አድማጭ አላገኘም ። ብቻ አንድ ነገር ከፉኛ ያመዋል ። ያቃጥለዋል ። እንደ ውስጥ እግር እሳት ድብን አርጎ ያለበልበዋል ። ሕመሙ የደዌ ሳይሆን የጽዮን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሞት ያስከተለው የአንጀት ውስጥ እጢዬ ነው ። ኀዘን ሰቀቀን ሆኖበት ፣ ባይተዋር መንፈሱን በማላጭ እየተተለ ያገንትረ ዋል።

እንተነህ ፣ እባዶ ቤት ውስጥ ከርሞት ብሎ እንደ ተኛ ማሙሽ በአንድ እጁ ቆርኪ ፣ በሌላኛው ቆሎ እንደ ጨበጠ በሩን ታኮ ገባ ። ማሙሽ ለአንተነህ የአክስቱ ልጅ ነው ። የአንተነህ አክስት ማሙሽን ከ5 ዓመት በፊት ሆስፒታል ውስጥ እንደ ወለዱት ወዲያው ሕይወታቸው በማለፉ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ለማሙሽ እናቱም አሳዳጊውም እመት ያስለፍ ናቸው ።

"እንደምን አለህ ማሙሽዬ?" እንተነህ ማሙሽን ሳም ሳም አረገና የደረቀ ጉንጩን ጠርጎለት እጉኑ አስቀመ ጠው ። እንደ ወትሮው በማቅላመጥ ሊያሜውተው አልሞከ ረም ። ብቻ ስለ ጽዮን አሚሚት እቡና ላይ ዐዋቂዎች ሲያወሩ የሰማውን እንዲያወራለት ፈልጎ ማሙሽን ጸጉሩን እየደባበሰ ይጠይቀው ጀመር ።

"ማሙሽዬ! ጽዮን መቼ ነው የሞተችው?"

"እ ... እ? ... ትልቴ ቤት ነበረች ከነእቴቴጋ ።"

እንተነህ በልቡ "አይ የልጅ ነገር! ልጆች ወሬ ማምታ ታት ልማዳቸው ነው" አለና ወዲያው ደግሞ ነገሩ ከንከኖት "አልሞተችም እንዴ ማሙሽዬ?" ሲል ጠየቀው ።

"ሞተች !" አለ ማሙሽ ።

"መቼ ሞተች?"

"ትናንትና ... ከትናንት ወዲያ ..."

"ምን ሆና?"

"መኪና ገጭታት .... "

ማሙሽ ወዲያው አጭር ፊቱን ሰብስብ ፣ አፉን ከፊት



t.me/OLDBOOKSPDF

አረገና ቆሎ የፈሐበጠ መዳፏን አቀኝ ዐይኑ ላይ ደቀና "እማዬ! ..."እያለ በማልቀስ ከእንተነህ እጅ አፈትልኮ ከቤት ወጣ ። ለእንተነህ ነገሩ ሁሉ ግራ ሆነበት ።

"ማሙሽ ምን ነካህ?" አለች የእንተነህ ታናሽ እህት ከትልቁ ቤት ወጥታ ወደ ማሙሽ እየሔደች ።

"እማዬ! ..." ማሙሽ ለቅሶውን ቀጠለ ።

"እዪሀህ ትመጣለች!" እቅፏ አርጋ አባበለችው ።

"መቼ?" ማሙሽ ህቅ — ህቅ እያለው ጠየቀ ።

"አሁን ትመጣለች!" ይዛው ወደ ትልቁ ቤት ገባች ።

እንተነህ ከእናቱ ጋር ለመገናኘት አልፈለገም ። የእ መት ያሰለፍ ነገር ቆርጦለታል ። የእሱና የጽዮን ፍቅር መቅና አጥቶ ለአሳዛኝ ፍጻሜ የበቃው በእመት ያሰለፍ ክፉ ቀልብ እንደሆነ ስላመነ በሕይወቱ የመጨረሻ ጠላቱ አርጎ ጠልቷ ቸዋል ። ታስሮ እንዲት ቀን እንኳ ሳይጠይቁት መቅረታቸ ውም የጥላቻው አንዱ ምንጭ ነው ።

በረኸኛው ተንፍሶ ከተኛበት ተነሣና ትንሿን ቤት ለቆ ወጣ ። አሁንም ግቢው ጭር እንዳለ ቢሆንም ከትልቁ ቤት ግን በርካታ ሰዎች ሲያወሩ ተሰማው ። ወሬ ወዳድ እናቱ እንደ ልማዳቸው ጐረቤት ጠርተው ቡና በመጠጣት ላይ እንዳሉ ዐወቀ ። ለእናቱም ለግቢውም ባይረበት ጥላቻ ወደ ትልቁ ቤት ፊቱን መለስ ሳያደርግ የዋንዛውን ዛፍ ዐልፎ ግቢውን ለቆ ወጣ ።

ከፊት ለፊት ራቅ ብሎ የነጽዮን ግቢ ይታየዋል ። ያኔ ጽዮንን በፈለገ ቁጥር ዙሪያውን የሚያንዣብብበት ግቢ ዛሬ እሷ አፈር ብትገባ "ጥፋ ከዚህ" ብሎ የሚያባርረው መሰለው ። ስለ አሚሚት ማንን አግኝቶ ማንን እንደሚጠይቅ አያው ቅም ። ብቻ "ታማ ሞተች" ከሚል የተለየ መልስ እንደማያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገኘ ልቡ ያውቃል ።

በአንድ ሬት ወላጆቹጋ ለትሶ በመድረስ የጽዮንን ፎቶግራፍ ከተሰቀለበት ግድግዳ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ለማየት ፤ በሌላም በኩል ጽዮንን ካጣበት መንደር ርቆ እግሩ ወደ መራው ምንጥቅ ብሎ ለመሔድ እያሰበ ጥቂት ይቆይና ሳያውቀው ወደ እነጽዮን ግቢ እያለተሰ ያመራል ።

የግቢውን በር ተራምዶ ወደ በረንዳው ሲጠጋ የጽዮንን ስም በለቅሶ ሲጠራ የሰሙት ሳጁን ገረመው ከንባለቢታቸው ተከታትለው ብቅ አሉ ። እንተነህ ተፈትቶ ማየታቸው ለጊዜው ቢያስደስታቸውም ፤ የጽዮንን ስም እየጠራ ማልቀሱ ደግሞ ወዲያው ግራ አጋብቷቸው ይነገጡ ። "ምን ነካት? ምን ሆነች?" የጽዮን ወላጆች በሥጋት አፍጠው ጠየቁት ። አፍታም ሳይቆይ ጽዮንም ከሌላ ክፍል ጋቢ ተከናንባ ወጣችና "እንተነህ!" ብላ ወደ እሱ ተንደረደረች ።

ሁሉ ነገር ሰክኖ ካበቃ በኋላ የጽዮን እናት በኀዘኔታ ከንፈራቸውን መጠው ፤ "... ጣቢያ አልነገሩህም እንዴ? እኛ ደግሞ እዚህ ሰፈር ያለው ደ ሃምሳ አለቃው ፖሊስ ስለ ሰማ ፤ የወሬ ወሬ እንተም ትሰማና እዚያ እንጉል ቢታ ትውቃያለህ ብለን ነበር ። ከእንግዲህ ነጻ ሆነህ ከተፈታህ ... መቼም ያለሃቸው ታላቅ ወንድም እንተው ነህና ያለ እናት የቀሩ ታናናሾችህን በደንብ መጠበቅና ማጽናናት አለብህ ። ..." አሉት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋው 3.95

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

t.me/OLDBOOKSPDF